# የንስሐ ሕይወት

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሽኖዳ ፫ኛ የግብፅ ኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ



ውርስ - ትርጉም
በዲያቆን እሸቱ ታደሰ ወንድም አገኘሁ

አዲስ አበባ፤ 1989 ዓ.ም ታተመ

www.ethiopianorthodox.org

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

## ማስታወሻነቱ

የሕይወት ዘመናቸውን ሁሉ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሰጥተው በመንፈሳዊ ተጋድሎ ሳሉ ዐረፍተ ዘመን ለገታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሁሉ ይሁንልኝ።

የኮምፒዩተር ለቀማና የገጽ ቅንብር፣ ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት
Computer Typesetting and Design by - Ethiopia Book Centre

## ምስጋና

ይህን የትርጉም ሥራ ከመጀመሪያ አንሥቶ ለኅትመት እስከ በቃ ድረስ መንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ ድጋፋቸውንና ማበረታቻቸውን ያለማቋረጥ በመስጠት ከጎኔ ላልተለዩኝ መንፈሳውያን ወገኖቼ:- የለቀማውን ሥራ በጥራት ላከናወኑልኝ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት የኮምፒዩተር ሠራተኞች:- በተለይም ደግሞ የትርጉሙን ረቂቅ ያለመሰልቸት በማንበብ:- በማረምና በማስተካከል እንዲሁም ጠቃሚ ምክራቸውን በመለገስ ለረዱኝ መምህራን ለመልአከ ምሕረት ብርሃኑ ሙሉጌታ እና ለአቶ ግርማ ከበደ የላቀ መንፈሳዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ተርጓሚው

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ


መቅድም ........ ፮
መግቢያ ........ ፯
ክፍል አንድ
ስለንስሐ በጠቅላላው ........ ፱
፩. ንስሐ ምንድን ነው? ........ ፱
፪. የንስሐ ሂደትና አፈጻጸም ........ ፲፯
፫. የንስሐ ጥሪ ........ ፳
፬. ተስፋ መቁረጥ አይገባም ........ ፳፮
፭. ንስሐ–በግል ትጋትና በእግዚአብሔር ረድኤት መካከል ........ ፴
፮. የንስሐ አስፈላጊነት ........ ፴፩
፯. የንስሐ መሰናክሎች (እንቅፋቶች) ........ ፴፫
፰. ንስሐና ቤተ ክርስቲያን ........ ፴፬
ክፍል ሁለት
ለንስሐ የሚያበረታቱ ሁኔታዎች ........ ፴፯
፩. ማንነትህን ካወቅህ ከኃጢአት በላይ ነህ ........ ፴፯
፪. ኃጢአት ምን እንደሆነ ብታውቅ ትሸሸዋለህ ........ ፵፭
፫. የኃጢአትን ውጤት ብታውቅ ከኃጢአት ትሸሻለህ ........ ፶፰
፬. የኃጢአትን ቅጣት ብታውቅ ኃጢአትን ትፈራ ነበር ........ ፷፪
፭. ሌሎች ለንስሐ የሚያበረታቱ ነገሮች ........ ፸፬
ክፍል ሦስት
እንዴት ንስሐ ይገባል? ........ ፸፮
፩. ከራስ ጋር መሆን ........ ፸፯
፪. ምክንያትንና ለራስ ይቅርታ ማድረግን ማስወገድ ........ ፸፱
፫. ንስሐ ለመግባት አለመዘግየት – አጋጣሚውን መጠቀም ........ ፹፯
፬. ልብን አለማደንደን ........ ፺፪
፭. የመጀመሪያውን እርምጃ ማስወገድ – ከጥቃቅን ቀበሮዎችም መጠንቀቅ ........ ፻፩
፮. መሰናክሎችንና የኃጢአት ምንጮችን ማስወገድ ........ ፻፱
፯. ለኃጢአት ጊዜ አለመስጠት ........ ፻፲፱
፰. ጠባይን መመርመር – ከድብቅ ኃጢአቶችም መጠንቀቅ ........ ፻፳፬
፱. ከሚወዱት ኃጢአት መሸሽ – ደካማ ጎንን ማረም ........ ፻፳፰
፲. ዘለዓለማዊውን ሕይወትና የሚጠበቅብንን ማሰብ ........ ፻፴፩
፲፩. የኃጢአትን ፍቅር ለማስወገድ ፍቅረ እግዚአብሔርን ማጽናት ........ ፻፴፬
፲፪. ከእግዚአብሔር ጋር መታገልና ዕርዳታውን ገንዘብ ማድረግ ........ ፻፴፰
ክፍል አራት
የንስሐ ምልክቶች ........ ፻፵፭
፩. ኃጢአትን መናዘዝ ........ ፻፵፭
፪. ስለሠሩት ኃጢአት መጨነቅና ማፈር ........ ፻፵፱
፫. መፀፀት – መከራን መቀበልና ዕንባ ........ ፻፶
፬. ጥልቅ ኀዘንና ራስን ማዋረድ ........ ፻፶፫
፭. የኃጢአትን ውጤት ማስተካከል ........ ፻፶፯
፮. ለኃጢአተኞች ማዘን ........ ፻፶፯
፯. ሌሎች ስሜቶች ........ ፻፶፰
፰. መንፈሳዊ ጽናት (ጥንካሬ) ........ ፻፶፰
፱. በተቀደሰ ሕይወት መኖር ........ ፻፷
፲. ንጽሕና ........ ፻፷፩
ክፍል አምስት
የልብ ንጽሕና ........ ፻፷፪
፩. ከኃጢአት መንጻት ........ ፻፷፪
፪. ንጽሕናን መፈተን ........ ፻፷፭
፫. ከኃጢአት ሃሳብና ሕልም መንጻት ........ ፻፷፯
፬. ከማያስፈልጉ ነገሮች መንጻት ........ ፻፷፯
፭. የንጽሕና አወንታዊ ገጽታ ........ ፻፷፱
፮. ልብን ኃጢአትን ከማወቅ ማንጻት ........ ፻፸
ክፍል ስድስት
ንስሐን ከፈተና መከላከል (መጠበቅ) ........ ፻፸፩
፩. ወደ ኃጢአት አለመመለስ ........ ፻፸፩
፪. በሁለት ሃሳብ አለማንከስ ........ ፻፹፪
፫. የብርሃንና የጨለማ ልዩነት ........ ፻፹፭
፬. ነፍስን መንከባከብ ........ ፻፹፱


www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሽኖዳ ፫ኛ የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የተዘጋጀውን «The Life of Repentance & Purity» የተሰኘ መጽሐፍ በአነበብኩት ጊዜ የራሴን ማንነት በሚገባ ስለተመለከ ትኩበት ወደድኩት። ለሁለተኛ ጊዜ አንብቤ የሚጠቅመኝን ፍሬ ሃሳብ ለማስቀረት በማስታወሻዬ ላይ መጻፍ ከጀመርኩ በኋላ ሙሉ በሙሉ ለመተርጐምና በየጊዜው እየተመለከትኩት መንፈሳዊ ሕይወቴን ልመረ ምርበት ወሰንኩ። የመጀመሪያውን ሥራ ከፈጸምኩ በኋላ የተመለከቱት መንፈሳውያን ወንድሞቼና እኅቶቼ በሚገባ በማዘጋጀት ከፍጻሜ እንዳደርሰው አበረታቱኝ። ሁለተኛውን ዙር ሥራ በማጠናቀቅ ወንድሞችና መምህራን እንዲያዩትና እንዲያርሙት የተሰማቸውንም ስሜት እንዲነግሩኝ ሰጠኋቸው። ሁሉም ቢታተም የሚጠቅም መሆኑን ገለጡልኝ።

ይሁን እንጂ በሃሳቡ ብስማማም አቅሙ ስላልነበረኝ ለአንድ ዓመት ያህል አቆየሁት። እግዚአብሔር በፈቀደው ጊዜ የሚያስፈልገውን ሁሉ ስለአመቻቸልኝ እነሆ የቤተ ክርስቲያናችን ልጆች እንድንጠቀምበት ለመታተም በቃ።

ይህ መጽሐፍ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በቅድስና ሕይወታቸው በተደጋጋሚ የሚነሡትን:- እኛም ዘወትር በቅድስና ሕይወታቸው በምሳሌነት የምናወሳቸውን አበው መንፈሳዊ ሕይወት በጥልቀት በመመርመር የንስሐን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በጉልህ የሚያሳይ ነው። በይበልጥ ደግሞ ከቅድስና ደረጃ ለመድረስ በሚደረገው የሕይወት ጉዞ ብዙ መውደቅ መነሣት መኖሩንና እስከፍጻሜው በመጽናት የሥጋን ፈተና ታግሠውና ንስሐን ዋነኛ ምርኩዝ አድርገው የተጓዙ ሁሉ የሚገባቸውን አክሊል እንደተቀዳጁ በሚገባ ቋንቋና አገላለጥ በማስረዳት ሰው ሁሉ የንስሐን ሕይወት እንዲወደውና ለንስሐም እንዲዘጋጅ:- ፈጥኖም እንዲወስን:- የሚያበረታታ ጥልቅ መንፈሳዊ ምክር ይገኝበታል።

በአጠቃላይ ይህን መጽሐፍ ያነበበ ሁሉ በንባቡ መጨረሻ ስለመንፈሳዊ ሕይወቱ አንድ ጠቃሚ ውሳኔ በመወሰን ወደ ተግባራዊ የሕይወት ለውጥ ማለትም ኦርቶዶክሳዊ የክርስትና ሕይወትን በተግባር ወደመኖር እንደሚሸጋገር ተስፋ አደርጋለሁ።

አምላካችን እግዚአብሔር በንስሐ ሕይወት ጸንተን በመኖር የመንግሥቱ ወራሾች ለመሆን ያብቃን።

ተርጓሚው ዲያቆን እሸቱ ታደሰ ወንድም አገኘሁ።



# መግቢያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

የሰው ልጆች ሁሉ በክርስቶስ አምነው በመጠመቅ በክርስትና ሕይወት እንዲኖሩ ተጠርተዋል። በክርስትና ለሚኖር የሰው ልጅ ሁሉ ደግሞ ዕለት ዕለት ከሚሠራው ኃጢአት ንስሐ መግባትና ንጽሕናን ገንዘብ ማድረግ ይጠበቅበታል። ምክንያቱም በጥምቀት የተሰጠውን ልጅነት እንዳያጣና በየጊዜው ከፈጣሪው ከሚያገኘው ጸጋ እንዳይለይ የእግዚአብሔር በረከትም እንዳይጎድልበት ስለሠራው ኃጢአት ከልብ እያዘነ በመፀፀት የንስሐን ሕይወት መኖር ለክርስቲያን ሁሉ ዋና ተግባሩ በመሆኑ ነው።

ንስሐ በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ የሚሰጥበት ታላቅ ምሥጢር ነው። የሚታየው አገልግሎት የተነሳሒው ፀፀትና ኑዛዜ – የቄሱ የንስሐ ጸሎት ሲሆን የማይታየው ጸጋ ደግሞ ተነሳሒው የሚያገኘው ሥርየተ ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር ሰውን ከመውደዱ የተነሣ ከሰው ልጅ አንድ ስንኳ እንዳይጠፋ የሰውን በደል ሁሉ ይቅር ለማለት ታላቁን የምሕረት አዳራሽ መግቢያ በር ንስሐን ከፈተ። በዚህም መሠረት ማንም ሰው ከተያዘበት የኃጢአት ቁራኝነት ነፃ ወጥቶ በሰላም መኖር የሚችለው ኃጢአቱን ለመምህረ ንስሐው በመናዘዝና ከልቡ ንስሐ በመግባት በሚያገኘው ሥርየት ነው። ስለዚህ ንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር መኖርን ማለትም ክርስትናን ለጀመሩ ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጆች ሁሉ አስፈላጊ ነው። ንስሐ ኃጥእና ጻድቅ ሳይለይበት ሰዎች ሁሉ በማንኛውም የማዕረግና የቅድስና ደረጃ ቢሆን ከእግዚአብሔር ይቅርታን በሕይወታቸውም መንፈሳዊ ተሐድሶና በበረከት ላይ በረከት የሚያገኙበት ምሥጢር ነው።

ንስሐ በየዕለቱ ከሚደረገው ጸሎት ውስጥ አንዱ ክፍል ነው። ሰው ሁሉ በጸሎቱ ውስጥ ስለኃጢአቱ ሥርየት:- ስለበደሉ ይቅርታ በመጠየቅ ፈጣሪውን መለመን ይገባዋልና ንስሐ በጸሎት ሕይወታችን ውስጥ ታላቅ ሥፍራ አለው።

ሰው የሆነ ሁሉ ፍጹም አይደለምና በየዕለቱ ስለምንበድል በየዕለቱ ደግሞ ንስሐ ያስፈልገናል። ውኃ ሲታጠቡበት ወይም ሲያጥቡበት የቆሸሸውን ልብስና አካል እንደሚያድስና እንደሚያነጻ ሁሉ ንስሐም በኃጢአት ያደፈውን ሕይወትና የቆሸሸውን አካለ ነፍስ ያድሳል – ያነጻልና፤ በየዕለቱ የሚበድል ሰው ሁሉ በየዕለቱ ንስሐ በመግባት መንፈሳዊ ሕይወቱን በንጽሕና መጠበቅ ይኖርበታል።

www.ethiopianorthodox.org

ንስሐ በመግባት ሕይወቱን ከኃጢአት የሚያነጻ ሰው የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን ራሱን ያዘጋጃል፤ እግዚአብሔርንም በተቀደሰ ሥራው፣ በምሕረቱና በቸርነቱ ያየዋል። ልቡናቸውን ከኃጢአት ያነጹ ሰዎች እግዚአብሔርን ያዩታልና ብፁዓን ናቸው ተብሏልና። ማቴ.፭፥፰።

ንስሐ ወደ እግዚአብሔር የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ:- በእግዚአብሔርም ቤት ለመኖር መጀመሪያው በንስሐ በር መግባት ነው። የንስሐን በር በመክፈት ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር የማስገባት ሥልጣን ለተሰጠው ካህን ኃጢአትን በመናዘዝና በፍጹም ልብ ንስሐ በመግባት ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ይቻላል። ከእግዚአብሔር ጋራ መኖርን ለሚጀምሩ ብቻ ሳይሆን በክርስትና ሕይወት ጉዞ ላይ ላሉት ሁሉ ንስሐ እስከ ፍጻሜ የሚዘልቅ ወዳጅና ጓደኛ ሊሆን ይገባል። ሰው በኑሮው ቢያጋድል የሚያቃና፣ ቢወድቅ የሚያነሣ ጓደኛ እንደሆን ሁሉ ከምግባር ድካም የሚያበረታ:- በኃጢአት በወደቁ ጊዜ ደግፎ የሚያነሣ ንስሐ ለሰዎች ሁሉ ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ ንስሐን የዘለቄታ ወዳጅ ጓደኛ ማድረግ ተገቢ ነው።

በመሆኑም በዚህ መጽሐፍ ስለንስሐና የንስሐ ሕይወት ለማወቅ የሚያስችል መሠረታዊ ትምህርት ተዘጋጅቶ ቀርቧል። አንባብያንም በዚህ መጽሐፍ በመጠቀም መንፈሳዊ ሕይወታቸውን በንስሐ እየመሩ ለተቀደሰው ሰማያዊ ክብር እንዲበቁ ተጋብዘዋል።

ክፍል አንድ

# ስለ ንስሐ በጠቅላላው

## ፩. ንስሐ ምንድን ነው?

ንስሐ – ነስሐ ከሚል የግዕዝ ግስ የወጣ ቃል ነው። የቃሉ ፍች ሐዘን፣ ፀፀት፣ ቁጭት፣ ምላሽ፣ መቀጮ፣ ቅጣት፣ ቀኖና፣ የኃጢአት ካሣ ማለት ነው። (የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት) አንድ ሰው ንስሐ ገባ ሲባልም ዐዘነ፣ ተጠጠተ፣ ተመለሰ፣ ክፉ ዐመሉን ተወ፣ ጠባዩን ለወጠ ማለት ነው። ንስሐ ማለት ደግሞ አንድ ሰው በሠራው ጥፋት፣ ባደረገው ስህተት፣ በፈጸመው ኃጢአት ማዘኑና መቆርቆሩ፣ መፀፀቱ – ዳግመኛም ያንን የመሰለ ኃጢአት ላለማድረግ የሚወስነው ውሣኔ ነው።

በአጠቃላይ መልኩ ንስሐ ከፍ ብሎ የተገለጠው ትርጉም ሲኖረው በሰዎች ሕይወት ውስጥ ደግሞ የሚከተሉትን ፍችዎች ይዞ እናገኘዋለን።

### ሀ. ንስሐ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው

ከእግዚአብሔር መለየት ኃጢአት ነውና፤ ንስሐ የሚገባ ሰው ከሠራው ኃጢአት በሙሉ ልቡ ይመለሳል – የበደለውን ፈጣሪውን ስለበደሉ ይቅርታ ይጠይቃል። እግዚአብሔር አምላክም በነቢያት አድሮ ሕዝቡ ከኃጢአት ንስሐ እንዲገቡና ወደ እርሱ እንዲመለሱ ተናግሯል። «ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከሥርዓቴ ፈቀቅ ብላችኋል፤ እርሷንም አልጠበቃችሁም። ወደእኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ» ሚል.፫፥፯ በማለት ጥሪውን አስተላልፏል። በመጽሐፈ ምሳሌም «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል» በማለት ተጽፏል። ምሳ.፳፰፥፲፫። በሉቃስ ወንጌል የምናገኘው አባካኙ ልጅ ኃጢአቱ በመረረውና በተጠጠተ ጊዜ ወደልቡ ሲመለስ ወደአባቱ ለመምጣት ወሰነ:- አባቱም በሐሴት ተቀበለው። ሉቃ.፲፭፥፲፰–፳። እውነተኛ ንስሐም ሰዎች በበደልና ኃጢአት ምክንያት ወደአጡት ሥፍራ ለመመለስ የሚኖራቸው ናፍቆትና የሚወስኑት ውሳኔ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ለ. ንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ነው፤

ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ነውና። ስለዚህ ነገር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን እንለምናችኋለን» ፪ቆሮ.፭፥፳። በማለት ተናግሯል። ንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ብቻም ሳይሆን የእግዚአብሔር በሰዎች ልቡና ውስጥ ማደርም ነው። ሰው ኃጢአትን ከእርሱ ካላስወገደ የእግዚአብሔር ማደሪያ ሊሆን ስለማይችል ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ማለት የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን መዘጋጀት ነው። ፪ቆሮ.፮፥፲፮።

ሐ. ንስሐ ከኃጢአት እንቅልፍ መንቃት ነው፤

ኃጢአት በመንፈሳዊ ሕይወት ማንቀላፋት ነውና። ኃጢአተኛ ያለበትን ሥፍራ:- የወደቀበትን ጉድጓድ አያውቀውምና በንስሐ መቀስቀስ ያስፈልገዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን ዕወቁ» በማለት ለሮም ሰዎች የጣፈው ከኃጢአት እንቅልፍ ነቅተው ለንስሐ እንዲበቁ ለመቀስቀስ ነው። ሮሜ.፲፫፥፲፩። በዚህ አገላለጥ ንስሐ የሰው ወደቀደመ ማንነቱ መመለስ ነው። ከኃጢአት የተነሣ ማንነቱን አጥቷልና። የጠፋው ልጅም «ወደ ልቡ ተመለሰ» እንደተባለ። ሉቃ.፲፭።

መ. ንስሐ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት መመለስ ነው፤

ኃጢአት የነፍስ ሞት ነውና። ቅዱስ ጳውሎስም «በኃጢአታችን ሞተን ሳለን በክርስቶስ (ሥጋችንን ተዋሕዶ ሕያዋን አደረገን) አዳነን» ብሏል። ኤፌ.፪፥፭። ዳግመኛም «አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልኻል» ሲል ተናግሯል። ኤፌ.፭፥፲፬። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊውም «እኛ...ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን እናውቃለን።» በማለት ምስክርነቱን ገልጧል። ፩ዮሐ.፫፥፲፬። ቅዱስ ያዕቆብ ደግሞ «ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን – የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ።» በማለት ኃጢአት የነፍስ ሞት ንስሐ ደግሞ ሕይወት መሆኑን አስተምሯል። ያዕ.፭፥፳። ስለዚህ ንስሐ መንፈሳዊ የሕይወት ትንሣኤ ነው ኃጢአት በመንፈሳዊ ሕይወት መሞት ነውና።



ሠ. ንስሐ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ እግዚአብሔርን የሚያስወድድ ከንጹሕ ልብ የሚመነጭ ጸጋ ነው። ለዚህ ነው «ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ:- እናንተም ትጠራላችሁ (ትነጻላችሁ)፤ ከርኵሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ። አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ:- አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ:- የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ:- መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ:- በትእዛዜም አስኬዳችኋለሁ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ:- ታደርጉትማላችሁ» በማለት የተነገረው። ሕዝ.፴፮፥፳፭—፳፯።

ረ. ንስሐ ከኃጢአትና ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ መውጣት ነው። እግዚአብሔር ካልፈቀደለትና ኃይሉን ካልሰጠው በቀር ተነሳሒ ልቡና ማግኘት ለሰው ልጅ በተለይም ኃጢአት ለሠለጠነበት:- ዲያብሎስ ለነገሠበት ሰው ከባድ ነው። ይህንንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እውነት እውነት እላችኋለሁ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው። ባሪያም ለዘላለም በቤት አይኖርም...እንግዲህ ልጁ (ወልደ እግዚአብሔር) አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።» ዮሐ.፰፥፴፬—፴፮። በማለት ከዚህ የኃጢአት ባርነት ነፃ መውጣት የሚቻለው ከእግዚአብሔር በተሰጠችና በምትሰጥ ንስሐ መሆኑን አስትምሮናል። በእውነት ንስሐ የገባ በፍጹም ልቡ ወስኖ ኃጢአትን የተወ ሰው በእርግጥ ከባርነት ነፃ እንደሚወጣ «እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል።» በማለት አረጋግጧል። ዮሐ.፰፥፴፪።

ሰ. ንስሐ ስለእግዚአብሔር ፍቅርና ስለ ቅድስና ብሎ ኃጢአትን መተው ነው። ሰው በብዙ ምክንያቶች ኃጢአትን ሊተው ይችላል:- ለምሳሌ ሰውን ፈርቶ፣ የሚፈልገውን ዓይነት ኃጢአት ለመሥራት አቅም ሳይኖረው ቀርቶ፣ የሚፈልገውን ኃጢአት ለመፈጸም ሁኔታው ሳይመቸው ቀርቶ—ወዘተ.። ይህ ዓይነቱ ንስሐ ሊባል አይችልም። በመጀመሪያ ኃጢአትን ለመሥራት ማሰብን ከልቡና ፈጽሞ ማጥፋት ይገባል። የኃጢአት ፍቅር ከልቡ ሳይወጣ የኃጢአት ፍላጎት እያለው ኃጢአትን ያልሠራ ሰው ኃጢአትን ትቷል ሊባል አይችልም። ንስሐ የሚባለው ኃጢአትን ከልቡና፣ ከማሰብና ከመሥራት ፈጽሞ መከልከልና መተው ነው። «ኃጢአትን የሚሠውር አይለማም የሚናዘዝና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል።» ሲል ጠቢቡ ሰሎሞን ተናግሯል። ምሳ.፳፰፥፲፫።

www.ethiopianorthodox.org

ሸ. እውነተኛ ንስሐ ኃጢአትን ከተዉ በኋላ በፍጹም መልሶ አለመሥራት ነው። ኃጢአትን መተው ማለት አንዱን ትቶ ሌላውን ለመሥራት የሚመጣ ሃሳብንና መሻትን ሁሉ ከልቡና ማስወገድ ነው። ሰይጣንም አንዱን ኃጢአት ለማሠራት በተሳነው ጊዜ በዚያው ኃጢአት ደግሞ አይፈትንም፤ ሌላ አዲስ የኃጢአት ዘር በልቡና በመዝራት ሌላ ኃጢአት በማስመኘትና በማሠራት ሰውን ለመጣል ይሞክራል እንጂ። ቅዱስ ቢሾይ የተባለ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን አባት– «ሰይጣን አንዱን ኃጢአት ደግሜ እንድሠራ የተፈታተነኝ መሆኑን አላስታውስም» በማለት ከፍ ብሎ የተነገረውን አባባል አረጋግጦታል። ስለዚህ ኃጢአትን ፈጽሞ መተው እንጂ ከአንዱ ወደሌላው የኃጢአት ዓይነት እየተዛወሩ ኃጢአትን መሥራት ንስሐ አይደለምና ኃጢአትን ጨርሶ መተው ይገባል።

ቀ. ንስሐ ስለአለፈው ስህተት አብዝቶ ማልቀስ፤ ያለፈውን የኃጢአት ኑሮ ማውገዝና መኰነን ነው፤ ኃጢአትን ፈጽሞ በመተው ከልቡናው የኃጢአትን ሃሳብ ጨርሶ ያስወገደ ሰው ልቡ ንጹሕ ስለሆነ ያለፈውን ኃጢአቱን እያሰበ ያለቅሳል የቀደመ የበደል ኑሮውንም ይረግማል። ነቢዩ ኢዩኤል «አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ:- በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ።» በማለት የሚመክረን ለዚህ ነው። ኢዩ.፪፥፲፪። ሰው በፍጹም ልቡ ካልተመለሰ ስለኃጢአቱ እያዘነ ሊያለቅስ አይችልም።

በ. ንስሐ ፍጹም የሆነ የሕይወት ለውጥ እንጂ ጊዜያዊ ስሜት አይደለም፤ ተነሳሒው በስሜት ተነድቶ ለጊዜው የሚያሳየው ፀፀት ንስሐ አይባልም። በፍጹምና በመላው ሕይወቱ በመለወጥ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አለበት። ይህ የሕይወት ለውጥም በራሱ ውስጥና ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት፣ በአስተሳሰቡ መለወጥ፣ በአቋሙና በጠባዩ መለወጥ፣ ስለሕይወት ባለው አመለካከት መለወጥ፣ በአነጋገር ሥርዓቱ መለወጥ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነት (ከክህደት ወደ ማመን) በመለወጡ ይታወቃል። በልቡናው መለወጡ ደግሞ የሚወደውን ኃጢአት በመጥላቱና በምትኩ ልቡናው በእግዚአብሔር ፍቅር በመሞላቱ የተነሣም መንፈሳዊ የሕይወት ተሐድሶ በማግኘቱ ይታወቃል። ይህንን ለማረጋገጥ ነው ቅዱስ ጳውሎስ «በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ» ያለው። ሮሜ.፲፪፥፪። ከዚህ በመነሣት ነው እንግዲህ ንስሐ ፍጹም የሆነ የሕይወት ለውጥ እንጂ በጊዜያዊ ስሜት ላይ የተመሠረተ አይደለም የተባለው።



ተ. ንስሐ ኃጢአትን ሲሠሩ ከመኖር ይልቅ ከእግዚአብሔር ጋር መኖርን መሻት (መምረጥ) ነው፤ ከእግዚአብሔር ጋር መኖርን መምረጥ ማለት እግዚአብሔር የማይወደውንና የማይደሰትበትን ኃጢአትን ከመሥራት ተከልክሎ እግዚአብሔር የሚወደውንና የሚደሰትበትን ጽድቅ የሚገኝበትን መልካም ምግባርና ትሩፋት በመሥራት እርሱን በማምለክና በማገልገል መኖርን መምረጥ ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መኖርን መረጠ ማለትም መንገዱን የእግዚአብሔር መንገድ፣ ፈቃዱን የእግዚአብሔር ፈቃድ፣ ሃሳቡንም የእግዚአብሔር ሃሳብ አደረገ ማለት ነው። ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት–የማያልፈውንም ርስት መረጠ ማለት ነው። ንስሐም ኃጢአትን የኃጢአት ውጤት የሆነውንም የገሃነም ኑሮ ትቶ ከእግዚአብሔር ጋር በመንግሥተ ሰማይ መኖርን መምረጥ ነው መባሉ ለዚህ ነው። ከዚህ አንፃር ነው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል» በማለት ምርጫውን ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ያደረገው። መዝ.፸፫፥፳፰።

ቸ. ንስሐ የአእምሮ መታደስ ነው፤ ኃጢአት የአእምሮ መበላሸት ነውና፤ ኃጢአትን የሚያመላልስ አእምሮ የተበላሸ ነው። በኃጢአት ዕድፍ ንጽሕናውን ያጣው አእምሮ የሚታደሰው ኃጢአትን ማመላለስ የተወ እንደሆነ ነው። ይህም በንስሐ ነው። ይህን ሲገልጥ ቅዱስ ጳውሎስ «በልባችሁ መታደስ ተለወጡ» ሮሜ.፲፪፥፪ በማለት ተናግሯል።

ነ. ንስሐ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ የሚያስችል ወደ መንግሥተ እግዚአብሔርም የሚያስገባ ቁልፍ ነው፤ ንስሐ የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ በር ነው። (በንስሐ አማካኝነት በኃጢአት የተዳደፈው ልብ ካልጸዳ በቀር እግዚአብሔር በሰው ልቡና ሊያድር አይችልም) የሰው ሕይወት በንስሐ ከታጠበና ንጹሕ ከሆነ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ የተዘጋጀ ይሆናል። በዚህ መሠረት ንስሐ አምስቱን ጠባባት ወደ ሠርጉ ቤት ለመግባት ያስቻላቸው የመብራት ዘይት ነው። ማቴ.፳፭፥፩–፲፫። ደናግሉ ተዘጋጅተው በመጠበቃቸው ሙሽራው በመጣ ጊዜ ሊቀበሉትና አብረውት ወደሠርጉ ሊገቡ እንደቻሉ ሁሉ በንስሐ ተጣጥበው ከኃጢአት ተለይተው ምግባርና ሃይማኖት ዘይታቸውንና መብራታቸውን አዘጋጅተው የተገኙ ምእመናን ሁሉ ሙሽራው ወልደ እግዚአብሔር በሚገለጥበት ዕለተ ምጽዓት በደስታ ሊቀበሉትና አብረውም ወደሠርጉ ቤት መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ይችላሉ። ከዚህ በመነሣት ነው ንስሐ ወደመንግሥተ እግዚአብሔር የምታስገባ ቁልፍ ናት የተባለው።

www.ethiopianorthodox.org

ፕ. ንስሐ በቀራንዮ በመስቀል ላይ እኛን ለማዳንና ከኃጢአት ባርነት ነፃ ለማውጣት የፈሰሰልንን የክርስቶስን ደም እንድናስብ የሚያደርግ መንፈሳዊ ሀብት ነው፤ ንስሐ ኃጢአትን የምንቃወምበት፣ ልቡናችንን ከሥጋዊ ፈቃድ የምናነጻበትና ነገረ መስቀሉን ለማሰብ የሚያስችለውን ጥልቅ መንፈሳዊ ፍቅር የምናገኝበት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። በንስሐ ከኃጢአት ያልነጻ ልቡና ፍቅረ እግዚአብሔር ስለማይኖረው የተደረገለትን አምላካዊ ቸርነት አያስተውልም። ስለዚህ ንስሐ ገብተን ልቡናችንን ለፍቅረ እግዚአብሔር ማዘጋጀት ይገባናል።

ኦ. ንስሐ ከኃጢአት የሚያነጻ ሱራፌል ከመንበረ ሥላሴ የወሰዱት የእሳት ፍም ነው። በእርሱ የኃጢአተኛው ኃጢአት ተወግዷልና ንስሐም ኃጢአታችን የሚወገድበት ሰይጣንን የምናቃጥልበት እሳት ነው። ኢሳ.፮፥፯። ንስሐ ከሕይወታችን ኃጢአትን የምናስወግድበት ብቻ ሳይሆን ከፍርድ መዝገብም ኃጢአታችንን የምናስፍቅበት ብቸኛ መንገድ ነው። እግዚአብሔርም በነቢዩ ኤርምያስ አድሮ «በደላቸውን እምራቸዋለሁና ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና።» ኤር.፴፩፥፴፬። በማለት የተናገረው ቀድሞ የሠራነውና በፍርድ መዝገብ የተጻፈው ኃጢአታችን የሚደመሰሰው በንስሐ አማካኝነት መሆኑን ሲያስተምረን ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዘመነ ሥጋዌው «ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ።» በማለት ከፍርድ ለመዳን የሚቻለው በንስሐ አማካኝነት ከኃጢአት በመለየት መሆኑን አስረድቷል። ሉቃ.፲፫፥፫።

ከ. ንስሐ ከሚመጣው የመጨረሻ መከራና ሐዘን መዳኛ ወይም ማምለጫ መንገድ ነው። የነነዌ ሰዎች ከኃጢአታቸው የተነሣ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደመጣባቸው በነቢዩ ዮናስ አማካኝነት በተሰበከላቸው ጊዜ ሊወርድ ከነበረው የእሳት ዝናም ለመዳን የቻሉት በንስሐ ለቅሶ ነው። ዮና.፫፥፲። በነቢዩ ኤርምያስ «አሁንም መንገዳችሁንና ሥራችሁን አሳምሩ፣ የአምላካችሁንም የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤ እግዚአብሔርም የተናገረባችሁን ክፉ ነገር ይተዋል» ኤር.፳፮፥፲፫። በማለት የተነገረው ስለዚህ ነው።

ወ. ንስሐ እግዚአብሔር የሰውን ኃጢአት ይቅር የሚልበትና ከኃጢአት ውጤት የሚያድንበት መሣሪያ ነው፤ የሰው ኃጢአት ቢበዛም እግዚአብሔር ፈቃዱ ሰው ሁሉ ከሞተ ነፍስ እንዲድን ነው – ከልዑል መንበሩ ስቦ ሰው ያደረገው – የሰውን ባሕርይ ገንዘብ አድርጎ በመሞት ሞትን ለማጥፋት



ያስወሰነው ለሰው ያለው ፍቅር ነው። ከዚህ ታላቅ ፍቅሩ የተነሣ ለሰው ድኅነት ንስሐን ሰጠ። ስለዚህ ነው ንስሐ እግዚአብሔር በኃጢአት የወደቁ ሰዎችን ከኃጢአታቸው ለማንጻት፣ ያጡትን ውስጣዊ ሰላም ለመስጠትና በኃጢአት ምክንያት ወደአጡት የቀደመ ክብራቸው እንዲመለሱ የተሰጠ አምላካዊ ጸጋ ነው የተባለው።

ዐ. ንስሐ ከሰዎች ጋር ለመታረቅ የተዘረጋ የእግዚአብሔር እጅ ነው። ንስሐ በኃጢአት ምክንያት ከፈጣሪው ጋር ለመገናኘት ያልቻለው የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር እንዲገናኝ እግዚአብሔር የከፈተው የሕይወት መንገድ ነው። ንስሐ እግዚአብሔር የሰውን የቀደመ ኃጢአት ይቅር የሚልበትና የሚያጥብበት መንፈሳዊ ሳሙና ነው። ሰው በንስሐ የታጠበ እንደሆነ ከበረዶ ይልቅ ይነጻል:- መዝ.፶። ንስሐ በኃጢአት ምክንያት የፈረሰው (የተናደው) የሰው መንፈሳዊ ተስፋ ዳግመኛ የሚገነባበት መሣሪያ ነው። ንስሐ የምሕረት፣ የይቅርታ፣ የሕይወት በር ነው። ንስሐ ሰውንና መላእክትን፣ መሬትንና መንግሥተ ሰማያትን የሚያገናኝ ረቂቅ መንፈሳዊ ድልድይም ነው። ለዚህ ነው ንስሐ ከሰዎች ጋር ለመታረቅ የተዘረጋ የእግዚአብሔር እጅ ነው የተባለው።

ዘ. ንስሐ እግዚአብሔር ወደሰው የሚጣራውን ጥሪ ሰምቶ ወደ እርሱ መመለስ ነው፤ ይህም በኅሊና ውስጥ ለሚደመጠው የእግዚአብሔር የጥሪ ድምፅ መልስ መስጠት ነው። የተቀደሰውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አለመቃወም የእግዚአብሔርን ጥሪ መስማት ነው። ልብን ማደንደንና የእግዚአብሔርን ቃል አለመቀበል የተቀደሰውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መቃወም ነው። የሐዋ.፯፥፶፩። የእግዚአብሔርን መንፈስ አለማሳዘን የእግዚአብሔርን ጥሪ መስማት ነው። ኤፌ.፬፥፴። በአርባ (፵) እና በሰማንያ (፹) ቀን ስንጠመቅና የሥላሴ ልጅነትን ስናገኝ የተቀበልነውን በውስጣችን የታተመውን መንፈስ ቅዱስ ከውስጣችን አለማጥፋትና የሚፃረረውን ኃጢአትን ከመሥራት መጠበቅ የእግዚአብሔርን የጥሪ ድምፅ መስማት ነው። ፩ተሰ.፭፥፲፱።

ዠ. ንስሐ ስለአለፈው ኃጢአት ከመፀፀት የተነሣ የተሰበረ ልብ ነው፤ በኃጢአቱ ተፀፅቶ ወደ ፈጣሪው ወደ እግዚአብሔር የሚመለስ የተሰበረ ልብ ነው። የተሰበረ ልብ ማለት በአምላኩ ፊት ስለሠራው ኃጢአት ያፈረ – የተዋረደ – ትሑት ልብ ነው። ይህም በደሉን ዐውቆ በእግዚአብሔር ፊት የተንበረከከ ጉልበት፣ የሚያነባ ዓይን፣ የተፀፀተና ያዘነ ልብ ማለት ነው። በትሕትና የተዋረደ ልብ ደግሞ የፀፀት ዕንባን የሚያመነጭ የዋህና

www.ethiopianorthodox.org

ገር ነው። ለዚህ ነው ነቢዩ ዳዊት «የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው» ያለው። መዝ.፶፥፲፯።

የ. ንስሐ – ሰዎች ስለኃጢአታቸው ተጸጽተው ከእግዚአብሔር ጋር እንዳይታረቁ በብርቱ በሚጥረው ሰይጣን ላይ የተገኘ ታላቅ ድል ነው፤ ምክንያቱም በፈቃደ ሰይጣን በግብረ ኃጢአት የተያዙ ሰዎች ከዲያብሎስ ግዞት ነፃ የሚወጡት በንስሐ ነውና። ለብዙ ዘመናት በተሠራ ኃጢአት የተገነባ የበደል ሕንፃ በአንዲት ሰዓት ንስሐ እንዳልነበረ ሆኖ ይፈርሳል። ስለዚህም ንስሐ የበደለውን እንዳልበደለ ኃጥኡን ጻድቅ፣ ዘማዊውን ድንግል ታደርጋለች ሲል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተናግሯል።

ንስሐ የሰማያዊም የምድራዊም ደስታ ምንጭ ነው። አንድ ኃጢአተኛ ንስሐ ቢገባ በሰማይ ደስታ እንደሚደረግ በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፏል። ሉቃ.፲፭፥፯–፲። በአንድ ኃጥእ ንስሐ መግባት ሰማያውያን ቅዱሳን መላእክትና ጻድቃን ሁሉ ሐሤት ያደርጋሉ:- እንደ ፈጣሪአቸው የሰው ድኅነት ያስደስታቸዋልና። በምድርም በንስሐ ምክንያት ከኃጢአት እሥራት መፈታትና ከአጋንንት ግዞት ነፃ መውጣት:- ከኃጢአትም ተለይቶ በንጽሕና በቅድስና መኖር ይገኛልና ንስሐ ሥጋዊ ያይደለ የመንፈሳዊ ደስታ – ምንጭ ነው መባሉ ትክክል ሆኖ እናገኘዋለን። ኢሳ.፷፩፥፩። ንስሐ የድል አድራጊነት ሕይወት ነውና የደስታ ምንጭ ነው። ይህን ቅዱስ ዳዊት «ለጥርሳቸው ንክሻ ያላደረገን እግዚአብሔር ይመስገን። ነፍሳችን እንደወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች:- ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን» መዝ.፻፳፫፥፮–፯። በማለት አብራርቶታል።

ንስሐ ወደረጅሙ የቅድስናና የንጽሕና ሕይወት የሚደረገው ጉዞ መጀመሪያ እንጂ የመንፈሳዊ ሕይወት ፍጻሜ ግብ ወይም መጨረሻ አይደለም። ንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ግንኙነት መጀመሪያ ነው። ንስሐ ፍጻሜው ቅድስና ለሆነው የክርስትና ጉዞ መንደርደሪያ ነው። የክርስትና ሕይወቱን በንስሐ ያልጀመረና ንስሐን በጉዞው ሁሉ ምርኩዝ ያላደረገ ከመጨረሻው ግብ ሊደርስ አይችልም። ስለሠራው ኃጢአት ያልተፀፀተ – ንስሐ ያልገባና ለመግባትም ያልተዘጋጀ ሰው ጌታችን «የሰማይ አባታችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ማቴ.፭፥፵፰። በማለት የተናገረውን አምላካዊ ትእዛዝ ሊፈጽም አይችልም።



## ፪. የንስሐ ሂደትና አፈጻጸም

### ንስሐ ሦስት የአፈጻጸም ደረጃዎች አሉት

#### ሀ. የንስሐ የመጀመሪያ ደረጃ

የንስሐ የመጀመሪያ ደረጃ ኃጢአትን መተው ብቻ ሳይሆን ንስሐ ለመግባት ማሰብ ወይም መፈለግ ነው። ይህ ኃጢአትን ከመተው የሚቀድም ነው። ሰዎች ንስሐ ለመግባት ባልፈለጉና ባላሰቡ መጠን በኃጢአት እየተደሰቱ ኃጢአትን እየሠሩ ይኖራሉ። በእነርሱ አመለካከትም የያዙት የኃጢአት ኑሮአቸው መልካም ስለሚመስላቸው አይለወጡም። ስለዚህ ንስሐ ለመግባት ማሰብና መፈለግ የንስሐ የመጀመሪያ ደረጃ ነው።

#### ለ. ሁለተኛው ደረጃ

በንስሐ ሂደት ሁለተኛው ደረጃ ኃጢአትን መተው ነው። ኃጢአትን መተው ሲባልም ኃጢአትን ከኀሊናና ከልቡና ጨርሶ በፍጹም ማጥፋት ነው። ይህም ኃጢአትን ከማሰብ መለየት ማለት ነው። ምክንያቱም ሰው በተግባር ኃጢአትን ባይፈጽምና በልቡ ግን የኃጢአት ፍቅር ቢኖር ኃጢአትም በልቡናው የሚመላለስ ከሆነ ይህ ሰው ንስሐ ገብቷል ለማለት አይቻልም። የዚህ ዓይነቱ ሰው ኃጢአትን የተወው ወይም ኃጢአት ከመሥራት የተቆጠበው የእግዚአብሔርን ሕግ ለመጠበቅ ብሎ ነው እንጂ ኃጢአትን ጠልቶ አይደለምና በልቡናው የኃጢአት ፍቅር ቅሪት እያለ ኃጢአትን ትቷልና ንስሐ ገብቷል ሊባል አይችልም። ስለዚህ ፀፀቱ ወይም ንስሐው ልቡናው ከኃጢአት እስኪነጻ ድረስ መሆን አለበት። ከዚህ አንፃር ኃጢአትን መተው የንስሐ ሁለተኛ ደረጃ ነው።

#### ሐ. ሦስተኛው ደረጃ

የንስሐ የመጨረሻ ደረጃ ኃጢአትን መጥላት ነው። ይህም ኃጢአትን በፍጹም ልብ መጥላት፣ አለማሰብና ባሕርይን ለኃጢአት አለማስገዛት ማለት ነው። ይህ ደግሞ የፍጹምነት ደረጃ ነው። ሰው ኃጢአትን ከልቡ ከአ ስወገደና ፍጹም ካላሰባት ከፍጹምነት ደረጃ ደርሷልና ንጹሕ ነው ይባላል።

ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ውስጥ ከፍተኛውንና ዋነኛውን ኃጢአት ለመተው የሚችለው በክርስትና ሕይወቱ የዕለት ተዕለት ብስለት የሚገለጡለትን ረቂቃን ኃጢአቶች በመተው ነው። እግዚአብሔር የሰው

www.ethiopianorthodox.org

ልጆችን ሁሉ የሚወደን ስለሆነ በኃጢአታችን ብዛት ተስፋ ቆርጠን እንዳንጠፋ ሲል ኃጢአታችንን የሚገልጥልን ቀስ በቀስ ነው። በየጊዜው በሚያጋጥሙን መንፈሳውያን ክስተቶች ውስጥ፣ በምናነባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት:- በምናያቸው የተለያዩ ነገሮችና ወዘተ.ውስጥ ሊስተካከሉ የሚገባቸውን የተሰወሩ ኃጢአቶቻችንንና መንፈሳዊ ድክመቶቻችንን ይገልጥልናል። እነዚህን ኃጢአቶቻችንንና ድክመቶቻችንን የምናስወግድበት መንፈሳዊ መሣሪያ– ንስሐ እንደሚያስፈልግም እንረዳለን። ከዚህ የተነሣም በክርስትና ሕይወታችን ሁሉ እስከ መጨረሻ አብሮን የሚዘልቀውን የንስሐ ሕይወት እንጀምራለን። ምክንያቱም ዛሬ በአንዱ ኃጢአት የተሸነፈ ሰይጣን ነገ በሌላ ኃጢአት ሊፈትነን ይመጣልና ጦርነቱ አይቋረጥም – በጦርነቱ መውደቅ መነሣት ስላለ ንስሐም ማብቂያ የሌለው የመላሕይወት ባልንጀራ ነው።

ክፉ መሥራት ብቻ ሳይሆን መልካምን ለመሥራት አለመቻልም (አለመሥራት) ንስሐ የሚያስፈልገው ኃጢአት ነው። ሰው ለንስሐ የሚገባ ፍሬ ማፍራት ይጠበቅበታል። በማቴዎስ ወንጌል «እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ» ተብሏልና። ማቴ.፫፥፰። ለንስሐ የሚገባ ፍሬን ያደረገ ደግሞ በገላቲያ ፭፥፳፪ የተዘረዘሩትን የመንፈስ ፍሬዎች ያፈራል። እንግዲህ መንፈሳዊ ፍሬ ሊያፈራ ሲገባ ፍሬ የሌለው የሆነ ሰው ሊያደርግ የሚገባውን ባለማድረጉ ኃጢአተኛ ስለሆነ ንስሐ መግባት አለበት። ምክንያቱም በመጽሐፍ «በጎ ለማድረግ ዐውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው» ተብሏልና። ያዕ.፬፥፲፯።

ስለዚህ ንስሐ አንዴ ፈጽመን የምናልፈውና የምንዘነጋው ሳይሆን በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ከእኛ ጋር የሚኖር ነው።—ከሰው ወገን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በስተቀር በምድር ላይ አንድ ቀን እንኳ ቢኖር ከኃጢአት ነጻ የሆነ የለም። ሁላችን ኃጢአተኞች ስለሆንን ለሁላችን ንስሐ ያስፈልገናል። በየዕለቱ ከሥጋዊ ባሕርያችን የተነሣ ከኃጢአት የማንነጻ ከሆነ ንስሐ መግባት ለክርስቲያኖች ሁሉ የዕለት ተግባራችን መሆኑ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን:- እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» በማለት ይህን አረጋግጦልናል። ፩ዮሐ.፩፥፰።

## የኃጥአንና የቅዱሳን የንስሐ ሕይወት

ለሰው ሁሉ ንስሐ አስፈላጊ ነው። በየትኛውም ማዕረግና የቅድስና ደረጃ ያሉ ሰዎች ሁሉ ንስሐ ያስፈልጋቸዋል። እንዲህ ሲባል ግን በዓለም የሚኖሩ



የኃጥአን ንስሐና የቅዱሳን ንስሐ አንድ ዓይነት ነው ማለት አይደለም። በኃጥአንና በቅዱሳን ንስሐ መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ።

ኃጢአት የሠሩ በዓለም የሚኖሩ ሰዎች ንስሐ የሚገቡት ፍቅረ እግዚአብሔርን በማጣት ግልጽ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ትእዛዛት በመተላለፍ ስለሚሠሩት ኃጢአት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ቅዱሳን ንስሐ የሚገቡት ወደ ቅድስናና ፍጽምና በሚያደርጉት ጉዞ በሰውነት ባሕርይ የተነሣ ስላልፈጸሟቸው ጥቃቅን ነገሮች ነው። ልቡናቸው በፍቅረ እግዚአብሔር የተነደፈ ነውና አጉድለናል ወይም አልፈጸምንም ስለሚሉት ነገር ሁሉ ይፀፀታሉ ንስሐም ይገባሉ። ቅዱሳን ንስሐ ይገባሉ ስንል ኃጢአት ሠርተው ነው ማለት እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል።

ቤተ ክርስቲያን በየቀኑ ንስሐ የምንገባበትንና ኃጢአታችንን ስንናዘዝ የምናደርገውን የጸሎት ቅደም ተከተል (ሥርዓት) ሠርታልናለች። በዚሁ መሠረት:-

ሀ. ኃጢአትን ለመምህረ ንስሐ መናዘዝና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን (ቅጣትን) ለመቀበል መዘጋጀት በመዝሙር ፮ እና ፶ ያለውን መጸለይ።

ለ. ስለሠሩት ኃጢአት የእግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅ:-

ሐ. እግዚአብሔር በኃጢአቱ ላይ ተፀፅቶ ምሕረት የሚለምነውን ሰው ሁሉ እንዲጠብቅ ስለሌሎች ወገኖችም መጸለይ:-

መ. እግዚአብሔር የይቅርታንና የምሕረትን መንገድ እንዲመራ መለመን:- በመዝሙር ፻፲፰ ያለውን።

ሠ. ስለአለፈው ኃጢአት ራስን መውቀስ፤

ረ. መንፈስን ለንስሐ ማነቃቃት – ሞትን፣ ዳግም ምፅዓትንና የፍርድን ቀን እያሰቡ ይቅርታን መለመን ናቸው።

እነዚህን ስድስት ነጥቦች ዘወትር በጸሎታችን ያስታወስን እንደሆነ በየቀኑና በየሰዓቱ ንስሐን እንድናስብ ያደርጉናል። ስለዚህ ንስሐ መግባት የሚያስፈልግበትን ወቅት አልፌአለሁና ንስሐ መግባት አያስፈልገኝም የሚባልበት አንዳች ነገርና ምክንያት የለም:- ከፍጹምነት አልተደረሰምና። ከዚህ በመነሣት ነው ንስሐ ለክርስቲያን ሁሉ በዕለት ተዕለት ኑሮው ውስጥ ያስፈልገዋል የሚባለው።

www.ethiopianorthodox.org

## ፫. የንስሐ ጥሪ

የሰው ልጆችን አብዝቶ የሚወደውና መጥፋታቸውን የማይሻው ፈጣሪ ከጥልቅ ፍቅሩ የተነሣ ልጆቹን ዘወትር ወደንስሐ ይጠራቸዋል። እግዚአብሔርን የሚያስደስተው የሰው ልጆች ድኅነት በመሆኑ ወደንስሐ ከመጣራት አይሰለችም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው» በማለት ፈጣሪአችን ለሰው ያለውን ፍቅር ገልጦታል። ፩ጢሞ.፪፥፬። የሰዎችን መዳን መሻት ብቻም ሳይሆን ወደንስሐ እንዲመለሱ ከቸርነቱ የተነሣ ስለኃጢአታቸው ከመቅጣት ይታገሣል። ይህንንም ቅዱስ ጴጥሮስ «ነገር ግን ሁሉ ወደንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወድዶ ስለእናንተ ይታገሣል» በማለት አረጋግጦታል። ፪ጴጥ.፫፥፱። ይህ የእግዚአብሔር ትዕግሥት ሰፊ ነውና የጥሪውን ድምፅ የሚሰሙት ሁሉ ሊጠቀሙበት እንዲችሉ የፈጣሪ ፈቃዱ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በአቴና ከተማ በአርዮስፋጎስ መካከል የግሪክ ሰዎችን ሲያስተምር «እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት (በኃጢአት የመኖርን ዘመን) አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤» ብሏል። የሐዋ.፲፯፥፴። በሕዝቅኤልም እግዚአብሔር ሞት በሚስማማው ባሕርይ የተፈጠረውን የሰውን ሞት የማይወድ በንስሐ ወደ ሕይወት መመለሱ ግን የሚያስደስተው መሆኑን ተናግሯል:- «ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ። የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ። አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ:-...ስለምን ትሞታላችሁ የሚቼን ሞት አልፈቅድምና ይላል ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ።» ሕዝ.፲፰፥፴—፴፪።

አምላካችን እግዚአብሔር ይወደናል:- ከፍቅሩ የተነሣም በንስሐ አማካኝነት ከበደላችን ታጥበን የቸርነቱና የማታልፍ መንግሥቱ ተካፋይ እንድንሆን ይፈልጋልና ሰዎችን ወደንስሐና ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ከመጥራት አላቋረጠም። «እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድ ትመጣላችሁ...ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም።» በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የሚያሰማው የእግዚአብሔርን የንስሐ ጥሪ ነው። የሐዋ.፫፥፲፱—፳። ቅዱስ ያዕቆብም «ማንም ኃጢአተኛን



ቢመልስ ኃጢአቱን እንዲሸፍን ይወቅ» ብሏል። ያዕ.፭፥፳። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ (ሥግው ቃል) ከልዑል መንበሩ ወርዶ ሰው የሆነው:- የእኛን ኃጢአት ተሸክሞ ስለሞታችን ሞቶልን መከራን ተቀብሎ ያዳነን፤ ኃጢአታችንን ሸፍና ነውና እኛም ልንፈጽመው ያስፈልጋል።

እግዚአብሔር ወደንስሐ እንድንመለስ የሚያቀርብልን ጥሪ ለእኛ ያለውን ጥልቅ ፍቅር የሚገልጥ ነው። የሚከተሉት ጥቅሶች የዚህ ማረጋገጫ ናቸው።

> «ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።» ሚል.፫፥፯።

> «ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል — ንስሐ ግቡ ከጣዖቶቻችሁም ተመለሱ:- ፊታችሁንም ከርኩሰታችሁ ሁሉ መልሱ።» ሕዝ.፲፬፥፮።

> «አሁንስ ይላል እግዚአብሔር፥ በፍጹም ልባችሁ በጾምም በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ። ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ:- አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ፥ ቁጣው የዘገየ ምሕረቱም የበዛ ከክፋትም የተፀፀተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ።» ኢዩ.፪፥፲፪—፲፫።

እግዚአብሔር የሚያቀርብልንን የንስሐ ጥሪ አድምጠን ወደ እርሱ ብንመለስ፥ ኃጢአትን ትተን ንስሐ ብንገባ፥ ከኃጢአታችን ሊያጥበንና ሊያነጻን ፈቃዱ መሆኑን በቃል ኪዳን አጽንቶልናል። ለምሳሌም የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

> «ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ፤ የሥራችሁን ክፋት ከዓይኔ ፊት አስወግዱ:- ክፉ ማድረግን ተዉ:- መልካም መሥራትን ተማሩ።... ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጣለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደባዘቶ ትጠራለች።» ኢሳ.፩፥፲፮—፲፰።

> «ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ:- እናንተም ትጠራላችሁ:- ከርኵሰታችሁም ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ። አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ—አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ።» ሕዝ.፴፮፥፳፭—፳፯።

www.ethiopianorthodox.org

የምንኖረው በኃጢአት ዓለም በመሆኑ ከኃጢአትም ተለይተን በንጽሕና መኖር ባለመቻላችን ፈጣሪአችን እግዚአብሔር በሕይወት እንድንኖር – እንድንነጻና እንድንቀደስ አስፈላጊአችን ወደሆነው ንስሐ ይጠራናል። በዮሐንስ ወንጌል እንደተጻፈው የመድኃኒታችን ሰው መሆን ዋና ምክንያቱ የሰው ልጆችን ወደድኅነት መጥራት ስለሆነ «ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁምና» በማለት ጌታችን ድኅነትን ወደምታስጥ፥ ሥርየተ ኃጢአትን ወደምታስገኝ ንስሐ ይጠራናል። ዮሐ.፲፪፥፵፯። እንዲሁም ደግሞ በማርቆስ ወንጌል «ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለመድኃኒት አያስፈልጋቸውም፤ ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም።» በማለት ከኃጢአት የተነሣ በመንፈሳዊ ደዌ የተያዙትን ሕመምተኞች ከኃጢአት ደዌ ወደምትፈውስ ንስሐ የሚጠራን መሆኑን ይነግረናል። ማር.፪፥፲፯። ከዚህም በተጨማሪ መድኃኒታችን በኃጢአት ምክንያት የጠፋነውን የሰው ልጆች ወደሕይወት ሊጠራን እንደመጣ «የሰው ልጅ የጠፋውን ለማዳን መጥቷልና» በማለት ነግሮናል። ማቴ.፲፰፥፲፩።

ስለዚህ ንስሐ ስለእኛ ድኅነት – ወደ ተቀደሰውም ሕይወት እንድንገባ የተሰጠን እንጂ በላያችን በግድ የተጫነ ሸክም አለመሆኑን በመረዳት ልንጠቀምበት ያስፈልጋል። ንስሐ ብንገባ፣ የእግዚአብሔርንም ጥሪ ብንቀበል ምክሩንም ብንሰማ በሕይወት እንኖራለን – ከሞተ ነፍስም እንድናለን። እምቢ ብንልም ንስሐ ባንገባ የኃጢአታችንን ዋጋ በጊዜው ማግኘታችን የማይቀር ነው። የምንወደውን ለመምረጥም ሙሉ ነፃነት አለን። በነቢዩ ኢሳይያስ እንደበት «እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ:- እምቢ ብትሉ ግን ብታምፁም ሠይፍ ይበላችኋል:- የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሯልና።» በማለት ተነግሮናል። ኢሳ.፩፥፲፱–፳። እኛ ግን መልካሙን ብንሠራ የእግዚአብሔርንም የንስሐ ጥሪ ብንቀበልና ከኃጢአታችን ሥርየት አግኝተን በተቀደሰ ሕይወት በእግዚአብሔር መንግሥት ብንኖር መልካም ነው። ሐዋርያውም «እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን:- ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን እንለምናለን።» በማለት ከእግዚአብሔር ጋር እንድንታረቅ የጥሪውን ድምፅ አስተላልፎአል። ፪ቆሮ.፭፥፲፰–፳።

ሰዎች ከበደሉት ፈጣሪአቸው ከእግዚአብሔር ጋር ሲታረቁ የኃጢአት ማስተሥረያ ይሆን ዘንድ ቤተ ክርስቲያን ንስሐ ለሚገቡ ሰዎች ቅጣት እንዲሆን ቀኖና ትሰጣለች:- ይህም መልካም ሥርዓትና ጠቃሚም ነው። በፈቃዳችንም ይሁን እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ አስታውቆን ንስሐ



ብንገባ:- በማንኛውም መንገድ ብንፈጽመው ቀኖና ወይም ስለኃጢአት የምንቀበለው መንፈሳዊ ቅጣት ጠቃሚ ነው። ስለዚህ በሕይወታችን ውስጥ ንስሐና የእግዚአብሔር የንስሐ ጥሪ ፈንታ ሊሰጠው እንደሚገባ ለማጠየቅ «እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ:- በልባችሁም አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ:- እላችኋለሁና – ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር ይችላል። አሁንስ ምሣር በዛፎች ሥር ተቀምጧል:- እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል ወደ እሳትም ይጣላል።» በማለት አስገንዝቦናል። ማቴ.፫፥፰–፲። ቅዱሳንንም ቢሆን የሚያስደስታቸው የኃጢአተኛው ወደንስሐ መመለስ መሆኑን «አሁን ለንስሐ ስለአዘናችሁ ደስ ብሎኛል» ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክት ያስረዳናል። ፪ቆሮ.፯፥፱። ከዚህ ሁሉ በመነሣት ነው እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ቀኖና በንስሐ ለሚገኘው ሥርየተ ኃጢአትና ድኅነት ጠቃሚ ነው የምንለው።

በአጠቃላይ የንስሐ ጥሪ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ዋነኛውን ሥፍራ ይዞ ይገኛል። የሐዲስ ኪዳን መግቢያ የንስሐ ጥሪ ነው። ጸያሔፍኖት መጥምቀ መለኮትና ነቢየ ልዑል የተባለው ቅዱስ ዮሐንስ የስብከቱ መጀመሪያ ያደረገው «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» የሚለውን የንስሐ ጥሪ ድምፅ ነው። ዮሐ.፫፥፪። በዚህ አዋጅ መጥምቁ ዮሐንስ በንስሐ ያልታደሰና ያልነጻ ሰው ከእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የሌለው መሆኑን አስረድቷል። «እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ:- ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል:- እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል።» እያለ የንስሐ ጥምቀትን አጥምቋል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስብከቱን የጀመረው በንስሐ ጥሪ ነው። «ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር።» ተብሎ ተጽፏል። ማቴ.፬፥፲፯። በማርቆስም «ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና:- ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ።» ይላል። ማር.፩፥፲፭። ቅዱሳን ሐዋርያትም ደግሞ የንስሐን ጥሪ እንደአስተላለፉ መጽሐፍ ይነግረናል። «ወጥተውም ንስሐ እንዲገቡ ሰበኩ።» ማር.፮፥፲፪።

www.ethiopianorthodox.org

የመጀመሪያው የንስሐ ሰባኪ ኖኅ ነው። በኋላ ግን ብዙ ነቢያት መስለውታል። ለምሳሌ በኢሳ.፩፥፲-፳፤ በሕዝ.፲፰፤ በዮና.፫፤ በኢዩ.፪፤ በኤር.፴፩ የምናነበው ነቢያተ እግዚአብሔር ያስተጋቡትን የንስሐ ጥሪ ነው። የንስሐ ጥሪ ከፍ ብለን እንደተመለከትነው በወንጌል ደግሞ የበለጠ ግልተ ሆኖአል።

የንስሐን ጥሪ ማስተጋባትና ሰዎችን ለንስሐ መጥራት የበጎች ምእመናን ጠባቂዎች የሆኑ የመምህራን፤ የሰባክያን፤ የካህናተ ቤተ ክርስቲያን፤ የመንፈሳውያን አማካሪዎች ተግባርና ኃላፊነት ነው። ይህንም የተለያዩ ቅዱሳን አበው ያረጋግጡልናል። «ሁል ጊዜ ኃጢአትህን እያሰብክ ንስሐ ግባ» (ቅዱስ እንጦንስ)

> «ኃጢአትን ባትሠራት መልካም ነው፤ ኃጢአት ከሠራህ ሳትቆይ ንስሐ ብትገባ መልካም ነው። ንስሐ ከገባህ ዳግመኛ ወደ ኃጢአት ባትመለስ መልካም ነው። ወደኃጢአት ካልተመለስክ ይህ በእግዚአብሔር ዕርዳታና ቸርነት መሆኑን ብታውቅ መልካም ነው። ይህንን ካወቅህ ስለአለህበት ሁኔታ እግዚአብሔርን ብታመሰግን መልካም ነው።»—(ቅዱስ ባስልዮስ)

> «በቀን ውስጥ ባሉት ሃያ አራት ሰዓታት ሁሉ ንስሐ መግባት ያስፈልገናል። ለአንድ ሰዓት እንኳ ራስህን ያልገዛህበትን ቀን፤ ስለኃጢአት ያሰብክበትን ቀን፤ በደልህን ያላሰብክበትን ቀንና፥ ራስህን ለማስተካከል ያልሞከርክበትን ቀን ከሕይወትህ ዘመን ውስጥ አትቁጠረው:- አልተጠቀምክበትምና። (ቅዱስ ይስሐቅ)

በዚህም የንስሐ ጥሪ ለማንኛውም ክርስቲያን የሚቀርብና ሊቀርብም የሚገባ የተቀደሰ የእግዚአብሔር ጥሪ መሆኑን እናስተውላለን። ይህ የንስሐ ጥሪ እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ብዙ ሰዎች ቀርቦላቸው ተጠቅመውበታል። ለምሳሌ በፈቃደ እግዚአብሔር የተቀባው ንጉሥ ዳዊት በበደለ ጊዜ የእግዚአብሔር የንስሐ ጥሪ በነቢዩ በናታን አፍ ወደ እርሱ መጣች - እርሱም በጥሪው ተጠቅሞ ንስሐ በመግባት ከፈጣሪው ጋር ለመታረቅ በቅቷል። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚያቀርበው የንስሐ ጥሪ እርሱ ለልጆቹ የአዳም ዘሮች ሁሉ ያለውን አክብሮትና ጽኑ ፍቅር የሚገልጥ ነው።



እግዚአብሔር አምላክም የሚያቀርብላቸውን የንስሐ ጥሪ ተቀብለው ምሕረትና ይቅርታ ድኅነትንም ሽተው ወደ እርሱ የሚመለሱትን ሁሉ ይቀበላል። ለዚህ ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፤

- የጠፋው ልጅ — ሉቃ.፲፭።
- አምስት ባሎች የነበሯት ሣምራዊት ሴት — ዮሐ.፬።
- በጌታ ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ — ሉቃ.፳፫፥፳፱።
- በተሰቀለ ጊዜ ስለሰቀሉት የሚያደርጉትን አያውቁምና ብሎ መድኃኒታችን የጸለየላቸው አይሁድ — ሉቃ.፳፫፥፴፬።
- ቀራጩ ዘኬዎስ — ሉቃ.፲፱፥፲።
- ቀራጩና በኋላ ሐዋርያ የሆነው ማቴዎስ የተባለው ሌዊ.ማቴ.፲፥፫። ማቴ.፱፥፱።

የሚከተለው የጌታችን አባባል ወደ እርሱ የሚመጡትን ኃጢአተኞች የሚቀበላቸው መሆኑን ያረጋግጥልናል።

«ወደ እኔ የመጣውን ከእኔ ከቶ አላወጣውም»። ዮሐ.፮፥፴፯። ይህን ሰው ፍለጋ ግን ዘወትር በልቡና ደጃፍ ቆሞ በንስሐ ጥሪ ያንኳኳል:- የሚከፍትለት ቢያገኝ። ራእ.፫፥፳።

የእግዚአብሔር ቸርነት ከሠራነው ኃጢአት ሁሉ በላይ ነው። የኃጢአታችንንና የበደላችንን ብዛት ከእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት ጋር ስናነፃፅረው በውቅያኖስ ባሕር ላይ እንደወደቀች ቆሻሻ ነው። ትንሺ ቆሻሻ ውቅያኖሱን እንደማታደፈርሰውና የውቅያኖሱ ባሕር እርሷን ከአሟሟት በኋላ ንጹሕ እንደሚሆን ሁሉ እግዚአብሔርም እኛ የምንሠራውን ኃጢአት ሁሉ ሳይቆጥር በቸርነቱ የሚቀበለን እርሱ በምሕረቱ ያድነናል። ከብዙ ኃጢአታችን በኋላ በንስሐ ወደ እርሱ መመለሳችንን መቀበሉ ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር የሚያመለክት ነው።

ስለዚህ የኃጢአታችንን ብዛትና ክብደት ኃጢአተኞችን ለማንጻት ለድኅነተ ዓለም ከፈሰሰው የክርስቶስ ደም በላይ አድርገን መመልከት የለብንም። ከእግዚአብሔር ፍቅርና ከቸርነቱም በላይ አድርገን ማሰብ የለብንም። አንድ የቀድሞ ቅዱስ አባት «እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር ሊያሸንፍ የሚችል ኃጢአት ከቶውኑ የለም» እንዳሉ ኃጢአታችን ብዙ ነው ብለን ተስፋ ሳንቆርጥ የቀረበልንን የንስሐ ጥሪ በማድመጥ ወደ ፈጣሪአችን ቸሩ እግዚአብሔር ልንመለስ ይገባናል።

www.ethiopianorthodox.org

## ፬. ተስፋ መቁረጥ አይገባም

ተስፋ መቁረጥ ብዙ ሰዎች የሚፈተኑበት ችግር ነው። ተስፋ የመቁረጥ ፈተና በሰዎች መንፈሳዊ አመለካከትውስጥ በተደጋጋሚ የሚያመነጫቸው ብዙ ጥያቄዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል የሚከተሉትን እንመለከታቸዋለን።

### ሀ. የምጠቅም አይደለሁምና ተስፋ የለኝም

ተስፋ መቁረጥ የአጋንንት ውጊያ ነው። ተስፋ በማስቆረጥ ንስሐ እንዳንገባ ለማድረግ ሰይጣን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ስለዚህ ይህን ውጊያ አስቀድመን ማወቅና በመዳን ተስፋ ልንጸና ይገባናል። በነቢዩ በሚክያስ አንደበት «...ጠላቴ ሆይ ብወድቅ እነሣለሁና፤ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልህ...» በማለት የተነገረው ተስፋ መቁረጥ ሰይጣንን የሚያስደስተው ስለሆነ በተስፋ እንድንጸና ለመምከር ነው። ሚክ.፯፥፯–፲። ተስፋ በመቁረጥ ንስሐ አለመግባት በኃጢአት ከመውደቅ የበለጠ አደገኛ መሆኑን ማስተዋል ይገባል። ተስፋ በመቁረጥ ጌታውን አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ወደቀ፤ ሞተም። ተስፋ መቁረጥ ወደጠለቀ ገቢረ ኃጢአት የሚመራ በመሆኑና ተስፋ የሚቆርጥ ኃጢአተኛ ሰውም ከመጥፎ ወደ ከፋ ኃጢአት የሚያመራ ስለሆነ ምንም ፈተና ቢበዛ ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ በተስፋ መቆምን መምረጥ ጠቃሚ ነው። ሰይጣን በሠራው ኃጢአት የተነሣ ንስሐ ለመግባት ተስፋ ያስቆረጠውን ሰው ወደ ከባድ ኃጢአት እንዲያመራ፤ ወደንስሐም እንዳይመለስ፤ ከንስሐ ሓባቱም እንዲሸሽ፤ ከቤተ ክርስቲያንም እንዲቀርና በኃጢአት እንዲኖር ያደርገዋል። አባቶቻችን ነቢያት በተስፋ መቁረጥ የጦር ሜዳ ከአጋንንት ጋር ብዙ ተዋግተዋል። ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊትም «አቤቱ የሚያስጨንቁኝ ምንኛ በዙ:- በእኔ ላይ የሚቆሙት ብዙ ቻው። ብዙዎች ነፍሴን አምላክሽ አያድንሽም አልዋት። አንተ ግን አቤቱ መጠጊያዬ ነህ። ክብሬንና ራሴንም ከፍ ከፍ የምታደርገው አንተ ነህ።» በማለት የተናገረው ቃል የዚህን ውጊያ ጽናት ያሳያል። መዝ.፫፥፩–፫። ቅዱስ ዳዊት በመውደቁ ተስፋ አልቆረጠም:- ወደ ፈጣሪው ተመለሰ፤ እግዚአብሔርም ወደ ክብሩ መለሰው። ዳዊትን ብቻ ሳይሆን ብዙዎችን ስለዳዊት ብሎ ደግሞ አድኗቸዋል። ፩ነገ.፲፩፥፴፪፤ ፴፬፤ ፴፮። ስለዚህ የኃጢአት ሸክም በከበደበትና በንስሐ መመለስ መጥፎ ወይም ዋጋቢስ



በሚመስልበት ጊዜ ውጊያው የጠላት ሰይጣን መሆኑን አስተውሎ ተስፋም ሳይቆርጡ በትዕግሥት በንስሐ ለመመለስና የእግዚአብሔርን ምሕረት ለማግኘት የበቁትን ቀደምት አበው ማስታወስና ልቡናን በተስፋ ማጽናት ተገቢ ነው።

እኛ በራሳችን ተስፋ ብንቆርጥም እግዚአብሔር ግን እኛን ለማዳን ተስፋ አይቆርጥም። የእግዚአብሔር የጸጋ ሥጦታ የሆነው የመዳን ተስፋ በውስጣችን ቢሠራ ተስፋ አንቆርጥምና ራሳችንን በመናቅ ተስፋ መቁረጥ አይገባም፥ ይልቁኑ ለመዳን በትጋት ወደንስሐ መመለስ እንጂ።

### ለ. ከወደቅኹበት ኃጢአት በፍጹም ልላቀቅ ስለማልችል እንዴት ንስሐ እገባለሁ?

ውጊያው የእግዚአብሔር ነውና እርሱም ይዋጋልናልና መፍራትና ማፈር የለብንም። ፩ሳሙ.፲፯፥፵፯። ሁል ጊዜ የእግዚአብሔርን ኃይል እንጂ የራሳችንን ጉልበት መመልከት የለብንም። በኤርምያስ እንደተጻፈው «አንተ እግዚአብሔር አምላኬ ነህና መልሰኝ እኔም እመለሳለሁ» ማለት ያስፈልጋል። ኤር.፴፩፥፲፰። እግዚአብሔርን ተስፋ አድርገን ኃጢአትን ብንዋጋ እርሱ ያሸንፍልናልና ከመፍራትና ከማፈር የተነሣ ንስሐ ከመግባት ወደ ኋላ ማለት አያስፈልግም። በእርሱ በተማመንን መጠን እግዚአብሔርም ኃይሉንና ብርታቱን ሊሰጠን የታመነ ነው።

### ሐ. ያለሁበት ሁኔታ ንስሐ ለመግባት የሚያስችል አይደለምና ምንም ተስፋ የለኝም

እግዚአብሔር ለመካኗ ሴት የተናገራትን ማሰብ ይገባል። «አንቺ ያልወለድሽ መካን ሆይ ዘምሪ» ኢሳ.፶፬፥፩። ይህ ቃል የሚያመለክተው ሴቲቱ መውለድ አልችልም በማለት ተስፋ ቆርጣ ከማዘን ይልቅ በእግዚአብሔር ተስፋ እንድታደርግ የተነገራት መሆኑን ነው። ስለዚህ በእኛ ግምት ብቻ ፈጽሞ የመዳን ተስፋ እንደሌለን ማሰብ አይገባም። ተስፋ የሚያስቆርጠውን ነገር ለእግዚአብሔር መተው ተገቢ ነው። እርሱ በመመለሳችን ተስፋ አለውና።

### መ. ከኃጢአቴ ብዛት የተነሣ ንስሐም አልገባም ጥረትም አላደርግም

ይህ አባባል ወይም ሃሳብ ለሕይወት መጥፎ አዘማሚያ ነው። እዚህ ደረጃ ቢደረስም ተስፋ መቁረጥ ግን አይገባም። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ እኛን ለማዳን ፈቃዱ ነውና። ቅዱሳን፤ ጻድቃንና መላእክት ሁሉ ስለእኛ ነፍስ መዳን ይጸልያሉና:- ይማልዱልናልና:- ንስሐን እንድንፈልጋት

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርም ይረዳናል። በመጽሐፍም «ስለበጎ ፈቃዱ መፈለግን ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና» በማለት ተጽፏል። ፊል.፪፥፲፫። ስለዚህ እኛ ደግሞ አምላካችን እግዚአብሔርን ወደ አንተ መመለስን እፈልጋለሁና መመለሱን ስጠኝ እንበለው።

ሠ. ከዚህ በኋላ በውኑ የቀረውን የሕይወቴን ዘመን ሁሉ ከኃጢአት ተለይቶ መኖር ይቻለኛልን? ልቤ ኃጢአትን ስለሚወድ ሥጋዬን ማሸነፍ እችል ይሆን? ንስሐ ብገባም ዳግመኛ ወደኃጢአት መመለሴ አይቀርም ይባል ይሆናል።

ከንስሐ በፊትና በኋላ የሚኖረን ልብ አንድ ዓይነት እየመሰለን ተስፋ በመቁረጥ ማሰብ የለብንም። እግዚአብሔር ከንስሐ በኋላ አዲስ ልብ ይሰጠናልና። እርሱ «አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ» ብሏል። ሕዝ.፴፮፥፳፮። እግዚአብሔር ንስሐ በገባን ጊዜ የኃጢአትን ፍቅር ፈጽሞ ከእኛ ያጠፋል:- ስለኃጢአትም ፈጽሞ እንዳናስብ ያደርገናል። ሕይወታችንንም ይለውጠዋልና በዚህ ምክንያት ንስሐ ከመግባት አንዘግይ።

ረ. ምንም እንኳ ንስሐ ብገባ የአእምሮዬ ሃሳብ ከቀድሞው ሊለወጥ አይችልም ይባል ይሆናል

ነገር ግን አንፍራ:- እግዚአብሔር ሃሳባችንን ሁሉ ያነጻዋል። የታደሰ ልቡናንም ይሰጠናል። ሮሜ.፲፪፥፪። ወደንስሐ የተመለሱ ሰዎች በታላቅ መንፈሳዊ ኃይል እንደሚታደሱ አንዘንጋ። ንስሐ የሚገባ ሰው ፍቅሩ ከፍተኛ ነው። ከኃጢአት የተመለሰችው ሴት ለዚህ ማስረጃ ልትሆን ትችላለች። ሉቃ.፯፥፵፯።

ሰ. አሁንም – እግዚአብሔር ይቅር ይለኝ ይሆን? እኔንስ ይቀበለኝ ይሆን እንላለን

እግዚአብሔር አምላካችን ግን «ወደ እኔ የመጣውን ከእኔ ከቶ አላወጣውም» ብሏል። ዮሐ.፮፥፴፯። መዝ.፻፫። እግዚአብሔር ወደእርሱ በመጣን ጊዜ መቀበል ብቻ ሳይሆን በፍቅሩ ያጥበናል:- ከበረዶም ይልቅ ነጭ እንሆናለን። መዝ.፶፥፯። የቀደመ ኃጢአታችንንም ይቅር ይለናል። እርሱ «በደላቸውን እምራቸዋለሁና:- ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ ደግሜ አላስብምና» በማለት ተናግሯል። ኤር.፴፩፥፴፬። በሕዝቅኤልም «እርሱ ከኃጢአቱ ተመልሶ ፍርድንና ቅን ነገርን ቢያደርግ:-...የሠራው ኃጢአት ሁሉ አይታሰብበትም:- ፍርድንና ቅን ነገርን አድርጓል በእርግጥ በሕይወት ይኖራል።» ብሏል። ሕዝ.፴፫፥፲፬–፲፮። ዕብ.፰፥፲፪። እግዚአብሔር



ሰው የሆንላትና በመስቀል ተሰቅሎ የሞተላት ነፍስ የተወደደች መሆኗን እናስብ። ስለዚህም እግዚአብሔር ይቅር አይለኝም ማለትን ትተን በንስሐ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለማግኘት ተስፋችን ጽኑ ይሁን።

ሸ. እግዚአብሔር ይቅር ሊለኝና ሊቀበለኝ ቢወድም ኃጢአቴ ግን የከፋ ነው ይባል ይሆናል

የእግዚአብሔር ቃል ግን «እላችኋለሁ ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ይቅር ተብለዋል። እግዚአብሔር ወልድን አላውቀውም ያለው ቅዱስ ጴጥሮስ እንኳን ንስሐ ገብቶ ይቅርታን አግኝቷል። የኃጢአትን መጠንና ብዛት ሳያይ ወደ እርሱ የተመለሱትን ሁሉ ይቅር ለማለት እግዚአብሔር የታመነ ነው። የጥጃ ምሥል ሲሠራ የተባበረው ካህኑ አሮን ንስሐ በገባ ጊዜ ይቅርታን አግኝቷል። ዘጸ.፴፪፥፪–፭። ታላቁ ካህን ኢያሱም ንስሐ በገባ ጊዜ እግዚአብሔር ተቀብሎታል። ዘካ.፫፥፩–፭። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቸርነት እናስብ እንጂ በኃጢአታችን ክብደት ተስፋ አንቁረጥ፣ በእግዚአብሔር ፊት ሁሉ ቀላል ነውና።

ቀ. በኃጢአት ብዙ ቆይቻለሁና ዛሬም ለንስሐ ዕድል አለኝን ይባል ይሆናል

እግዚአብሔር ጊዜው ቢዘገይም ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ ይቀበላል። በአሥራ አንድ ሰዓት የመጡትን ተቀብሏልና። ማቴ.፳፥፱። በመጨረሻ ሰዓት ንስሐ የገባውን ፈያታዊ ዘየማን (ከጌታ ቀኝ የተሰቀለውን ወንበዴ) ተቀብሏልና። ሉቃ.፳፫፥፵፫። ሥጋውያን በሥጋም የምንኖር እስከሆንን ድረስ ንስሐ የመግባት ዕድላችን በሩ ክፍት ነው። በሲኦል ወይም በገሃነም ግን ንስሐ የመግባት ተስፋ የለም። ሉቃ.፲፮፥፳፮። ስለዚህ ብዙ ዘመን በኃጢአት ኖሬአለሁና የንስሐ ዕድሌ ተሟጧል ከማለት ይልቅ የእግዚአብሔርን ምሕረት ተስፋ ማድረግ የሚበጅ መሆኑን መዘንጋት አይገባም።

በ. ኃጢአቴ መንፈስ ቅዱስን እንደመሳደብ ይቆጠርብኛል በማለት ይፈራ ይኾናል

ነገር ግን እስከ መጨረሻው እግዚአብሔርን አላውቅም ካላንና በመጨረሻው ሰዓትም ቢሆን ወደ ፈጣሪን ወደ እግዚአብሔር ከተመለስንና ንስሐም ከገባን ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ አስገዛን ማለት ነውና ኃጢአታች ይሠረይልናል። ስለዚህ የሆነ ያልሆነ ምክንያት እየፈጠረ ንስሐ እንዳንገባ የሚያዘናጋን ሰይጣን መሆኑን በማወቅ ፈንታ ሳንሰጠውና ተስፋ ሳንቆርጥ ንስሐ መግባትን ገንዘብ ማድረግ ያስፈልጋል። ያለንስሐ ሥርየተ ኃጢአት አይገኝምና።

www.ethiopianorthodox.org

## ፭. ንስሐ – በግል ትጋትና በእግዚአብሔር ረድኤት መካከል

እግዚአብሔር ንስሐ የሚገቡትን ይቀበላል ብለን ስንናገር ተነሣሒው ሰው ይሰንፋል፣ ያንቀላፋል፣ እግዚአብሔር እስኪቀሰቅሰው ድረስ ቁጭ ብሎ ይጠብቃል ማለት አይደለም። ይህን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም» ይላል። ዕብ.፲፪፥፬። በዚህ አባባልም ሰው እስከ ደም መሥዋዕትነት ድረስ ኃጢአትን መዋጋት፤ የኃጢአትንም ሃሳብ ከልቡናው አውጥቶ መጣልና መንፈሳዊ ጥንካሬን ገንዘብ ማድረግ እንደሚገባው እንማራለን። ከዚህም በተጨማሪ በኤፌሶን ምዕራፍ ስድስት ወደተገለጠው ውጊያ ይገባል። «ስለዚህ የዲያብሎስን ሽንገላ ለመቃወም የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ልበሱ...በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ:- ሰይጣን የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ነውና።» ኤፌ.፮፥፲–፲፰። ስለዚህ በሃይማኖት ሆነን በጽናት የዲያብሎስን ውጊያ እንድንቃወም «በመጠን ኑሩ:- ንቁም ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ በሙሉ ያን መከራ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት» በማለት ይመክራል። ፩ጴጥ.፭፥፰–፱።

እግዚአብሔር እንድንጸና ይሻል፤ ስንጸናም በረድኤቱ ኃይል ይሆነናል። ስለዚህ ኃጢአትን በጽናት በመዋጋት ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ማሳየት ያስፈልጋል። እግዚአብሔርም የኃጢአትን ብርታት ለመቋቋም የሚያስችል ኃይልና ጽናት እንዲሰጥ አብዝቶ መጸለይ ይገባል። የተፈተነና የጸና ሰው የጌታ መከራ ተካፋይ ነው።

የጠፋው ልጅ አባቱ እርሱን ፍለጋ ወደአለበት ማለት በኃጢአት ወደሚኖርበት ሥፍራ እስኪሄድ አልጠበቀም። ነገር ግን ወደልቡ ተመልሶ የነበረበትን ሕይወት አስታወሰ – የሚሻለውንም መፍትሔ ስለዐወቀ ወደ አባቱ ተመለሰ:- ልጁ ወደ እርሱ በመጣ ጊዜም አባቱ ተቀበለው። ሉቃ.፲፭፥፲፩–፴፪። የነነዌ ሰዎችም ማቅ ለብሰው አመድ ነስንሰው ራሳቸውን በፍጹም በማዋረድ ስለኃጢአታቸው (በኃይል) በማልቀስ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ:- እግዚአብሔርም ተቀበላቸው። ዮሐ.፫። ሚል.፫፥፯። ኢሳ.፩፥፲፮። ኢዮ.፪፥፲፪–፲፫። ስለዚህ በንስሐ ሕይወት ውስጥ ኃጢአተኛው የእግዚአብሔርን ምሕረትና ይቅርታ – የኃጢአትንም



ሥርየት ለማግኘት የበኩሉን ጥረት ማድረግና ለመዳንም ንስሐ ግዴታው መሆኑን ማወቅ አለበት። በዚህም ንስሐ የሰው ሁሉ መንፈሳዊ ግዴታ መሆኑን እናስተውላለን።

ንስሐ ስንገባ የሚኖረን ለውጥ ውስጣዊ የሕይወት ለውጥ መሆን አለበት። ያለውስጣዊ ለውጥ በውጭ በታይታ መመለስ ብቻ እርካታ አግኝተን እንዳንቀር ያስፈልጋል። በንስሐ ዋናው ተግባራችን በውስጣችን ማለት በልቡናችን የመንፈስ ቅዱስ ረድኤትና በረከት እንዲሞላና በእኛ ሕይወት ውስጥም የሚሠራውን ሥራ በአኩቴት በመቀበል – ውስጣዊ የሕይወት ለውጥ እንዲኖረንም መንፈሳዊ ተጋድሎ ማድረግ ነው።

## ፮. የንስሐ አስፈላጊነት

ያለንስሐ ድኅነት የለም። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ» በማለት ያስገነዘበው ለዚህ ነው። ሉቃ.፲፫፥፫። በቆርኔሌዎስ ቤት ተሰብስበው የነበሩ ሰዎችም የቅዱስ ጴጥሮስን ስብከት በሰሙ ጊዜ «እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ለሕይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው» በማለት እምነታቸውን የገለጡት ድኅነት በንስሐ መሆኑን በመረዳታቸው፣ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን በማወቃቸው ነው። የሐዋ.፲፩፥፲፰።

አንዳንድ ሰዎች ጌታችን ለይቅርታና ለድኅነት ደሙን አፍስሶ፣ ሥጋውን ቆርሶ፣ ነፍሱን ክሶ አድኖናልና ንስሐ ለምን እንገባለን የክርስቶስ ደም አይበቃምን ይላሉ። እንደሚከተለውም እንመልስላቸዋለን።

ንስሐ የእኛን ኃጢአት ለመደምሰስ የፈሰሰልንን የክርስቶስን ደም ለይቅርታና ለኃጢአታችን መደምሰሻ (ይቅር የምንባልበት እንዲሆን) ያደርጋል። መዳን ለሰው ሁሉ ነው። የክርስቶስ ደምም ለሁሉም ነው። ነገር ግን ሊቀበሉትና ሕይወት ሊያገኙበት የሚችሉት ንስሐ የገቡ ብቻ ናቸው። የክርስቶስ ደም ከማንኛውም ኃጢአት ያነጻናል። ነገር ግን ይህን ሥርየት የምናገኘው በኃጢአቶቻችን ላይ የተናዘዝንና ንስሐ የገባን እንደሆን ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ «...የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃናል። ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።» በማለት የመሰከረው። ፩ዮሐ.፩፥፯–፱።

www.ethiopianorthodox.org

ንስሐ ጥምቀትን ትቀድማለች መጀመሪያ ላልተጠመቁ ሰዎች በንስሐ ውስጥ ይቅርታ አለና። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመጀመሪያው ስብከቱ «ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ» ያለው ለዚህ ነው። የሐዋ.፪፥፴፰። ቤተክርስቲያንም ጎልማሶችን ስታጠምቅ በመጀመሪያ ሃይማኖታቸውን እንዲያውቁ ካስተማረች በኋላ ንስሐ እንዲገቡ በማድረግ ነው። ንስሐ ያልገቡትን ማጥመቅ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የተከለከለ ነው። ንስሐ በውስጡ ይቅርታን ብቻ ሳይሆን እምነትንም ይይዛል። በወንጌል «ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ።»ይላልና። ማር.፩፥፲፭። ያለንስሐ የሆነ እምነት ማንንም አያድንም። ንስሐ ከቅዱስ ቁርባን በፊት ነው። ንስሐ ያልገባና ከኃጢአቱ ሥርየትን ያላገኘና ያልነጻ ሰው ቅዱስ ቁርባንን መቀበል የለበትም። በመጽሐፍ «ቅዱሳን ሁኑ:- ከእኔም ጋር ወደ መሥዋዕቱ ኑ።» ፩ሳሙ.፲፮፥፭። በማለት የተጻፈው ቃል የሚያስረዳው ወደተቀደሰው መሥዋዕት ከመቅረብ አስቀድሞ ከኃጢአት መንጻት የሚገባ መሆኑን ነው። ከዚህ ጋር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ:- «ስለዚህ ሳይገባው ይህን ሕብስት የበላ ወይም የጌታን ደም የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። ሰው ግን ራሱን ይፈትን፤ እንዲሁም ከሕብስቱ ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና።» በማለት የተናገረው ቃል ቅዱስ ቁርባን ከንስሐ በኋላ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

ንስሐ ከሁሉም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በፊት ነው። ምክንያቱም ምሥጢራትን ሁሉ ለመፈጸም የሚያበቃው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንዲሁም በረከት የሚገኘው በንስሐ ስለሆነ ነው። በሉቃስ ወንጌል ታሪኩ የተመዘገበው የጠፋው ልጅ ወደአባቱ ቤት ለመግባት የቻለው ንስሐ ከገባ በኋላ ነው። ሉቃ.፲፭።

ንስሐ ኃጢአትን ለመደምሰስ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ እጅግ አስፈላጊና ዓይነተኛ መፍትሔና መሣሪያም ነው። በመጽሐፍም «ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም» በማለት መጻፉ ይህንኑ ለማስተማር ነው። የሐዋ.፫፥፲፱። ቅዱስ ይስሐቅ «ንስሐ ካልተገባበት ኃጢአት በቀር እግዚአብሔር ይቅር የማይለው የለም» በማለት የተናገረው ቃልም ይህንኑ የሚያጸና ነው።

ስለዚህ ከጥምቀት በፊትም ሆነ በኋላ ንስሐ ለክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። ከጥምቀት በፊት



ሰውነትን ለማንጻትና ለጥምቀት ለመዘጋጀት ከጥምቀት በኋላ ደግሞ የተሠራውን ኃጢአት ለመደምሰስ ንስሐ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው።

## ፯. የንስሐ መሰናክሎች (እንቅፋቶች)

ሰይጣን ከሚዋጋቸው የድኅነት መንገዶች ውስጥ ንስሐን የሚያክል የለም። ምክንያቱም ንስሐ ጠላት ዲያብሎስ የክርስቲያኖችን ሕይወት ለማጥፋት የገነባውን የኃጢአት ሕንፃ ሁሉ በእግዚአብሔር ቸርነት እንዳልነበረ በማድረግ ስለሚያፈርስበት ነው። ከዚህ የተነሣ የሰው ልጅ ንስሐ እንዳይገባ፤ ቢገባም ቶሎ እንዳይሆን የተቻለውን ከማድረግ ፈጽሞ አያርፍም። ጠላት ዲያብሎስ ሰዎችን በኃጢአት ለማቆየት ወይም ንስሐ የሚገቡበትን ጊዜ ለማራዘም ከሚጠቀምባቸው የንስሐ መሰናክሎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ።

ሀ. እንቅፋት መፍጠር:- እነዚህ ድንገተኛ ፈተናዎች ወይም አጋጣሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ አጋጣሚዎች ወይም ፈተናዎች ተነሳሒው በድፍረት ወደንስሐ እንዳይመጣና ከኃጢአቱ እንዳይመለስ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ናቸው:- ይህ ተጽእኖም ንስሐ የሚገባበትን ጊዜ በማራዘም ዓይነተኛ የንስሐ መሰናክል ነው።

ለ. ኃጢአተኛው ራሱን ከእርሱ የበለጠ ኃጢአት ሠሩ ከሚላቸው ጋር በማነፃፀር የተሻለ እንደሆነ እንዲገምትና ንስሐም እንደማያስፈልገው ራሱን ማሳመን:- ቅድስና ግን ከኃጢአተኛ ሕይወት ጋር ሊነፃፀር አይገባም። ኖኅ በብዙ ኃጢአተኞች መካከል ቅዱስ እንደነበረና በእግዚአብሔር ትእዛዝ መኖርን ከኃጢአት ጋር ሳያነፃፅር ለቅድስና እንደበቃ ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል። የዮሴፍ፤ የሎጥና የሙሴ ሕይወትም የዚህ ማረጋገጫ ነው።

ሐ. ከሥጋ ድካም የተነሣ በአካባቢ ተጽእኖ መመራት:- ተነሳሒው ሰው በዓለም የማይታለል ጽኑ አቋም እንዲኖረው ያስፈልጋል። ቅዱስ ጳውሎስ «ይህን ዓለም አትምሰሉ» እንዳለ። ሮሜ.፲፪፥፪። ዓሣ ትንሽ ሲሆን ማዕበል በሚያናውጠው ባሕር ውስጥ ይዋኛል። ክርስቲያንም እንዲህ ሊሆን ይገባዋል። ዳካማ ሥጋን ቢለብስም ፈተናውን ተቋቁሞ ለንስሐ መብቃትና በመንፈሳዊ ሕይወት መኖር ይገባዋል።

መ. መዘግየት:- ዲያብሎስ ንስሐ እንዳንገባ የሚዋጋን በቀጥታ አይደለም። ነገር ግን የተለያዩ ስውር ፈተናዎችን እየደቀነ ንስሐ

www.ethiopianorthodox.org

እንዳንገባ ያዘገየናል። መዘግየት ከሚያስከትለው አደጋ መካከል አንዱ ለንስሐ የተዘጋጀውን ልቡና መለወጥና ለንስሐ ያለውን ዕድል ማጥፋት ነው። ኃጢአት ወዲያው ካልተቀጨና ከቀጠለ ሥር ይሰዳል:- ከዚያም ለንስሐ የተዘጋጀውን ፍላጎት ሊያጠፋው ይችላል።

ሠ. ተስፋ መቁረጥ:- ይህ ንስሐ የማይቻልና ሊደረግ የማይሞከር እንደሆነ አድርጎ ማሰብ ነው። ሰይጣን በኃጢአት ከመውደቃችን በፊት የእግዚአብሔርን ቸርነትና ይቅርታ በማሰብ ኃጢአት እንድንሠራ ያደርገናል፣ ከሠራነው በኋላ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፍርድና ጨካኝ እንደሆነ ያሳስበናል ንስሐ እንዳንገባም ተስፋ ያስቆርጠናል።

ረ. ተነሳሒው ራሱን በማድነቅ (በመመጻደቅ) ኃጢአተኛ እንዳልሆነ እንዲያስብ በማድረግ:- ንስሐ ከአንድ በኃጢአት የተበላሸ ሕይወት ወደሌላ አዲስ የተቀደሰ ሕይወት የሚደረግ መንፈሳዊ ለውጥ ነው። ሰውም መልካም ነው ብሎ የሚገምተው የራሱ ሕይወት በኃጢአት የተዳደፈ መሆኑን ካላመነ በቀር ሊለወጥ አይችልም። በሕይወቱ ውስጥ መንፈሳዊ ለውጥ ከሌለ ደግሞ ስለንስሐ አያስብም:- ንስሐም አይገባም። ስለዚህ ራሱን የማይመረምር:- ሌሎችም ስለእርሱ የሚነግሩትን የማይሰማ ሰው ንስሐ ሊገባ አይችልም። ንስሐ ለትሑታን ቀላል ናት:- ራሳቸውን ትልቅ ለማያደርጉና ቅዱሳን እንደሆኑ ለሚያስቡ ትዕቢተኞች ግን ከባድ ናት። ኃጢአቱን ለሚመለከት ቀራጭ ቀላል ናት:- ኃጢአተኛ እንዳልሆነ ላሰበው ስምዖን ግን ከባድ ናት። ሉቃ.፯።

ንስሐ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ዐውቀው ለሚናዘዙባት ሰዎች ቀላል ናት:- ንስሐ መግባት የሚከብዳቸው ሰዎች ግን የሠሩትን ኃጢአት መልካም በማስመሰልና እንደጽድቅ ሥራ በመቁጠር ለኃጢአታቸው ማካካሻን ይፈልጋሉ። እነዚህ ኃጢአታቸውን አይናዘዙም:- ንስሐም አይገቡም።

በአደባባይ ለሚቆሙና በሕዝብ ፊት ለሚያገለግሉ ሰዎች ንስሐ እንደሚያስፈልጋቸው መናገር ምናልባት ሊከብድ ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች ንስሐ በመግባትና የንስሐን አስፈላጊነት በመናገርም ምሳሌ ሊሆኑ ይገባል።



ሰ. በልቡና ውስጥ ፈሪሃ እግዚአብሔር አለመኖሩ:- ቅዱስ ይስሐቅ – «ፈሪሃ እግዚአብሔር ከሌለ ንስሐ መግባትም የለም» ብሏል። አንዳንድ ሰዎች በፍቅር ሰበብ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ከልቡናቸው ፈጽመው ያስወግዳሉ። በዚህ ጊዜም ስለ ንስሐ ሕይወታቸው ግድ የለሽ ይሆናሉ:- በኃጢአትም ይወድቃሉ። ከኃጢአት የተነሣም ፍርሃትን አውጥቶ በመጣል ወደንስሐ የሚያቀርበውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ያጣሉ። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ – «ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፤ ፍርሃት ቅጣት አለውና:- የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።» እንዳለው ሰው ፍቅር ከሌለው ኃጢአቱን ለመናዘዝና ንስሐ ለመግባት የሚገፋፋው ፈሪሃ እግዚአብሔርም አይኖረውም። ፍቅር ከሌለበት ልቡና ፈሪሃ እግዚአብሔር ሊመነጭ አይችልምና – ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለው ልቡናም የንስሐ መሰናክል ነው። ለዚህ ነው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ያለው። መዝ.፻፲፥፲።

## ፰. ንስሐና ቤተ–ክርስቲያን

በማንኛውም ክርስቲያን የንስሐ ሕይወት ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ከፍተኛ ነው። ይህ ከፍተኛ ድርሻዋም ትምህርቷን፣ ምክሯን፣ ትምህርተ አባንፍሷን፣ ጉብኝቷንና ክትትሏን፣ የመንፈስ ቅዱስን ሀብትና የማዳን ሥራ ለሰዎች መናኘትና ምእመናንን ለቅዱስ ቁርባን ማብቃቷ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ኃጢአተኛውን ወደንስሐ ትጠራለች። ፪ቆሮ.፭፥፳። ይህን የንስሐ ጥሪዋንም የምታስተላልፈው በትምህርተ ወንጌል ነው። ቤተ ክርስቲያን ካልሰበከችና ወደ ሕይወት ካልጠራች ማንም ንስሐ የሚገባ የለም። ስለዚህ በማንኛውም ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ችግሮች አጋጣሚ በአጥቢያዋ ወይም በሰበካዋ ያሉትን ምእመናን ሁሉ በመጎብኘት ወደንስሐ ትጠራለች። አባት የሚወደውን ልጁን እንደሚጠብቅ–እናትም ልጆቿን እንደምትንከባከብ ቤተ ክርስቲያንም የምእመናንን ሕይወት ለእግዚአብሔር መንግሥት ታዘጋጃለች።

ተነሳሒው ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት ሊያገኝ የሚችልበት ከቤተ ክርስቲያን የተሻለ ተገቢ ሥፍራ የለም። በቤተ ክርስቲያን ተነሳሒው ምሥጢረ ንስሐን ይማራል – ያውቃል:- ንስሐ በመግባትም ከኃጢአቱ

www.ethiopianorthodox.org

ሥርየትን–ይቅርታንና ምሕረትን–የሕይወትንም ቅድስና ያገኛል። በምሥጢረ ንስሐ አማካኝነት ኃጢአተኛው ሰው ልቡናውን ከፍቶ የበደለውን ሁሉ ይናዘዛል – በካህኑ አማካኝነትም ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር ይናገራል። ይህም ለካህኑ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው። ማቴ.፲፰፥፲፰። ዮሐ.፳፥፳፫። በዚህ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አማካኝነት ኃጢአተኛው ለካህኑ ከተናዘዘ በኋላ ሥርየትና ይቅርታን ስለሚያገኝና የልቡናው ኃጢአት ስለሚታጠብለት በልቡ ሰላም ይሆናለታል– አዲስ ሕይወትም ይጀምራል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በምሥጢረ ንስሐ መንፈሳዊ ምክር ትሰጣለች። የእግዚአብሔር ቃል «ካህናቱን ስለሕጉ ጠይቅ» ሐጌ.2፥11። እንዳለ ምእመኑ ከመምህረ ንስሐው ትክክለኛውን መንፈሳዊ የሕይወት መርሕ የሚማረው በቤተ ክርስቲያን ነው። ምሳ.፲፬፥፲፪። ምሳ.፫፥፭።

በቤተ ክርስቲያን ምእመኑ የትም ሊያገኘው የማይችል መንፈሳዊ ሕይወቱንና ድክመቱን በተመለከተ የሚያማክረውና የሚታመን ምሥጢረኛ (ከባቴ አበሳ) ልብ ያገኛል። ይህም እውነተኛው የእግዚአብሔር አገልጋይ ካህኑ ነው። ከታማኙ ካህን ለምእመኑ ችግሮች ሁሉ መንፈሳዊ መፍትሔ፣ ቅንነት የተሞላበት ዕርዳታና ፍጹም ፍቅር የተሞላው የሕይወት መመሪያ ይገኛል።

በቤተ ክርስቲያን ምእመኑ ከንስሐ ሕይወት በተጨማሪ የምሥጢረ ቁርባንን በረከት ሁሉ ያገኛሉ። ዮሐ.፮፥፶፬–፶፮። ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ይህን ጸጋ ማግኘት አይቻልም። አንዳንድ ሰዎች፤ ንስሐ መግባት ከኃጢአት ይቅርታን የሚያስገኝ ከሆነ ቤተክርስቲያን፣ ኑዛዜ፣ ቅዱስ ቁርባን – ወዘተ ምን ይጠቅማል? ለምንስ ያስፈልገኛል? ይላሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ በንስሐ ይቅርታን ለማግኘት የሚያበቁና የሚያዘጋጁ ናቸው። ሰው በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት በኃጢአቱ ላይ በመናዘዝና በንስሐ ታጥቦ ሥጋውን ደሙን በመቀበል ይቅርታንና ምሕረትን ያገኛል።

ክፍል ሁለት

# ለንስሐ የሚያበረታቱ ሁኔታዎች

## ፩. ማንነትህን ካወቅህ ከኃጢአት በላይ ነህ:-

ንስሐችን እግዚአብሔርን በመውደድና መንፈሳዊ ሕይወትን በማወቅ ጽኑ መሠረት ላይ የተገነባ መሆን አለበት። ከዚህ አንፃር ሰው እግዚአብሔር ምን ያህል እንደ አከበረው ያወቀ እንደሆን ራሱን በኃጢአት አያዋርድም:- ስለዚህም አይወድቅም። ነገር ግን ሰው ማን ነው? አንተስ ማነህ?

ሀ. አንተ እግዚአብሔር የሕይወት እስትንፋስ ሰጥቶ የፈጠረህ ፍጥረት ነህ:- ዘፍ.፪፥፯።

አንተ አፈር ብቻ አይደለህም። ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋና ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ የተፈጠርክ ሕያው ሰው ነህ። ሕያው በመሆንህም ለጊዜው በምድር የምትኖር ብትሆንም በክብር ወደ አምላክህ በመሄድ ሰማያዊ ሕይወትን ለመኖር የተፈጠርክ መሆንህን አስብ። ስለዚህም በመንፈስ ኑር። ከዓለም:- ከሥጋዊ ሥራም ተለይ።

ለ. አንተ በመልኩና በምሳሌው የተፈጠርክ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ:- ዘፍ.፩፥፳፮–፳፯።

በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠርክ ከሆንክ እንዴት ኃጢአትን ትሠራለህ? በኃጢአት ወድቀህስ እንዴት የእግዚአብሔር ምሳሌ ልትባል ትችላለህ? ስለዚህ ነገር ቅዱስ አባታችን አትናቴዎስ:-

«ሰው በበደለ (ኃጢአትን በሠራ) ጊዜ የእግዚአብሔር ምሳሌ መሆኑ ይቀራል:- ቅድስናውን ያጣልና» በማለት ተናግሯል።

ጌታችንም ሰው የሆነው ወደነበርንበት የቅድስና ሕይወት ሊመልሰን ነው። የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያወቀ ሰው ኃጢአት አይሠራም – ኃጢአትን ባለመሥራትም አባቱን የሚመስል ይሆናልና። አባቱን የማይመስል ልጅም ልጅ አይደለም። ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጅ ነህና

www.ethiopianorthodox.org

ከኃጢአት በመለየት ልጅነትህን ልታረጋግጥ ይገባኻል። በዚህም አባትህ ትመስላለህና። «የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር» እንደ ተባለ። ዮሐ.፰፥፴፱። የእግዚአብሔር ልጆች የኖሩት የተቀደሰ ሕይወት ካልኖርን የእግዚአብሔር ልጆች አይደለንም። በመሆኑም በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ ልንል አንችልም። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም:-

«...ጻድቅ እንደሆነ ካወቃችሁ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደተወለደ ዕወቁ» ፩ዮሐ.፪፥፳፱። በማለት የእግዚአብሔር ልጆች ኃጢአትን በመተው ጽድቅን የሚያደርጉ መሆን እንዳለባቸው አስተምሮአል። ከዚሁ ጋር በማያያዝም «ልጆች ሆይ – ማንም አያስታችሁ እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው። ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው። ...ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም:- ...ከእግዚአብሔር ተወልዷልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም። የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው።» ፩ዮሐ.፫፥፯–፲። ካለ በኋላ ደግሞ «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን እንዳያደርግ፥ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደው ራሱን እንዲጠብቅ ክፉውም እንዳይነካው እናውቃለን» ፩ዮሐ.፭፥፲፰። በማለት የእግዚአብሔር ልጆች የሚባሉት ከኃጢአት ሥራ የተለዩት መሆናቸውን አብራርቶ ነግሮናል። እግዚአብሔርን አባታችን ሆይ ለማለት የሚችሉትም ከኃጢአት የተለዩት ናቸው።

ስለዚህ ኃጢአት በሠራህ ጊዜ ሁሉ ነፍስህን ወደጉድጓድ እንደ ጣልካትና አንተም የእግዚአብሔር ልጅ ለመባል የማትችል መሆንክን አትዘንጋ።

ሰዎች ሁላችን የእግዚአብሔር ልጅ የመባልን ተግባራዊ ትርጉም በሚገባ ልናውቅ ያስፈልጋል። ይህንንም ለማወቅ ሁልጊዜ በምናስበው፣ በምንናገረውና በምንሠራው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች መስለን እንደሆን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል። የእግዚአብሔርን ልጆችም ልንመስል ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር ቃልም – «እግዚአብሔር መንፈስ ነው።» ዮሐ.፬፥፳፬። «ከመንፈስ የተወለደውም መንፈስ ነው።» ዮሐ.፫፥፮። ይላልና የሚበድል ሰው ደግሞ እንኳን የእግዚአብሔር ልጅ ሊሆንና ሊባል ቀርቶ እግዚአብሔርንም አላየውም:- አያውቀውም። ፩ዮሐ.፫፥፮።

የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህን ስታስብ እግዚአብሔር በምን ዓይነት ሕይወት ትኖር ዘንድ እንደጠራህ አስተውል። ቅዱስ ጳውሎስም ስለዚህ



ነገር «..።ጅጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ» ኤፌ.፬፥፩። በማለት ይመክራል። ቅዱስ ዮሐንስም:- «በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባል» ፩ዮሐ.፪፥፮። ሲል ያስተምረናል። ጌታችንም ደግሞ «እኔ ለናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና።» በማለት የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ ሊመላለስበት ስለሚገባው መንገድና ሊሠራ ስለሚገባው ነገር አስትምሯልና ከዚህ አንፃር ራስህን መርምር።

ሐ. አንተ የእግዚአብሔር ማደሪያ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነህ:- ስለዚህ ማረጋገጫ እንዲሆንህ በመጽሐፍ የተጻፈው እንዲህ ይላል።

«ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ» ምሳ.፳፫፥፳፮። ይህ አባባል የሰው ልብ የእግዚአብሔር ማደሪያ መሆኑን ያመለክታል። ሐዋርያው ጳውሎስም «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ:- የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል:- የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና:- ያውም እናንተ ናችሁ።» ፩ቆሮ.፫፥፲፮። እንዲሁም ደግሞ:- «እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና:- እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል ‹በእነርሱ እኖራለሁ – በመካከላቸውም እመላለሳለሁ:- አምላክም እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።» ፪ቆሮ.፮፥፲፮። በማለት ሰዎች የእግዚአብሔር ማደሪያዎች ለመሆን መመረጣቸውን ተናግሯል።

የእግዚአብሔር የማይቋረጥ ፍላጎቱም – ከመጀመሪያው አንሥቶ ያለው መሻት ወደሰው ነው– በሰው ልቡና ያድር ዘንድ ሰውም ከኃጢአት እንዲለይና የተቀደሰ የእግዚአብሔር ማደሪያ እንዲሆን፤ ስለዚህም እግዚአብሔር የሰውን ልቡና «ይህች ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት እኔም በእርሷ አድራለሁ» መዝ.፻፴፪፥፲፬። ይላታል። ሰውም «አቤቱ ጌታዬ ሆይ ለአንተማ ማደሪያ የታነፁ አብያተ መቅደስ አሉህ» ይለዋል። እግዚአብሔር ግን ከታነፀ ሕንፃ በበለጠ የእጄ ሥራ ለሆነው ሕያው ቤተመቅደስ ሲል ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቆርሶ ቤዛ ሆኖአልና አንተ የበለጠ ታስፈልገዋለህ። ሕንፃው ቤተ መቅደስ ለአንተ ተሠራ አንተ ደግሞ የእግዚአብሔር ማደሪያ ሕያው ቤተ መቅደስ እንድትሆን ተፈጥረኻል። ሕንፃው ቢፈርስ ዳግመኛ ሊሠራ ይችላል። አንተ ብትፈርስ ግን ዳግመኛ በዚህ ዓለም አትሠራም ስለዚህ እግዚአብሔር አንተን በጽኑ ይፈልግኻል።

ለዚህ ነው ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ መምህራንን፣ ካህናትን፣ ሰባክያንን እንዲሁም በተራዳኢነታቸው ሊጠብቁህ ቅዱሳን መላእክትን የላከልህ። ይህ

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ በኃጢአት የቆሸሸከውንና በዓለም የተጣልከውን አንተን ለማግኘትና ለማዳን የተደረገልህ ነው። አንተንም የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤተመቅደስ ለማድረግ ነው።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ማደሪያ ከሆንክ ደግሞ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት «አቤቱ እስከ ረጅም ዘመን ድረስ ለቤትህ ቅድስና ይገባል» መዝ.፺፫፥፭። እንዳለው ሁሉ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ የተቀደሰ ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔርም ማደሪያ እንደመሆንህ ከኃጢአት ርቀህ ንጽሕ ጠብቀህ መኖርን ገንዘብ ማድረግ ይገባሃል። ቅዱስ ጳውሎስ «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ።» ፩ቆሮ.፫፥፲፯ ያለውንና ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ...መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።» ፩ጴጥ.፪፥፭። ያለውን በአንክሮ ማስተዋልና ራስህን መጠበቅን አትዘንጋ። በሉቃስ ወንጌልም ጌታ «ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች ማረፊያ አላቸው ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም» ሉቃ.፱፥፶፰። በማለት እንደተናገረው እግዚአብሔር የሚፈልገው ማደሪያ ሊጠጋበት የሚሻውም ሥፍራ የአንተ ልቡና ነውና ልቡናህን በንጽሕና በቅድስና መጠበቅን ችላ አትበለው።

በእርግጥ ደግሞ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ይደሰታል፡- በምሳሌ — «ደስታዬም በምድሩ፡- ተድላዬም በሰው ልጆች ነበረ» ምሳ.፰፥፴፩። እንዳለው። ከዚህም የተነሣ ዘወትር የልቡናህን ደጅ ሲያንኳኳ ይኖራል። የእርሱ ማደሪያ የሆነ ልብህ ይከፈትለት ዘንድም እንዲህ በማለት ተናግሮኻል። «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፡- አባቴም ይወደዋል፡- ወደእርሱም እንመጣለን፡- በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።» ዮሐ.፲፬፥፳፫። በዚህ ሁኔታ አብና ወልድ ወደአንተ ሕይወት ይመጣሉ በአንተ ልቡናም ያድራሉ። በዚህም መሠረት የእግዚአብሔር ማደሪያ ትሆናለህ።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነ ቤተ መቅደስ የሆነው ልብህ የሚደነቅ ይሆናል። አባታችን ያዕቆብም «ይህ ሥፍራ እንዴት ያስፈራ! ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም ይህም የሰማይ ደጅ ነው።» ዘፍ.፳፰፥፲፯። ሲል የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነ ሰውነት ምንኛ የከበረ መሆኑን ጠቁሟል። ስለዚህ የከበረውን የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነ ሰውነትህን በኃጢአት እንዳይቆሸሽ በንስሐ እያጠብክ በንጽሕና ትጠብቀው ዘንድ ይገባኻል።



ዲያብሎስም በኃጢአት ይፈትንህ ዘንድ ወደአንተ በመጣ ጊዜ፡-

- እኔ ለአንተ አይደለሁምና ከእኔ ወግድ በለው፤
- እኔ የእግዚአብሔር መቅደስና የመንፈስ ቅዱስም ማደሪያ ነኝ በለው፤
- በእኔ ያድር ወደቤት ልቡናዬ ይገባ ዘንድ እግዚአብሔር በር ልቡናዬን የሚያንኳኳ ሰው ነኝ በለው፤
- እኔ አብና ወልድ ማደሪያቸው ሊያደርጉኝ ወደ እኔ የሚመጡ ሰው ነኝ በለው፤
- እኔ የሥላሴ ማደሪያ ነኝ በለው።

መ. አንተ የመሲህ ክርስቶስ ወገንና የመንግሥቱም ወራሽ ነህ፡-

እርሱ ክርስቶስ አምላክ ሲሆን በትሕትና ራሱን ዝቅ አድርጎና ወዶህ ወንድም ሆይ ይልኻል በሥጋ ተዛምዶኻልና — የአንተን ደካማ የሥጋ ባሕርይ ገንዘብ አድርጎአልና፡- አንተ ግን ተንጠራርተህ ወደ ላይ ፈጣሪህን ወንድሜ ልትለው አይገባህም። ምንም እንኳ ሥጋህን ለብሶ እንዳንተው ሰው ቢሆን ፍጡር አይደለምና አምላክ እንጂ። እርሱ ሰዎችን ወንድሞች ማለቱ እጅግ ግሩም ነገር ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ስለዚህ የሕዝቡን ኃጢአት ለማስተሥረይ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው» በማለት ክብሩን ዝቅ አድርጎ ለሰው ወንድም እንደሆነ ተናግሯል። ዕብ.፪፥፲፯። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከትንሣኤው በኋላ ማልደው ወደ መቃብር ሄደው ያገኛቸውን ሴቶች፡- «ሄዳችሁ ወደገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ» በማለት ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትን ወንድሞች እንዳላቸው እንመለከታለን። ማቴ.፳፰፥፲። በተጨማሪም ጌታ ሽቱ ልትቀባው ወደመቃብሩ ማልዳ የሄደችውን መግደላዊት ማርያምን ወደ ደቀመዛሙርቱ ሲልካት፡- «...ነገር ግን ወደወንድሞቼ ሄደሽ — እኔ ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ...ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው» በማለት መናገሩ ተጽፏል — ዮሐ.፳፥፲፯።

ይህም የሚያሳየው ጌታ ሰዎችን ወንድሞች ብሎ ይጠራቸው እንደነበረ ነው። ወንድሞቼ ያለውም ደቀ መዛሙርቱን ብቻ አይደለም ሌላውንም የሰው ዘር ሁሉ እንጂ — ትሕትናው ሁሉን ለማስተማር ተገልጧልና። እርሱም በቃሉ፡- «ወንድሞቼ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርጉ ሁሉ እነርሱ ወንድሞቼም እኅቶቼም ናቸውና።» በማለት በግልፕ ተናግሯል። ማቴ.፲፪፥፶። ይህም ፈቃዱን የሚፈጽሙ የሰው ልጆች

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ ወንድሞች ተብለው እንዲጠሩ የተመረጡ መሆናቸውን የሚያሳ
ነው። የተመረጥነው ወንድሞች ልንባል ብቻ ሳይሆን ወራሾቹም ጭም
ልንሆን ነው። ማቴ.፳፭፥፴፫። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህን
ሲያስረዳ:-

«የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን። ማለት
የእግዚአብሔር ወራሾች ነን አብረንም እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል
ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።» ሲል ተናግሯል። ሮሜ.፰፥፲፯።

እንግዲህ በኃጢአት የምትኖር ከሆነ የክርስቶስ ወዳጅ የክብሩም ወራሽ
ልትሆን እንደማትችል መዘንጋት የለብህም። «ጽድቅ ከዓመፃ (ከኃጢአት)
ጋር ምን ተካፋይነት አለውና» ፪ቆሮ.፮፥፲፬–፲፭ በማለት የተጻፈው ይህን
የሚያመለክት ነው። የጽድቅን መንግሥት ለመውረስና የጻድቁ
(የእውነተኛው) የእግዚአብሔር ልጅ ወይም ወዳጅ ለመሆን ከዓመፀ
(ከኃጢአትና) ከዓመፀኛው ከዲያብሎስ ራስን መለየቱ ተገቢ ነው። ይህም
ኃጢአትን በመናዘዝና ንስሐ በመግባት የምታደርገው ነው።

ሠ. አንተ የመንፈስ ቅዱስ አንድነት የመለኮታዊ ክብርም ተካፋይ ደግሞ ነህ:-

ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣
የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን።»
በማለት አስረድቷል። ይህ ኅብረት ከተቀደሰ ምግባር የተነሣ የሚገኝ
የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ
ይሠራል፤ በአንተ ላይም ይኖራል፤ አንተንም ተጠቅሞ ነፍሳትን ለማዳን–
የክርስቶስን አካል ለማነፅ ይሠራል። እርሱ በአንተ ካልሠራ አንተ በራስህ
ምንም አይደለህምና። ቅዱስ ዳዊትም «እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ
ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ» ሲል የተናገረው ቃል ይህንኑ የሚያስረዳ
ነው። መዝ.፻፳፮፥፩።

ዘወትር መልካምና የተቀደሰውን ነገር ሁሉ የሚያሠራህ መንፈስ ቅዱስ
ነው። ክፉ ሥራ (ኃጢአትን) በሠራህ ጊዜ ግን የዲያብሎስ ተገዥ ሆነኻልና
ብቻህን ትሆናለህ። ያን ጊዜም ከመንፈስ ቅዱስ አንድነት ትለያለህ። ከዚህም
የተነሣ ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ እያለ ይመክርኻል። «የታተማችሁበትን
የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ አታሳዝኑ።» ኤፌ.፬፥፴። «መንፈስን
አታጥፉ።» ፩ተሰ.፭፥፲፱። ይህን በማወቅ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ከአንተ
እንዳይለይና አንተም የኃጢአት ተገዥ እንዳትሆን ዘወትር «አቤቱ ቅዱስ
መንፈስህን አትውሰድብኝ» እያልክ መጸለይ ይኖርብኻል። መዝ.፶፥፲፩።
በዚህ ዓይነት የኖርክ እንደሆነ ከእግዚአብሔር ከሰጠህ የጸጋ ተካፋይነት



መካከል የእግዚአብሔር ልጅ መሆን አንዱ መሆኑን ቅዱስ ዳዊት
«ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ።» በማለት ተናግሯል። መዝ.፹፩፥፮።

እንግዲህ ከዚህ ልዕልና በኋላ – በጸጋ የመለኮት ሥጦታ ተካፋይ ከሆንክ
በኋላ ኃጢአትን መሥራት ለምን ይጠቅምኻል? ኃጢአትን በሠራህ ጊዜ
የሰይጣን ወገንና ባሪያው ትሆናለህ እንጂ የምታገኘው ጥቅም የለም:-
የኃጢአት ባሪያ መሆን በሞት ጥላ መኖር ነውና። በመጽሐፍም «ኃጢአትን
የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው።» ፩ዮሐ.፫፥፰። ተብሏል። ከዚህም ኃጢአትን
የሚያደርጋት ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን ክብር የማያውቅ ነው። ስለዚህ
ኃጢአትን በብርቱ ሽሻት ወደ አንተም ብትመጣ ከእርሷ ራቅ።

ረ. አንተ የክርስቶስ አካል ነህ:- ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት።

ጉልላቷ ደግሞ ክርስቶስ መሆኑ ተነግሯል። ቤተ ክርስቲያን ሲባል
የምእመናንን አንድነትም ይጨምራል። የምእመናን አንድነትም ቤተ
ክርስቲያን ነውና። ይህንን ቅዱስ ጳውሎስ «እርሱም ሁላችን የእግዚአብሔር
አብን የባሕርይ ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት እስክንደርስ
የክርስቶስ አካል ለመሆን ፍጹማን እስክንሆን ድረስ አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣
ሌሎቹም ነቢያት፣ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች:- ሌሎቹም እረኞችና
አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ።» ሲል አብራርቶታል። ኤፌ.፬፥፲፩።
በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ ደግሞ የክርስቶስ የአካሉ ክፍሎች መሆናቸውን
«ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፤ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች
ስለሆንን ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት ይመግበዋል –
ይከባከበውማል።» ሲል ገልጦታል። ኤፌ.፭፥፴። ስለዚህ በሰውነታችን
ኃጢአት መሥራት የለብንም። ኃጢአት ከክርስቶስ ጋር ኅብረት የለውምና።
በክርስቶስ አካልም ኃጢአት ሊሠራ አይገባምና። ይህንን አስመልክቶም
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ
አታውቁምን?» ካለ በኋላ «ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት
በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤተ መቅደስ እንደሆነ
አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ
በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።» ብሏል። ፩ቆሮ.፮፥፲፭–፳።
የተገዛንበት ዋጋ ሰው የሆነ አምላክ የክርስቶስ ደም መሆኑ የታወቀ ነው።
እንግዲህ ሥጋችን የክርስቶስ አካል ከሆነ እንደምን ኃጢአት እንሠራለን?
ከዚህም በላይ ደግሞ እርሱ ክርስቶስ በዓለም ፍጻሜ ሲመጣ «ተርቤ
አብልታችሁኛልን? ወዘተ.» በማለት የሚጠይቀን ራሱ ፍጹም የእኛ ወገን
በመሆኑ ነውና ማቴ.፳፭፥፴፭ እንዴት ኃጢአት እንሠራለን። ኃጢአተኛ

www.ethiopianorthodox.org

ራሱን ከክርስቶስ ወገንነት የእርሱም አካል ከመሆን ይለያል:- የክርስቶስ አካል ቅዱስ ነውና።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛ የእርሱ አካላት መሆናችንን ሲገልጽ:- «እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ።» ብሏል። ዮሐ.፲፭፥፭። እንግዲህ እውነተኛ ቅርንጫፍ ሆነን እውነተኛ የወይን ፍሬ አፍርተን ይሆን? ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል። እውነተኛ የወይን ፍሬም የእግዚአብሔር ልጆች የክርስቶስ አካላት የሆኑ ክርስቲያኖች የሚሠሩት ከኃጢአት የተለየ የተቀደሰ ምግባራቸው ነው። ስለዚህ ሕይወታችንን ከኃጢአት በመጠበቅ የተወደደ የወይን ፍሬ አፍርተን መገኘት ይገባናል። ከእርሱም ጌታ ሊጠጣ የወደደው ወይን የሚገኝበት የተመረጠ የሕይወት ቅድስናና የንጽሕና ፍሬ ልናፈራ የተገባ ነው። ማቴ.፳፮፥፳፱። ዮሐ.፩፥፯። ከሁሉ በላይ ጌታችንን የሚያስደስተው የሰው ልጆች ከኃጢአት ወደጽድቅ መመለስና ለሰማያዊው መንግሥቱ መብቃት ነው።

መልካም ፍሬ የማናፈራ፣ የተቀደሰ ምግባር የማንሠራ:- ከኃጢአት የማንርቅ ከሆንን የወይኑ አካላት አይደለንም። በኃጢአት የሚመላለስ ሰው የወይኑ የክርስቶስ አካል – ከእርሱም የሚገኘውን ሁሉ የሚቀበልና ፍሬ የሚያፈራ ቅርንጫፍም ሊሆን አይችልም:- እንዲህ ዓይነቱ ቅርንጫፍ ይቆረጣል – ወደ እሳትም ይጣላል። ይህንንም ሲገልጽ ጌታችን:- «በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እኖራለሁ:- እርሱም ብዙ ፍሬ ያፈራል። በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፍ ወደውጭ ይጣላል:- ይደርቅማል። እነርሱም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሏቸዋል:- ያቃጥሉአቸውማል።» በማለት ተናግሯል። ዮሐ.፲፭፥፮–፯።

ከዚህ የተለየው ኃጢአትን የማይሠራና የተቀደሰው ቅዱሱ ግን የወይን ግንድ የተባለ የክርስቶስ አካል ነውና የሚጠበቅበትን የጽድቅ ፍሬ ያፈራል። ገላ.፭፥፳፪። ስለዚህ የክርስቶስ አካል መሆንክን አስበህ እንደመልካሙ ቅርንጫፍ ጣፋጭ የሆነ የንጽሕና ፍሬ ለማፍራት ራስህን ከኃጢአት ልትጠብቅ ይገባሃል።

ሰ. አንተ የክርስቶስን ሥጋና ደም የምትቀበል ነህ:- አንተ የክርስቶስን ሥጋውን በልተህ ደሙንም ጠጥተህ ሥጋው ከሥጋህ ደሙም ከደምህ ጋር ተዋሕዷል። ሥጋወደሙ ከተቀበለው አፍህ የማይገባ ንግግር አይወጣም። እንዲገባ ከተፈቀደው በላይም አይገባበትም። ስለዚህም አንደበትህ



እግዚአብሔር ለማይደሰትበት ኃጢአት ለሆነ ነገር መከፈት የለበትም በአንተ ያለው የፈጣሪህ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነውና – ተቀድሰኻልና።

በክርስቶስ ሥጋና ደም የተቀደሰው አካልህ ለኃጢአት መሣሪያ መሆን እንደሌለበት አስተውል፤ ማን መሆንክንና ለአንተ የሚገባውም ምን መሆኑን አትዘንጋ፤ በመዘንጋት ከኃጢአት መውደቅ ሊመጣ ይችላልና። ሰዎች ሁሉ የክርስቶስ አካላት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች መሆናቸውን ሲረሱ ኃጢአትን የሚሠሩ መሆናቸውን በማስተዋል አንተ የእግዚአብሔር ማደሪያ መሆንክን እያሰብክ ከኃጢአት ራቅ።

## ፪. ኃጢአት ምን እንደሆነ ብታውቅ ትሸሸዋለህ:-

አንድ ሰው ንስሐ ለመግባት ማንነቱን ማወቁ ብቻ በቂ አይደለም። ጠላቱ የሚሆን ኃጢአትንም ደግሞ ማወቅ አለበት – ሲያውቀው ይሸሸዋልና። ሰው የኃጢአትን ምንነት፣ መጥፎነቱን፣ ቅጣቱንና የሚያስከትለውን ውጤት ያወቀ እንደሆነ ይሸሸዋል።

### ኃጢአት ምንድን ነው?

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ «ኃጢአት ስታድግ ሞትን ትወልዳለች።» ካለ በኋላ በሮም መልእክቱ ደግሞ «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው።» ብሏል። ያዕ.፩፥፲፭። ሮሜ.፮፥፳፫። ስለዚህ ኃጢአት የኀሊናም የመንፈስም ሞት ነው። ከዚህ በመነሣት ነው የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ቤት በተመለሰ ጊዜ አባቱ «...ደስም ይበለን፤ ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም።» በማለት የተናገረው። ሉቃ.፲፭፥፳፬። ኃጢአትን የሚሠራ ሰው በነፍሱ ምውት ነው፤ ከአባቱ ከእግዚአብሔርም የተለየና ወደ ዓለም የኰበለለ ሰው ጠፍቷል። ከኃጢአቱም ያልተመለሰ ምውት መሆኑን ሲገልጽ ቅዱስ ጳውሎስ «ቅምጥሊቱ ግን በሕይወትዋ ሳለች የሞተች ናት።» ብሏል። ፩ጢሞ.፭፥፮። ለኤፌሶን ምእመናን በጻፈው መልእክት ደግሞ «በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ምውታን ነበራችሁ።» ካለ በኋላ «እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ በክርስቶስ ሕይወትን ሰጠን» በማለት ኃጢአት መንፈሳዊ ሞት እንደሆነና ከዚህ መንፈሳዊ ሞት የሚያድን እግዚአብሔር መሆኑን ነግሮናል። ኤፌ.፪፥፩። ኤፌ.፪፥፭።

www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአት የሚሠራ ሰው የሞተ ነው። ምክንያቱም ሕይወትን ከሚሰጥ ሕይወት ከሆነ ከእግዚአብሔር ተለይቷልና ነው። በወንጌልም «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ሕያው የሆነ የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም።» ተብሎ ተጽፏል። ዮሐ.፲፩፥፳፭። ጌታችንም «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ።» ብሏል። ዮሐ.፲፬፥፮። የሥጋ ሞትም የነፍስ ከሥጋ መለየት ነው፤ የነፍስ ሞት ወይም መንፈሳዊ ሞት ግን ከእግዚአብሔር መለየት ነው።

ኃጢአተኛ የሕይወትን ትርጉም አያውቅምና ስለንስሐ ስትነግረው በሕይወቴ እንድደሰት ተወኝ ይልኻል፤ ምድራዊና ዓለማዊ ደስታ ሕይወት እንደሆነ ያስባልና።

እንግዲህ ኃጢአት ሞት ከሆነ እኛ በእውነት ሕያዋን እንሆን? በምድርም ላይ ምን ያህል ዘመን እንኖር ይሆን? አባታችን ቅዱስ ያዕቆብ «የሕይወቴ ዘመኖች ጥቂትም ክፉም ሆኑብኝ፤ አባቶቼ በእንግድነት የተቀመጡበትንም ዘመን አያህሉም» ሲል የተናገረው ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ይሆናል። ዘፍ.፵፯፥፱። በሕይወት የኖርነው በእግዚአብሔር ቤት የኖርንበት ለቃሉ የተገዛንበት ጊዜ ብቻ ነው። ኃጢአት የሠራንበት ጊዜ ደግሞ በሞት የቆየንበት በመንፈሳዊ ሕይወት የሞትንበት ነው። ስለዚህ ዕድሜአችን ይህን ያህል ነው ብለን ከተወለድንበት ቀን አንሥቶ ያሉትን ዓመታት ቆጥረን መናገር የለብንም – አብዛኛውን በኃጢአት ምውታን ሆነን አሳልፈነዋልና። በመሆኑም በሕይወት እንኖር ዘንድ ከኃጢአት መለየት ይገባል። ከኃጢአት ሳንለይ የእግዚአብሔር ልጆች ነን አንበል በኃጢአታችን ምውታን ስንሆን የሕያው እግዚአብሔር ልጆች ልንባል አንችልምና።

## ኃጢአት በዓለም መታለልና መጥፋት ነው

በሉቃስ ወንጌል ላይ ተመዝግቦ የምናገኘው የጠፋው ልጅ፣ የጠፋችው በግና የጠፋችው ድሪም ታሪክ ኃጢአት በዓለም ተታልሎ መጥፋት መሆኑን የሚያብራራ ነው። ሉቃ.፲፭። እግዚአብሔርም የጠፋውን ልጁን፣ የጠፋችውን በጉንና ድሪሙን ከመፈለግ እንደማያቋርጥ ይኸው ታሪክ ያስረዳናል። በኃጢአት መንገድ በተጓዝን ጊዜ መጥፋታችንን ከእግዚአብሔርም እጅ መውጣታችንን ማወቅ አለብን። ኃጢአተኛ ሰው በማወቅም ሆነ ሳያውቅ በኃጢአት የሚኖር በመሆኑ የጠፋ ነው። ከአባቱ ቤት የወጣ ልጅ፣ ከእረኛው የተለየ በግ፣ ባለቤት የሌለው ገንዘብ ነውና የጠፋ ነው።



## ኃጢአት በዓለም መሸነፍና መዋረድ ነው

በመታገሥ ኃጢአትን ማሸነፍ አቅቶት ክፉ ሲናገሩት ክፉ የሚመልስ ሰው ለኃጢአት ተሸንፏል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ» ሮሜ.፲፪፥፳፩። በማለት የሰጠውን ምክር በሥራ ላይ ለማዋል መጣር እንጂ ትዕግሥት አጥቶ በክፋት መሸነፍ አይገባም። ቃየን ወንድሙን በመግደሉ በኃጢአት ተሸነፈ። መጀመሪያ ያሸነፈ ቢመስለውም በኋላ ግን እግዚአብሔር ባነጋገረው ጊዜ መውደቁንና መሸነፉን ዐወቀ። ዘፍ.፬፥፲፬። ሄሮድስም መጥምቁ ዮሐንስን በአሠረው ጊዜና በገደለው ጊዜ አሸናፊ እንደሆነ ራሱን ቆጠረ፣ ክርስቶስ በተገለጠ ጊዜ ግን ተዋረደ – ለኃጢአትም ተሸንፏልና። ማቴ.፲፬፥፲።

ማንም ሰው የበላይነትን በፈለገ ጊዜና ሌሎችን በናቀ ጊዜ ያን ጊዜ በኃጢአት ተሸንፏል:- የሚያየውን ማስተዋል:- የሚሰማውን ማድመጥ አልቻለምና፤ መሸነፉን እንደማሸነፍ ድካሙንም እንደብርታትና ኃይል ቆጥሮታልና። ማቴ.፲፫፥፲፫።

ሰዎች በዚህ ዓይነት ስለክርስቶስ መስቀል ሳይገባቸውና ጣዕመ መስቀሉን ሳይረዱት የክርስቶስን መሰቀል እንደድካም ይቆጥሩታል። መስቀሉ ግን በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ኃይል አለው። ጠላቶቹ ጌታን በመስቀ ላቸው ከቅናታቸው የተነሣ ድል ያደረጉ መሰላቸው:- ነገር ግን ተሸናፊዎች ነበሩ። ሐሰተኛነታቸውና ትዕቢታቸው እነርሱን ጣላቸው፣ የተናቀውና የተሰቀለው ክርስቶስ ግን በመስቀሉ በፍቅሩና በትሕትናውም ጭምር በሞትም ደግሞ አሸነፋቸው። በሐሰት ተነሣሥተው የወሰኑት ውሳኔና የፈረዱበት የመስቀል ላይ ሞት ኃጢአት ነበርና በኃጢአታቸው ተዋረዱ ተሸነፉም። ስለዚህ ኃጢአት መዋረድና መሸነፍ ነው።

## ኃጢአት ከእግዚአብሔር መለየት ነው

ኃጢአት ከእግዚአብሔር መለየት መሆኑን ሲያመለክት ቅዱስ ጳውሎስ «ብርሃን ከጨለማ፤ ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው?» ብሎአል። ፪ቆሮ.፮፥፲፬–፲፭። ብርሃን የሆነ ክርስቶስ ጨለማ ከሆነ ከአጋንንት ሥራ ጋራ ምንም ኅብረት የለውም። እንዲሁ ሁሉ ደግሞ ብርሃን የሆነ እግዚአብሔር የብርሃናት ጌታ እርሱ ጨለማ ከሆነ የሰይጣን ሥራ– ከኃጢአት ጋር ምንም አንድነት የለውም። ኃጢአትን የሚሠራ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር የለውምና ለዚህ ነው ኃጢአት

www.ethiopianorthodox.org

ከእግዚአብሔር መለየት ነው የተባለው። የጠፋው ልጅም በበደሉ ምክንያት ከአባቱ ቤት ወጣ ከአባቱም ተለየ። ሉቃ.፲፭፥፲፩–ፍ።

ደግሞ ኃጢአት ከእግዚአብሔር መለየት ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር መጣላትና የእርሱ ጠላትም መሆን ነው። ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ቢጣላ አካላዊ ቃል ዓለሙን ከራሱ ጋር ሊያስታርቅ ሰው ሆነ። ምድራዊውን ከሰማያዊው ጋራ አስታረቅህ ብለን የምንቀድሰውና ከቅዳሴ በፊት ከቁርባን በፊትም ጸሎተ ንስሐ የምንደግመው ለዚህ ነው።

በኃጢአት ያለ ሰው ቤቱንና አባቱን እግዚአብሔርን ትቷል። ቅዱሳት መጻሕፍትንና ትእዛዛተ እግዚአብሔርን፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ትቷል። ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርን አቋርጧል:- በመሆኑም ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቷል:- ከእርሱም ተለይቷል። ይህ የእግዚአብሔርና የሕዝቡ መጣላት በነቢዩ በኤርምያስ ዘመን እጅግ አስፈሪ በሆነ ደረጃ ላይ በመድረሱ እግዚአብሔር ነቢዩን «እንግዲህ አልሰማህምና ስለዚህ ሕዝብ አትጸልይ፤ ስለእነርሱም ልመናና ጸሎት አታድርግ–አትማልድላቸውም።» ብሎታል። ኤር.፯፥፲፮። ከዚህም በላይ የእግዚአብሔር ጥላቻ ከከፍተኛ ደረጃ የደረሰ ለመሆኑ «ሙሴና ሳሙኤል በፊቴ ቢቆሙም ልቤ ወደዚህ ሕዝብ አያዘነብልም:-» ሲል እግዚአብሔር ለነቢዩ ኤርምያስ የተናገረው ቃል ምስክር ነው። ኤር.፲፭፥፩።

ኃጢአት ሲበዛ ከእግዚአብሔር መጣላትም – ከእርሱ መራቅም እንደዚሁ ይበዛል። ስለዚህ ነው በአዲስ ኪዳንም ጌታችን ሰነፎቹን ደናግል «እውነት እላችኋለሁ አላውቃችሁም» ሲል የመለሰላቸው። ሌሎችንም ደግሞ «ከቶ አላውቃችሁም:- እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ!» ብሏቸዋል። ማቴ.፳፭፥፲፪። ማቴ.፯፥፳፫። በሉቃስም እንዲሁ «እላችኋለሁ:- ከወዴት እንደሆናችሁ አላውቃችሁም ሁላችሁ ዓመፀኞች – ከእኔ ራቁ» ብሎ ኃጢአተኞችን ምን ያህል እንደሚጠላ ተናግሯል። ሉቃ.፲፫፥፳፯። እነዚህ የጌታ ቃላት ሁሉ አስፈሪና አስደንጋጭ ናቸው። በእግዚአብሔር አንደበት አላውቅህም መባል ምንኛ አሳፋሪ እንደሆነ መመዘን ይቻላል። እንግዲህ በዚህ ዓይነት በዓለምና በኃጢአት ለመኖር የሚወድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት መሆኑ ነው። ቅዱስ ያዕቆብም «ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኗል።» በማለት የተናገረውና ያዕቆ.፬፥፬። ቅዱስ ዮሐንስም «ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ...ማንም



ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።» ሲል የተናገረው ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው። ፩ዮሐ.፪፥፲፭።

በሌላ በኩል ግን የእግዚአብሔር ወዳጆች ለእግዚአብሔር ባላቸው ቅርበት ፍቅራቸውን ይገልጣሉ። እግዚአብሔርም እንደ እነዚህ ላሉት ወዳጆቹ ጥልቅ ፍቅሩን ይገልጥላቸዋል። በቃሉም ያነጋግራቸዋል። ለምሳሌ ያህልም ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመለከታለን።

በመጀመሪያ የምንጠቅሰው የእግዚአብሔር ወዳጅ አባታችን አብርሃም ነው። አባታችን አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆኑ በብዙ ሥፍራ ተነግሯል። ስለዚህም በጸሎታችን ጊዜ እግዚአብሔርን ስለወዳጁ ስለ አብረሃም ብሎ የምንጠይቀውን ነገር እንዲያደርግልን እንለምነዋለን። አብርሃም እግዚአብሔርን የሚያፈቅር የእግዚአብሔር ወዳጅ ነው። እግዚአብሔር ሰዶምን ሊያጠፋ በወሰነ ጊዜ «እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሠውራለሁን?» ሲል መናገሩ በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል ላለው ጽኑ ወዳጅነት ምስክር ነው። ዘፍ.፲፰፥፲፯። እግዚአብሔር ለአብርሃም ሳይነግር ሰዶምን አለማጥፋቱ ስለዚህችም ሀገር ከአብርሃም ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ እጅግ የሚደነቅ ነው። ይህ ሰው ለመሆኑ ማነው ? በውኑ እርሱ «አፈርና አመድ» አይደለምን? ዘፍ.፲፰፥፳፯። እግዚአብሔር ግን ስለ አብርሃም እንዲህ ይላል:- «እርሱ የማፈቅረውና የምወደው ባሪያዬ ነው። ስለማደርገው ነገር ሁሉ ለእርሱ መንገር አለብኝ:- እንደሌሎቹ ሰዎች ሁሉ በሚፈጸመው ነገር እንዲገረም እርሱን መተው ተገቢ አይደለም።»

ስለዚህ እግዚአብሔር ያሰበውን ለአብርሃም ነገረው፤ ስለሁኔታውም ከእርሱ ጋር በፍቅር ተወያዩ:- አብርሃምም እግዚአብሔርን «በውኑ ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ታጠፋለህን?...ይህ ከአንተ ይራቅ...እንዲህ ያለው አድራጎት ከአንተ ይራቅ። የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን? በማለት ሃሳብ ሲያቀርብ እንመለከታለን። ይህ ዓይነቱ አነጋገር ከምንፈራቸው ወይም ከምናከብራቸው ሰዎች ጋር የምንነጋገርበት ዘዴ አይደለም፤ አብርሃም ግን ከፍጹም ወዳጅነት በመነጨ ድፍረት ከእግዚአብሔር ጋር እንዲህ ተነጋገረ። ውይይቱንም በመቀጠል «ሃምሣ ጻድቃን በከተማይቱ ውስጥ ቢገኙ...ከሃምሣው ጻድቃን አምስት ቢጎድሉ:- ...ምናልባት ከዚያ አርባ ቢገኙሳ...ሰላሣ...አሥር።» አለው። እግዚአብሔርም «ስለ አሥሩ አላጠፋትም» ሲል መለሰ። ዘፍ.፲፰፥፳፪–፴፫።

ይህም የእግዚአብሔር ወዳጅ ከመሆን የተገኘ ነው። የዚህ ዓይነቱን ወዳጅነት ይዘው የተገኙ ሰዎችን ማግኘት የሚያስደንቅ ነው። ከእግዚ

www.ethiopianorthodox.org

አብሔር ጋር የሚያነጋግር–ለመነጋገርም የሚያበቃ ወዳጅነት ካላቸው ሰዎች ጋር እርሱም ይነጋገራል። ታዲያ ማነው ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገር–እግዚአብሔርም የሚያነጋግረው?

ለአብርሃም የሆነው ሁሉ እንዲሁ ደግሞ በሙሴ ሆኗል። ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ እንደ አብርሃም ሁሉ የእግዚአብሔር ወዳጅ ስለነበር ከፈጣሪው ጋር ሲወያይና ሲማከር ተገኝቷል። እሥራኤል (አይሁድ) ከወርቅ የተቀረፀ የጥጃ ምስል ሠርተው ማምለክ ጀመሩ። ያን ጊዜ እርሱ ያደረገላቸውን ተአምራት ሁሉ:- ዘንግተው እርሱንም ክደው ለጣዖት በመስገዳቸው እግዚአብሔር ተቆጣ። እነርሱንም ለማጥፋት ወሰነ። ነገር ግን አስቀድሞ ለሙሴ ሊነግረው ወደደ። ለሙሴም ሕዝቡ ምን ያህል እንደረከሱ ከነገረው በኋላ «እኔ ይህን ሕዝብ አየሁት – እነሆም አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው። አሁንም ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ» ዘጸ.፴፪፥፲። አለው። በዚህ ምንባብ እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ሲሆን ሙሴን ግን እንደ አማካሪ ሲያወያየው እንመለከታለን። ከዚህ ንግግር እግዚአብሔር «ተወኝ» ሲል ለሙሴ ከተናገረው ቃል ይልቅ የነቢዩ ሙሴ መልስ እጅግ የሚያስገርም ነው። ቅዱስ አባታችን ያዕቆብ እግዚአብሔር «ሊነጋ አቀላልቷልና ልቀቀኝ» ባለው ጊዜ «ካልባረከኝ አልለቅህም» ዘፍ.፴፪፥፳፮ እንዳለው ሁሉ ሙሴም ፍጹም ፍቅር በተሞላበት ድፍረት «ከመዓትህ ተመለስ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ።» ዘጸ.፴፪፥፲፪። በማለት መለሰለት። ማነው በምድራዊ አለቃው ፊት እንዲህ በድፍረት የሚናገር? የሚገርመው ነገር እግዚአብሔር በሙሴ ንግግር ተስማምቶ የሙሴን ፈቃድ መፈጸሙ ነው። መጽሐፉም «እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፉት ራራ።» ዘጸ.፴፪፥፲፬፤ ይላል። እንግዲህ እግዚአብሔር ከወደዳቸው ከወዳጆቹ ጋር እንዲህ ሲሠራ የሚመለከት ልቡና ከመንፈሳዊ ቅናት የተነሣ ራሱን ለውጦ እነዚህን የእግዚአብሔር ወዳጆች መከተልን መምረጥ ያስፈልገዋል።

ስለ ሙሴ ሌላ ምሳሌ እናንባለን። በቅዱስ መጽሐፍ እንደተጻፈው በሲና ተራራ ላይ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር አርባ መዓልትና ሌሊት ቆይቷል። ዘጸ.፴፬፥፳፰። ነገር ግን አሠርቱን ትእዛዛት ለመጻፍ በውኑ ለእግዚአብሔር እንኳን አርባ ቀን ቀርቶ ጥቂት ደቂቃዎችም አያስፈልጉትም። ለሙሴ ስላለው ፍቅር ግን ሙሴ አርባ መዓልትና ሌሊት በተራራው ላይ እንዲቆይ ተወው። ሙሴ የእግዚአብሔር ሰው በመሆኑ እግዚአብሔር ተደስቶበታል:- እንዲሁ ደግሞ ሙሴም ከእግዚአብሔር ጋር ቃል በቃል ለመነጋገር እድል በማግኘቱ ደስተኛ ነበር።



እግዚአብሔር ብዙ ወዳጆች አሉት – እነዚህንም በግልጽ «ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም።...ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ።» ሲል ነግሮአቸዋል። ዮሐ.፲፭፥፲፭። ዮሐ.፲፭፥፭። ዮሐ.፲፭፥፴፮። በወንጌልም ስለወንጌላዊው ዮሐንስ በመደጋገም «ኢየሱስ የሚወደው ደቀመዝሙር» እየተባለ ተነግሯል።

እግዚአብሔር ለሚወዳቸው የሰማይን መክፈቻ በእጃቸው ሰጥቷቸዋል። ቢወዱ የሚከፍቱበት ባይወዱ የሚዘጉበት ሥልጣንም ጭምር ሰጥቷቸዋል። ከዚህም የተነሣ እጅግ በሚያስደንቅ ድምፅ ነቢዩ ኤልያስ «ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም።» ብሎ ሲናገር እንመለከተዋለን። ፩ነገ.፲፯፥፩። «ከአፌ ቃል በቀር» የሚለው ሐረግ አስፈሪና አስገራሚ ነው:- እግዚአብሔር ቢፈቅድ እንኳን አላለም – ይልቅ እርግጠኛ በመሆን ተናገረ እንጂ። እንደተናገረውም ሰማያት ተዘጉ – ሳይከፈቱም ለሦስት ዓመት ከስድስት ወራት ቆዩ። ኤልያስ እንዲከፈቱ በተናገረ ጊዜም ሰማያት ተከፈቱ – ጠልና ዝናብም ሆነ።

ስለእነዚህ ለቅዱሳን ስለተሰጡት የሰማይ መክፈቻዎች ስለያዙአቸውም ቅዱሳን:- እነርሱ

«እንደሚጸልዩ ሳይሆን ጸሎትን እንደሚቀበሉ፣ ከአባቱ ሀብት ለሰዎች ሁሉ ይሰጥ ዘንድ ሥልጣን እንዳለው ልጅ»

ናቸው ተብሎ ተነግሯል። እኛም እንግዲህ ይህን የመሰለ ጸጋ የተሰጣቸውን የእግዚአብሔር ወዳጆች ታሪክ ባነበብን ጊዜ ለዚህ ጸጋ ልንቀና ይገባናል። «ቅንዑ ለአንተ ተዓቢ ጸጋ» እንዳሉ አበው።

እግዚአብሔር ለእነዚህ ለሚወዳቸው ከጸጋው በመስጠት ብቻ አይረካም – ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠብቃቸዋል – በእነርሱ ላይም አንዳች ክፉ ነገር እንኳ እንዲነገርባቸው አይሻም። የመጀመሪያው ምሳሌም ሙሴ ነው። ሙሴ ከእሥራኤል ሕግ ውጭ ኢትዮጵያዊቱን ባገባ ጊዜ ወንድሙ አሮንና እኅቱ ማርያም ስለእርሱ ተቆጡ – አንጎራጐሩም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በሙሴ ላይ ስለተናገሩት ነገር ተቆጣ። ሙሴ ቢታገሣቸውም እግዚአብሔር ግን አልታገሣቸውም:- ስለዚህም ሦስቱንም ጠርቶ «ቃሌን ስሙ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ። ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም:- እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው። እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ:- በምሳሌ አይደለም:- የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል። በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ

www.ethiopianorthodox.org

ዘንድ ስለምን አልፈራችሁም?» አላቸው። ዘኍ.፲፪+፩—፰። ማርያምንም በለምፅ መታት:- እንደ አመዳይም ነጭ ሆነች። ከሰፈር ውጭም ሰባት ቀን ተዘግታ ተቀመጠች። ዘኍ.፲፪+፱+፲፭። ይህም ለአባታችን አብርሃም የተነገረውን ኪዳን እንድናስታውስ ያደርገናል:- እግዚአብሔር «የሚባርኩህን እባርካለሁ:- የሚረግሙህንም እረግማለሁ» ብሎታልና። ዘፍ.፲፪+፫። ይህም እግዚአብሔር ለወደዳቸው የሰጠው ግሩም ክብር ነው። የሚባረኩ ብቻ ሳይሆኑ ለበረከትም እንዲሆኑ ነግሮአቸዋል። ዘፍ.፲፪+፪። ይህም ኤልያስ በመበለቲቱ ቤት፤ ዮሴፍም በጲጥፋራ ቤትና በግብፅ፤ ኤልሳዕም በሱናማዊቱ ሴት ቤት ለበረከት እንደሆኑ ማለት ነው።

ሌላው እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ልጆቹ የሚሰጠው የሚያስደንቅ ክብር ተአምራት እንዲያደርጉ በሚሰጣቸው ኃይል ነው። እርሱ ብቻ ሊያደርገው የሚችለውን እነርሱ እንዲያደርጉት ያስችላቸዋል። በእነርሱ ተአምራትም እርሱ ይመሰገናል። ወዳጆቹም በስሙ ተአምራት በማድረጋቸው የከበሩ ይሆናሉ። እርሱ «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል:- እናንተን የሚያከብር እኔን ያከብረኛል:- እኔም ደግሞ አከብረዋለሁ።» ብሎአል። ማቴ.፲+፵። ክብራቸውም ታላቅ ነው። ይህንንም ሲገልጽ «እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ።» ብሏቸዋል። ማቴ.፲፱+፳፰። ምናልባት ብቸኛው ፈራጅ እግዚአብሔር አይደለምን? እንዴት ፈራጅ ያደርጋቸዋል? የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል። እርሱ ግን የሚሰጠው መልስ አለው:- ምንም እንኳ የመፍረድን ሥልጣን ከባሕርይ አባቴ ያገኘሁት የባሕርይ ገንዘቤ ቢሆን ዮሐ.፭+፳፪። ደስታዬ በሰው ልጆች ነው:- የሰው ልጆችን አፈቅራቸዋለሁ:- አከብራቸዋለሁም። እኔ በምድር ሁሉ ላይ ፈራጅ ብሆን እነርሱ ደግሞ በምድር ላይ ይፈርዳሉ፤ እኔ የነገሥታት ንጉሥ ብሆን እነርሱ ከእኔ ጋር ይመራሉ፤ እኔ በታላቅ ክብር በደመና ብመጣ ከእኔ ጋር በደመና ይመጣሉ፤ ዘወትር ከእኔ ጋር ይሆናሉ — እኔ ባለሁበት በአዚያ እነርሱ ደግሞ ይሆናሉ።

እንግዲህ እግዚአብሔር በማፍቀር፤ አብሮአቸው በመሆን፤ እነርሱን ከክፉ በመጠበቅ፤ የሰማያትን መክፈቻ በመስጠት፤ ክብራቸውን ሰው ሁሉ እንዲያውቀው በማድረግና ሰዎችም እንዲያከብሯቸው በማዘዝ ቅዱሳኑን ምን ያህል እንደሚወዳቸውና እንደሚያከብራቸው ተመልክተናል።

ኃጢአት ግን የዚህ ሁሉ ተቃራኒ ነው:- ኃጢአት እግዚአብሔርን፤ ቅዱሳን መላእክትንና የቅዱሳንን ሁሉ ተራዳኢነት ማጣት ነው።



## ኃጢአት እግዚአብሔርን ማጣት ነው

በኃጢአት የሚኖር ሰው ራሱንና ልቡናውን ከእግዚአብሔር በመለየቱ እግዚአብሔርን ያጣል። ስለሆነም ኃጢአት ከሁሉ በፊት የእግዚአብሔርን ፍቅር ማጣት ነው። ጌታችንም «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል» ዮሐ.፲፬+፳፫—፳፬። ከማለቱም በላይ «ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።» ፩ዮሐ.፪+፲፭ ሲል ወንጌላዊው ዮሐንስ ይህንን አባባል የበለጠ ያብራራዋል። እግዚአብሔርን የሚወድ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ወደሚያቀርበው ያዘነብላል። ወደ ኃጢአት የሚያዘነብል ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍቅር ከልቡናው ያስወጣዋል — በአንድ ጊዜ ኃጢአትንም እግዚአብሔርንም መውደድ አይቻልምና።

በተጨማሪም ኃጢአት ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ፤ በእርሱ ላይ ማመፅ እርሱንም መናቅ ጭምር ነው። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እንደቀላል ነገር መቁጠርና ሁሉን ማየት በሚችል በእግዚአብሔር ፊት ትእዛዛቱን መተላለፍና ፈሪሃ እግዚአብሔርን ማጣት ነው።

ጻድቃን ግን እንዲህ አይደሉም። ለምሳሌ ጻድቁ ዮሴፍ የኃጢአት ግብዣ በቀረበለት ጊዜ «ይህን ክፉ ሥራ እንዴት አደርጋለሁ በእግዚ አብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ።» ሲል መልስ መስጠቱ ከመንፈሳዊ ጥንካሬና እግዚአብሔርን ከመፍራት የተነሣ ነው። ዘፍ.፴፱+፱። ኃጢአት በቀረበለት ጊዜ እግዚአብሔር በፊቱ ነበር። ኃጢአትንም እግዚአብሔርን እንደመቃወም ቆጠረው እንጂ ሴቲቱንና ባልዋን እንደ መቃወም ብቻ አልቆጠረውም። ቅዱስ ዳዊትም ፈጣሪው እግዚአብሔርን «አንተን ብቻ በደልሁ:- በፊትህም ክፋትን አደረግሁ።» ሲል መናገሩ ተመሳሳይ ትርጉም ያለው ነው። መዝ.፶+፬።

እንዲሁ ሁሉ ደግሞ ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን መቃረንም ጭምር ነው። ኃጢአት በእግዚአብሔር መንግሥት፤ በቅድስናው በጽድቁም ላይ ማመፅ ነው። ግዛቱ የሆነ ልቡናንም ለሌላ ገዥ (ዲያብሎስ) አሳልፎ መስጠት ነው። እግዚአብሔር እንደማይወሰን ሁሉ የእርሱን ባሕርይ የምትቃረን ኃጢአትም ወሰን የላትም። ቅጣቷም ወሰን የሌለው ነው።

## ኃጢአት መንፈስ ቅዱስን መቃወም ነው!

በውስጣችን ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ ለእግዚአብሔር ልጆች እንደሚገባ በቅድስና እንድንኖርና የጽድቅን ሥራም እንድንሠራ

www.ethiopianorthodox.org

ይፈልጋል። በኃጢአት የምንመላለስ ከሆነ ግን መንፈስ ቅዱስን እንቃወማለን። በቅዱስ መጽሐፍም:- «ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።» ኤፌ.፬፥፴። ተብሏል። ስለዚህ ኃጢአትን የሚሠራ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንፈስ ያሳዝናል። መጽሐፍ «መንፈስን አታጥፉ» ፩ተሰ.፭፥፲፱ በማለት ይመክራልና። መንፈስ ቅዱስ በሰው ልቡና ውስጥ የሚሠራ ከሆነ በፍቅር የነደደ፣ ለመልካም ነገር የሚፋጠን፣ ስለእግዚአብሔር መንግሥት የተቀደሰ መንፈሳዊ ቅናት እንዲያድርበት ይሆናል። ምክንያቱም አምላካችን እግዚአብሔር በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና። ዕብ.፲፪፥፳፱። እግዚአብሔርን በሕይወቱ የያዘ ሰው የሚያቃጥል እሳትን የተሸከመ ነው። በመጽሐፍም «መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል» መዝ.፻፫፥፬ የሚያደርግ ተብሎ ተጽፏል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ» ብሏል። ሮሜ.፲፪፥፲፩። ለዚህ ነው ቅዱሳን ሐዋርያትም በእሳት አምሳል እየተከፋፈለ የወረደውን መንፈስ ቅዱስን ሊቀበሉ የቻሉት። የሐዋ.፪፥፫—፬።

በመጽሐፍ ቅዱስ አባባል ከዚህ በላይም እንደተገለጠው ማንም ኃጢአትን የሚሠራ ሰው መንፈስ ቅዱስን ከእርሱ ያስወጣል። መንፈስ ቅዱስም ይርቀዋል። ይህ ሰውም በመንፈሳዊ ሕይወቱ እየተዳከመና እየቀዘቀዘ ይሄዳል። ቀስ በቀስም የእግዚአብሔር መንፈስ ከእርሱ እየራቀ ይሄዳል። መንፈስ ቅዱስ ፈጽሞ ከኃጢአተኛው ሰው በተለየ ጊዜ፣ ያንጊዜ ልክ ንጉሥ ሳኦልን ርኩስ መንፈስ እንደአሰቃየው ይህንንም ሰው ያሰቃየዋል። ፩ሳሙ.፲፮፥፲፬። እንዲህ ያለው ሁኔታ ነው ንጉሥ ዳዊትን «አቤቱ ከፊትህ አትጣለኝ:- ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ» እያለ ወደፈጣሪው እንዲጸልይ ያደረገው። መዝ.፶፥፲፩። እንደዚህ እንደዳዊት ከልብ ሆኖ መጸለይ ያስፈልጋል። ያለበለዚያ መንፈስ ቅዱስ ከሕይወት ሲርቅና ርኩስ መንፈስ ሲቀርብ ዝም ማለት መቃረን ነው። መንፈስ ቅዱስን መቃወም ደግሞ በልቡና ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ፈጽሞ እምቢ ማለት ነው። ከኃጢአት ብዛት የተነሣ ሰው እስከ ሞት እንኳ ቢሆን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ሊቃወም ይችላል። በዚህም ምክንያት መንፈስ ቅዱስ በሰው ልቡና ውስጥ ሥራውን ካልሠራ ሰው ንስሐ ሊገባ አይችልም። ሰው በኃጢአቱ እንዲፀፀትና ንስሐ እንዲገባ የሚያበረታው መንፈስ ቅዱስ ነውና። ዮሐ.፲፮፥፰። ሰው ደግሞ ንስሐ ካልገባ ይቅርታን ሊያገኝ አይችልም። ቅዱሳን «ንስሐ ሳይገባበት ከቀረው በቀር ይቅር የማይባል ኃጢአት የለም» ብለው እንደተናገሩት። መንፈስ ቅዱስን



መቃወምም ሥርየት የሌለው ኃጢአት ነው ተብሏል። እንግዲህ ገና ከመንፈስ ቅዱስ መለየት ደረጃ ላይ አልደረስንምና የእግዚአብሔር መንፈስም ወደንስሐ እየመራን ነውና በልቡናችን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ከመቃወም ፈቀቅ ልንል ይገባናል። በቀደመ ኃጢአታችን የእግዚአብሔርን መንፈስ አሳዝነንነው ከሆነ ዳግመኛ እንዳንበድል:- ከልቡናችንም አርቀነው ከሆነ ውስጣዊ ተቃውሞአችንን እንድንተው:- በእጅጉ ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር መንፈስ በእኛ ውስጥ ሆኖ የተቀደሰውን ሥራ እንዲያሠራን ደግሞ ኃጢአትን መጥላት ተገቢ ነው። ኃጢአት በጣም አደገኛ ነው የሰውን የተቀደሰ ባሕርይ ያዋርዳል—ያረክሳልና።

## ኃጢአት የሰዎች የባሕርይ ርኵሰት ነው

ስለ ኃጢአተኞች «ሁሉ ዐመፁ:- በአንድነትም ረከሱ፣ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም:- አንድም ስንኳ የለም።» ተብሎ ተነግሯል። መዝ.፲፫፥፫። ሰው ከኃጢአት የተነሣ ካልረከሰና አርአያና ምሳሌነቱን ካልአጣ በስተቀር በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረ ክቡር ፍጥረት ነው። ስለዚህ በኃጢአት ከወደቁ በኋላ «ኃጢአት ለሰው ባሕርይ የሚስማማ ነውና ይቅርታ ሊደረግልኝ ይገባል» የሚለው የደካሞች አመለካከት ተቀባይነት የለውም። እግዚአብሔር ሰውን ለኃጢአት ባርያና ተገዥ አድርጎ አልፈጠረውምና ኃጢአት ሠርቶ ደካማ ስለሆንኩ ነው ማለት ተገቢ አይደለም። ዘፍ.፩፥፴፩። በኃጢአት ከረከሰ በኋላ ግን የሰው ባሕርይ ጎስቁሏል:- ስለዚህ ነው ሐዋርያው «እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥኩ የሥጋ ነኝ።...እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ:- ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» ሲል የተናገረው። ሮሜ.፯፥፲፬፤ ፳፬። ኃጢአት የሰውነት ባሕርይን ያጎሰቁላል—ከሰማያዊ ክብሩም ያዋርዳል ይጥላል።

ኃጢአት መዋረድ ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ልጅነት በመውጣት ተዋርዶ የሰይጣን ልጅ ለመሆን የበቃው በኃጢአት መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል። ከዚህ ውርደት የተነሣ በሰው ውስጥ የነበረው ብርሃን ጭለማ ይሆናል። እርሱም የነበረበትን ታላቅ ክብር ረስቶ የተናቀ ይሆናል። ኃጢአተኛ ሰው በራሱ ይዋረዳል—እራሱንም ያጠፋል። በውኑ የንጉሥ ልጅ በቆሻሻ ሥፍራ ይቀመጣልን? አይቀመጥም። የእግዚአብሔር ልጅማ እንዴት?

www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአተኛ ሰው በራሱ የተዋረደ ብቻ ሳይሆን በሰዎች ዘንድም ወራዳ ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው ሴትን አይቶ የተመኛት ሰው ነው። ይህን የመሰለው ሰው በሃሳቡ ሰማያዊ የሆነውን የሚያስብ ቢሆን ለራሱ:- ‹ይህች ሴት የእግዚአብሔር መቅደስ ናት–የመንፈስ ቅዱስም ማደሪያ:- እንዴትስ እርሷን አረክሳታለሁ? የእግዚአብሔርን ሕንፃ ማፍረስ አይቻለኝምና› በማለት ራሱን ይወቅስ ነበር። በመጽሐፍ «ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል:- የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና።» ተብሎ ተጽፏልና። ፩ቆሮ.፫፥፲፯። የሰውን ባሕርይ የሚያረክሰው ኃጢአት ሰው የእግዚአብሔር መቅደስ መሆኑን በመርሣት ባሕርይን አጎሳቁሎ ራስን ለርኵሰት ተገዥ ማድረግ ነው። ይህ ደግሞ የሰውን ባሕርይ ብቻ ሳይሆን ምድርን ሁሉ የሚያረክስ ነው። ለዚህ ነው በመጽሐፍ ስለታላቂቱ ጋለሞታ «በዝሙትዋ ምድርን ያጠፋች» ተብሎ የተነገረው። ራእ.፲፱፥፪።

## ስለኃጢአት የሚባል ሌላ ምን አለ?

### ኃጢአት መቆሸሽ:- ርኵሰትና ውርደት–ነው

ኃጢአት መቆሸሽ ነው። ለዚህ ነው የወደቁት መላእክት «ርኩሳን መናፍስት» ተብለው የተጠሩት። ማር.፩፥፯። ይህንንም አስመልክቶ እግዚአብሔር «የእሥራኤል ቤት በምድራቸው በተቀመጡ ጊዜ በመንገዳቸውና በሥራቸው አረከሱአት፤ መንገዳቸውም በፊቴ እንደመርገም ደም ነበረ።» በማለት በሕዝቅኤል አድሮ ተናግሯል። ሕዝ.፴፮፥፲፯። ስለሰንበትም ደግሞ «በእኔና በእነርሱ መካከል ምልክት ይሆኑ ዘንድ ሰንበታቴን ሰጠኋቸው። ነገር ግን በትእዛዜ አልሄዱም፤ ሰንበታቴንም ፈጽመው አረከሱ።» ብሎአል። ሕዝ.፳፥፲፫። ስለካህናቱ ኃጢአት ሲናገር ደግሞ «ክህነትን:- የክህነትንም ቃል ኪዳን አፈረሱ (አረከሱ)» ብሎአል። ነፍስ መግደልን አስመልክቶም በመጽሐፍ ቅዱስ «እጃችሁ በደም ጣታችሁም በበደል ረክሳለች።» የሚል ተጽፏል። ኢሳ.፶፱፥፫። ስለዝሙትም «በግልሙትናሽና በኃጢአትሽ ምድሪቱን አረከስሽ።» ይላል። ኤር.፫፥፪።

ኃጢአት (መቆሸሽን) ርኩሰት ነው ስንል ዝሙትንና ነፍስ መግደልን ብቻ ሳይሆን የአፍንና የምላስንም ኃጢአት የሚያጠቃልል ነው። በምላስ ስለሚሠራ ኃጢአት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ «ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ አይደለም:- ከአፍ የሚወጣው (ምላስ የምትናገረው) ግን



ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው።» ሲል አስተምሮአል። ማቴ.፲፭፥፲፩። ጌታችን ርኩሰት የሚለውን ቃል ኃጢአትን በአጠቃላይ ለማመልከት ተጠቅሞበታል። ስለጻድቃን ሲናገርም «ነገር ግን ልብሳቸውን ያላረከሱ ጥቂት ሰዎች አሉ። የተገባቸውም ስለሆኑ ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ።» ይላል። ራእ.፫፥፬። ስለኃጥአን ደግሞ «ነገር ግን በገባችሁ ጊዜ ምድሬን አረከሳችሁ፤ ርስቴንም አጐሰቈላችሁ።» ብሏል። ኤር.፪፥፯።

እንግዲህ ኃጢአት ርኩሰት ከሆነ ራሳችንን ከኃጢአት ማራቅ ይኖርብናል። በኃጢአት የሚኖር ሰው የረከሰ መሆኑ ይሰማዋል። ከአንደበት የሚወጣውም ኃጢአት ሁሉ የሚያረክስ ነው:- ሰውን የሚያረክሰው ከአፍ የሚወጣ ነው ተብሏልና።

ዝሙት የርኩሰት የመጨረሻ ደረጃ በመሆኑ ኃጢአት ዝሙትም ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ስለእሥራኤል ልጆች ኃጢአት «ይሁዳ አመነዘረች፤ እሥራኤል አመነዘረች» የሚል ተጽፎአል። ሕዝ.፲፯።

ኃጢአት ጸጋን ማጣትና ውርደትም ነው። በምሳሌ:- «ኃጢአት ግን ሕዝብን ታስነውራለች» ተብሏል። ምሳ.፲፬፥፴፬። በተጨማሪም ኃጢአት ደዌ ነው። ስለዚህም ነቢዩ ኢሳይያስ «እግዚአብሔርን ትተዋል። የእሥራኤልንም ቅዱስ አቃልለዋል ራስ ሁሉ ለሕመም ልብም ሁሉ ለድካም ሆኖአል። ከእግር ጫማ አንሥቶ እስከ ራስ ድረስ ጤና የለውም:- ቁስልና እበጥ የሚመግልም ነው:- አልፈረጠም:- አልተጠገነም:- በዘይትም አልለዘበም።» በማለት ተናግሯል። ኢሳ.፩፥፭–፮። ሰው ኃጢአት በሠራ ጊዜ የመንፈስ በሽተኛ ይሆናል።

ኃጢአት አለማወቅም ነው። ይህም እግዚአብሔርን፤ እምነትን፤ መልካም የሆነውን ሁሉ አለማወቅ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔርም «በሬ የገዥውን አህያም የጌታውን ጋጣ አወቀ:- እሥራኤል ግን አላወቀም:- ሕዝቤም አላስተዋለም» በማለት ተናግሯል። ኢሳ.፩፥፫።

በአጠቃላይ ኃጢአት ጉድለት:- ሕፀፅ፤ መታወር፤ ጨለማና እግዚአብሔርን መርሳት ነው። ጨለማ ነው መባሉም እውነት ነው:- ምክንያቱም በባሕርዩ ብርሃን ከሆነ ከብርሃናት ጌታ ከእግዚአብሔር ይለያልና። ከዚህ አንፃር ነው ስለኃጢአተኞች:- «ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ» የተባለው። ዮሐ.፫፥፲፱። በተጨማሪ ደግሞ በመክብብ «ሰነፍ ግን በጨለማ ይሄዳል።» የሚል ተጽፏል። መክ.፪፥፲፬። እንግዲህ ሁለት ነገሮች ከኃጢአት እንድንሸሽ ያደርጉናል። እነዚህም የኃጢአት ክፉ ባሕርይና አስፈሪው የኃጢአት ፍጻሜ (ዘለዓለማዊው እሳት) ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

## የኃጢአት ፍጻሜዋ ምንድን ነው?

### ፫. የኃጢአትን ውጤት (ፍጻሜ) ብታውቅ ከኃጢአት ትሸሻለህ

### የኃጢአት ውጤት ፍርሃትና እረፍት ማጣት ነው

ኃጢአት የሰውን ውስጣዊ ሰላም ያሳጣል:- ልቡናንም በጭንቀት በመሙላት ፈሪ ያደርጋል። ቅዱሱ ግን አይፈራም። ነቢዩ ዳዊትም እንዲህ ብሏል። «ሠራዊትም ቢሰፍርብኝ ልቤ አይፈራም። ሰልፍም ቢነሣብኝ በዚህ እተማመናለሁ።» መዝ.፳፮፥፫። ኃጢአተኛ ግን ያለማቋረጥ ይፈራል ሰላምም የለውም። «ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሔር።» ኢሳ.፵፰፥፳፪። በድጋሚም «ክፉዎች ግን እንደሚናወጥ ባሕር ናቸው ውኆቹም ጭቃና ጉድፍ ያወጣሉና። ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል አምላኬ።» ኢሳ.፶፯፥፳።

ፍርሃት የተጀመረው ከመጀመሪያው የአዳምና ሔዋን ኃጢአት ነው። አዳም ከኃጢአቱ በፊት እግዚአብሔርን ስለመፍራቱ አልተጻፈም። በተቃራኒው ግን አዳምና ሔዋን በገነት ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገሩ – በደስታም ይኖሩ ነበር። ከኃጢአቱ በኋላ ግን አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ፊት ማየት ስለአስፈራቸው ከገነት ዛፍ ሥር እንደተደበቁ ተጽፎ እናገኛለን። እግዚአብሔርም በጠራው ጊዜ አዳም በመፍራትና በመንቀጥቀጥ «በገነት ድምፅህን ሰማሁ:- ዕራቁቴንም ስለሆንኩ ፈራሁ፤ ተሸሸግሁም።» ሲል ተናግሯል። ዘፍ.፫፥፲።

ሰው ሁሉ ፊቱን ለማየት የሚሻው ቸርና ሰውን ወዳጅ የሆነው እግዚአብሔር ለኃጥአን አስፈሪ ሆነ– ስለዚህም ሰው ከእርሱ ዕይታ ለመሰወር ሲሸሽ እንመለከታለን። ከሰው ሁሉ የበለጠ ደግ የሆነውና የአፉ ቃላትም እጅግ ጣፋጭ የሆነው እግዚአብሔር ለኃጥአን አስፈሪ ሆነ። እግዚአብሔርን የምትወድ ነፍስ ግን የምትወደውን እርሱን ትሻዋለች:- ታገኘዋለችም። መኃ.፫፥፪–፬። ለኃጢአተኛ ነፍስ ግን በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ አስፈሪ ነው። ዕብ.፲፥፴፩።

እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ዘንድ አስፈሪ ነው። ቅዱሳኑ ግን ወዳጆቹ ናቸውና በእርሱ ሐሤት ያደርጋሉ። ታላቁ ቅዱስ እንጦንስ ደቀመዛሙርቱን:- ‹ልጆቼ እግዚአብሔርን አልፈራውም› አላቸው። እነርሱም ደንግጠው ‹ይህን መናገር ከባድ ነው› አሉት። እርሱም መልሶ ‹ልጆቼ ሆይ



ስለምወደው ነው:- በፍቅር ፍርሃት የለምና:- ፍቅርም ፍርሃትን ያስወግዳልና› አላቸው። ፩ዮሐ.፬፥፲፰።

እግዚአብሔር ዛሬ ወደ እኛ ቢመጣ በደስታ ከሚቀበሉት ወይስ ከኃጢአታቸው የተነሣ ከሚሸሹት ወገን እንሆን? ሰዎች ሞትንና ፍርድን – የመጨረሻውንም የፍርድ ቀን ይፈራሉ። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ኃጢአትን መተው ነው። የኃጢአተኞች የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ፍርሃትና ሞት ነውና። በመጽሐፍም «በዚያን ጊዜ ተራራዎችን:- በላያችን ውደቁ:- ኮረብቶችንም ሰውሩን ይሉ ዘንድ ይጀምራሉ።» ተብሎ የተነገረው የኃጥአን ፍጻሜ ሞትና ፍርሃት መሆኑን የሚያመለክት ነው። ሉቃ.፳፫፥፴። ሆሴ.፲፥፰። ከዚህም በላይ ሞትን ሲሹ እንኳን የማያገኙት መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ– «በዚያም ወራት ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ:- አያገኙትምም:- ሊሞቱም ይመኛሉ:- ሞትም ከእነርሱ ይሸሻል።» ሲል በይበልጥ ያብራራል። ራእ.፱፥፮።

አዳም ኃጢአትን በሠራ ጊዜ ከዚያ በፊት ያልነበሩት ሦስት ባሕርያትን ገንዘብ አደረገ። እነዚህም ፍርሃት:- ድንጋጤና ሰላም ማጣት ናቸው። እነዚህ ሦስቱ ከኃጢአቱ ያገኛቸው ወይም ከኃጢአቱ የተነሣ የመጡበት ናቸው። ፍርሃት ነፍስን የሥነ ልቡና ሕመምተኛ ያደርጋታል። ከኃጢአት የተለየ ሰው ውስጣዊም ሆነ አፍአዊ (ውጫዊ) ሰላምና ደስታ አለው። በኃጢአት የሚኖረው ግን ሁለቱንም የለውም።

አእምሮ ከኃጢአት የተነሣ ይፈተናል – ይጨነቃልም። የጲላጦስ ታሪክ ለዚህ በቂ ማስረጃና ምሳሌ ይሆናል። ጲላጦስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም በደል እንደሌለበት ባወቀ ጊዜ «እነሆም በፊታችሁ መርምሬ ከምትከሱበት ነገር አንድ በደል እንኳ በዚህ ሰው አላገኘሁበትም።» አለ። ሉቃ.፳፫፥፲፬። በፍርድ ወንበር በተቀመጠ ጊዜ ደግሞ ሚስቱ «ስለ እርሱ ዛሬ በሕልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁና በዚያ ጻድቅ ምንም አታድርግ» ብላ ላከችበት። ማቴ.፳፯፥፲፱። ይህን ሁሉ እያወቀ የሞት ፍርድ ከፈረደበት በኋላ የራሱን ኅሊና ለመሸንገል– «እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ እናንተ ተጠንቀቁ» ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ። ማቴ.፳፯፥፳፬። በዚህም አእምሮው ምንኛ እንደተፈተነ እንረዳለን።

ኃጢአት ኅሊናን ያደክማል። ሰው ኃጢአትን እስኪሠራው የኃጢአት ክፋትና የሚያስከትለው አደጋም አይሰማውም ወይም አይታወቀውም። ምክንያቱም ኃጢአትን የሚያሠራው ክፉ መንፈስ ኃጢአትን እስኪፈጽም ወይም ከፈጸመ በኋላ እስከ ጥቂት ጊዜ ድረስ አእምሮውን ስለ ሚገዛውና

www.ethiopianorthodox.org

ኅሊናውን ስለሚያደነዝዘው ነው። የኃጢአትን አደጋ የሚረዳው ከዚህ ሲነቃ ነው። የአስቆሮቱ ይሁዳ ታሪክ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ይሁዳ ጌታውን አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ የሚሠራውን ሥራ አደገኛነት አያስተውልም ነበር – ጌታውን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ ወደ አእምሮው ሲመለስ ነው ጌታችን ይነግረው የነበረው ሁሉ ትዝ ያለው። ሉቃ.፳፪፥፳፪። ማቴ.፳፮፥፵፱። ሉቃ.፳፪፥፵፰። ከዚህ በኋላም ኃጢአቱ ታየው። ማቴ.፳፯፥፫። ነገር ግን ኅሊናው ሰላም አልነበረውም – ከኅሊናው ወቀሳ ለማምለጥ ሌላ ኃጢአት ይሠራ ዘንድ አሰበ:- ይህም ተስፋ መቁረጥ ነው። ተስፋ በመቁረጡም ታንቆ ሞተ። ማቴ.፳፯፥፭። የኅሊናው ድካም ሰላም ነሥቶ ለሞት አበቃው።

ከኃጢአት በኋላ ስላለው ፍርሃት፣ ድንጋጤና ሰላምና እረፍት ማጣት ሌላው ምሳሌ የቃየል ሕይወት ነው። ዘፍ.፬፥፲፫–፲፬። ቃየል ወንድሙን በግፍ በመግደሉ ያተረፈው አንዳችም ነገር የለም። ያተረፈው ነገር ቢኖር መጨነቅ፣ ሰላም ማጣትና ተቅበዝባዥ ሆኖ መኖርን ብቻ ነው። ለዚህ ነው በመጽሐፍ «ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሔር» ተብሎ የተጻፈው። ኢሳ.፵፰፥፳፪።

ከዚህ በተቃራኒ ጻድቃን በሰላም፣ በፍቅርና ደስታ ይኖራሉ። በቅዱስ መጽሐፍ «የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም...ነው» ተብሎ ተጽፏልና። ገላ.፭፥፳፪።

እንግዲህ ለኃጢአተኛ ማልቀስና ጥርስ ማፋጨት የማይቀርለት ከሆነ በዚህ ምድር እያለ መከራን ቢቀበል ይሻለዋል በኋለኛው ሕይወት ተስፋ አለውና:- በዚህ ምድር ቅጣቱን ካልተቀበለ ለቅሶውና ጥርስ ማፋጨቱ በፍርድ ቀን ስለሚሆን ተስፋም አይኖረውም።

ከዚህ በላይ ከጠቃቀስናቸው የኃጢአት ውጤቶች በተጨማሪ ደግሞ የሚከተሉትንም እናያለን። ኃጢአት ሰውን ፈጽሞ ይለውጣልና።

### ሀ. የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ መሆንን ማጣት

ሰው በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረ ነው። ከዚህም ሌላ ሕያው፣ ነባቢና ለባዊ በመሆኑ ሰውም ደግሞ የሕያውነት፣ የነባቢነትና የለባዊነት ባሕርይ ስላለው በዚህ የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ነው። ከዚህ ሌላም እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና ሰዎችም ቅድስናን ገንዘብ በማድረግ «እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ሲል የተናገረውን ቃል በመፈጸም የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። ኃጢአት ደግሞ ርኵሰት በመሆኑና ውጤቱም ሞት ስለሆነ በኃጢአት የወደቀ ሰው ሕያውና ቅዱስ የሆነው የእግዚአብሔር አርአያ መሆኑን ያጣል። ውስጣዊም ሆነ አፍአዊ ማንነቱ የኃጢአት መግለጫ በመሆኑ የእግዚአብሔር ወገን መሆኑን ያጣል። ማር.፲፬፥፳፩። ፩ዮሐ.፫፥፲። ስለዚህ በኃጢአት የወደቅን ሁሉ ንስሐ በመግባት ያጣነውን– አምላክ ያደለንን ጸጋ ገንዘብ ለማድረግ አብዝተን ልንተጋ ይገባል።

### ለ. ክብርን ማጣት

ሰው ሲፈጠር እግዚአብሔር በሰጠው ሕይወት በክብር እንዲኖር ነበር። ኃጢአትን ከሠራና ከፈጣሪው ከተጣላ በኋላ ‹አፈር ነህና ወደአፈር ትመለሳለህ› ተባለ። የተሰጠውንም ሰማያዊ ክብር ብቻ ሳይሆን በምድርም ክብርን አጥቶ ተዋረደ። ለእንስሳት የነበረውንም እንዲበላ ሆነ። ዘፍ.፫፥፲፰። ዘፍ.፩፥፳፰። ሊገዛቸው የተፈጠሩት እንስሳትና አራዊት እንዲያጠቁት ሆነ። ዘፍ.፩፥፳፮። ዘፍ.፫፥፲፯። መሬት እንኳ አመፀችበት። ዘፍ.፫፥፲፰። ዘፍ.፬፥፲፪።

በኃጢአት የሚኖር ሰው ክብሩንና ሊሰጠው የሚገባውንም አክብሮት ያጣ ነው። እንዲህ ዓይነት ሰው የዲያብሎስ የእጆቹ አሻንጉሊት ነው። ራሱን በራሱ እንኳ ማክበር የማይችልና ራሱን ያዋረደ ነው። የጠፋው ልጅ– ሉቃ.፲፭፣ ናቡከደነፆር– ዳን.፭፥፳–፳፩፣ እንዲሁም በኃጢአት የተነጣ ክብሩንና ኃይሉን ያጣው ሶምሶን– መሳ.፲፮፥፲፱–፳፩። ለዚህ በቂ ምሳሌዎች ናቸው።

ስለዚህ ኃጢአትን እንድንሠራና ከክብራችን እንድንዋረድ ኃጢአትን መልካም አስመስሎ የሚፈትነን ጠላት ዲያብሎስን እምቢ ማለትና መዋጋት አስፈላጊ ነው።

### ሐ. ንጽሕናን ማጣት

ቅዱስ ሰው ከኃጢአት ንጹሕ ነው። ከመልካም ነገር በቀር ምንም አያውቅም። ኃጢአትን ሲጀምር ክፋትን ያውቀዋል። ንጽሕናውንም ያጣል። አዳምና ሔዋን ከኃጢአት በፊት ንጹሐንና በነፃነት የሚኖሩ ነበሩ። ኃጢአትን በሠሩ ጊዜ የጸጋ ልብሳቸው ተገፍፎ እርቃናቸው ስለተገለጠ የሚሸፈኑበት ቅጠል ፈለጉ። ኃጢአት የኅሊና ነፃነትንና የልቡና ንጽሕናን ያሳጣል። ሰው በንስሐ የተመለሰና ከኃጢአት የተለየ እንደሆነ ያጣውን



www.ethiopianorthodox.org

ነፃነትና ንጽሕና ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊያገኘው ይችላልና ንስ[illegible] መግባትና በንጽሕና መኖር ጠቃሚ ነው።

## ፬. ኃጢአት የሚያስከትለውን ቅጣት ብታውቅ ኃጢአትን ትፈራ ነበር

እግዚአብሔር መሐሪና ለምሕረቱም ገደብ እንደሌለው ሁሉ ፍርዱም እውነትና ፍጹም መሆኑንና በደልን ይቅር የሚል ኃጢአትንም የማይወድ መሆኑን ማወቅ ይገባል።

አንዳንድ የእግዚአብሔርን ቸርነትና የትዕግሥቱን ብዛት ለኃጢአት መሥሪያ ሽፋን የሚያደርጉ ሰዎች አሉ። ኃጢአትን ለመሥራት ወይም የሚኖሩትን የኃጢአት ሕይወት ላለመተው የእግዚአብሔርን ቸርነት ምክንያት ያደርጋሉ። ይሁን እንጂ ይህ ሃሳባቸው ስህተት ነው። ይህን ሃሳባቸውን ለውጠው ወደንስሐ መመለስ አለባቸው፤ ቀደምት ቅዱሳን አበው ሁሉ በዚህ ውስጥ አልፈዋልና። ከዚህ በኋላ ዳግመኛ ወደ ኃጢአት አልተመለሱም። ስለዚህም በጸጋ ላይ ጸጋ ተጨመረላቸው፤ ፍቅረ እግዚ አብሔርም በዛላቸው። የእግዚአብሔር ምሕረትና ትዕግሥት በግዴለሽነት ኃጢአትን የሚሠሩበት ሳይሆን ከኃጢአት ርቀው ወደጸጋ እግዚአብሔር ለሚቀርቡ ንስሐ ለሚገቡ ነው። ከእግዚአብሔር ቸርነትና ምሕረት አንፃር ፍርዱንና ቅጣቱንም አስቦና ተረድቶ ወደንስሐ መመለስ ይገባል።

### የእግዚአብሔር ቸርነትና ጭከና

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ

«እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት:- ጭከናው በወደቁት ላይ ነው:- በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር ቸርነቱ በአንተ ላይ ነው:- ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ።» ሮሜ.፲፩፥፳፪። በማለት ተናግሯል።

የእግዚአብሔርን ቸርነት በመተማመን ጭከናውን መርሣት– ምሕረቱንም ተስፋ በማድረግ ፍርዱን ደግሞ መዘንጋት አይገባም።

### የእግዚአብሔር ምሕረቱ ትክክለኛ ነው

የእግዚአብሔር ጠባይዓት አንዱ ከሌላው የማይነጣጠሉ ናቸው። ስለዚህም እግዚአብሔር በምሕረቱ እውነተኛ ፈራጅ ነው:- ፍርዱም በምሕረት ነው። የእግዚአብሔር ፍርድ ቸርነትን የተሞላ ነው:- ቸርነቱ (ምሕረቱም) በቅን ፍርድ ላይ የተመሠረተ ነው። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን ምሕረትና ፍርዱን መነጣጠል አይቻልም።

ይህ የእግዚአብሔር ምሕረትና በቅን ፈራጅነት መዋሐድ የማዳን ሥራ ሁሉ መሠረት ነው። የእግዚአብሔር ምሕረት ከቅን ፍርዱ ተለይቶ በራሱ የቆመ ቢሆን ኃጢአታችሁ ተሰረየላችሁ በማለት ብቻ ምሕረቱን ማደል በቂ ነበር እናም ሁሉም ነገር ክርስቶስ መስቀል ሳያስፈልገው ያበቃ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ኃጢአትን ይቅር አለ በፈራጅነቱም የኃጢአታችንን ዋጋ ከፈለ።

እግዚአብሔር ቅን ፈራጅ በመሆኑ ሥጋን ተዋሕዶ ሰው በመሆን ሞተልን:- የኃጢአታችንንም ዋጋ እርሱ መሥዋዕት ሆኖ ከፈለልን።

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ባለው ግንኙነት የእግዚአብሔርን አመለካከት በመስታወት ፊቱን በሚያይ ሰው ሁኔታ መረዳት ይቻላል። መስታወት በፊቱ የቆመውን ሰው ገጽ እንደሚያሳይ እግዚአብሔር በፊቱ በቆምን ጊዜ ውስጣዊ ማንነታችንን (ገጻችንን) ያሳየናል። ንስሐ ገብተን ከፊቱ ብንቆም የእግዚአብሔርን ቸርነቱን እናያለን። በግድየለሽነት የምንኖር ንስሐ የማንገባ ሆነን በፊቱ ብንቆም ደግሞ በጭካኔውና በፈራጅነቱ እግዚአብሔርን እናየዋለን። ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር ለሚወዱት ቸር ለኃጢአተኞች ደግሞ ንስሐ ለማይገቡት ጨካኝ ፈራጅ ነው። ይህን የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ለሁለቱ ማርያሞች በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር በተገለጠው መልአክ መረዳት እንችላለን። መልአኩ ለመቃብሩ ጠባቂዎች አስደንጋጭና አስፈሪ ነበር – «ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደሞቱም ሆኑ።» ማቴ.፳፰፥፬። ይኸው መልአክ ሁለቱን ሴቶች የሚያስደስት ዜና ነገራቸው – የደስታቸው ምንጭም ሆነ:- «እናንተስ አትፍሩ:- የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ ዐውቃለሁና:- እንደተናገረ ተነሥቷልና በዚህ የለም።» አላቸው። ማቴ.፳፰፥፭–፮።

የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና በአጠቃላይ በቅዱሳን መላእክት አገልግሎትና ተልእኮ ውስጥ እናየዋለን። ሁላችንም ብንሆን ስለምሕረት መላእክት እናውቃለን:- እነርሱ የሚቀጡና ቀሳፊም ደግሞ ናቸው። መልአኩ ኤልያስን ከተኛበት ቀስቅሶ ምግብ እንደመገበውና ከምግቡም የተነሣ ኤልያስ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ሳይበላ ኃይል እንደአገኘ እናውቃለን:- ፩ነገ.፲፱፥፰። የአጋር ልጅ በውኃ ጥም የተነሣ ለሞት በደረሰ

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ዓይኗን እንደከፈተላትና ልጇም ከሞት እንደተረፈ ተጽፏል ዘፍ.፳፩፥፲፯–፲፱። የእግዚአብሔር መልአክ በጉድጓድ የነበሩት አናብስት ዳንኤልን እንዳይበሉ መንጋጋቸውን እንደዘጋ እናውቃለን:- ዳን.፮፥፳፪። እንዲሁም መልአኩ ወደ እሥር ቤት ገብቶ ጴጥሮስን ፈትቶ አስወጥቶታል የሐዋ.፲፪፥፯–፲።

መላእክት ለምሕረት የሚላኩ ቢሆኑም መቅሰፍትና መዓት የሆነ ቅጣትን ከማምጣት የሚያግዳቸው አይደለም።

ቀጥለን ቀሳፊ መላእክትን እንመለከታለን። አንዱ ምሳሌ ግብጻውያንን በሞተ በኲር የቀጣው መልአክ ነው:-

> «በዙፋን ከተቀመጠው ከፈርዖን በኵር ጀምሮ በግዞት እስካሉት እስከ ምርኮኞቹ በኩር ድረስ– በግብፅ ምድር የተገኘውን በኩር ሁሉ መታ። የሞተ የሌለበት ቤት አልነበረምና በግብፅ ምድር ታላቅ ልቅሶ ሆነ።» ዘጸ.፲፪፥፳፱–፴።

እንዲሁ ሁሉ ዳዊት ሕዝቡን በቆጠረ ጊዜና ኃጢአት በሠራ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ በኢየሩሳሌም ላይ ሠይፉን አንሥቷል:- ሰባ ሺህ ሰውም በአንድ ቀን ሞቷል። ፩ዜና.፳፩፥፲፬። ሌሎቹ ደግሞ በራእይ የተጠቀሱት አስፈሪ የመለኮት ድምፅ ይዘው የሚገለጡ ሰባቱ መላእክት ናቸው። ራእ.፰፥፱። ከሁሉም ይልቅ መላእክት ለመጀመሪያ የተገለጡት በቀሳፊነት – በአስፈሪነት አዳምንና ሔዋንን ከገነት ሲያስወጡ መሆኑን ሁላችን እናውቃለን። ዘፍ.፫፥፳፬። ወደሎጥ የተላኩት ሁለቱ መላእክትም ሎጥን ከመዓት ሲያድኑ የሕዝቡን ዓይኖች ግን አሳውረው ነበር። ዘፍ.፲፱፥፲–፲፩።

ይህ እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ምሕረቱን ከጭካኔው ጋር የመላእክቱንም እንዲሁ የሚያስረዳ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ጭካኔ ከእኛ ኃጢአት የተነሣ መሆኑን መረዳት ይገባል።

## አስፈሪው የእግዚአብሔር ቅጣት

እግዚአብሔርን ወሰን የሌለው ቸርነቱ በኃጢአቱ የበደለውን ሰው ከመቅጣት አይከለክለውም። ሰው በኃጢአት የተነሣ የእግዚአብሔርን ቅድስና ይፃረራል:- ንጽሕናውን ይቃወማል:- ትእዛዙን ይጥሳል:- ስለዚህም ይቀጣል። የተወሰኑ ምሳሌዎችን መጥቀስ እንችላለን:-

- የሰውን ልጅ ከምድረ ገጽ ያጠፋው የጥፋት ውኃ– ዘፍ.፮፥፯።
- የሰዶምና ገሞራ መቃጠል:- ዘፍ.፲፱፥፳፬–፳፭።



ሁለቱንም ቅጣቶች ስናስብ ራሳችንን እንጠይቃለን:- በውኑ የእኛ ኃጢአትና በደል ከእነዚያ ሰዎች ያነሰ ነውን:- የሌሎቹስ ኃጢአት ከሎጥ ሚስት ኃጢአት ያነሰ ነውን? እርሷ የጨው ሐውልት ሆናለችና።

በእውነቱ በብሉይ ኪዳን እነዚህን ቅጣቶች ያመጣ እግዚአብሔር በሐዲስ ኪዳን ተለውጦ ይሆን? እርሱ «ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለም ያው የሆን» ዕብ.፲፫፥፰። መለወጥም በእርሱ ዘንድ የሌለ:- በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ የሌለ» ያዕ.፩፥፲፯። እርሱው አይደለምን?

በእርግጥ በቅዱስ ጴጥሮስ ፊት የዋሹትን ሐናንያና ሰጲራ በሞት እንዲወድቁ ያደረገም እርሱ ነው። በካህናት:- በጳጳሳትና በፓትርያርኮችም ፊት የሚዋሹ ስንት ይሆኑ?

ለታላቁ ባሪያው ለቅዱስ ጳውሎስ «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን ፈርጄበታለሁ።...መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው።» ብሎ በቆሮንቶስ ኃጢአተኛ እንዲበይን ሥልጣን የሰጠው እርሱ ነው። ፩ቆሮ.፭፥፭።

በኃጢአተኞች ላይ ከሚፈረዱት የእግዚአብሔር ቅጣቶች የተወሰኑት ትእዛዙን በሚተላለፉ ላይ የተወሰኑትና በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጡት መርገሞች ናቸው። ዘዳ.፳፰፥፲፭–፷፰።

እነዚህ ውሳኔዎች እጅግ የሚያስፈሩና በእውነት የሚያስደነግጡም ናቸው። የሚያመለክቱትም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ቢሆንም ኃጢአትን ፈጽሞ ካለመውደዱ የተነሣ የማይታገሣት መሆኑን ነው። ስለዚህ ከአስፈሪው ቅጣት ለመዳን ኃጢአትን ትተን ንስሐ ልንገባ ያስፈልገናል።

በእርግጥ መርገም ወደዓለም የመጣው በኃጢአት ምክንያት ነው። በአዳም በደልና ኃጢአት ምድርም ተረገመች። ዘፍ.፫፥፲፯። ይህ እርግማን በኋላ በሰውም ላይ ሆነ:- እግዚአብሔር ቃየልን «አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ።» ብሎታል። ዘፍ.፬፥፲፩። ቀደም ብሎም አዳምንና ሔዋንን ያሳተ እባብም «አንተ የተረገምህ ነህ» ተብሏል። ዘፍ.፫፥፲፬። በዚህ አንጻር ኃጢአተኛ ዲያብሎስን ይመስለዋልና «ኃጢአተኛ የዲያብሎስ ልጁ ነው» ሊባል ይችላል። ፩ዮሐ.፫፥፲። ወይም ደግሞ «የእፉኝት እባብ ልጆች» ሊባሉ ይችላሉ። ማቴ.3፥7። የጥፋት ውኃም የመርገም ውጤት ነበር። ዘፍ.፰፥፳፩። የመርገም መተላለፍ መጀመሪያ የሆነው የከነዓን መረገም ነው። ዘፍ.፱፥፳፭።

www.ethiopianorthodox.org

ሕግን በመተላለፍ የተነሣ የሚመጡ መርገሞች የሚያስከትሉአቸው ቅጣቶችም ብዙ ናቸው:- ለምሳሌም ሞት፣ በሽታ፣ ቸነፈር፣ ድህነት፣ መሸነፍ፣ በደል፣ ሰላም ማጣትና ድል መሆን ናቸው። ዘዳ.፳፰።

በአዲስ ኪዳንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍሬ ያላፈራችውን የበለስ ዛፍ ረግሟታል። ማር.፲፮፥፲፮። ከዚህ ሁሉ እንግዲህ የሠራነውን ኃጢአት ተናዝዘን ንስሐ እንድንገባ በቂ ምክር ተሰጥቶናል። ይህ ሁሉ ደግሞ «እኛን የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሰዎች ሊገስጸን ተጻፈ።» ፩ቆሮ.፲፥፲፩።

እንግዲህ ከአስፈሪው የመጨረሻ የፍርድ ቀን በፊት ኃጢአታችንን በንስሐ እንባ ልናጥብ ያስፈልጋል።

## አስደንጋጩ የዘለዓለም ቅጣት

የመጨረሻው የፍርድ ቀን አስደንጋጭና አስፈሪ ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ «እነሆ ምድሪቱን ባድማ ሊያደርግ:- ኃጢአተኞቿንም ከእርሷ ዘንድ ሊያጠፉ ጨካኝ ሆኖ በመዓትና በጽኑ ቁጣ ተሞልቶ የእግዚአብሔር ቀን ይመጣል።» ሲል ገልጦታል። ኢሳ.፲፫፥፱። «በዚያ ቀን እግዚአብሔር ብቻ ከፍ ከፍ ይላል። ጣዖቶቻቸውም ሁሉ ፈጽመው ይጠፋሉ። እግዚአብሔርም ምድርን ያናውጥ ዘንድ በተነሣ ጊዜ ሰዎች ከማስደንገጡና ከግርማው ክብር የተነሣ ወደ ድንጋይ ዋሻና ወደምድር ንቃቃት ውስጥ ይገባሉ።» ኢሳ.፪፥፲፯–፳፩።

ስለዚህ ቀን ነቢዩ ሚልክያስም

> «እነሆ እንደምድጃ እሳት የሚነድድ ቀን ይመጣል ትዕቢተኞችና ኃጢአትን የሚሠሩ ሁሉ ገለባ ይሆናሉ። የሚመጣውም ቀን ያቃጥላቸዋል:- ሥርንና ቅርንጫፍንም አይተውላቸውም:- ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።» ሚል.፬፥፩

በማለት ተናግሯል።

የእግዚአብሔር ቀን በእርግጥ አስፈሪና አስደንጋጭ መሆኑን ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ እንደሚከተለው አስቀምጦታል።

> «ደመና ጭጋግም በዙሪያው ናቸው። ጽድቅና ፍርድ የዙፋኑ መሠረት ናቸው። እሳት በፊቱ ይሄዳል:- ጠላቶቹንም በዙሪያው ያቃጥላል:- መብረቆቹ ለዓለም አበሩ:- ምድር አየችና ተናወጠች:- ተራሮችም ከእግዚአብሔር ፊት ከምድር ሁሉ ጌታ ፊት እንደሰም ቀለጡ።» መዝ.፺፯፥፩–፫።



ይህ አስደንጋጭና አስጨናቂ ቀን በሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ተገልጦአል:-

> «ስድስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ አየሁ:- ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ:- ፀሐይም እንደማቅ ጠጉር ጥቁር ሆነች:- ጨረቃም በሞላው እንደደም ሆነ:- በለስም በብርቱ ንፋስ ተናውጣ ቃርያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደምድር ወደቁ:- ሰማይም እንደመጽሐፍ ተጠቅሎ አለፈ:- ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከሥፍራቸው ተወሰዱ። የምድርም ነገሥታትና መኳንንት ሻለቃዎችም ባለጠጋዎችም:- ኃይለኛዎችም ባሪያዎችም ጌቶችም ሁሉ በዋሾችና በተራራዎች ዓለቶች ተሰወሩ:- ተራራዎችንና ዓለቶችንም በላያችን ውደቁ በዙፋንም ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቁጣ ሰውሩን ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና፣ ማንስ ሊቆም ይችላል?» ራእ.፮፥፲፪–፲፯።

ይህን ሁሉ ጭንቀትና ድንጋጤ የሚጋፈጡት ኃጥአን ናቸው።

የእግዚአብሔር ቅዱሳንና ጻድቃንማ በደመና ተነጥቀው ወደጌታቸው ይወጣሉ:- ለዘለዓለምም ከእግዚአብሔር አምላካቸው ጋር ይሆናሉ— በእርሱ ክብር ይኖራሉ። ለጻድቃንስ «በማይነገርና:- ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ ይላችኋል።» ተብሎላቸዋል። ፩ጴጥ.፩፥፰። ቅዱሳንም የእግዚአብሔርን በገና አንሥተው:-

> «ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ:- ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው። የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው። ጌታ ሆይ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና:- የጽድቅም ሥራህ ስለተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ እያሉ ይዘምራሉ» ራእ.፲፭፥፫–፬።

እነዚህ ጻድቃን በመንግሥተ ሰማይ በእግዚአብሔር መንግሥት በሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም ከቅዱሳን ሁሉ ጋር የዘለዓለማዊው ደስታ ተካፋይ ይሆናሉ:- ኃጢአተኞቹ ግን በማያቋርጥ መከራ በዘለዓለም ስቃይ ይኖራሉ።

## የኃጥአን መከራና ስቃያቸው

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእነርሱ — «እነዚያም ወደዘላለም ቅጣት— ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።» ብሏል። ማቴ.፳፭፥፵፮።

www.ethiopianorthodox.org

ዳግመኛም «የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል:- ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ አመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ። ወደ እቶነ እሳትም ይጥሉአቸዋል። በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደፀሐይ ያበራሉ።» ብሏል። ማቴ.፲፫፥፵፩–፵፫።

ይህ ዘለዓለማዊ መከራ – ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ጨለማውና የማይጠፋው እሳት እጅግ ከባድ ነው:- ከባድነቱን መረዳት የሚቻለው ግን የጻድቃንን ዕጣ ፈንታ በማየትና በመረዳት ሲያነፃፅሩት ነው። ይህን ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ገልጾታል:-

> «በዚያ ቀን በቅዱሳኑ ሊከብር:- በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ:- ከጌታ ፊት ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ።» ፪ተሰ.፩፥፱–፲።

በሌላም ሥፍራ ደግሞ:-

> «ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል አስቀድሞ በአይሁዳዊ ደግሞም በግሪክ ሰው:- ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል።» ብሏል። ሮሜ.፪፥፰–፲።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ–

> «የእውነትን ዕውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደ ርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና – የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችን ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ።»

ሲል የተናገረው ቃል አስደንጋጭና አስጨናቂ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ዕብ.፲፥፳፮–፳፯። ይህንም ለማረጋገጥ:-

> «የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሠክሩበት ያለርኅራኄ ይሞታል። የእግዚአብሔርን ልጅ የናቀ–ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደርኩስ ነገር የቆጠረ:- የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል? በቀል የእኔ ነው:- እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ያለውን እናውቃለንና ደግሞም – ጌታ በሕዝቡ ይፈርዳል። በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው።» ብሏል። ዕብ.፲፥፳፰–፴፩።



ፍቁረ እግዚእ የተባለው ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም በራእዩ –

> «የሚፈሩና የማያምኑ:- የርኩሳንም የነፍስ ገዳዮችም የሴሰኛ ዎችም:- የአስማተኛዎችም:- ጣዖትንም የሚያመልኩ:- የሐሰተኛዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው:- ይኸውም ሁለተኛ ሞት ነው።»

በማለት ተናግሮአል። ራእ.፳፩፥፰። የኃጢአተኞችንም ቅጣት ሲገልጽ

> «እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ከተዘጋጀው ከእግ ዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል:- በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሰቃያል:- የስቃያቸው ጢስ ለዘላለም እስከዘላለም ድረስ ይወጣል:- ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ:- የስሙንም\ ምልክት የሚቀበል ሁሉ ቀንና ሌሊት እረፍት የላቸውም።» ራእ.፲፬፥፲–፲፩

ብሉአል። እናም «ለዘለዓለም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ።» ራእ.፳፥፲። ይህንን ጭንቅና መከራ ለመግለጽ በኃጢአት የረከሰችውን የባቢሎንን ቅጣት ምሳሌ አድርጎ የሚከተለውን ጽፏል።

> «ራስዋን እንደአከበረችና እንደተቀማጠለች ልክ ስቃይና ኀዘን ስጧት።...ከእርሷም ጋር የተቀማጠሉ የምድር ነገሥታት የመቃጠልዋን ጢስ ሲያዩ ስለእርሷ ዋይ ዋይ እያሉ ያለቅሳሉ። ሥቃይዋንም ከመፍራት የተነሣ በሩቅ ቆመው አንቺ ታላቂቱ ከተማ ብርቱይቱ ከተማ ባቢሎን ወዮልሽ ወዮልሽ በአንድ ሰዓት ፍርድሽ ደርሶአልና እያሉ ይናገራሉ።» ራእ.፲፰፥፯–፲።

ይህ ፍርድና ቅጣቱ ምንኛ የሚያስፈራ ነው። ሰው የሠራውና የተናገረው ሁሉ አንድም ሳይቀር በሰዎችና በመላእክት ፊት ሲገለጥ እጅግ አሳፋሪ ነው። በዚያች ሰዓት ማን ሊሰወር ማንስ ሊደበቅና ሊያመልጥ ይችላል?

እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን አይምረውም። በንስሐ ቢመለስ ግን ምሕረትን ያደርግለታል። በዚያ የፍርድ ቀን በሁሉ ግንባር የሁሉ ሥራ ሲገለጥ እጅግ የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ነው። ዛሬ በዚህ ምድር ኃጥኡም ጻድቁም ተደበላልቆ ሁሉም አብሮ ይኖራል:- ያን ጊዜ ግን እንዲህ

www.ethiopianorthodox.org

አይደለም—— እግዚአብሔር ምርቱን ከግርዱ ፍሬውን ከገለባው፣ በጉን ከፍየሉ:- የቀኙን ከግራው:- በዘለዓለም ሕይወት የሚኖሩ ቅዱሳንንና ጻድቃንንም ከኃጢአተኞች ይለያል። በኃጢአተኞችና በቅዱሳን መካከል ኅብረትና አንድነት ፈጽሞ አይኖርም። ኃጥአንንም ከፊቱ ያባርራቸዋል። በወንጌል እንዳለው እንደአልዓዛር ሁሉ የጻድቁ ነፍስ ከቀደሙት ቅዱሳን አበው—ከነቢያት፣ ከሐዋርያት፣ ከሰማዕታት፣ ከሊቃውንትና ቅዱሳን መላእክት እቅፍ ታርፋለች:- በሰማይም ታላቅ ደስታ ይደረጋል:- ጻድቁም የቅዱሳን ጻድቃንና የመላእክት አንድነት አባል ይሆናል። ኃጥኡ ግን ዕድል ፈንታው ከጻድቃኑ ተለይቶ በውጭ በጨለማ መኖር ስለሆነ ከጻድቃንና ከቅዱሳን መላእክት ጋር ወዳጅነትና ኅብረት የለውም። በመጽሐፍ በግልጽ እንደተጻፈ እንዲህ ሲል:-

«ነዌም እየጮኸ — አብርሃም አባት ሆይ—ማረኝ በዚህ ነበልባል እሰቃያለሁና—የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን—ልጄ ሆይ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደተቀበልህ አስብ—አልዓዛርም እንዲሁ ክፉን ተቀበለ። አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል—አንተም ትሰቃያለህ:- ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ—ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደእኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጓል አለ።» ሉቃ.፲፮፥፳፬-፳፮። ኃጢአትም ቅዱሳንንና እግዚአብሔርን ማጣት ስለሆነ ኃጥአን ከቅዱሳን ጋር አንድነት የላቸውም።

## ሁለቱ የኃጢአት ቅጣቶች ምድራዊና ዘለዓለማዊ

ሰው በንስሐ አማካኝነት ከዘለዓለማዊው ቅጣት ሊድን ይችላል። ነገር ግን በእግዚአብሔር የተወሰነበትን ምድራዊ ቅጣት መቀበል ይኖርበታል።

ለምሳሌ — የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አዳምና ሔዋን በበደሉት በደል የተነሣ የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው። ከዚህ የዘለዓለም የሞት ፍርድ ሞትን በሞቱ አጥፍቶ ስለእነርሱ ኃጢአት እርሱ መከራን ተቀብሎ መድኃኔዓለም ነፃ አወጣቸው። ይሁን እንጂ በምድር ላይ ሊቀበሉት የተወሰነባቸውን ቅጣት ከመቀበል አላመለጡም:- እግዚአብሔር አምላክ:-



«ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን:- በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርሷ ትበላለህ...ወደመጣህበት መሬት እስክት መለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ:-...»

በማለት ረግሞአቸዋልና። ዘፍ.፫፥፲፯—፲፱። አባታችን አዳም የተቀጣው ይህ ምድራዊ ቅጣት በመስቀል ላይ ካሣ ከተከፈለልን በኋላ እንኳን ዛሬም በሰው ሁሉ ላይ ይሠራል። በሔዋንም አስቀድሞ በሴቶች ያልነበረ ምጥና ጣር ከያኔ ጀምሮ ተፈረደባት:- ዛሬም በእናቶቻችንና በእኅቶቻችን ያለና የምናየው ነው። ከዚህም ሰው በንስሐ አማካኝነት ከሰማያዊው ዘለዓለማዊ ቅጣት ቢድንም በምድር ላይ ሣለ ደግሞ ምድራዊ ቅጣቱን መቀበሉ የማይቀር መሆኑን እንገነዘባለን።

የተለያዩ ዓይነት ምድራውያን ቅጣቶች አሉ:-

ከኃጢአት የተነሣ የሚመጣ፣ እግዚአብሔር የሚያመጣው ቁጣ፣ ማኅበረሰቡ (የፍትሐብሔር ሕግና ቤተክርስቲያን) የሚያመጡት ቅጣቶች ናቸው።

ሀ. ከኃጢአቱ ባሕርይ የሚመነጭ ቅጣት:-

ዘማዊው ሰው በአባለዘር በሽታ ይቀጣል:- መድኃኒት የሚወስደውም ጤናውን ያጣል:- የሚይጨስ ደግሞ ሳንባውን ይጎዳል:- የማያጠና ተማሪም በፈተና በመውደቁ በሕይወቱ ጉዞ አንድ ዓመት ወደኋላ ይዘገያል:- ቁማርተኛውና ጠጪው ሜት ቃሚውም ይደኸያል። እነዚህ ኃጢአቶች የሚያስከትሉት ዘለዓለማዊ ቅጣት በንስሐ አማካኝነት ሊቀር ይችላል:- በምድር ያደረሱት ጥፋት ግን አሻራው ሳይጠፋ ይኖራል።

ለ. ከእግዚአብሔር ቁጣ የተነሣ የሚመጣ ቅጣት:-

የኤልሳዕን ባሪያ (አገልጋይ) ጊያዝን የመታው ለምፅ—፪ነገ.፭፥፳፯። የሙሴንና የአሮንን እኅት ማርያምን የመታው ለምፅ:- ዘኍ.፲፪፥፲። ግብፃውያን የተመቱበት የሻህኝ ቁስል — ዘጸ.፱፥፲። በዳዊት ምርጫ ሰባሺህ ሰው የፈጀው ቸነፈር:- ፪ሳሙ.፳፬፥፲፭። ከእነዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር የሰጠውን በረከት ሊነሣ ይችላል። ዘዳ.፳፰፥፳፭—፳፯። ኃጢአት ወደሞት የሚያደርስ ክፉ መንገድ ነው:- ራሱም ኃጢአት ሞት ነውና። የኤሊ ታሪክ ለዚህ በቂ ማስረጃ ሊሆነን ይችላል። ፩ሳሙ.፬፥፲፰። ስለዚህ ሰው ሁል ጊዜ ስለሠራው ሥራ ሁሉ ራሱንና ሕይወቱን ሊመረምር ያስፈልጋል:- በዚህም የእግዚአብሔርን ቁጣ ሊያመጣ ከሚችል ኃጢአት መራቅ ተገቢው ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ሐ. ከማኅበረሰቡ (በፍትሐብሔር ወይም በቤተክርስቲያን) የሚመጣ ቅጣት

ኃጢአተኛ ሰው በኅብረተሰቡ ዘንድ የተናቀ፣ የተዋረደና የተጠላ:- ክብሩን ያጣ ይሆናል። ከዚህም የተነሣ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያጣል። ከዚህ በተጨማሪ ኃጢአተኛው ሰው በፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት ይቀጣል። ሊታሠር:- ከባድ ሥራ እንዲሠራ:- ከመኖሪያ አካባቢው እንዲወጣ:- ሊፈረድበት ይችላል። በገንዘብ ሊቀጣ ወይም ከሥራው ሊባረር ይችላል።

በሌላም በኩል ኃጢአተኛው ሰው በቤተክርስቲያን ሕግ መሠረት ሊቀጣም ይችላል። ለተወሰነ ጊዜ ከቅዱስ ቁርባን መከልከል:- ወደቅጥረ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገባ መከልከል:- ክህነትን መያዝ–ወዘተ። የቤተ ክርስቲያን ሕግና ቅጣቷ ጠበቅ ያለ እንደሆነ ምእመናን እግዚአብሔርንና ሕገ ቤተ ክርስቲያንንም በመፍራትና በማክበር ለቅድስና ሊበቁ ይችላሉ።

## ቅዱሳን የእግዚአብሔር ወዳጆችና የተቀጡት ቅጣት

ሀ. ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት

ዳዊት የሰው ሚስት አይቶ ጎመዠ – ዝሙት ሠራ:- የሠራውን ዝሙት ለመደበቅ ነፍስ ገደለ። በዚህ ኃጢአቱ ተፀፅቶ ንስሐ ገባ – ፪ሳሙ.፲፪፥፲፫። ከንስሐው የተነሣ እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር አለው። ይሁን እንጂ ከምድራዊ ቅጣቱ ሊያመልጥ አልቻለም ከዘለዓለም ቅጣት ነው እንጂ። የዳዊት ንስሐው ጥልቅና በልቅሶ የታጀበ ነበር። መዝ.፮፥፯። ነገር ግን በመንግሥቱ ላይ የገዛ ልጁ ተነሥቶበት ሰላም ነሣው። ፪ሳሙ.፲፪፥፲–፲፭።

ከዚህም ሌላ ዳዊት የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለመሥራት በተነሣ ጊዜ በእጅህ ደም አለና አንተ ለመሥራት አትችልም ተብሎ ተከለከለ። ፩ዜና.፳፪፥፫–፰። እንግዲህ እግዚአብሔር ወዳጁ ዳዊትን ስለሠራው ኃጢአቱ ከዘለዓለማዊ ቅጣት ይቅር ብሎ ቢያድነውም በምድር ግን ቅጣቱ ስላልቀረለት ቤተ መቅደሱን የእግዚአብሔርን ቤት እንዳይሠራ ተከለከለ።

ዳግመኛም ዳዊት ሳይታዘዝ ሕዝቡን በቆጠረ ጊዜ እግዚአብሔርን በደለ:- ስለበደሉም ንስሐ ገባ። እግዚአብሔርም ይቅርታን ሰጠው:- ከሰማያዊ ቅጣት ያድነው እንጂ በምድር ላይ ግን ከሦስት ቅጣቶች ከድርቅ፣ ከቸነፈርና ከጦርነት አንዱን እንዲመርጥ ተወሰነበት።



እንግዲህ የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነው ቅዱሱ እንዲህ ከሆነ ኃጢአተኞች የምንሆን የእኛስ ጉዳይ እንዴት ይሆን?

ለ. ነቢዩ ሙሴ

ሙሴ እግዚአብሔር እጅግ የሚወደው ሰው ከመሆኑም በላይ የብዙ ድንቅ ተአምራት ባለቤት ነው። ሙሴ ለእሥራኤል ውኃ ልናፈልቅላችሁ እንችልምን በማለት ደፍሮ በተናገረ ጊዜ ኃጢአትን ሠራ። ዘኁ.፳፥፯–፲፪። ከዚህም የተነሣ ሰማያዊ ቅድስናውን ሳያጣ ዮርዳኖስን መሻገርንና የሚናፍቃትን ምድረ ርስት ኢየሩሳሌምን (ከነዓንን) ማየት ግን ሳይችል ቀረ። ተቀጣ። ዘዳ.፫፥፳፮–፳፱። የሚወደው ሙሴ በበደለ ጊዜ ከሚገባው ቅጣት ያልተወው እግዚአብሔር ዛሬም ያው ስለሆነ ከኃጢአት ተመልሰን ንስሐ ብንገባ ይሻላል።

ሐ. አባታችን ቅዱስ ያዕቆብ

አባታችን ያዕቆብ የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበር። ሮሜ.፱፥፲፫። ከማኅፀንም ጀምሮ የተመረጠ ነበር። ዘፍ.፳፭፥፳፫። ያዕቆብ አንድ ቀን አባቱን በማታለል የወንድሙን የኤሳውን በረከት ለራሱ በማድረግ እግዚአብሔርን በደለ። እግዚአብሔርም ስለዚህ በደሉ አልተወውም ማለት ይቅርታ ሳያደርግለት አልቀረም:- አልጨከነበትም። ዘፍ.፴፪፥፴። ዘፍ.፳፰፥፲፬–፲፭። ይሁን እንጂ ሳይቀጣው ግን አልቀረም። እርሱ አባቱን እንደአታለለ ልጆቹ ደግሞ እርሱን አታለሉት። ዘፍ.፴፯፥፴፩–፴፬። አጎቱ ላባም ቢሆን የፈለጋትን ራሔልን ሳይሆን ሊያን እንዲያገባ ብዙም ዓመት ሥራ እንዲሠራለትና እንዲገዛለት አታለለው። እነዚህን የሕይወት ዘመናቱን ያዕቆብ «የሕይወቴ ዘመኖች ጥቂትም ክፉም ሆኑብኝ።» ብሏቸዋል። ዘፍ.፵፯፥፱።

እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር ይላል ይቅርታን ለማግኘት ግን ሰው ንስሐ መግባት አለበት። ይህም ከሰማያዊው የዘለዓለም ቅጣት ነፃ ሊያወጣና ከመከራ ሊያድን ይችላል። ነገር ግን ምድራዊ ቅጣቱ ሊቀር አይችልም። መፍራትም ሰማያዊውንም ምድራዊውንም ቅጣት ነው።

መ. ሙሴ ፀሊም

ሙሴ ፀሊም በልጅነቱ ዘመን ጨካኝ ነፍሰገዳይ ነበር። በኋላም ንስሐ ገብቶ ከተመለሰ ወዲያ ወደ ገዳም በመግባት መነኮሰ። በመቀጠልም ከከፋት እየራቀ:- በጸጋ እግዚአብሔር እያደገ ደግና ፍቅረ ቢጽ የበዛለት አባት ለመሆን በቃ። አልፎ አልፎም የገዳሙን መነኮሳት የውኃ መቅጃ ደብቆ

www.ethiopianorthodox.org

በመውሰድ ውኃ እየሞላ ያስቀምጥላቸው ነበር። ከዚህ በኋላም እግዚአብሔር ራእይ የማየትንና የገቢረ ተአምራትን ሀብት ሰጠው። በቅድስናውም ወደብቃት እየደረሰ ለብዙዎችም የሚመክር መንፈሳዊ አባት ሆነ። ቆይቶም የቅስና ማዕረግ ተሰጠው። ከዚህ ወዲያማ ከጥቂቱ የበረሃ ምሰሶዎች መካከል አንዱ ሆነ። ከዚህ ሁሉ የንስሐ ሕይወት:- ቅድስናና የጸጋ ስጦታ ባሻገር እግዚአብሔር የቀደመውን ኃጢአቱን የረሳለትና ምድራዊ ቅጣቱን የተወለት ይመስለን ይሆናል። አይደለም።

ሙሴ ፀሊም የነበረበት ገዳም በወንበዴዎች ተወረረ። መነኮሳት ሁሉ ሸሹ:- እርሱንም እንዲሸሽ ለመኑት:- አባታችን ሙሴ ፀሊም ግን በልጅነቴ ብዙዎችን ገድያለሁና ይገድሉኝ ዘንድ ይገባል:- መጽሐፍ «ሠይፍን የመዘዘ በሠይፍ ይጠፋል ብሏልና» አላቸው። ማቴ.፳፮፥፶፪። እንደተናገረውም በሥጋ ሞተ።

## ፭. ሌሎች ለንስሐ የሚያበረታቱ ነገሮች

እስከ አሁን ድረስ ሰውን ከልቡ መንጭተው ለንስሐ የሚያበቁትን ነጥቦች በየደረጃው ተመልክተናል። ከእነዚህ ሌላ ደግሞ ሰውን ወደንስሐ የሚያደርሱት ውጫዊ ነገሮች አሉ። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

### በጸጋ መጐብኘት

እግዚአብሔር «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነትን ወደማወቅ ሊደርሱ» ይወዳል። 1ጢሞ.2፥4። ጸጋውም ኃጢአተኞችን ሁሉ ወደንስሐ ትጠራለች። «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።» ተብሎ እንደተጻፈ። ፊል.፪፥፲፫። ለምሳሌ ጳውሎስ የተባለው ሳውል አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ ክርስቲያኖችንም የሚያንገላታ ነበረ። ፩ጢሞ.፩፥፲፫። በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር በደማስቆ መንገድ ተገልጦለት «ሳውል ሳውል–ስለምን ታሳድደኛለህ? ...የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብኻል» በማለት ገሠፀው። የሐዋ.፱፥፭። ሳውል ቤተክርስቲያንን ማሳደዱንና ክርስቲያኖችን መክሰሱን የተወው ከልቡናው ሽቶት አይደለም። የእግዚአብሔር ጸጋ በጊዜው ጠርቶት ነው እንጂ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቸርነቱ ታረቀው ለታላቅ አገልግሎትና ለሐዋርያነት ጸጋም ጠራው።

ሌላው ምሳሌ ነቢዩ ዮናስ ነው:- ወደነነዌ ሄዶ የታዘዘውን ላለመፈጸም ከእግዚአብሔር ፊት ሸሸ – እግዚአብሔር ይቅር ያለ እንደሆነ የእኔ ቃል ሐሰት ይሆናል ብሎ፤ በእርግጥም እግዚአብሔር የነነዌን ሰዎች ንስሐ



ተቀብሎ ይቅር ባላቸው ጊዜ ዮናስ ከከተማው ውጭ ተቀምጦ «አቤቱ– አንተ ቸርና ይቅር ባይ:- ታጋሽም:- ምሕረትህም የበዛ:- ከክፉው ነገርም የተነሣ የምትፀፀት አምላክ እንደሆንህ አውቄ ነበርና...አሁንም አቤቱ ከሕይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ» አለ። ዮና.፬፥፩–፫። በዚህ ሁኔታ እያለም የእግዚአብሔር ጸጋ ጐበኘው ከኀዘኑ ይጽናና ዘንድ። እግዚአብሔርም ዮናስ ወደልቡ ተመልሶ ንስሐ እስኪገባ ድረስ በቃሉ ያነጋግረው ነበር። ነቢዩንም የእግዚአብሔር ጸጋ በድምፁ ውስጥ ጐበኘው። ከፈጣሪውም እንዲታረቅ መንገድ ሆነው።

ሰውን ወደንስሐ ለመጥራት እግዚአብሔር ሰውንም ሊልክ ይችላል። ነቢዩ ዳዊት በበደለ ጊዜ እግዚአብሔር ናታንን ወደ ዳዊት ልኮታል – ወደ ንስሐ እንዲመለስ ይመክረው ዘንድ። ፪ሳሙ.፲፪፥፲፫። መዝ.፶። ይህ የዳዊት፤ የጳውሎስና የዮናስ ንስሐ ውስጣዊ አይደለም:- ለንስሐ ያበቃቸው ከእነርሱ ውጭ የሆነ በጸጋው የጐበኛቸው የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ሰዎች ሁሉ ሳናስበው ከእግዚአብሔር የተላኩልንን ሰዎችና የተናገሩንን ቃላት ሳንቀበል በመቅረታችን የእግዚአብሔር ጥሪ ሊያልፈን ይችላልና ጸጋው ሲጐበኘን በእንቢታ ወይም በግድየለሽነት እንዳንኀዳ መጠንቀቅ ይገባል የእግዚአብሔር ጸጋ የሚገለጥበት እግዚአብሔርም ሰውን የሚጐበኝበት መንገድ አይታወቅምና። የእግዚአብሔር ጸጋ በደስታ ብቻ ሳይሆን በመከራና በደዌም ሊጐበኝ ይችላል። ጠላትንም በሰው ላይ በማስነሣትም ወደንስሐ ይጠራል። በዚህም የተነሣ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ሲጠራቸው በጥንቃቄና በማስተዋል የጥሪውን ድምፅ የሚጠብቁና የሚያደምጡ መሆን አለባቸው። ይህችን የእግዚአብሔርን የጸጋ ጉብኝት በንቃት ልንጠብቃትና በማስተዋል ልንከተላት ይገባል።

አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጸጋ ከራሳቸው ያሳድዳሉ። በቅዱስ ጳውሎስ አድሮ የእግዚአብሔር ጸጋ ሲጐበኘው – ፊሊክስ «አሁንስ ሂድ:- በተመቸኝም ጊዜ ልኬ አስጠራሻለሁ» ብሎ የእግዚአብሔርን ጸጋ ከራሱ አሳድዷል። የሐዋ.፳፬፥፳፭። እኛ ግን እግዚአብሔር ሲናገረን በጸጋም ሲጐበኘን ልቡናችንን ከፍተን ወደንስሐ ልንመጣ ያስፈልጋል። አግሪጳ እንደተለወጠው ሁሉ የሐዋ.፳፮፥፳፰። የእግዚአብሔርን የጸጋ ጉብኝት ማስተዋልና ጥሪውን መስማት በልቡና ውስጥ የመዳን ተስፋ እንዲፈነጥቅ ያደርጋል። ስለዚህ ጆሮዎቻችንና ልቡናችን የእግዚአብሔርን የጸጋ ጥሪ ለማድመጥ የተከፈቱ መሆን አለባቸው። እኛም እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ሰዎችን በጸጋ እንደሚጐበኝ ማወቅ ይኖርብናል።

www.ethiopianorthodox.org

### ክፍል ሦስት

# እንዴት ንስሐ ይገባል?

ወደ ንስሐ በሚወስደው የሕይወት ጐዳና ላይ ማንኛውም ሰው ሊከተላቸው የሚገባ መርሖዎች አሉ:- እነዚህም ከዚህ ቀጥሎ በቅደም ተከተል የምንመለከታቸው ናቸው።

## ፩. ከራስ ጋር መሆን

ንስሐ መግባት የራስን ፈቃድ ይጠይቃል:- ሰው ንስሐ ለመግባት ፈቃዱ የራሱ ነው። የእግዚአብሔርም ፈቃድ ሰው ንስሐ እንዲገባ ነው:- ስለዚህም ነው «እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነትን ወደማወቅ ሊደርሱ ይወዳል» በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው። ፩ጢሞ.፪፥፬።

ከዚህ ተያይዞም በምን ላይና እንዴት ንስሐ ይገባል? የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። ለዚህ መልስ ለመስጠት ደግሞ ከሚከተሉት መካከል በአንደኛው ወይም በሌላኛው የምትመደብ ስለሆንክ ከራስህ ጋር መሆን ይገባኻል።

ሀ. ምናልባት ያለህበትን የኃጢአት ባሕርና የጥፋት አዘቅት አልተገነዘብክ ይሆናልና ከራስህ ጋር መሆን ያስፈልግኻል።

ለ. እስከ አሁን የሠራኸውን ኃጢአት ዐውቀህ ከዚህ ለመገላገል ዕድልና ጊዜ ስትጠብቅ ሌላ ኃጢአት ወይም የባሰ በደል ትጨምር ይሆናልና በኃጢአት ተከበህ ከመውደቅህ በፊት ወደራስህ ተመልሰህ ከአንተው ጋር መሆን ያስፈልግኻል።

ከራሳችን ጋር የሆንን እንደሆነ ድካማችንንና ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር መናገር አይከብደንም። መዝ.፶፥፩–፲፯። ለእግዚአብሔር የነገርነውን ኃጢአታችንን ለመምህረ ንስሐችን መናገርም አያስፈራንም። ይህም ጸሎተ ንስሐ ከተደረገልን በኋላ ሥጋውን ደሙን ለመቀበል የተዘጋጀን ያደርገናል። ከራሳችን ጋር የሆንን እንደሆነ በልቡናችን ከኃጢአት ለመለየት ኃጢአትንም ለመተው እንወስናለን። ለፈጣሪአችን



ለእግዚአብሔር ታማኝ ውሣኔአችንን የገለጥንለት እንደሆን ደግሞ እርሱ ሊባርከን በመንፈሳዊ ውሳኔአችንም ጠንካሮች ሊያደርገን ፈቃዱ ነው።

ማንም ቢሆን በመንፈሳዊ ሕይወቱ በበረታ ቁጥር ሰይጣንም ሊጥለው ከመቼውም የበለጠ ኃይሉን አጠናክሮ ሊፈትነው እንደሚተጋ የተረጋገጠና የማይጠረጠር ነው። ምክንያቱም ከእርሱ ባርነትና ቁጥጥር ሥር እንድንወጣ ከቶውኑ ስለማይፈልግ ነው። ቢሆንም ታዲያ ፈተናውን ቢያጸናብንም በሚከተሉት ሁለት ዘዴዎች ልናመልጠው እንችላለን።

ሀ. ሰይጣን ራሳችንን ስንገዛና ከራሳችን ጋር ስንሆን – ኃጢአታችንንም ስናስተውል፥- ስለንስሐም ስናስብ ይፈራል። በዚህ ጊዜ ከእርሱ ማምለጥ ይቻላል።

ለ. ሰይጣን ራሳችንን ስንገዛ ከእግዚአብሔር ጋር እንደምንሆን:- እግዚአብሔርም ኃይል መንፈሳዊ እንደሚሰጠን ያውቃልና ይህም ያስፈራዋል። ሊቋቋመው የማይቻለው የመለኮት ኃይል ከእኛ ጋር ይሆናልና:- በዚህም ከእርሱ እናመልጣለን።

ሰይጣን ብዙዎች ራሳቸውን ሲገዙና ከራሳቸው ጋር ሲሆኑ ወደንስሐ መመለሳቸውን ያውቃል። ለምሳሌም ያህል የጠፋው ልጅ – ከራሱ ጋር በሆነ ጊዜ:- የወደቀበትን የኃጢአት ዐዘቅት ዐወቀ–ወዲያውም ተጸጸተ– ንስሐም ገባ–ወደአባቱም ቤት ተመለሰ–በዚህም ከሰይጣን እጅ አመለጠ። ሉቃ.፲፭፥፲፩–፳፬።

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን አባቶች:- የመምህራንና የሰባክያነ ወንጌል ተግባር በኃጢአት የወደቀው ሁሉ ራሱን እንዲመረምርና በሕግጋተ እግዚአብሔር ራሱን መዝኖ ለንስሐ እንዲበቃ መጥራትና መጋበዝ – እንደጠፋው ልጅም በደሉን ዐውቆ «ወደልቡ እንዲመለስ» ማድረግ መሆኑን ማወቅ ይገባል።

ዲያብሎስም ሰው ከራሱ ጋራ እንዳይሆንና ከግዛቱ እንዳይወጣ በሁለት መንገድ ይፈታተነዋል:-

ሀ. የረሳናቸውንና በመዘንጋት ሳንፈጽማቸው የቀረነውን የተለያዩ ተግባራት በፊታችን በመደቀንና ከማንወጣበት የተዘበራረቀ የሃሳብ ባሕር ውስጥ በመዝፈቅ–ንስሐን እንዳናስብ ያደርጋል። ከዚሁ ጋር ደግሞ የተለያዩ ሥራዎችን በመደቀን ወደራሳችን ተመልሰን ለማሰብ ጊዜ እንዳይኖረን ያደርጋል። መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችን:- ስብሰባዎችንና ውይይቶችን ሳይቀር በመጠቀም ስለሕይወታችን

www.ethiopianorthodox.org

በማሰብ ዕቅድ እንዳናወጣና ከራሳችን ጋር እንዳንሆን ያደርጋል። በዚህ ሁሉ ይሞክረናል። ቢሆንም ይህን ሁሉ ታግሠን ከራሳችን ጋር ከሆንንና ሌሎች ተግባራትንም በተጓዳኝ ለማከናወን ከበቃን በሚቀጥለው ዘዴ ይጠቀማል።

ለ. ከራሳችን ጋር እንኳ ብንሆን በረቀቀ ጥበቡ ወደ አእምሮአችን በመግባት አቋመ ልልና ራስን ከመግዛት የሚገኘውንም ጥቅም እንዳናስተውልና ይህም እንዲቀርብን ለማድረግ ይሞክራል። እስከመጨረሻው ውድቀቱ ድረስ ተስፋ አይቆርጥም። በዚህ ስንቋቋመው ከእኛ ይለያል:-

ነገር ግን በሌላ መንገድ ይመጣብናል። ራሳችንን ስለኃጢአታችን ኮንነን በእንባ ወደንስሐ ከመግባት ይልቅ ኃጢአታችንን በምክንያት የተደገፈ አድርገን እንድንቆጥርና ራሳችንን በከንቱ እንድናጽናና ያደርገናል። ስለዚህ ዓላማችን ራሳችንን ከኃጢአት ለማንጻት ነው እንጂ ራሳችንን በማታለል ለመጽናናትና በኃጢአትም ለመኖር ስላይደለ በተቻለን መጠን ለአእምሮአችን ታዛዥና ለልቡናችን ታማኝ መሆን ያስፈልገናል። የቀራጩንና የፈሪሳዊውን ታሪክ እናስታውስ:- ቀራጩ በትህትና ሆኖ ኃጢአቱን ተናዘዘ – ልመናውና ኑዛዜውም ተቀባይነትን አገኘ:- ፈሪሳዊው ግን በመመጻደቅ ኃጢአቱን በመሸፋፈኑ በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀ ሆነ። ሉቃ.፲፰፥፲፫። ስለዚህ ምክንያት በመደርደርና በመመጻደቅ ሌሎችንም በመናቅና በሌሎች በመፍረድ ስርየት ማግኘት አይቻልምና ራስን ከመደለል መራቅ እንደሚገባ ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ዮሐንስ ተናግረዋል። እንዲህ ብለው። «አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ:- የምታመካኘው የለህም በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኰንናለህና።» ሮሜ.፪፥፩። «ለኃጢአታቸው ምክንያት የላቸውም።» ዮሐ.፲፭፥፳፪። ስርየት የሚገኘው በንስሐ ነው እንጂ ምክንያት በመደርደር አይደለም። ንስሐ መግባትም ስርየተ ኃጢአትን ለማግኘት የበቃን ያደርገናል። ከፈሪሳዊው ይልቅ ቀራጩ በራሱ ላይ እንደፈረደ ሁሉ በግራ ከተሰቀለው ወንበዴ ይልቅ በቀኝ የተሰቀለውም በግራ ከተሰቀለው ወንበዴ ይልቅ በቀኝ የተሰቀለውም እንዲሁ በራሱ ፈረደ– «ስለአደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው» በማለት በራሱ የፈረደው ፍርድና የገባው ንስሐ ለገነት አብቅቶታልና እርሱን ልናስታውስ ይገባል። ሉቃ.፳፫፥፴፩።

እንግዲህ ራሳችንን ስለኃጢአታችን እንውቀስ–እንዲህ ብናደርግ ለንስሐ የሚያበቃ የተሰበረ ልብ ይኖረናልና የእግዚአብሔርም ወዳጆች



እንሆናለንና። በመጽሐፍም «በልቡናቸው ትሑታን ለሆኑ እግዚአብሔር ቅርብ ነው» ተብሏልና። ቅዱስ እንጦንስም ደግሞ «እኛ ራሳችንን ከወቀስንና በራሳችን ከፈረድን እግዚአብሔር ደግሞ በእኛ ደስ ይለዋል» በማለት በእውነት ተናግሯል። ስለዚህ ከራሳችን ጋር ስንሆን:- ኃጢአታችንንም ስናስተውል በራሳችን ላይ ከመፍረድ በቀር ለራሳችን ይቅርታ በማድረግ በሌላው ላይ መፍረድና ማመካኘት አስፈላጊ አይደለም:- ይህ ለአዳምና ለሔዋንም አልጠቀማቸውምና።

ታላቁ ቅዱስ መቃርዮስም:- «ወንድሞቼ ሆይ:- በእናንተ ሳይፈረድባችሁ አስቀድማችሁ እናንተ በራሳችሁ ላይ ፍረዱ» በማለት መክሯል። እግዚአብሔርም በፍርድ ከሚቀጣን እኛው ራሳችንን ብንቀጣ የቀለለና መልካም ነው። ስለኃጢአታችን በራሳችን በምንፈርድበት ጊዜ ሁሉ ደግሞ ቅዱስ እንጦንስ «እኛ ኃጢአታችንን ያስታወስን እንደሆነ እግዚአብሔር ይተዋቸዋል:- እኛ ግን ኃጢአታችንን የዘነጋን እንደሆነ እግዚአብሔር ያስታውሰናል» ሲል የተናገረውን ማስታወስና ማስተዋል መልካም ነው። ቅዱስ ዳዊት ስለኃጢአቱ በነቢዩ በናታን በተነገረው ጊዜና በራሱ ላይ በፈረደ ጊዜ ወዲያው ኃጢአትህ ተሰረየችልህ የሚል የምሥራችን ሰማ። «ዳዊትም ናታንን:- እግዚአብሔርን በድያለሁ አለው። ናታንም ዳዊትን:- እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልኻል:- አትሞትም።» አለው። ፪ሳሙ.፲፪፥፩–፲፫። እኛ ግን ናታን መጥቶ እስኪነግረን ድረስ መጠበቅ የለብንም። ቀድመን ስለበደላችን በራሳችን ልንፈርድ ይገባናል:- ራሳችንንም መውቀስ ያስፈልገናል። በዚህም ንስሐ ገብተን ከእግዚአብሔር በምናገኘው ይቅርታ ከራሳችን ጋር ለመሆን ዘወትር ልንተጋ ይገባናል።

## ፪. ምክንያትንና ለራስ ይቅርታ ማድረግን ማስወገድ

በንስሐ ሕይወት ለመኖር የምንሻ ከሆነ ለወደቅንበት ኃጢአት ምክንያት መደርደርና ለራሳችን ይቅርታን ለመስጠት መሞከር የለብንም። ኃጢአትን ከፈጸሙና ከሠሩ በኋላ ለኃጢአት ያበቃ ሌላ ምክንያት ማቅረብና በዚያም አንፃር ለመጽናናት መሞከር በራሱ ኃጢአት ነው። በዚህ ዓይነት ለኃጢአቱ ምክንያት እየደረደረ የሚጽናና ሰው ኃጢአትን እየለመደ ወደባሰ አዘቅት ከመውረድ በቀር ንስሐ ለመግባት አይችልም። ምንም ምክንያት ቢደረደር ኃጢአት ምን ጊዜም ኃጢአት ነውና ለሠራነው ኃጢአት የተለያዩ ምክንያቶችን በማበጀት ራሳችንን እያጽናናን ነፃ ለመሆን መጣር የለብንም።

www.ethiopianorthodox.org

ስለሠሩት ኃጢአት ምክንያትን የደረደሩ አዳምና ሔዋንም ባቀረቡት ምክንያት ከመቀጣት አልዳኑም። እግዚአብሔርም አዳም ስለአቀረበው ምክንያት «የሚስትህን ቃል ሰምተኻልና ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝኩህ ዛፍም በልተኻልና» በማለት ለኃጢአቱ የሚገባውን ቅጣት ሰጠው እንጂ አልተወውም። ዘፍ.፫፥፲፯። ይባስ ብሎ በእነርሱ ምክንያት በመጣው መርገም ቅጣቱ በትውልዳችን ሁሉ ሆነ። እንደ እነርሱ ሁሉ እኛም ዘወትር ምክንያት በመደርደር ከኃጢአታችን የተነሣ ከሚመጣው ቅጣት ለማምለጥ የምንሞክር ሆንን፤ ስለዚህም ንስሐ ለመግባት በጣም ስንቸገር እንታያለን።

ታላቁ ጻድቅና ርእሰ አበው የሆነ አባታችን አብርሃም እንኳ ሚስቱ ሣራን እኅቴ ናት ብሎ በተናገረ ጊዜ ንጉሡ አቤሜሌክ ወደቤቱ ወሰዳት – በሌሊትም በሕልም ነገሩን ተረድቶ አብርሃምን «ይህ ያደረግህብን ምንድር ነው? ምንስ ክፉ ሠራሁብህ? በእኔና በመንግሥቴ ላይ ትልቅ ኃጢአት አውርደሃልና የማይገባ ሥራ በእኔ ሠራኽብኝ» አለው። አብርሃምም የሠራውን ሥራ በምክንያት ለማካካስ በመሞከር «በዚህ ሥፍራ እግዚአብሔርን መፍራት በእውነት እንደሌለ–ለሚስቴም ሲሉ እንደሚገድሉኝ ስላሰብሁ ነው።» በማለት መለሰ። ዘፍ.፳፥፱–፲፩። አብርሃም ለጥፋቱ ኃላፊ ያደረገው ሌሎችን እንጂ በራሱ አልፈረደም እንዲያውም ሣራን– «በገባንበት ሀገር ሁሉ ለእኔ የምታደርጊው ወሮታ ይህ ነው:- ወንድሜ ነው ብለሽ ስለእኔ ተናገሪ አላት።» ዘፍ.፳፥፲፫። ምክንያቱም ከላይ እንደተጠቀሰው ለኃጢአቱ መሸፈኛ ምክንያት አግኝቷልና። ስለዚህም «ሚስቴ ናት» ብሎ አልተናገረም። ከስህተቱም አልታረመም። ለኃጢአቱ ዘወትር መሸፋፈኛ ምክንያት ለሚደረድር ሰው ምክንያት እስካገኘ ድረስ ‹በድያለሁ:- ኃጢአት ሠርቻለሁ› ማለት እጅግ ከባድ ነው።

አንዳንድ ሰዎች የሠሩት ኃጢአት ግልጥ ያለ ሆኖ ሣለ ምክንያት ከማቅረብ ግን አይቆጠቡም። ለእንደዚህ ዓይነቶች ሰዎች ምሳሌ የሚሆነው እንዲነግድበትና እንዲያተርፍበት ከጌታው አንድ መክሊት ተቀብሎ በመሬት ውስጥ የቀበረው ሰው ነው። ጌታው በመጣ ጊዜና ስለትርፉ በጠየቀው ጊዜ ላለመነገዱና ላለማትረፉ ምክንያት ከመስጠት አልተቆጠበም፤ በሠራው ሥራም አልተደናገጠም። እናም «ጌታ ሆይ ካልዘራህበት የምታጭድ ካልበተንህበት የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንክን ዐውቃለሁ:- ፈራሁም:- ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርኩት» አለው። ማቴ.፳፭፥፳፬–፳፭። ይሁን እንጂ ጌታው ያቀረበውን ምክንያት አልተቀበለውም ወደ እሳት እንዲጣል አዘዘ እንጂ።



የዮናስ አለመታዘዝና እምቢተኝነት ግልጽ ኃጢአት ነበር። ይሁን እንጂ ምክንያት ቀርቦለት ነበር። ስለሠራው ኃጢአት ንስሐ ከመግባት ይልቅ የሠራው ትክክል ስለመሆኑ «አቤቱ በአገሬ ሳለሁ የተናገርኩት ይህ አልነበረምን:- አንተ ቸርና ይቅር ባይ ታጋሽም ምሕረትህም የበዛ ከክፉ ነገርም የተነሣ የምትፀፀት አምላክ እንደሆንክ ዐውቄ ነበርና:- ስለዚህ ወደተርሴስ ለመኮብለል ፈጥኜ ነበርና። አሁንም አቤቱ ከሕይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ» በማለት ተናገረ እንጂ ኃጢአት ሠርቻለሁና ይቅር በለኝ አላለም። ዮና.፬፥፩–፫።

ሌላው ምሳሌ የንጉሥ ሳኦል ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር ያዘዘውን በመተላለፉና በጌልጌላ ሳለ ሳይገባው መሥዋዕት መሠዋቱ ግልጽ ኃጢአት ነበረ:- እርሱ ግን ለዚህ ኃጢአቱ ምክንያትን አቀረበ እንጂ የበደለውን በደል አላመነም ነበር። ስለዚህም ከመቀጣት አላመለጠም–ነቢዩ ሳሙኤል «አሁንም መንግሥትህ አይጸናም» አለው እንጂ። ፩ሳሙ.፲፫፥፲፩–፲፬።

እነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች ሰው ኃጢአቱን አምኖ በራሱ ላይ ከመፍረድ ይልቅ ለኃጢአቱ ምክንያት እየደረደረ በሰው ፊትና በራሱ ኅሊና ነፃ ለመሆን የሚያደርገውን ሙከራና ጥረት የሚያሳዩ ናቸው። በዚህም ምናልባት ሰዎችንና የራስን አእምሮ ለመሸንገል ይቻል ይሆናል እንጂ ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔርን ማታለልና ምክንያትም በመደርደር በፊቱ ነፃ መሆን አይቻልም። ከዚህም የተነሣ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምሳሌዎች የተዘረዘሩትን ምክንያቶች ሁሉ እግዚአብሔር አልተቀበላቸውም። «በእግዚአብሔርም ፊት አፍ ሁሉ ይዘጋ ዘንድ» እንደተባለው። ሮሜ.፫፥፲፱።

በእግዚአብሔር ዘንድ ለኃጢአት ምክንያት መደርደር መልካም አይደለም። ከዚህም ይልቅ በደልን ማመንና በኃጢአት ላይ መናዘዝ እግዚአብሔርን ያስደስተዋል:- ስርየትም ያስገኛል። እግዚአብሔርን ላለማገልገል የሚሰጥ ምክንያት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ለምሳሌም ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ በተጠራ ጊዜ – «እኔ አፌ ኮልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ:- ትናንት ከትናንት ወዲያ ባሪያህንም ከተናገርኸኝ ጀምሮ አፈ ትብ አይደለሁም» ብሎ ምክንያት ቢያቀርብም አልተቀበለውም። «እንግዲህ አሁን ሂድ እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ:- የምትናገረውንም አስተምርኻለሁ።» አለው። ዘጸ.፬፥፲–፲፪። ኤርምያስም እንደዚሁ ምክንያቱን «እነሆ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም» በማለት አቀረበ። እግዚአብሔርም የእርሱን ምክንያት ከመቀበል ይልቅ «ወደምሰድህ ሁሉ ዘንድ ትሄዳለህና:- የማዝዝህንም ሁሉ ትናገራለህና...ቃሌን በአፍህ ውስጥ

www.ethiopianorthodox.org

አትሬአለሁ።» በማለት ነግሮታል። ኤር.፩፥፮–፲። ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነው ከደቀመዛሙርቱ መካከል አንዱ «ጌታ ሆይ አስቀድሜ እንድሄድ አባቴን እንድቀብር ፍቀድልኝ» ባለው ጊዜ «ተከተለኝ:- ሙታናቸውንም እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው» በማለት መመለሱ ያቀረበውን ምክንያት እንዳልተቀበለው የሚያስረዳ ነው። ማቴ.፰፥፳፩–፳፪።

ቅዱሳን አባቶቻችን እነዚህን ለኃጢአት መሸፈኛ የሚቀርቡትን ደካማ ምክንያቶች ሁሉ አሸንፈው ነው ለድል የበቁት። እንግዲህ ምክንያተኝነትን እንዴት ልናስወግድ እንችላለን? ይህን ድል ልናገኝ የምንችለው የበደልነውን በደል የሠራነውንም ኃጢአት ያለምንም ምክንያት በማመንና በመናዘዝ–ንስሐም በመግባት ነው። ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ሕዝቡን ከቆጠረ በኋላ ለሠራው ኃጢአት ምክንያት አላቀረበም–ነገር ግን በደሉን በማመን–«ባደረግሁት ነገር እጅግ በድያለሁ:- አሁን ግን አቤቱ ታላቅ ስንፍና አድርጌአለሁና የባሪያህን ኃጢአት ታርቅ ዘንድ እለምንሃለሁ» ብሎ ንስሐ ገብቶአል። ፪ሳሙ.፳፬፥፲። ይህም ትሑት የሆነ ሰው ንስሐ የሚገባበት መንገድ ነው።

በእውነት ንስሐ ለሚገባ ሰው ምክንያት መደርደርን ከራሱ ማስወገድ ቀላል ነው። እውነተኛ የሆነ የንስሐ ሕይወት የሌለው ደግሞ በኃጢአቱ የተነሣ ስለበደለው በደል ራሱን ከመውቀስ ይልቅ ምክንያት ይደረድራል። ብዙ ሰዎች ኃጢአታቸውን አምነው በራሳቸው ከመፍረድ ይልቅ የሚከተሉትን ምክንያቶች ያቀርባሉ:- በእነዚህ ምክንያቶችም ራሳቸውን በማጽናናት ከንስሐ ይርቃሉ:-

ሀ. እኔ የሠራሁት ኃጢአት ሰው ሁሉ የሚሠራውን ነው እንጂ የተለየ አይደለም:- እንዴት ከሰው ልለይ? ይላሉ።

በእነዚህ ሰዎች ሃሳብ እነርሱ የሠሩት ብዙ ሰዎች የሚፈጽሙትን ኃጢአት ከሆነ በግል ሊጠየቁበት አይገባምና በተናጠልም ንስሐ ሊገቡበት አያስፈልጋቸውም። ለእነርሱ ኃጢአትን መሥራት የኅብረተሰቡ ኃጢአትን መፈጸም ምክንያት እንደሆናቸው ይቆጥራሉ። ይሁን እንጂ ኃጢአት ኃጢአት ነውና የፈጸመው ሰው ይጠየቅበታል። ስለዚህም ከኃጢአት መለየት ይገባል እንጂ ሕዝቡ ኃጢአት ሠርቷል በማለት በኃጢአት ባሕር ውስጥ መዘፈቅ አይገባም። ለምሳሌ በኖኅ ዘመን ሕዝቡ ሁሉ በኃጢአት በነበሩበት ጊዜ ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ነበር እንጂ የሕዝቡን ሕይወት ምክንያት አድርጎ ኃጢአት አልሠራም። ዘፍ.፮፥፭። ዘፍ.፯፥፳፫። ይህን በተመለከተ ቅዱስ ጳውሎስም «ይህን ዓለም አትምሰሉ» በማለት



መክሯል። ሮሜ.፲፪፥፪። አሥር ያህል እንኳ ጻድቃን ያልተገኙባት የሰዶም ከተማ ከሕዝቡ የከፋ ኃጢአት የተነሣ ስትቃጠል ሎጥ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ነበር። ከሕዝቡ ጋር ለመመሳሰል ብሎ ለኃጢአት አልተገዛም። ዘፍ.፲፱። መላው የግብፅ ሕዝብ ጣዖት ሲያመልኩ ጻድቁ ዮሴፍ የሚያመልከው እግዚአብሔርን ነበር እንጂ በአምልኮ ጣዖት አልተባበረም። ዘፍ.፴፱። በባቢሎን የተማረኩት ሠለስቱ ደቂቅና ዳንኤል እንዲሁ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር እንጂ በጣዖት አምልኮ ከባቢሎናውያን ጋር አልተባበሩም። ዳን.፩፥፰።

ማንኛውም ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ የዓለማውያንን ኑሮ ለመለወጥ ባይቻለው እንኳ ዓለምንና ዓለማውያንን ከመምሰል ከእነርሱም ጋር ከመቀላቀል መጠንቀቅና መራቅ ይገባዋል:- የሕብረተሰቡ (የዓለማውያኑ) ኃጢአት ባሕር ሆኖ እርሱን እንዳያሰጥመው። እግዚአብሔርን የሚወድ ልብ ጠንካራ ነው። ምንም እንኳ ወደንስሐ በሚያደርገው ጉዞ ላይ ብዙ ፈተናዎችና መሰናክሎች ቢያጋጥሙትም ሁሉንም በተቻለው መጠን ተቋቁሞ ከግቡ ለመድረስ ይጥራል።

ለ. ብዙ ሰዎች የተለያዩ መሰናክሎችን እንደ ምክንያት ያቀርባሉ። ነገር ግን ፈያታዊ ዘየማንን (በጌታ ቀኝ የተሰቀለውን ወንበዴ) መሰናክል ንስሐ ከመግባት አላገደውም። ሉቃ.፳፫፥፴፩–፴፪።

በማርቆስ ወንጌል የተጠቀሱትም ሰዎች ሽባውን ሰው ከጌታ ፊት ለማቅረብ የቤቱን ጣራ እስከ ማንሣት ሲደርሱ በፊታቸው የተደረደሩት መሰናክሎች ሁሉ አላገዷቸውም። ማር.፪፥፩–፲፩። ‹ከአንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም› እንደሚባለው ጽኑ ልብ የፈለገውን ነገር ለማድረግ በመቶዎች የሚቆጠሩ መንገዶችን ማዘጋጀት ይችላል። «የእግዚአብሔርም ጸጋ የምትሻው የሚፈልጋትን ብቻ ነው፤ የሻት ያገኛታልና» በማለት አበው እንደተናገሩት። እንዲህ የሆነ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም ያበረታል:- ጻድቃንና ቅዱሳን መላእክትም በዙሪያ ሆነው ይራዳሉ። ስለዚህም መሰናክልን ምክንያት በማድረግ ከንስሐ መሸሽ የለብንም። ቀራጩ ዘኪዎስም ከጌታ ለመገናኘት መሰናክል አጋጥሞት ነበር። ቁመቱ አጭር ነበርና ጌታን ማየት አልቻለም ነበር:- ቀራጭ በመሆኑ በአይሁድ ዘንድም የተጠላ ነበር:- የዘመኑም ባለሥልጣን ነበር። ነገር ግን ከዚህ ሁሉ መሰናክል አልፎ ጌታውን ለማየት ዛፍ ላይ ወጣ–ያን ጊዜም ጌታ በቤቱ እንደሚውል ነገረው። ሉቃ.፲፱፥፩። እንግዲህ የእኛም ልቡና እንደዚህ ሁሉ በየምክንያቱ ከንስሐ ሕይወት የሚያርቁ መሰናክሎችን ሁሉ አልፎ ለንስሐ የሚበቃ ሊሆን ይገባል።

www.ethiopianorthodox.org

ሐ. አንዳንድ ሰዎች ንስሐ ላለመግባታቸው የውጫዊ ፈተናዎችን መደራረብ ምክንያት አድርገው ያቀርባሉ።

ጠንካራ ልቡና ያለው ሰው በኃጢአት ለመውደቁ የፈተናን ብዛት ምክንያት አያደርግም። የውጭ ተጽእኖን ለኃጢአቱ ምክንያት አድርጎ የሚያቀርብ ሰው ለትእዛዛተ እግዚአብሔር ክብሬታ ለእግዚአብሔርም ፍቅር የሌለው ነው። ወይም ደግሞ ፍቅሩ ደካማ ነው። ይህን የመሰለው ሰው በእግዚአብሔር ይታመናል ለማለት ያስቸግራል–ሃይማኖተ ጎደሎ ነው። ለምሳሌ ጻድቁ ዮሴፍ የጲጥፋራን ሚስት ለማማገጥ ውስጣዊ ፍላጎት አልነበረውም። በሴቲቱ ግፊት ኃጢአትን ሊሠራ ለኃጢአቱም ምክንያት ሊያቀርብ ይችል ነበር:- ባሪያ:- ታዛዥ–ባይተዋር ስለሆንኩ ኃጢአትን ሠራሁ ለማለት በቂ ምክንያት ነበረው:- እርሱ ግን «እንዴት አድርጌ በእግዚአብሔር ፊት ይህን ኃጢአት እሠራለሁ» አለ። ዘፍ.፴፱፥፱።

ሳኦል ያለምንም በደል ዳዊትን ባሳደደው ጊዜ እግዚአብሔር ሳኦልን በዳዊት እጅ አሳልፎ ሰጠው። ዳዊትም ሳኦልን ለመበቀል በቂ ምክንያቶች ነበሩት። ሀ. ኃጢአተኛ ስለሆነ:- ለ. ክፉ ስለሆነ:- ሐ. እግዚአብሔር ንቆ ከሥልጣኑ ስለአወረደው:- መ. ለዳዊት ጠላቱ ስለሆነ:- ፩ሳሙ.፲፮፥፲፬። ፩ሳሙ.፲፮፥፩። ነገር ግን ዳዊት «እግዚአብሔር በቀባው ሰው ላይ እጄን አላነሣም» አለ። ፩ሳሙ.፳፬፥፬–፯። የቅዱስ ዳዊት ልብ ኃጢአት ለመሥራትና ንስሐ ላለመግባት ምክንያት የማይደረድር ንጹሕና የተቀደሰ ልብ ምሳሌ ነው።

መ. ብዙዎች– «እኔ ደካማ ነኝ – የእግዚአብሔር ትእዛዛትም ከባድና አስቸጋሪ ናቸውና ምን ላድርግ? ይላሉ።

የእግዚአብሔርን ዕርዳታ የረሳን እንደሆነ በእርግጥ ደካሞች ነን። እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሰው ብቻውን አይደለምና። ሰው በባሕርዩ ደካማ ቢሆንም በእግዚአብሔር ዕርዳታ የማይችለው ነገር የለም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።» ፊል.፬፥፲፫። በማለት እንደተናገረው። የሚጸልይ ሰው ከእግዚአብሔር ኃይልን ለማግኘት ይጸልያልና ደካማ አይደለም:- ጸሎቱም ኃይል ታደርጋለች። በሕይወቱም ውስጥ እግዚአብሔር በበረከትና በረድኤት ሥራውን ይሠራል። ይህም በኃጢአት ላይ ኃይልን ይሠጠዋል።

ዳዊት እኔ ደካማ ነኝ – እግዚአብሔር ግን ይረዳኛል ባይል ኖሮ ጎልያድን ባልተዋጋም ነበር። የእርሱ የባሕርይ ደካማነት በእግዚአብሔር



ትእዛዝና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከሚሠራው ሥራ ሊያስቀረው አልቻለም:- በመጀመሪያ ለውጊያው ስላልተመለመለ ሊመለስ ይችል ነበር:- ዳግመኛም ጎልያድ ግዙፍ–ተዋጊና ባለብዙ መሣሪያ በመሆኑ ሰው ሁሉ ስለሚፈራው ዳዊትም ሊፈራው ይችል ነበር:- ሦስተኛም ዳዊትን ማንም እንዲዋጋ አልጠየቀውም ነበር:- በመጨረሻም የጦር መሪዎች ሁሉ ሳኦልን ጨምሮ ጎልያድን ፈርተውት ነበር። ስለዚህ ዳዊት እኔ ትንሽና ደካማ ነኝ ለማለት በቂ ምክንያት ነበረው። የእግዚአብሔር መንፈስ ግን ዳዊትን እንዲዋጋና ሕዝቡን እንዲያድን ወደጎልያድ መራው አደፋፈረውም። ሁሉም ሰዎች የሁኔታውን ክብደት ተረድተው ነበር–ዳዊት ግን በእምነት ለድል በቃ።

እግዚአብሔር አምላካችን ልንፈጽመው የማንችለውን እንድንፈጽም አያዝዝምና የእግዚአብሔር ትእዛዛት ከባድና አስቸጋሪ እንደሆኑ ማሰብ የለብንም። ፈጣሪአችን ያዝዘናል የምንፈጽምበትንም ኃይል ይሠጠናል። ከትእዛዙ ጋር ጸጋው ደግሞ አለ:- መንፈስ ቅዱስም በእኛ አድሮ ተግባሩን ለመፈጸም ያበረታናል። ያለበለዚያ ሊውጠን እንደሚያገሣ አንበሳ ሆኖ የሚመጣውን ሰይጣን መቋቋም ባልተቻለም ነበር። ፩ጴጥ.፭፥፰።

አባታችን አብርሃምን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ከብዶት የታዘዘውን ከመፈጸም አልገታውም። በእርጅና ያገኘውን ልጅ ለእግዚአብሔር እንዲሰዋ ሲጠየቅ እምቢ አላለም። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም አልችልም ብሎም አላመካኘም። ዘፍ.፳፪፥፪። ለአብርሃም ትእዛዛቱን እንዲፈጽም ኃይልን የሰጠው እግዚአብሔር ለእኛም ኃይሉን ሊሰጠን ይችላል። እግዚአብሔር ከወደደና ከፈደቀ በእርሱ ኃይል ሊደረግ የማይችል ነገር የለምና የኃጢአትን ኃይል ፈርቶ መንበርከክ አያስፈልግም። ንስሐ ለመግባትና ኃጢአትን ለማሸነፍ:- ከእግዚአብሔርም ጋር በፍቅር ለመኖር ውስጣዊ የሆነውን የልቡናን ደካማነትና ስጋት ጨርሶ ማስወገድ ይገባል። መንግሥተ ሰማይንም ለመውረስ የሚችሉት ለችግርና ለፈተና የማይንበረከክ ልቡና ያላቸው ሃይማኖተ ጽኑ ክርስቲያኖች ናቸው። በፈተና ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ማሰብ ያስፈልጋል – እርሱ– «በርታ ሰውም ሁን:- የምታደርገውንና የምትሄድበትን ሁሉ ታከናውን ዘንድ – በሙሴ ሕግ እንደ ተጻፈ ሥርዓቱንና ትእዛዛቱን ፍርዱንና ምስክሩንም ትጠብቅ ዘንድ በመንገዱም ትሔድ ዘንድ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ።» የሚል ነው። ፩ነገ.፪፥፪–፫።

www.ethiopianorthodox.org

ለሠሩት ኃጢአት ምክንያትና የተለያየ ማካካሻ የሚደረድሩ ሰዎች ስለነፍሳቸው ድኅነትና ስለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ግድየለሽ ወደመሆን ያዘነብላሉ። በአጠቃላይ ለእያንዳንዱ ኃጢአት ምክንያት መደርደርና በተለያዩ ማካካሻዎች ራስን መደለል የንስሐ ሕይወት አለመኖሩን የሚያረጋግጡ ናቸው። ምክንያተኛ ሰው ኃጢአቱን አምኖ ከመናዘዝ ይልቅ ምክንያት መደርደርን ይመርጣል። ለምን አትጸልይም? ለምን አታስቀድስም? ወዘተ ሲባል:- ኃጢአተኛ ሆኜ ነው ከማለት ይልቅ ተቸግሬ ነው:- ሥራ በዝቶብኝ ነው:- ጊዜ አጥቼ ነው:- ይላል። ሥራህን ለእግዚአ ብሔር አሳልፈህ ለምን አልሰጠህም ሲባል ደግሞ እግዚአብሔር የሚያየው የልብን ስለሆነ እኔም በልቤ ንጹሕ ከሆንኩኝ ባልጸልይ፣ ቤተክርስቲያን ተገኝቼ ባላስቀድስ ምንም ችግር የለውም—ምን አለበት ይላል።

ንጹሕ ልብ ለመጸለይ ያበረታል እንጂ አያዳክምም። ንጹሕ ልብ ፍቅረ እግዚአብሔርን የተሞላ ነው። እግዚአብሔርንም የሚወድ እርሱን ይፈልጋል:- ይጸልያልም። የመንፈሳዊ ሰው መለኪያው ንጹሕ ልቡናውና የጸሎት ሕይወቱ ነው። የልብ ንጽሕና ለጸሎት አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ከንጹሕ ልብ የሚወጣው ጸሎት በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰሚነትና ተቀባይነት ያገኛልና ነው። የማይጸልይና በኃጢአቱ ላይ የማያለቅስ ሰው ንጹሕ ልብ ሊኖረው አይችልም።

ምክንያተኛውን ሰው ለምን አትጾምም ብትሉት:- የሚጾም ሁሉ ጻድቅ ነው? ይላል። ስለሰዎች ምን አገባህ እግዚአብሔር የሚጠይቅህ ስለራስህ ነው ቢባል — ከእግዚአብሔር ጋር መኖር በምግብ ላይ ሳይሆን በልብ ንጽሕና ላይ የተመሠረተ ነው ይላል። ጾም ወደልብ ንጽሕና የሚያደርስ መሆኑን አያስተውልም።

በአጠቃላይ እንግዲህ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ኃጢአትን ለመተውና ንስሐ ለመግባት ምክንያትን እንቅፋት ወይም መሰናክል ማድረግ መልካም አይደለም። እግዚአብሔርን ለማግኘት የፈለገ ማንም ሰው ቢሆን ያገኘዋል:- ዋናው ነገር እግዚአብሔርን ለማግኘት መፈለግ ነው። ከፈለግነው እግዚአብሔር ሊያድነን:- ከኃጢአት ሊያነጻን:- በእኛም አድሮ የወደደውን መልካም ነገር ሁሉ ሊያደርግ ፈቃድ ነው። ዮሐ.፩፥፮።



## ፫. ንስሐ ለመግባት አለመዘግየት—አጋጣሚውን መጠቀም:-

አንዳንድ ሰዎች ንስሐ ለመግባት የገጠማቸውን የተመቻቸ አጋጣሚ ሳይጠቀሙበት በመቅረት ዕድሉ አምልጧቸዋል። እግዚአብሔር ሰው ሁሉ ኃጢአቱን መርምሮ ወደንስሐ እንዲመለስ:- የተቀደሰ ጸጋውን ሊያድለውና በልቡናውም አድሮ ለመሥራት አብዝቶ ይሻል። ሰው በተለያዩ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች — ለምሳሌም በመጻሕፍት፣ በዝማሬ፣ በበሽታ፣ በአደጋ፣ በሞት ወዘተ ተመክሮ ንስሐ ሊገባ ይችላል። በእነዚህ አጋጣሚዎች የሚጠቀምባቸው ሰውም አስተዋይ ነው። የጠፋው ልጅ «ተነሥቼ ወደ አባቴ ቤት እሄዳለሁ» ሲል እንደተናገረና ከአባቱ እንደታረቀ ወደቤቱም እንደተመለሰ። ሉቃ.፲፭፥፲፰። የማያስተውል ሰው ደግሞ ኤሳውን ይመስላል። ኤሳው ብኩርናውንና በረከቱን ሁሉ ከአጣ በኋላ ወደአባቱ ገብቶ በረከቱን ታናሽ ወንድሙ እንደወሰደበት ባወቀ ጊዜ «ታላቅ እጅግም መራራ ጩኸት ጮኸ። ቃሉንም አንሥቶ አለቀሰ።» ዘፍ.፳፯፥፴፬—፴፰። ከዚያ በኋላ «በረከቱን ሊወርስ በወደደ ጊዜ እንደተጣለ ታውቃላችሁና በእንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው ለንስሐ ሥፍራ አላገኘምና።» በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ስለእርሱ ተናግሯል። ዕብ.፲፪፥፲፯።

በመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን የተጠቀሰችውም ሴት ጌታዋ ሲጠራት እየሰማች ዝም አለች። ጌታዋ ትቷት ከሄደ በኋላ ተነሥታ ፈለገችው—ነገር ግን አላገኘችውም። ተጣራች እርሱ ግን አልመለሰላትም መኃ.፭፥፮። ዕድሉን አልተጠቀመችበትምና። እግዚአብሔር ግን ሌላ ዕድል ሰጣት።

ያመለጠው ዕድል ተመልሶ ሊገኝ የማይችልበት ጊዜ አለ። ቀደም ብለን በሌላኛው ምዕራፍ የጠቀስነው የፊሊክስና የንጉሥ አግሪጳ ታሪክ የሚያስተምረን ይህንኑ ነው። የሐዋ.፳፬፥፳፬—፳፯። ፊሊክስን የእግዚአብሔር መንፈስ ለንስሐ አነሣሣው እርሱ ግን ያገኘውን ዕድል በቀጠሮ አራዘመ። ከዚያ በኋላ ንስሐ ስለመግባቱ በመጽሐፍ አልተጻፈም። ንጉሥ አግሪጳም ለማመንና ንስሐ ለመግባት በተቃረበ ጊዜ ወደእርሱ የመጣችውን ዕድል ሳይጠቀምባት ቀረ ዳግመኛም አላገኛትም። የሐዋ.፳፮፥፲፱—፳፱።

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ግን ያገኘውን ዕድል ሳያመነታ ወዲያው ተጠቀመበት:- አመነ:- በፊልጶስም እጅ ተጠመቀ— «እነሆ ውኃ — እንዳልጠመቅ ማን ይከለክለኛል?» አለ። የሐዋ.፰፥፴፮።

እንግዲህ ንስሐ ለመግባት ጊዜ ማራዘምና በቀጠሮም መዘግየት አይገባም። ምክንያቱም ንስሐ ለመግባት ቀጠሮ የሚሰጡ ሰዎች ንስሐ

www.ethiopianorthodox.org

ገብተው ስለማያውቁና ነፍሳቸውንም ማዳን ባለመቻላቸው ነው። በቅዱስ መጽሐፍ እንደተጻፈው አይሁድ ጌታቸውን አምላካቸውን ምን ያህል በመቃወም በአምልኮ ጣዖት እንደጸኑ:- እግዚአብሔርም ቀድሞ በነቢያት — በኋላም ራሱ ሰው ሆኖ የቱን ያህል እንዳስተማራቸው እነርሱ ግን ለመዳን እምቢ ብለው የተሰጣቸውን ዕድል ሳይጠቀሙበት እንደቀሩ በሚገባ ማስተዋል ያስፈልጋል። ኢሳ.፩፥፲፰። ኤር.፫፥፲፯። ንስሐ ለመግባት ፈጽመው ፈቃደኛ ባለመፈለጋቸው የእግዚአብሔርን ማዳን አጡ።

ንስሐ መግባት ሲገባ በተደጋጋሚ የተለያዩ ምክንያቶችን በማብዛት መዘግየት ንስሐን እንደመቃወም የሚቆጠር ነው። ይህም በፈርዖን ሕይወት ውስጥ የታየ ነው። ፈርዖን ከነጐድጓድና በረዶ መቅሰፍት በኋላ — «በዚህ ጊዜ በደልሁ:- እግዚአብሔር ጻድቅ ነው:- እኔና ሕዝቤም ኃጢአተኞች ነን። የአምላክ ነጐድጓድ በረዶውም በዝቷልና ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ:- እለቅቃችሁማለሁ።» አለ። ዘጸ.፱፥፳፯–፳፰። ይሁን እንጂ ንስሐ አልገባም የተናገረውንም አልፈጸመም። ገና ደግሞ ዘገየ እንጂ። የአንበጣው መቅሰፍት ከወረደ በኋላ ደግሞ «አምላካችሁን እግዚአብሔርን እናንተን ደግሞ በደልሁ:- አሁን እንግዲህ በዚህ ጊዜ ብቻ ኃጢአቴን ይቅር በሉኝ:- ይህን ሞት ብቻ ከእኔ ያነሣልኝ ዘንድ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ለምኑ።» አለና ለሙሴና አሮን ነገራቸው። ዘጸ.፲፥፲፮–፲፯። እግዚአብሔር ከመዓቱ ቢታገሠውም ፈርዖን ግን ንስሐ አልገባም። ንስሐን በአንደበቱ ይናገር ነበር—በልቡ ውስጥ ግን ንስሐ አልነበረም። ፈርዖን በአሥሩም መቅሰፍቶች መማርና ንስሐ መግባት አልወደደም። በእያንዳንዱ መቅሰፍት ተመክሮ ንስሐ እንዲገባ ዕድል ተሰጠው:- ነገር ግን በመዘግየቱ በዕድሉ ሳይጠቀምበት ቀረ:- በዚህ ዓለም ዕድሉ በባሕረ ኤርትራ መስጠም ሆነ።

ንስሐ እንዲገቡ ዕድል ተሰጥቷቸው ያልተጠቀሙበት ሰዎች ያባለወይኑን ልጅ ደብድበው የገደሉትን የወይን ጠባቂዎች ይመስላሉ። ማቴ.፳፩፥፴፫–፵፫። እነርሱን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እላችኋለሁ:- የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ትወሰዳለች ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች።» ብሏቸዋል።

ታላቁ ሶምሶንም ሌላ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። ደሊላን በወደደ ጊዜ ኃጢአትን ጀመረ:- ከእርሱም ጋር የነበረው የእግዚአብሔር መንፈስ ተለየው:- ምክሯን ተቀብሎ መሪነቱን ለእርሷ ሰጠ:- አታልላዋለችና አሳልፋ ለጠላቶቹ ሰጠችው። እርሱ ግን በዚህ ተመክሮ ንስሐ ለመግባት አልወደደም። ጊዜውን ባራዘመ ቁጥር ጠላቶቹ ማረኩት:- ዓይኖቹን



አውጥተው እህል የሚፈጭ አገልጋይ አደረጉት። ይህ ሁሉ ንስሐ ለመግባት የመዘግየቱ ውጤትና የኃጢአቱ ዋጋ ነው። መሳ.፲፮፥፩–፳፱።

የእግዚአብሔር መላእክት ጻድቁ ሎጥ ከሰዶም እንዲወጣና ለመውጣትም እንዳይዘገይ ያጣድፉት ነበር። እጁንም ይዘው አወጡት:- ከዚያ በኋላ ራስህን አድን ብለው መከረውት ነበርና ለመዳን ደግሞ ፈጥኖ መውጣት ነበረበት። ስለዚህም ሰዶምን አመድ ካደረጋት የእግዚአብሔር ቁጣ፥ ከዚያ የእሳት ነበልባል ዳነ። ዘፍ.፲፱፥፲፭–፲፯። በፍጥነት ልናመልጣቸው ከሚያስፈልጉት ክፉ ነገሮች መካከል ዋነኛው ኃጢአት ነው። ከኃጢአት ለማምለጥ ደግሞ ብቸኛው መንገድ ሳይዘገዩ ንስሐ መግባት ነው።

ሰነፎቹ ቆነጃጅትም ሳይዘጋጁ ቆይተው የጎደላቸውን ለማሟላት ከሄዱ በኋላ ዘግይተው ሙሽራው ከገባ—የሠርጉ ቤትም ከተዘጋ በኋላ መጡ። ይሁን እንጂ በሩም አልተከፈተላቸውም ወደሠርጉ ቤትም መግባት አልቻሉም። ከሙሽራው ጋር ለመግባት የተዘጋጀላቸውን ዕድል ሊጠቀሙበት አልቻሉምና። ማቴ.፳፭፥፲፪።

ኤልዛቤልም ንስሐ እንድትገባ ጊዜና ዕድል ተሰጣት:- እርሷ ግን ንስሐ ለመግባት አልወደደችም። ንስሐ የምትገባበትን ጊዜ ባራዘመች መጠን ስለእምቢታዋ መቅሰፍት ታዘዘባት። ራእ.፪፥፳–፳፫።

ስለዚህ ሰዎች ሁሉ በሠራነው ኃጢአት ላይ ከመናዘዝና ንስሐ ከመግባት መዘግየትና የእግዚአብሔርን ቸርነትና ትዕግሥት መፈታተን የለብንም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ — «ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?» በማለት መክሮናልና በእግዚአብሔር ትዕግሥት ተጠቅመን ለንስሐ ለመብቃት መበርታት ያስፈልገናል።

## ንስሐ ለመግባት ያልዘገዩ ሰዎች ምሳሌ

ቅዱስ ዳዊት ልበ ንጹሕና ንስሐ ለመግባትም ፈጣን ሰው ነበር። የቀርሜሎሱ ናባል በበደለውና ባሳዘነው ጊዜ ለበቀል ተዘጋጅቶ ሣለ የናባል ሚስት አቢግያ ወደእርሱ ዘንድ መጥታ ስለአሰበው ነገር በገሠፀችው ጊዜ—ስለዝናውና ክብሩ ከእርሷ ጋር አልተከራከረም:- ነገር ግን — «ዛሬ እኔን ለመገናኘት አንቺን የሰደደ የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን። ወደ ደም እንዳልሄድ በእጄም በቀል እንዳላደርግ ዛሬ የከለከለኝ አእምሮሽ የተመሰገነ ይሁን። አንቺም የተመሰገንሽ ሁኚ።» አላት። ፩ሳሙ.፳፭፥፴፫። ንስሐው እጅግ በፍጥነት ነበር። በኦርዮ ሚስት ስለሠራው

www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአት ናታን በገሠፀው ጊዜ አላንጎራጎረም ነበር – ወዲያው – «እኔ በእግዚአብሔር ፊት በድያለሁ» በማለት ንስሐ ገባ እንጂ። ፪ሳሙ.፲፪፥፮–፲፫። መዝሙሮቹ ሁሉ በዕንባና በለቅሶ የተሞሉ ነበሩ። መዝ.፮። መዝ.፶።

ነቢዩ ዮናስ በሰበከው ስብከት «የነነዌ ከተማ ከአርባ ቀናት በኋላ ትቃጠላለች» በማለት ሲነገራቸው የነነዌ ሰዎች ግን አርባው ቀን እስኪሞላ አልጠበቁም ነበር። ወዲያው ንስሐ ገብተው ከእግዚአብሔር ቁጣ ዳኑ እንጂ። ዮና.፫፥፬–፮።

እንግዲህ እግዚአብሔር ለንስሐ የሰጠውን ዕድል ተጠቅም ወዲያው ንስሐ የሚገባ ሰው ደስ ሊለው ይገባል። ያ ዕድል ዳግመኛ አይገኝ እንደሆነስ ማን ያውቃል?

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ የታሠሩበት እሥር ቤት በተናወጠ ጊዜ የእሥር ቤቱ ጠባቂ ጳውሎስንና ሲላስን ምን ላድርግ አላቸው:- «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ» አሉት። ያን ጊዜውንም አምኖ እርሱ ከቤተሰቦቹ ጋር ተጠመቀ።–ለማመንና ንስሐ ለመግባትም ጊዜ አልወሰደም። የሐዋ.፲፮፥፳፭–፴፫። የእነዚህ ሰዎች ሕይወት እንዲህ ወዲያው ንስሐ ለመግባት የተዘጋጀና ታዛዥ ከሆነ እኛ ደግሞ የእነርሱን አርአያ ከመከተል ይልቅ ለምን በየምክንያቱ ንስሐ ለመግባት እንዘገያለን? በሕይወታችን ውስጥ እኔ ንስሐ እገባለሁ:- ወዲያው:- በዚያው ሰዓት:- ዛሬ–ወዘተ የሚሉትን ቃላት በተግባር መፈጸሙን መለማመድ በጣም ያስፈልጋል – መዘግየትን ያስወግዳሉና።

የቅዱሳን ሕይወት ለንስሐ ቀጠሮ መስጠትና መዘግየት የማይገባ መሆኑን ያስተምረናል። ይህም ከዚህ በላይ የጠቀስናቸውን የእግዚአብሔር ሰዎች የመሰለ ነው።

## ንስሐ ለመግባት ያገኙት ዕድል በመዘግየት ያመለጣቸው ሰዎች

ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን አግኝተው ለንስሐ እርሱ በሰጣቸው ዕድል ሳይጠቀሙ ቀርተው ይጠፋሉ።

ለምሳሌ:-

ቃየል:- ከቅንዓት የተነሣ በወንድሙ ላይ ተነሥቶ በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር:- «ኃጢአት በደጅ ሆና ታደባለች ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው:- አንተ ግን በእርሷ ንገሥባት።» ብሎት ነበር። ዘፍ.፬፥፯። ቃየል ይህን የንስሐ ጥሪ ሳይቀበል በመቅረቱ የቀረበለችን ዕድል አልተጠቀመበትም።



ሀብታሙ ሰው:- በወንጌል መንግሥተ ሰማይ ለመግባት የፈለገው ሀብታም ሰው የሚያድነውን ጌታ አገኘው:- ጌታም «ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ:- መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ መጥተህም ተከተለኝ» ባለው ጊዜ አዘነ እንጂ ፈቃደኛ አልሆነም። ያገኘውንም ዕድል ሳይጠቀምበት ቀረ። ማቴ.፲፱፥፲፮–፳፪።

ፈሪሳዊው:- ጌታን በቤቱ ጋብዞት ነበርና ጌታ በዚያ መኖሩን ሰምታ አንዲት ኃጢአተኛ የነበረች ሴት በእርሱ ፊት ስለኃጢአቷ ዕንባዋን ባፈሰሰች ጊዜ ፈሪሳዊው ግን ራሱን እንኳ አይመረምርም ነበር። ጌታም «እኔ ወደቤትህ ገባሁ ውኃ እንኳ ለእግሬ አላቀረብክልኝም እርሷ ግን በእንባዋ እራሴን አራሰች በጠጕሯዋም አበሰች።» አለው። ስምዖን በአገኘው ዕድል አልተጠቀመምና። ሉቃ.፯፥፴፮–፶።

በዚህ ዕድል ሳይጠቀሙና ንስሐ ሳይገቡ በመቅረታቸው ብዙ ነፍሳት እነሆ በሲኦል አሉ። እንግዲህ የእኛም ሃሳብ ከሲኦል እሳት ለመዳን ከሆነ ቅዱስ ጳውሎስ– «ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ» ያለውን ማሰብ አለብንና ንስሐ ለመግባት የጊዜ ቀጠሮ ከመስጠትና ከመዘግየት እንራቅ። ኤፌ.፭፥፲፮። ንስሐ የምንገባበትን ጊዜ የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር የሚያራዝምብን ሰይጣን መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። ሰይጣን ንስሐ አያስፈልጋችሁም አይልም:- ነገር ግን ወደፊት ሰፊ ጊዜ ስላላችሁ የሚያጣድፍ ነገር የለም በሚል ሃሳብ ያጓትትብናል፤ እናም ልናውቅበትና ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል።

ንስሐ ለመግባት ከወሰንን መዘግየት የለብንም ምክንያቱም:-

- ለነብሳችን ዋስትና የለንምና – የዛሬው መንፈሳዊነታችን እንዳለ ላይቆይ ይችላልና በመዘግየታችን ሰይጣን እንዳይጥለን፤
- በዙሪያችን ስለአሉትና ስለሚሆኑት ነገሮች እርግጠኞች አይደለንምና ጊዜዋንና ዕድልዋን ካገኘን ዘንዳ ማራዘም አይገባም:-
- ሲነጋም ምን ሊፈጠር እንደሚችል አናውቅምና ዛሬን ልንጠቀምበት ያስፈልጋል:-
- ጠላት ዲያብሎስ ከፊታችን የሚደቅነውን እንቅፋትና መሰናክል አናውቀውምና:-
- ያገኘነው ዕድል አምልጦን ሌላ ዕድል ስንጠብቅ የባሰ ኃጢአት ልንሠራ እንችል ይሆናልና – ኃጢአትን በስህተት ከመሥራት ልምድ ወደማድረግ:- ከዚያም ለኃጢአት ወደ መገዛት–በመጨረሻም ፍጻሜ ወደሆነውና ተስፋ ወደሌለው ዘለዓለማዊ ሞት መድረስ ይመጣልና መዘግየት መልካም አይደለም።

www.ethiopianorthodox.org

ፈጥኖ ንስሐ የማይገባ ሰው ፍቅረ እግዚአብሔር የሌለው፤ ሕገ እግዚአብሔርን የተላለፈ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅና ሕያው ለመሆን የማይሻ፤ በፍቅረ ኃጢአት ልቡናው የተሞላ፤ ንስሐ ለመግባት የማይፈልግና ለንስሐም ያልተዘጋጀ፤ የራሱን ሃሳብ ከፈቃደ እግዚአብሔር የበለጠ አድርጎ የሚያስብ፤ ለራሱ ሕይወት የማይጨነቅና የቅድስናን ሕይወት የማይናፍቅ በመንፈሳዊ ሕይወት የደከመ ነው። ስለዚህ ንስሐ ለመግባት በዘገየን መጠን ወደዚህ የሞት ሕይወት እያዘነበልን መሄዳችንን በማሰብ ከመዘግየት እንራቅ:- ቅዱስ ጳውሎስ– «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት...ልባችሁን እልከኛ አታድርጉት።» እንዳለ። ዕብ.፫፥፲፭።

## ፬. ልብን አለማደንደን

### ለእግዚአብሔር ጥሪ የሚኖረን ምላሽ መጠን:-

እግዚአብሔር ማንኛውንም ሰው ወደንስሐ ይጠራል። ሰዎች ለዚህ ጥሪ የሚሰጡት ምላሽ ግን እንደየልቡናቸው የተለያየ ነው። በዚህ ጥሪ ውስጥ ለሰው ካለው የማይለካ ፍቅር የተነሣ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ሁሉ መዳን ይፈልጋል። ፩ጢሞ.፪፥፬። ስለዚህም ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ ወደጥፋት በሚወስደው ኃጢአት የጸኑትን የሰው ልጆች ወደቅድስና ለመመለስ ነቢያትን፤ ሐዋርያትን፤ ሊቃውንትንና መምህራንን ሁሉ ላከ– በእነርሱም መለኮታዊ የሕይወት ጥሪውን አስተላለፈ። ያለማወቅንም ዘመን በይቅርታ አለፈው። በመጽሐፍም «እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዝዛል።» ሲል እንደተነገረ። የሐዋ.፲፯፥፴። በመምህራኑ አንደበት የእግዚአብሔርን የጥሪ ድምፅ እንድንሰማ እነርሱን ሰጠን። ዋናው ነገር ይህን የጥሪ ጩኸት የሚሰማ የሚያደምጥስ ማነው? ማንስ ይቀበለዋል? ጥሪውን ለመስማትስ ምን ዝግጅት አለ? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ነው።

የሰው ልቡና የእርጥብ ልምጭና የደረቅ እንጨት ያህል የተለያየ ነው። ልምጩን ቢያጥፉት ይታጠፋል:- ቢጠቀልሉት ቢዘረጉትም ይታዘዛል። ደረቁ እንጨት ግን እሺ አይልም:- ደረቅ ከመሆኑ የተነሣ ቢጫኑት እንኳ ይሰበራል። ይህን የመሰለው ደንዳና ልብ እግዚአብሔር ወደቅድስና ቢጠራውም በጄ ብሎ በንስሐ አይመለስም። ሰውነቱ ለበሽታው ከሚሰጠው መድኃኒት ጋር የተለማመደ ሰውም እንዲህ ነው። ከበሽታው ሳይድን እንደተሰቃየ ይሞታል። ሕይወቱ ኃጢአትን የተለማመደች ሰውም ልቡናውን በእግዚአብሔር ቃል ሰብሮ ወደንስሐ አይመለስም። በጀመረው [illegible]ት ተገዝግዞ ይሞታል እንጂ። በመጽሐፈ ምሳሌ– «ሰነፍን ብትወቅጠው ስንፍናው ከእርሱ አይርቅም» እንደተባለው። ምሳ.፳፯፥፳፪። እንዲህ ዓይነቱ ሰው እግዚአብሔር ሊያድነው ቢፈልግም እርሱ ደግሞ ለመዳን አይፈልግም።



ኃያሉ አምላክ እግዚአብሔር ምናምንቴዎችን ፈለገ:- እነርሱ እምቢ አሉ:- እርሱ ደካሞችን ጠራ – ጆሮዎቻቸውን ደፈኑ:- በራቸውን እንኳ አጠንክረው ዘጉት። የተወደደ የሕይወት ቃሉ ግን ሰውን ከተደበቀበት ሥፍራ እንኳን ይጣራል። መኃ.፪፥፳። እንዲህ የሆነበት ምክንያት ስለሰው ልቡና ጭካኔና መደንደን ነው። ልባቸውን ላደነደኑት አይሁድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ዘማውያንና ቀራጮች ከእናንተ ቀድመው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባሉ።» ብሎአቸዋል። ማቴ.፳፩፥፴፩።

ከእዚህ በተቃራኒ ደግሞ ልቡናቸው ገርና ወዲያው ተነሳሒ የሆነ ሰዎችም አሉ። ሰማርያዊቱ ሴት በአንድ ጊዜ ንግግር አምናለች። ዮሐ.፬። በኦርዮ ሚስት ላይ ኃጢአት የሠራው ዳዊት ናታን በደሉን በነገረው ጊዜ ወዲያው ንስሐ ገባ በቀንና በሌሊትም አነባ። መዝ.፶። ከዚህ በመነሣት ነው አበው «ለጻድቅስ አንዲት ቃል ትበቃዋለች» የሚሉት። ሳውል የተለወጠው በአንዲት ጌታችን በተናገራት ሐረግ ነው:- አመነ–ለሞትም እንኳን ታመነ። ፩ጢሞ.፩፥፲፫። የሐዋ.፱፥፲–፲፱። ቅዱስ ጴጥሮስም የዶሮውን ጩኸት ሲሰማ አምርሮ አለቀሰ:- ንስሐም ገባ። መልካምን ልብ ተነሳሒ ማድረግ ከባድ አይደለምና። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዛፍ ላይ ወደነበረው ዘኬዎስ ተመለከተ:- ቀራጩን ዘኬዎስንም አነጋገረው:- እርሱም አልዘገየም– ወዲያው በሕዝቡ ፊት ንስሐ ገባ። ሉቃ.፲፱፥፰። ከዚያ በፊት ጌታችን ጸሐፍትን፤ ፈሪሳውያንን፤ የአይሁድ ካህናትን አነጋግሮአቸዋል። አንዳቸውም ለንስሐ የተዘጋጀ ልቡና አልነበራቸውም። የዘኬዎስ ልብ ግን እንደእነርሱ ደንዳና አልነበረም።

ቀራጩ ሌዊ በኋላ ስሙ ማቴዎስ የተባለው – ሕይወቱን ለመለወጥ ያስፈለገው «ተከተለኝ» የሚለው አንድ የጌታ የጥሪ ድምፅ ብቻ ነበር። እናም ሁሉንም ነገር ትቶ ከተቀመጠበት የመቅረጫ ወንበር ተነሥቶ ጌታውን ተከተለ። ማቴ.፱፥፱።

ጴጥሮስና እንድርያስም ጌታ ከእንግዲህ ወዲያ ነፍሳትን የምታጠምዱ አደርጋችኋለሁና ተከተሉኝ ባላቸው ጊዜ የማጥመጃ መረባቸውን ከባሕር ዳር ትተው ተከተሉት። ማር.፩፥፲፰።

www.ethiopianorthodox.org

ቅንና ንቁ ልቡና የእግዚአብሔርን የጥሪ ድምፅ እስኪሰማ አይዘገይም። ለማንኛውም የተቀደሰ መለኮታዊ ምልክት ወዲያው ምላ ይሰጣል። ዘወትር እግዚአብሔር ለሚደሰትበት ሥራ የተዘጋጀና የተከፈተ ነውና። ቅን ልብ ስህተቱን ለማመንና ኃጢአቱን ለመናዘዝ አይቸገርም። ክፉ ልብ ግን አመፀኛ ነው።

ዳዊት ከቀርሜሎሱ ሰው ከናባል ጋር በመብል የተነሣ ሊዋጋ በተዘጋጀ ጊዜ የናባል ሚስት አቢግያ ስትወቅሰው ወዲያው ተፀፀተ — ከተሳሳተ መንገዱም ተመለሰ:- እንዲህም አላት:-

> «ዛሬ እኔን ለመምከር አንቺን የሰደደ የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን። ወደ ደም እንዳልሄድ በእጄም በቀል እንዳላደርግ ዛሬ የከለከለኝ አእምሮሽ የተመሰገነ ይሁን:- አንቺም የተመሰገንሽ ሁኚ።» ፩ሳሙ.፳፭፥፴፫።

ቅን ልብ ተግሣፅን ይቀበላል:- ክፉ ልብ ግን ምክርና ተግሣፅን አይቀበልም:- ሃሳቡንም ስለመልካም ነገር አይለውጥም። ትዕቢተኛ ነው። «እግዚአብሔር ደግሞ ትዕቢተኞችን ይቃወማል:- ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።» ያዕ.፬፥፮። ልበ ደንዳኖች ራሳቸውን ያጠፋሉ:- ሕዝብን ያጠፋሉ:- እግዚአብሔርን ያጣሉ።

## ጨካኝ ልብ ንስሐን ያዘገያል:-

ጨካኝ ልቡና ወደንስሐ የሚደረገውን ጉዞ ያዘገያል። ለዚህ ዋነኛ ምሳሌ የሚሆነው ፈርዖን ነው። እግዚአብሔር ያመጣቸው መቅሰፍቶች ሁሉ ልቡናውን ሊሰብሩት አልቻሉም። እግዚአብሔርን አምኛለሁ ብሎ የእግዚአብሔርንም ምሕረት ከአገኘ በኋላ ዳግመኛ ልቡን ከቀደመው የበለጠ ያስጨክን ነበር። እስኪጠፋ ድረስ ልቡናው ደንዳና ነበር። በመጽሐፍ— «ፈርዖንም ፀጥታ እንደሆነ ባየ ጊዜ ልቡን አደነደነ:- እግዚአብሔርም እንደተናገረ አልሰማቸውም» ዘጸ.፰፥፲፭። እንደተባለው እግዚአብሔር ፈርዖንን በእነዚህ መቅሰፍቶች ሁሉ ወደ ንስሐ ጠራው:- እርሱ ግን ስለልቡናው ጥንካሬና ስለጭካኔው ጠፋ — አልዳነምም።

በሁለተኛ ደረጃ ምሳሌ የምናደርገው በምድረ በዳ ሳሉ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ድንቅ ተአምራት ዘንግተው ልቡናቸውን ወደ እርሱ ከመመለስ ያደነደኑትን እሥራኤላውያንን ነው። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ልበ ደንዳና ይላቸው ነበር። ዘጸ.፴፪፥፱፤ ፴፫፥፫—፭፤ ፴፬፥፱።



ዘዳ.፱፥፮። በሕዝቅኤልም «እነርሱ ፊታቸው የተጨማተረ:- ልባቸውም የደነደነ ልጆች ናቸው።» ብሏቸዋል። ሕዝ.፪፥፬። በሌላም ሥፍራ «ምግባረ ጠንካራና ልበ ደንዳና ናቸው። ብሏቸዋል። ሕዝ.፫፥፯። ከልባቸው መደንደንና ከጭካኔአቸው የተነሣ ወደፈጣሪአቸው ወደ እግዚአብሔር አልተመለሱም። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በቸርነቱ መልካም ቢያደርግላቸውም እነርሱ ግን ንስሐ ለመግባት አልወደዱም። እግዚአብሔርም «ቀኑን ሙሉ ወደማይታዘዝና ወደሚቃወም ሕዝብ እጄን ዘረጋሁ» ይላል። ሮሜ.፲፥፳፩። እነዚህ እሥራኤል ግን ወደ እነርሱ የተመለሰውን የእግዚአብሔርን ይቅርታ አይተው እጃቸውንም ወደ እግዚአብሔር ዘርግተው ለመቅረብና ምሕረትን ከእርሱ ለመጠየቅ እምቢ ስላሉ ከፈጣሪአቸው ተለዩ:- ምድረ ርስትን አልወረሱም:- እነርሱም ልጆቻቸውም በምድረ በዳ ሞተው ቀሩ። ስለ እነርሱ ሙሴ ባይጸልይ ኖሮ እግዚአብሔር ጨርሶም ሊያጠፋቸው ነበር። ዘኍ.፴፪። የነቢያት ስብከትና ትንቢት፣ የእግዚአብሔርም ድንቅ ተአምራት ሁሉ በጭንጫ ላይ እንደወደቀው ዘር ሆነባቸው:- ልባቸውን ከጭንጫ የበለጠ አጠንክረዋልና።

ክፉ ልብ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ አይጠቀምበትም። ወደ ቤተ እግዚአብሔር ይሄዳል — ግን አይለወጥም። ንስሐ ሊገባ:- ሥጋውና ደሙንም ሊቀበል:- የእግዚአብሔርንም ተአምራት ሊያይ:- ትምህርቱንም ሊሰማ ይችላል— ግን ክርስትናን አይኖረውም ማለት ያየውን:- የሰማውን፣ የተማረውን በሥራ አይተረጉመውም። ክፉ ልብ የማይሰበር ዓለት:- የማይቀልጥ ብረት:- ቃለ እግዚአብሔርም የማይገባው — የማይገነባው ነው። ቅዱስ መጽሐፍ ግን «እርሱን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉት» በማለት ነው የሚመክረው። ዕብ.፫፥፯።

እንግዲህ የሚጠቅመው በተለያየ መልክና ሁኔታ ወደእኛ የሚመጣውን የእግዚአብሔርን ጥሪ በንቁ ዕዝነ ልቡና ማድመጥና:- በተከፈተ ትሑትና የዋሕ ልብ መቀበል ነው። በዚህ ዓይነት ዛሬ ልባችን ቢጨክን እንኳ ዳግመኛ ልባችን አይጨክንም። በመኃልይ የተጠቀሰችው ሴት እንኳ አስቀድማ በሯን ዘግታ ነበረ—በኋላ ግን ልቡናዋ ተለውጧል። መኃ.፭፥፬—፰።

ስለዚህ ልቡናችን ቅንና የዋህ እንዲሆን አስቀድመን ከራሳችን ጋራ ልንዋጋ ይገባል። ልቡናችን ቅንና የዋህ ቢሆን መልካሙ ነገር:- መንፈሳዊው ነገር ሁሉ ያሸንፈናል። እናም ወደንስሐና ወደ ፍቅረ እግዚአብሔር ያደርሰናል። ቅን ልቡና ያለው ሰው በመንፈሳዊ ነገር ሁሉ ይመሰጣል። በቅዳሴ፣ በመዝሙር፣ በመንፈሳዊ በዓላት፣ በቅዱሳት መጻሕፍት —

www.ethiopianorthodox.org

ይመስጣል። ስለተለየው መንፈሳዊ ወዳጁ በተመስጦ ያስባል። ኃጢአትን ቢሠራ እንኳን ቅዱሳን በመንፈስ ያዩኛል ብሎ ስለሚያስብ ከኃጢአት ይመለሳል። በዓይን ኅሊናው ሥነ ስቅለቱን እየተመለከተ ያዝናል– ይተክዛል:- በመስቀሉ ሥር ስታለቅስ የነበረችውን ድንግል ማርያምን ያስታውሳል–እርሱም ደግሞ ስለኃጢአቱ ያለቅሳል። የቅዱሳንን ገድልና ትሩፋት እያሰበ የራሱን ሕይወት ይመረምራል።

የየዋህ ክርስቲያን ዓይኖችና ውኃ የሞላው ሰፍነግ (ስፖንጅ) አንድ ናቸው። ውኃ የመጠጠ ሰፍነግ ቢነኩት የመጠጠውን ውኃ ወዲያው ይለቀዋል:- ቅንና የዋህ ልቡና ያለው ሰውም ስለኃጢአቱ ባሰበ ጊዜ ዕንባውን መቋጠር አይቻለውም። ቢበድል ወዲያው ይመለሳል:- ዳግመኛም አይበድልም። ለዚህ ዳዊትንና ቅዱስ ጴጥሮስን አብነት ልናደርጋቸው እንችላለን። እኛም ታዲያ ቅን፣ የዋህና ደግ ልብ ሊኖረን ያስፈልጋል።

የጨካኝ ልብ መጨረሻው አደገኛና ጎጂ መሆኑን ማወቅ ይገባል:- የጭካኔ ውጤቱ:- መንፈስ ደካማነት:- በኃጢአት መውደቅ:- ፍሬ አልባ ነት:- ደረቅ ሕይወት:- ፍጻሜውም እሳት ነው። ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ልባችን ጨካኝ ቢሆን እንኳ «ይህ ተፈጥሮዬ ነው ምን ማድረግ እችላለሁ?» ማለትን ከእኛ በማራቅ ክፉ ባሕርያችንን በንስሐና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እግዚአብሔር እንዲለውጥልን እርሱን በዕንባ መማፀን በጣም አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር ክፉ ባሕርያችንንና ጨካኝ ልቡናችንን ሊለውጥልን ይችላል። እኛም ደግሞ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠርን መሆናችንን መዘንጋት የለብንም። ዘፍ.፩፥፳፮። በእግዚአብሔር ኃይል ብዙ ጨካኝ ልብ የነበራቸው ሰዎች ወደ ርኅራኄ ተለውጠዋል። እነሙሴ ፀሊምን ከነፍሰ ገዳይነት ወደርኅሩኅ መነኩሴነት የለወጠ እግዚአብሔር የእኛንም ደንዳና ልቡና መለወጥ የሚቻለው መሆኑን ማመን ያስፈልጋል።

ከዚህ በመቀጠል ለልብ ክፋትና ጭካኔ ምክንያቱንና የሚታረምበትን መንገድ እንመረምራለን።

### የልብ ጭካኔ ምክንያቶችና መፍትሔዎቻቸው

ልቡናን በማስጨከን የተለመዱት ዐበይት ምክንያቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

#### ሀ. ኃጢአትን መለማመድ

ኃጢአት ልብን ጨካኝና ደንዳና ያደርገዋል። ደጋግሞ ኃጢአትን መሥራት ደግሞ የበለጠ ያደነድነዋል። ሰው በኃጢአት ውስጥ በቆየ ቁጥር



እግዚአብሔርን ይረሳል:- ትእዛዛቱንም:- ክርስቶስ ለእርሱ ብሎ መሞቱንም:- የተደረገለትን ቸርነትና የተከፈለለትን ካሣም ሁሉ ይዘነጋል። የኅሊናውን ወቀሳና የመንፈስ ቅዱስንም የጥሪ ድምፅ እንዳይሰማ ዕዝነ ልቡናው ደንቆሮ ይሆናል። ንስሐ መግባትና ኃጢአትን መተው ግን የልብን ክፋትና ጭካኔ ያስወግዳል።

#### ለ. ኃጢአት በመሥራት መደሰት

በኃጢአት ለሚደሰት ሰው የእግዚአብሔርን ፍቅሩንና ትእዛዛቱን መዘንጋት ቀላል ነው። ልቡናውም የደነደነ ይሆናል። ኃጢአት ሰው አእምሮውንና ኅሊናውን እንዲያጣ–ከአእምሮውና ከኅሊናው ቁጥጥር ውጭ እንዲሆን ያደርገዋል።

ሔዋን የበለስን ፍሬ ተመልክታ በጎመጀች ጊዜ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ረሳች። ያንን ብቻ አይደለም:- የሞት ፍርድንም የቅድስናን ሕይወትና ፍቅረ እግዚአብሔርንም ረሳች። እንዲሁ ሁሉ ሶምሶን ከደሊላ ጋር በነበረ ጊዜ ማስተዋሉን አጣ ልቡናውም ከእግዚአብሔር ጋር አልነበረም። ለኃጢአት የነበረው ፍቅር ሁሉንም ነገር:- መንፈሳዊ የሆነውን ነገር እንዲረሳ አደረገው። በእርሱ የነበረው መንፈስ ቅዱስም ተወው። ለጠላቶቹም አልፎ ተሰጠ። በዚያ ጊዜ ልቡናው ለመልካም ነገር የማይታዘዝ ደንዳና ጨካኝም ሆነ:- ለኃጢአትም በመገዛቱ ክብሩን አጣ። መሳ.፲፮።

ታሪኩ በወንጌል የተጻፈው ሀብታም ሰውም ኃጢአትን በመውደዱ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም የሚገባው መሆኑን ዘነጋ። በእርሱ የነበረው የገንዘብ ፍቅር ልቡናውን ስለአደነደነው የጌታን ትእዛዝ በሰማ ጊዜ በኀዘን ወጥቶ ሄደ። የፈለገውንም የዘለዓለም ሕይወት ለማግኘት አልቻለም። ማቴ.፲፱፥፳፪።

ደንዳና እንዲሁም ጨካኝ የነበረው የፈርዖን ልቡና በእሥራኤል ስቃይ ለመደሰት የሚሻ ስለነበረ እነርሱን ነፃ ለመስደድ ፈቃደኛ አልነበረም።

ከኃጢአት የተነሣ የደነደነ ልብ ፈጥኖ ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ አይሆንም። በንስሐ የሚገኘውንም የተቀደሰ ጸጋ ያዘገያል። ንስሐ ለመግባት መዘግየትም ልቡና በኃጢአት የተነሣ ደንዳናና ጨካኝ እንዲሆን ዕድል መስጠት ነው። ይህ ደግሞ ልቡናን ለንስሐ ጥሪ ምላሽ እንዳይሰጥ ያደርገዋል።

ሰው ኃጢአትን የተለማመደ እንደሆነ ንስሐ ከመግባት ይልቅ በኃጢአቱ ይቀጥላል:- በኃጢአቱ መቀጠሉ ደግሞ በሚሠራው ኃጢአት

www.ethiopianorthodox.org

እንዲደሰት ያደርገዋል። ከኃጢአት የሚገኘው ደስታ ልቡናን ያደነድነዋል ለመንፈሳዊ ነገርም እንዳይገዛ ያደርገዋል። ለዚህ መፍትሔው ከኃጢአት የተነሣ ደስታ አገኛለሁ ብሎ ማሰብን ፈጽሞ ከኅሊና ማራቅ ብቻ ነው። ይህን የመሰለ ሃሳብ ያለው ሰው ከኃጢአት የተነሣ ዘለዓለማዊ ሕይወቱን እንደሚያጣ ያወቀና የተፀፀተ ወይም ከኃጢአቱ የተነሣ ከእግዚአብሔር ዘንድ በተላከበት ቅጣት በኃጢአት መኖሩን የጠላ ሰው ነው። ይህ ደግሞ ለኃጢአት የነበረውን አመለካከት ፈጽሞ ከመለወጥ የሚገኝ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በልቡና መታደስ መለወጥ» የሚለውም ይህን ነው። ሮሜ.፲፪፥፪። በልቡናው መታደስ የተለወጠ ሰው ከኃጢአት የሚገኘውን ደስታ ይንቀዋል።

ሐ. ውጫዊ ተጽእኖ

በአንድ ሰው አካባቢ የሚኖር ጎጂ ውጫዊ ተጽእኖ ልቡናውን ጨካኝና ክፉ ሊያደርገው ይችላል። ሰው እንዲሁ ሁሉ መልካም ባልንጀራ ካለው መልካም ነገርን ይማራል። ከክፉ ሰው ጋር ባልንጀራ የሆነ እንደሆነ ግን የልቡና ክፋትን ይማራል። አክዓብ ከኤልዛቤል ክፋትን ባይማር ኖሮ ናቡቴን ባልገደለም ነበር። ፩ነገ.፳፩፥፩–፲፯። ሚስቱ ኤልዛቤል የኃጢአትን ውጤት–የሚያስከትለውንም ቅጣት አቅልላ አክዓብን መከረችው:- ልቡንም አስጨክናዋለችና ናቡቴን ገደለው።

የክፉ ባልንጀሮቹ ምክር በአባቱ በሰሎሞን ዙፋን የነገሠውን የወጣቱን ንጉሥ የሮብአምን ልቡና አስጨከነው። የእነርሱንም ምክር በመቀበሉ ከክብሩ ተዋረደ–ልቡናውም ከእግዚአብሔር ተለየ። ፩ነገ.፲፪፥፰–፲፩።

ኃጢአትን እንደቀላል ነገር በመቁጠር ሌሎች ሰዎችም እንዲፈጽሙት የሚመክሩ አንዳንድ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ለምሳሌ – መጠጥን:- ዝሙትን:- ማጨስን፥ መጨፈርን፥ መቃምን ወዘተ ለማያውቅ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያስጠኑ ናቸው። የእነርሱን ምክር የሚሰማ የሚከተለውም ሰው ኃጢአትን ይለማመዳል–ልቡናውም ወደክፋትና ወደመደንደን ይሄዳል። ስለዚህ አበው – «ባልንጀራህን ንገረኝና ማንነትህን እነግርሃለሁ» ማለታቸው ትክክል ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከማይሆን ባልንጀርነት መጠበቅ ያስፈልጋል።

ወደኃጢአት የሚያደርሱ መጻሕፍትንና ፊልሞችን መመልከትም ለልቡና ክፋትና ጭካኔ አስተዋጽኦ አለው:- እነዚህን የሚወድ ሰው እግዚአብሔር በማይደሰትበት ሥፍራ ይገኛል። እነዚህን መጻሕፍትና ፊልሞች በማንበብና በማየት የሚያገኘው ዕውቀት መንፈሳዊ አመለካከቱን



ይቀንሰዋል–በዚያው መጠን ደግሞ ልቡናው እየደነደነ ይሄዳል። ስለሆነም የምናነበውን መጽሐፍና የምናየውን ፊልም:- የምንከተለውንም አመለካከት በጥንቃቄ መምረጥ ያስፈልገናል። በቤታችን ውስጥ እንኳ ሆነን የምናደምጠውን መመርመር ይገባናል። ማንኛውንም ምክርና ትምህርት ከመቀበላችንና በተግባር ከመፈጸማችን አስቀድሞ መፈተንና መልካምነቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው በመጽሐፍ «ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ግን ያዙ» ተብሎአልና። ባልንጀራችንን በመምረጥም ጠንቃቆች እንሁን። ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቅዱሳንን ሕይወት አብነት ማድረግም በእጅጉ ጠቃሚ ነው።

መ. ለእንቅፋቶች (ፈተናዎች) መንበርከክ

ለክርስቲያን በሕይወቱ ፊት የሚደቀኑትን እንቅፋቶች (ፈተናዎች) ማለፍ እንጂ ለእነርሱ መንበርከክ አይገባም። የሰዎችን የመንፈሳዊ ሕይወት ጉዞ ለማደናቀፍ እንቅፋት ከመደቀን የበለጠ ለአጋንንት የሚቀላቸው ነገር የለም። እንዳንጸልይ፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዳናነብ:- ወደመንፈሳውያን የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት እንዳንሄድና እንዳናገለግል የጤንነትን ችግር በፊታችን ይደቅናሉ። ገንዘብን በማስወደድ በልግስና እንዳንሰጥ ያደናቅፉናል:- የሥራን ብዛት ምክንያት በማድረግ በዓላትን እንዳናከብር ያደርጉናል:- በተሰጠን የኅሊና ነፃነት የሠራነውን ስህተት እንድንሸፋፍን ያደርጉናል:- በዚህም ውሸትንና ለሥጋዊ ነገር ፈንታ መስጠትን እንማራለን። ለእነዚህ እንቅፋቶች ከተንበረከክን ግድየለሽነትን ስለምንለምድ ልቡናችን እየጠነከረና ጨካኞች እየሆንን እንሄዳለን። ለመልካም ነገር ጠንካራ የሆነ ልቡና እነዚህን እንቅፋቶች እየተወጣ በዚህም መንፈሳዊ ደስታን እያገኘ ይኖራል። ፈተና በገጠመው ጊዜ ሁሉ ቅዱስ ጴጥሮስ «...በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት» በማለት የተናገረውን ያስታውሳል። ፩ጴጥ.፭፥፱።

ሠ. የእግዚአብሔርን ቸርነት (ደግነት) አለማስተዋል

የእግዚአብሔርን ቸርነትና ደግነቱን አለማስተዋል ወደልቡና ክፋትና ጭካኔ ይመራል። ሰው በሠራው ኃጢአት እግዚአብሔር ያልቀጣው እንደሆነ ያልተቀጣው ከእግዚአብሔር ቸርነት የተነሣ መሆኑን በመዘንጋት ሕጉን መተላለፍና እግዚአብሔርንም መዳፈር ይጀምራል። ልቡናውም በዚሁ መጠን ይደነድናል–ይጨክናል። የሠራውን ኃጢአት ዐውቆ እግዚአብሔርን ስለመበደሉ ራሱን የሚኰንን ቅን ልቡና ያለው ሰው ደግሞ አይታጣም። የእግዚአብሔርን ቸርነት ባለማስተዋል በኃጢአት ላይ ኃጢአትን በመጨመር ልቡናውን ስለሚያደነድን ሰው ቅዱስ ጳውሎስ

www.ethiopianorthodox.org

«ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?» በማለት ተናግሯል። ሮሜ.፪፥፬።

አንዳንድ ጊዜ ስለፈሪሃ እግዚአብሔር ማውሳትና ስለ ሕገ እግዚአብሔርም መናገር ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም ክፉ ልብን ሊለውጥ ይችላልና ነው። የሚያፈቅር ሰው ስለፍቅረ እግዚአብሔር ቢነግሩት ይጠቀማል:- ለጨካኙ ሰው ደግሞ ስለፈሪሃ እግዚአብሔር ቢነገረው ሊጠቀም ይችላል። ቅዱስ ጳውሎስም «ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ» በማለት መክሯል። ሮሜ.፲፩፥፳። እንዲሁም ደግሞ «በፈሪሃ እግዚአብሔር ቅድስናን ፍጹም እናድርጋት።» ብሏል። ፪ቆሮ.፯፥፩።

ረ. ኩራት

ኩራት ልቡናን ጨካኝ ያደርጋል። ኩራተኛ ሰው የሚያስበው ስለራሱና ስለክብሩ ብቻ ነው። በፊቱም እግዚአብሔርንና ሰዎችን አይመለከትም። የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት ሲል ከማድረግ የሚቆጠበው ነገር የለም – ሁሉን ያደርጋል። ስለዚህም ጨካኝ ልብ ይኖረዋል። ትሑት ሰው ግን በእግዚአብሔር ፊት ልቡናው የተሰበረ ነው። ሰው በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ከአዋረደ ወደንስሐ መሔዱ አይቀርም። የልቡና ክፋትም ከእርሱ ዘንድ ይወገዳል:- ጸጋ እግዚአብሔርንም ያገኛል።

ሰ. መንፈሳዊ ጸጋን ማጣት

መንፈሳውያን ምሥጢራትን በግድየለሽነት የሚፈጽም ሰው ክብራቸውን ይቀንሳል። የሚፈጽማቸው ምሥጢራት እንኳን አይለውጡትም። ከእነርሱም ከሚገኘው በረከት አይሳተፍም መንፈሳዊ ጸጋውን አጥቷልና። ከዚህ የተነሣ ልቡናው እየደነደነ ይሄዳል። መጀመሪያ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ትሑትና እግዚአብሔርን የሚፈራ ነበር:- በሚኖርበት ቤቱ እንኳን ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት መሆኑን ያስብ ነበር። ቆይቶ ግን በቤተ ክርስቲያን ሲቆይ ኃጢአትን ባለመተዉና በኃጢአት መኖርን በመቀጠሉ – ኃጢአትን በመሥራቱና በመናገሩ ሁሉ ጭምር ያለበት ሥፍራ የማይለውጠው ይሆናል። በተቀደሰው መንበር ፊት ሲቀርብና ሥጋውና ደሙን ሲቀበል በግድየለሽነት ነው። ጸሎቱና የቅዳሴት መጻሕፍት ንባቡ ሁሉ መንፈሳዊ ተመስጦ ይጎድላቸዋል። ጾሙም የታይታ ነው። ልቡናው ኃጢአትን ከመለማመድ የተነሣ የደነደነ ነው። አልተለወጠም።



መንፈሳዊ አገልግሎትን በመደጋገም በመፈጸም የአገልግሎቱን ክብር ከልቡናችን ማጥፋትና የሚገኘውንም ጸጋ ማጣት የለብንም። ለምሳሌ – ገዳማትን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየ ሰው ለእነዚህ ገዳማት የሚሰጠው ክብርና ያለውም ፍቅር ዘወትር ከሚመላለሰው ሰው እጅግ የበለጠ ነው። ለመጀመሪያ ክህነትን የተቀበለ (ሥልጣነ ክህነት ያገኘ) ሰው ለቤተ መቅደሱና ለሥርዓቱ የሚሰጠው ክብር ዘወትር ከሚቀድሰው ካህን የበለጠ ነው። ይህም ሰዎች አንድን ነገር ደጋግመው መሥራታቸው ወይም ማየታቸው ለዚያ ነገር የሚሰጡትን ክብር በእጅጉ የሚቀንሰው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ይህ ደግሞ ልቡናን ወደማደንደን ያደርሳል:- ከጸጋ የተራቆተም ያደርጋል:- ይህም መልካም አይደለም።

ስለዚህ መንፈሳዊ አገልግሎትን የሚፈጽም ሰው አገልግሎቱን በመንፈሳዊ ማስተዋል:- በትሕትና ሊያደርገው ይገባል። በዚህ መልክ የሚያበረክተው አገልግሎት የከበረ ከመሆኑም በላይ የራሱንም ልቡና ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ጸጋን ያገኝበታል።

## ፫. የመጀመሪያውን እርምጃ ማስወገድ ከጥቃቅን ቀበሮዎችም መጠንቀቅ

ሰው ንስሐ ለመግባት ከወሰነ ወደኃጢአት ከሚመራው የመጀመሪያ እርምጃ መጠንቀቅ ይኖርበታል:- ምክንያቱም ኃጢአት በአንድ ጊዜ ያለውን ኃይል ተጠቅሞ አያጠቃም። ነገር ግን ቀስ በቀስ ነው እንጂ። ስለዚህም የኃጢአትን መነሻና የዕድገት ደረጃውን መመርመር ያስፈልጋል።

ኃጢአት ከመንካት (ከኃጢአት ጋር ከመገናኘት) ይጀምራል። ከዚያ በውስጣዊ ስሜት ይባባሳል:- በመቀጠልም ይቀጣጠላል። ሰውም በግድየለሽነት ወይም በስህተት ከኃጢአት ሊገናኝ ይችላል። ጊዜ ከሰጠው ኃጢአት ተጽእኖ ሊያደርግበት ይችላል። ይህንንም ተጽእኖ ካልተቋቋመው ስሜቱ ለኃጢአት ሊነሣሣ በውስጡም ሊቀጣጠልና በመጨረሻም ሊጥለው ይችላል። ጦርነቱ በኀሊናና በኃጢአት ወይም በመንፈስና በሥጋ መካከል ነው። ይህ ውጊያና ትግል ሰው ለኃጢአት መገዛትን እምቢ ማለቱን ይጠቁማል። ይህ ጦርነት እጅግ በጣም አሰልች ሊሆን ይችላል:- ይሁን እንጂ ከመሸነፍና ከመውደቅ ይልቅ በጦርነቱ ውስጥ ከፈቃደ ሥጋ ጋራ እየታገሉ መቆየቱ ይመረጣል። ሰውም በውጊያው በጸና መጠን ወደኃጢአት የሚወስደውን የመጀመሪያ እርምጃ በመቃወም ከኃጢአት ጋር በገጠመው ትግል አሸናፊ ሊሆን ይችላል።

www.ethiopianorthodox.org

ሰው ከብዙ ድካም በኋላ በኃጢአት ላይ ባለድል ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ በኃጢአት ተማርኮ ሊሸነፍ ይችላል። ስለዚህ በዚህ ጦርነት አሸናፊውን ለመወሰን አስቸጋሪ ነው። ኃጢአት ሁል ጊዜ እንድንፈጽማት ትገፋፋናለች — ባሕርይዋ ነውና። አንድ ጊዜ በኃጢአት ከወደቅን ደግሞ ጠላት ኃጢአትን ልምድ እስክናደርጋት ድረስ አይተወንም ይዋጋናል እንጂ። የባቢሎናውያንን የምርኮ ሕግ ማስታወሱ ለዚህ ማስረጃ ይሆናል:- ቅዱስ ዳዊት :- —

«በባቢሎን ወንዞች አጠገብ በዚያ ተቀመጥን:-ጽዮንንም ባሰብናት ጊዜ አለቀስን፤ የማረኩን በዚያ የዝማሬን ቃል ፈለጉብን:- የጽዮንን ዝማሬ ዘምሩልን አሉን:- የእግዚአብሔርን ዝማሬ እንዴት በባዕድ ምድር እንዘምራለን? መዝ.፻፴፮፥፩—፬።

በማለት እንደተናገረው ከተማረኩ በኋላ እንኳ በማይገባ ሥፍራ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲናገሩ ሰይጣን በሰዎች አድሮ ይዋጋቸው እንደነበረ ማስተዋል ይቻላል።

ሰው ኃጢአትን ከአሰበ እስኪያገኘው ድረስ እንዲናፍቀው ሰይጣን በልቡናው ያድራል:- በእጅጉ የበረታ የኃጢአት ፍላጎት እንዲያድርበትም ያደርጋል። አግኝቶም ኃጢአትን እስኪፈጽም ድረስ አይለቀውም ከኃጢአት ጋር የጀመረውን ግንኙነትም ፈጽሞ እስካላቋረጠ ድረስ። ስለዚህ ወደኃጢአት የሚያደርሰውን የመጀመሪያ እርምጃ ጨርሶ ማስወገድና ጦርነቱን ማቆም ይገባል።

የመጀመሪያውን እርምጃ ማስወገድ ኃጢአትን ለመጠየፍና ለመቃወም በቂ ማረጋገጫ ከመሆኑም በላይ ወደንጽሕናም ያደርሳል። በዚህ ደረጃ ከጠላት ዲያብሎስና ከመሣሪያው ከኃጢአት ጋር ምንም ድርድር ሊደረግ አይገባም።

የዛፍ ችግኝ ተክሎ ማሳደግ ካልፈለጉ ደግሞ ነቅሎ መጣል ይቻላል። ከበቀለና ከአደገ በኋላ ግን ለመንቀልና ለመጣል ቢፈለግ እጅግ አስቸጋሪ ነው። ኃጢአትም እንደዚሁ ነው። ሲጀመርና ገና በልቡና ውስጥ ተፀንሶ በአእምሮ ውስጥ ሲበቅል ተነቅሎ ካልተጣለ ሥር ከሰደደ—ከተለመደ በኋላ ከራስ ለይቶ ለመተው አስቸጋሪ ነው። ስለሆነም ኃጢአትን ከመጀመሪያው ነቅሎ ማጥፋት መልካም ነው። ከተቻለም ከኃጢአት ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ማስወገድ የበለጠ ያማረ ነው። በመጽሐፍም— «በዋዘኞች ወንበር



ያልተቀመጠ:- በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመ:- በክፉዎች ምክር ያልሄደ ምስጉን ነው።» ተብሎ ተጽፏል። መዝ.፩፥፩። ከዚህ ንባብ ሦስት የኃጢአት ደረጃዎችን እንመለከታለን:- እነዚህም መሄድ፣ መቆምና መቀመጥ ናቸው። ከመጀመሪያው ይልቅ የመጨረሻው የከፋ ነውና ኃጢአት በሰው ውስጥ እንዲያድግ ወይም ሰው በኃጢአት እንዲያድግ በውስጥ ከሚቀሰቀስ የኃጢአት ስሜት ራስን መጠበቅ ተገቢ ነው። ሰው ሁሉ ከመጀመሪያው የኃጢአት እርምጃ ራሱን ማራቅ አለበት:- ይህም የሚቻለው ንስሐ በመግባትና ልብንም ንጹሕ በማድረግ ነው።

በማንኛውም ደረጃ ክፉ ነገር በውስጣችን እንዲያድግ ማድረግ የለብንም። በመጀመሪያው ለክፉ ነገር ሃሳባችንን ከሰጠነው ተጽእኖ ሊያደርግብን ስለሚችል በተቃውሞአችን ልንጸና ያስፈልጋል። አለበለዚያ ፍጻሜአችን የማያምርና ወደ መንፈሳዊ ሞት የሚያመራ ይሆናል፥ የኃጢአትም ባሪያ እንድንሆን ያደርገናል። ስለዚህ ራሳችንን በመመርመር ልንጠነቀቅ ይገባል።

ሰው ወደኃጢአት በተራመደ መጠን ሃሳቡ ደካማ ይሆናል። ወደ ኃጢአትም ያዘነብላል። በውስጡም ለኃጢአት ሥፍራ ያዘጋጃል። ተጨማሪ እርምጃ በተራመደ ቁጥር በልቡ ውስጥ የነበረው ፍቅረ እግዚአብሔር ይቀንሳል። መውደቁም ግልጽ እየሆነ ይሄዳል። ስለዚህም በመጽሐፍ — «አንቺ ወራዳ የባቢሎን ልጅ ሆይ ሕፃናቶችሽን ይዞ በዓለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው» ተብሎአል። መዝ.፻፴፮፥፰—፱። የባቢሎን ልጅ (የምርኮ ሀገር) የተባለ ኃጢአት ነው። ልጆች የተባሉት ፈቃዳተ ኃጢአት ናቸው። እነዚህን ልጆች የተባሉ ፈቃዳተ ኃጢአት የሚፈጠፍጣቸው ዓለት የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ፩ቆሮ.፲፥፬። ስለዚህም ኃጢአትንና ፈቃዳቱን ሁሉ በክርስቶስ አጋዥነት የሚቋቋምና በአእምሮው ሲታሰብ ጀምሮ ኃጢአትን የሚጠላ ሰው ብፁዕ ነው።

ኃጢአት በሰዎች ሕይወት ውስጥ እንዴት እያደገ ሰዎችን በመንፈሳዊ ሞት እስከ መግደል እንደደረሰ ለማወቅና ለማስተዋል ከቅዱስ መጽሐፍ የሚከተሉትን ጥቂት ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል:-

ሔዋን:- ሔዋን ከእባብ ጋር መነጋገር በጀመረች ጊዜ አዲስ ሃሳብ ወደልቡናዋ ገባ ከዚያም ወደምኞት አደገ:- ይህ ምኞትም ልቡናዋን አሸነፈው — እርሷም ተንበረከከችለት። በልቧ የነበረው በእግዚአብሔር ማመን ቀስ በቀስ እየጠፋ እባብን ወደማመን ደረሰች:- ፈጽማ እባብ

www.ethiopianorthodox.org

የነገራትን ባመነች ጊዜ ወደቀች—አዳምም እርሷን ተከትሎ ወደቀ። የሞትም ፍርድ ተፈረደባቸው። ዘፍ.፫፥፩—፯።

ሔዋን ከመጀመሪያው እርምጃ ራሷን ማራቅ ነበረባት:- እግዚአብሔር የነገራትን ትታ እባብን ከማድመጥ፣ ከማመንና፣ ከመጐምዠት የተባለች ውንም ከመፈጸም መቆጠብ ነበረባት። የመጀመሪያውን እርምጃ መቃወም ባለመቻሏ ከትንሿ እስከ መውደቅና ሞት የሚያደርሰውን ኃጢአት ሠራች። ይህን ሁሉ ገና ከመጀመሪያው እባብን በመቃወም ከእርሷ ልታርቀው ትችል ነበር።

በኃጢአት እንዳይወድቅ የሚፈልግ ማንም ቢኖር ከእባብና ከእባብ ሃሳብ መራቅ አለበት። «ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፉልና።» ፩ቆር.፲፭፥፴፫።

ሶምሶን:- ሶምሶን የወደቀው ከማየት የተነሣ ነው። ዓይን ኃጢአትን ከማየት ልትቆጠብ ይገባል። ሶምሶን ምንም እንኳ ታላቅና ክቡር የእግዚአብሔርም መንፈስ ያደረበት ሰው ቢሆን የመጀመሪያውን የኃጢአት እርምጃ በመራመዱ የተነሣ ለመውደቅ በቅቷል። የአወዳደቁ መጀመሪያ ወደ ጋዛ ወርዶ ደሊላን ባየ ጊዜ ነው። ከአያት በኋላ በሥጋዊ ፍቅር ወደዳት—አብሯትም መኖር ጀመረ:- አላስተዋለምም ኃጢአትን ያጣጥም ነበርና። ባለማስተዋሉም ምሥጢሩን ሁሉ ለደሊላ ነገራት:- ክብሩን ከእርሷ ስለለወጠ በእርሷም አማካኝነት ምሥጢሩን ስለዐወቁበት ጠላቶቹ ድል ነሡት፤ እርሷም አሳልፋ ሰጥታዋለችና ፀጕሩን በላጩት ጊዜ ክብሩም ኃይሉም ከዳው—ይዘውም አዋረዱት—ዓይኑንም አውጥተው አገልጋይ ባሪያ አደረጉት። መሳ.፲፫፥፳፭፤ ፲፬፥፯፤ ፲፮፥፳፩። ከመጀመሪያው ዓይኑን ኃጢአትን ከማየት ቢከለክል—ልቡናውን ከመመኘት ቢመልስ የመጀመሪያውን እርምጃ ቢያስወግድ ኖሮ ለዚህ ባልበቃም ነበር።

ሎጥ:- ሎጥ ወደሰዶም ከመውረዱ በፊት ከአብርሃም ጋር ይኖር ነበር። በኋላም የሀብትና የብቸኝነት ፍላጎት ባደረበት ጊዜ የምድሪቱን ልምላሜ ብቻ በመመልከት ለም መሬት ፍለጋ ከአብርሃም ተለየ። ፍላጎቱም ከአብርሃም ለየው። ይህም የመጀመሪያው ውድቀቱ ነበር። ሰዶምን ለምልማ ባያት ጊዜም በዚያ ለመኖር ወደደ። በራሱ ፍላጎትም መኖሪያውን መረጠ:- ይህ ደግሞ ሁለተኛው ስህተቱ ነበር። ሎጥ የተመለከተው የምድሪቱን አረንጓዴ ልምላሜ ብቻ ነው እንጂ ሰዶምን የሞሏት በፍትወተ ኃጢአት የተቃጠሉ ሰዎች ነበሩ። የሎጥ ምርጫ መንፈሳዊ አልነበረም—እርሱ መንፈሳዊውን ነገር አልተመለከተም—የእግዚአብሔርንም ፈቃድ



አልጠየቀምና። ከዚህ የተነሣ ሥጋዊ ምድራዊ ነገርን ተመልክቶ ሀብትንም ሽቶ አብርሃምንና ድንኳኑን ትቶ ተለየው። ወደሰፊ ምድር ለመሄድ በዚያም ከኃጢአተኞችና ከክፉዎች መካከል መኖርን መረጠ። ምድራዊ ሀብት ወዳለበት ሄደ። እግዚአብሔር ወደሚመለከበት ግን አይደለም። ሀብት ምድራዊን አስቀድሞ መንፈሳዊ ሕይወቱን ሁለተኛ አደረገ ዘፍ.፲፫፥፲—፲፬። «ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና እየሰማ በአመፀኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበርና።» ፪ጴጥ.፪፥፰።

አብሮአቸው መኖር ከጀመረ በኋላ ከሰዶማውያን ተደባለቀ:- ልጆቹንም ለእነርሱ ዳረ። ከእነርሱ ጋር በመመሳሰሉም መንፈሳዊ አባትነቱን ንቀው ክብር ነሡት:- እግዚአብሔርም እንደአዘነባቸው ሊነግራቸው ቢሞክር ተሣለቁበት:- የዚህ ሁሉ ፍጻሜም የሰዶም በእሳት መጋየት ሆነ። ሎጥም ያለውን ሀብት ሁሉ በዚያ አጣ:- ሀብቱን ብቻ ሳይሆን ሚስቱንም ጭምር በዚያ አጣ። ዘፍ.፲፱፥፲፬። ትንሿ የመጀመሪያ ፍላጎቱ ባትገዛውና ለፍላጎቱ ታዛዥ ሆኖ ከአብርሃም ባይለይ ለእርሱ መልካም ነበር። አብርሃም የእግዚአብሔር ቅዱስ ነውና:- በመጀመሪያ በልቡናው የበቀለውን ሰፊ መሬት የመያዝ ምኞትና ባለብዙ ሀብት የመሆን ፍላጎቱን መዋጋትና መቅጨት ነበረበት። የመጀመሪያውን እርምጃ ቢገታ የመጨረሻው ጥፋትና ኪሣራ አይደርስበትም ነበር።

ዳዊት:- ዳዊት ሠራዊቱ ከፍልስጥኤማውያን ጋር በመዋጋት ላይ በነበረበት ጊዜ እርሱ መዝናናትን ፈልጎ በቤተ መንግሥቱ ዋለ። ስለጦርነቱም ምንም ሃሳብ አልነበረውም። በሰገነቱ ሲናፈስ የተመለከታትን የኦርዮን ሚስት ወድዶ በእርሷ ላይ ፈቃዱን ፈጸመ—ቆይቶም የራሱን ኃጢአት ለመሸፈን ኦርዮን አስጠርቶት ወደቤቱ እንዲሄድ ባዘዘው ጊዜ ኦርዮ ወገኖቼ ሲዋጉ እኔ ወደ ቤቴ ገብቼ እበላና እጠጣ ዘንድ ከሚስቴም ጋር እተኛ ዘንድ አይሆንልኝም ብሏልና በዚያ ቅጽበት ከዳዊት ይልቅ እርሱ ጀግና ነበር። ፪ሳሙ.፲፩፥፲፩።

ዳዊት ንጉሡ ሳአል ባሳደደው ጊዜ፣ በዋሻዎች እየኖረ ይዋጋ በነበረ ጊዜ አልበደለም ነበር። ሲመቸው:- በቤተ መንግሥት መኖር ሲጀምር:- የሚታዘዙለት አሽከሮችና ባሮች ሲኖረው ወታደሮቹን ለውጊያ ልኮ እርሱ ግን በቤቱ ተኛ። ሲዝናናም አየ—ተመኘም—ኃጢአትንም ሠራ የፈጸመውን ለመደበቅም ሲል ሌላ ኃጢአትን ሠራ፤ ዋሸም ቀጥሎም ነፍስ ገደለ። ፪ሳሙ.፲፩፥፰—፲፫። የመጀመሪያውን በቤተ መንግሥት የመዋል ሃሳብ

www.ethiopianorthodox.org

ቢዋጋው ኖሮ አያይም ነበርና አይወድቅም ነበር። ይሁን እንጂ ከዚህ በኋላ ስለኃጢአቱ እያለቀሰ አልጋውን በዕንባ እያራሰ ያድር ነበር። መዝ.፮፥፮–፯።

ሰሎሞን:- ማስተዋልንና መንፈሳዊ ጥበብን ከእግዚአብሔር ለምና ያገኘው – እግዚአብሔርም ሁለቴ ተገልጦ ያነጋገረው (፩ነገ.፲፩፥፱) ንጉሥ ሰሎሞን እንዴት እንደተሳሳተ ስንመረምር ይገርመን ይሆናል። ኃጢአት በአንዴ ሳይሆን ቀስ በቀስ በልቡናው አድጎ ነው በመጨረሻ የጣለው። የመጀመሪያው እርምጃ ከባዕዳን ሴቶች ወገን ሚስት ማግባቱ ነው። ፩ነገ.፲፩፥፲፯–፳፬። ይህ ሁኔታ ሰሎሞን ሌሎችንም ባዕዳን ሴቶች እስከወደደ ድረስ ቀጠለ። ፩ነገ.፲፩፥፩። በዚህ ድርጊቱም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፈ። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለእነዚህ ባዕዳን ሴቶች በተራራ ላይ ቤተ ጣዖት (መሠዊያ) ሠራላቸው። ፩ነገ.፲፩፥፯–፰። ከዚህ በኋላ ልቡናው ወደጣዖት አዘንብሏልና ፍጻሜው መልካም አልሆነም:- በእግዚአብሔርም ፊት ክፋትን አደረገ። ይህ ሁሉ በመጀመሪያው እርምጃ ከፈጸመው ስህተት የመጣ ነው።

እንግዲህ እኛም ብንሆን ከቀደምት አበው፣ ከነቢያት፣ በእግዚአብሔር ፊት በጥበባቸው ተመስግነው ከነበሩ ታላላቅ ሰዎች በኋላም በስህተትና በኃጢአት ከወደቁት ሰዎች አንበልጥምና ከመጀመሪያውና ወደኃጢአት ከሚወስደው እርምጃ መጠንቀቅ–ከእርሱም መሸሽ ያስፈልገናል። መጽሐፍም ኃጢአት «ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና:- እርሷም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው» ይላል። ምሳ.፯፥፳፮። ስለዚህ ኃጢአት ሊያጠፋን ሲያገግግ ሳይሆን ገና ከምንጩ ልንጠላውና ከእኛ ልናስወግደው ይገባናል። ይህን ብናደርግ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ስንፈጽም እንገኛለን። «ወይናችን አብቧልና የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮዎች:- ጥቃቅኑን ቀበሮዎች አጥምዳችሁ ያዙልን።» በማለት መኃ.፪፥፲፭። ወይን የተባለ በአጠቃላይ ቤተክርስቲያን ስትሆን በተናጠል ደግሞ የእያንዳንዱ ክርስቲያን ልቡና ነው። ቀበሮዎች የተባሉ ደግሞ በሰው ግምት ጥቃቅን የሚመስሉ–ስለዚህም ትኩረት የማንሰጣቸው ኃጢአቶች ናቸው። እነዚህ ኃጢአቶች ጥቃቅን ከመሆናቸው የተነሣ የሚያስተውላቸው ባለመኖሩ የሚያስከትሉት ጥፋትና አደጋ ከፍተኛ ነው። ስለሚናቁ ሳይታወቅ ቀስ በቀስ ያድጉና ሊገቱ ከማይችሉበት ደረጃ ይደርሳሉ። ስለሆነም በሕይወታችን ስለአሉት ጥቃቅን ቀበሮዎች እንድንመረምርና ፈልገን እንድናጠፋቸው – ማለትም ቀላልና ትንሽ ነው ብለን የምንንቀው ንቀንም የምንሠራው ኃጢአት በእኛ ዘንድ እንዳይኖር ያስፈልጋል። ምክንያቱም:-



«በመርከብ ላይ ያለች ቀዳዳ ካልተደፈነች ቆይታ መርከቡን ለመስጠም ታደርሰዋለች።»

«ዓባይ ሞልቶ የሚፈሰው በኢትዮጵያ ተራሮች ላይ በወረዱ የዝናብ ነጠብጣብ ነው።»

«የክርስቶስ መስቀል የተደበቀበት የቆሻሻ ክምር የጀመረው በአንድ ቅርጫት ቆሻሻ ነው።»

«ረጅሙ የኃጢአት ጉዞ የሚጀመረው በመጀመሪያይቱ አንዲት እርምጃ ነው።»

ስለዚህ ከእነዚህ ጥቃቅን ቀበሮዎች በእጅጉ ልንጠነቀቅና ራሳችንንም ልንጠብቅ ያስፈልጋል። እነዚህ ጥቃቅን ቀበሮዎች የተባሉት – ስንፍና፣ ግድየለሽነት፣ ምቾት፣ የማይገባ ንግግር፣ ዋዛፈዛዛ፣ የማይገባ ጠባይም –ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ። በትንሹ ነገር የሚጠነቀቅ በትልቁም እንዲሁ መሆኑን መዘንጋት አይገባም። ይህም እንግሊዞች – «ለሳንቲሞቹ ከተጠነቀቅህ ብሩ መጠራቀሙ አይቀርም።» የሚሉትን አባባል ይመስላል። እናም ትንሽ ነውና የሚያመጣው አደጋ የለም ብለን በግድየለሽነት የምንሠራው ኃጢአት መኖር የለበትም ይልቁንም ልናተኩርበት ይገባል እንጂ።

ጥቃቅኑ ቀበሮዎች የቅዱሳንንም ሕይወት ሲፈትኑ ታይተዋል። ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

አብርሃም:- ራሱን ለማዳን ብሎ ሁለት ጊዜ ሚስቱ ሣራን እኅቴ ናት በማለት ዋሸ። እግዚአብሔር ባይታደጋት ኖሮ በእርሱ ግድየለሽነት የተነሣ የሌላ ሰው ሚስት ትሆን ነበር። ዘፍ.፲፪፥፲–፳፤ ዘፍ.፳፥፩–፲፬። በአብርሃም ሕይወት ውስጥ የነበረው ቀበሮ የእምነት ደካማነት ሳይሆን ግድየለሽነት ነበር። በረሃቡና በችግሩ ጊዜ የረዳውን እግዚአብሔርን ትቶ ከግድየለሽነቱ የተነሣ የሰዎችን ዕርዳታ ተስፋ እንዲያደርግና ሰዎችን እንዲታመን አደረገው። በዚህ ጊዜም እንዲፈራና በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት እንዲያጣ ሆነ:- ይህም ለመዋሸት አበቃው–ባለማስተዋሉም ሚስቱን አሳልፎ ለመስጠት አበቃው።

ኢዮብ:- በጽድቁ መታመን በጀመረ ጊዜ ጥቃቅኑ ቀበሮዎች ወደ ኢዮብ ሕይወትም ገቡ። ራሱንም ባጸደቀ ጊዜ እግዚአብሔር ይፈትነው ዘንድ ወደደ። ኢዮ.፴፪፥፩። ከዚህ ፈተና የተነሣ ግን ማንነቱን ዐወቀ:- «እኔ የማላስተውለውን የማላውቀውን ድንቅ ነገር ተናግሬአለሁ» ኢዮ.፵፪፥፫።

www.ethiopianorthodox.org

በማለትም ራሱን ወቀሰ። እንግዲህ ራስን ጻድቅ አድርጎ መቁጠርና የራስን ጽድቅም መናገር ሊጥል ይችላልና ከዚህ ቀበሮ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ዮሴፍ:- ጻድቁ ዮሴፍን ለመሸጥ ያበቃው ስለራሱ መናገሩ ነው። ያየውን ሕልም ለገዛ ወንድሞቹ ቢነግራቸው ስለቀኑበት ጠሉት– ስለጠሉትም ለነጋዴ ሸጡት። ዘፍ.፴፯፥፰። ከዚህ አንፃር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሆነውን ሁሉ በልቧ መጠበቋ መልካም ነበር። ሉቃ.፪፥፶፩። ስለዚህ በመጽሐፍ «እንደጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ» ተብሏልና ጥበበኛ መሆን ይገባል። ኤፌ.፭፥፲፭። ምክንያቱም ትንሽ የሚመስለውና የሚናቀው ስህተት ከከፋ መከራ ከዘለዓለም ሞት ሊያደርስ ይችላልና በጥንቃቄና በጥበብ መኖርን ገንዘብ ማድረግ ጠቃሚ ነው።

በቤቱ ውስጥ ሥልጡን የሆነ ሰው በውጭም ያለጥርጥር ሥልጡን ይሆናል – በቅድስና ራሱን የጠበቀ ነውና።

ዲያብሎስ ለክፋቱ ጠቢብ ነው። ስለዚህ በአንድ ጊዜ እንደናዳ በሚወርድ ኃጢአት ሰውን ማጥመድና ማጥፋት አይሞክርም። የሚጀምረው ግን በትንሽና የመርፌ ቀዳዳ በምታክል ፈቃደ ኃጢአት በመግባት ነው። ለዚህ ነው አስተዋይና ጠንቃቃ መሆን መልካም ነው የተባለው– ግራ ቀኙን መመልከት። ብዙ ኃጢአቶች በትንሹ ደረጃ የሚጀምሩ ናቸው።

ዲያብሎስ በአንድ ጊዜ እንዳንጸልይ አያደርገንም – ነገር ግን ከተለመደው የጸሎት ጊዜ ያዘገየናል። ለጸሎት በነቃን ጊዜ በሆነ ባልሆነው ጥቃቅን ምክንያት ከመደበኛው የጸሎት ሰዓት እንድንዘገይ ያደርገናል። በዚህ ጊዜ የጀመሩትን ማቋረጥና ለእርሱም ፈንታ መስጠት አይገባም። ይህ የኃጢአት የመጀመሪያ ደረጃ ነውና። የኃጢአት የመጀመሪያ ደረጃ በራሱ ኃጢአት ነው ማለት አይደለም። ነገር ግን በየዋህነት ከሚዘወተር የግድየለሽነት ተግባር የሚመነጭም ሊሆን ይችላል። ዘወትር በቤቱ ተቀምጦ ሬዲዮ የሚያደምጥ:- ቴሌቪዥንና ትምህርታዊ ፊልሞችን የሚከታተል ሰው ከመንፈሳውያን ጉባኤያት ሊቀር ይችላል:- ወደሚያየውና ወደሚከታተለው የቴሌቪዥንና የሬድዮ መርሐ–ግብር አዘንብሏልና። ይህም ወደጥፋት የሚያደርስ የመጀመሪያ እርምጃ ሊሆን ስለሚችል ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

የኃጢአት የመጀመሪያ ደረጃዎች እንደየሰዉ ልዩነት የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ በየራሳችን ያለውን የኃጢአት የመጀመሪያ ደረጃ ፈልገን ልንዋጋው:- ከእኛም ልናስወግደው– ከዚህ አንፃርም ጠንቃቆች ልንሆን ይገባናል።



እንግዲህ ጥቃቅን ቀበሮዎችንም በማወቅ ራሳችንን እናድን:- ሌሎች በእነዚህ ጥቃቅን ቀበሮዎች የተነሣ ሲወድቁ እያየን እኛ ደግሞ ከራሳችን እናርቃቸው:- እኛም ከእነርሱ በመራቅ ሌሎችም ደግሞ ከጥቃቅኑ ቀበሮዎች እንዲርቁ አርአያ እንሁን። ይበልጡኑ በቅድስና እንኳ የሚኖሩትን ሳይቀር እንደአደናቀፉ እያሰብን እንጠንቀቅ:- በመጽሐፍም ደግሞ «ኃያላን እንዴት ወደቁ? የሰልፍም ዕቃ እንዴት ጠፋ?» መባሉን ማስተዋል ይጠቅማል። ፪ሳሙ.፩፥፳፯።

ከመጀመሪያው የኃጢአት እርምጃ መጠንቀቅን ገንዘብ ብናደርግ በሕይወታችን አስተዋይነትን እንማራለን። ከጥቃቅኑ ቀበሮዎች ራሳችንን የለየን ለመሆናችንም እርግጠኞች መሆን አለብን።

የውኃን ጥም መታገሥ የለመደው አፋችን ወይን አያምረውምና:- ዳቦ መራብንም የታገሠው ሆዳችን ሥጋ መብላት አያምረውምና:- ለትንሹ ኃጢአት የልቡናችንን በር ከዘጋን ወደጥፋት በሚወስደው መንገድ መጓዝ አንጀምርም።

### ፮. መሰናክሎችንና የኃጢአት ምንጮችን ማስወገድ

ማንኛውም ክርስቲያን የትኛውንም ዓይነት መሰናክል ከእርሱ ዘንድ ማስወገድ አለበት። እነዚህ መሰናክሎችም ሌሎች በመንፈሳዊ ጉዞአችን ፊት የሚያኖሩአቸውና እኛም በሌሎች ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ጉዞ ፊት የምናኖራቸው ናቸው።

#### መሰናክሎች (ማሰናከያዎች) አደገኞች ናቸው:-

በድፍኑ መሰናክል ማለት መውደቅ ማለት ነው። ማሰናከያ የሚያደርገው ሰውም ለወደቀው ሰው ሕይወት ተጠያቂ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት» በማለት ተናግሯል። ማቴ.፲፰፥፯። እንዲሁም ደግሞ «ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታሥሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር» በማለት አበክሮ አስገንዝቦአል። ማቴ.፲፰፥፮። ሉቃ.፲፯፥፪።

«ለዚያ ሰው ወዮ» የሚለው ሐረግ የኃጢአቱን ታላቅነት ያመለክታል። ይህን ያስተዋለው ቅዱስ ጳውሎስ «መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም።» በማለት ተናግሯል። ፩ቆሮ.፰፥፲፫። በመጽሐፍ እንደተጻፈው ማሰናከያን የሚያደርጉና ለሌሎች በኃጢአት መውደቅ ምክንያት የሆኑ በመጨረሻም ለመቀጣት የመጀመሪያ ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

«እንግዲህ እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል። የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ:- ወደእቶነ እሳትም ይጥሉአቸዋል።» ማቴ.፲፫፥፵—፵፪።

ማሰናከል ከባድ ኃጢአት ነው። ይልቁኑ ደግሞ ታናናሾችን ማሰናከል እጅግ የከፋ ነው። ሉቃ.፲፯፥፪። ታናናሾች የተባሉት የተነገራቸውን በቀላሉ የሚያምኑ ትሑታን ልብ፣ ሕፃናተ አእምሮ የሆኑ የዋሃን ናቸው። እነዚህ ኃጢአትን ያልለመዱ ክፋትንም የማያውቁ ናቸውና እንዲህ ያሉትን ማሰናከል ወይም ከመንፈሳዊ የሕይወት ጉዞአቸው ማደናቀፍ ከባድ ነው። ሔዋን ኃጢአትን የማታውቅ ነበረች። ከኃጢአት ጋራ ያስተዋወቃትና አሰናከሉም የጣላት እባብ ነው። ስለዚህም ዘወትር ራሱን እየተመታ እንዲገደል ተረገመ።

ማሰናከያን የሚያደርግ ሰው ለሕፃናት ክፋትን እንደሚያስተምር ሰው ነው። ሕፃናት ያሳዩአቸውን ያደርጋሉ:- የነገሯቸውንም ይናገራሉና ሕፃናትን ማታለል ታላቅ በደል ነው። ለሕፃናት የሚቀርቡ ማሰናከያዎች እጅግ አደገኛ በመሆናቸው ሕፃናትን ላለማሰናከል ከባድ ጥንቃቄ ሊደረግላቸው ይገባል። በመሆኑም ታናናሾችን ከማሰናከል በእጅጉ መጠበቅ ያስፈልጋል—በአእምሮ፣ በዕውቀት፣ በዕድሜ ታናናሾች የሆኑና የነገሯቸውን ሁሉ በየዋህነት የሚቀበሉ ብዙ ናቸውና።

ታናሹን የሚያሰናክል ባልታጠቀና መከላከያም በሌለው ሰው ላይ ተኩስ እንደከፈተ ወታደር ይቆጠራል። ስለዚህ በሌሎች ክርስቲያኖች መንፈሳዊ የሕይወት ጉዞ የማሰናከያ ድንጋይ ከማኖርና እንቅፋት ከመሆን በእጅጉ ልንጠነቀቅ ይገባል። እኛ ስለሠራነው ኃጢአት ንስሐ ገብተን በፍጹም ልባችንም ወደ እግዚአብሔር ተመልሰን ይቅርታ ልናገኝ እንችላለን። ያሰናከልናቸው ሰዎች በኃጢአት መኖርን ቢቀጥሉ የሚሰማን ስሜት እንዴት ያለ ነው? ምንም እንኳ ለእኛ ይቅርታ ቢደረግልንም ስለእነዚያ ሰዎች በእጅጉ ማዘናችንና በፀፀት መቃጠላችን አይቀርም:- በእኛ ምክንያት ሰው ጠፍቷልና ከመንፈሳዊ ጉዞው ተሰናክሏልና። ስለዚህ መሰናክል ላለመሆን ማሰናከያንም ላለማድረግ መጠንቀቅ ጠቃሚ ነው።

በሌላ በኩል ግን ማሰናከያው ወደእኛ የመጣብን እንደሆነ የማሰናከያውን ድንጋይና የኃጢአት ምክንያት የሆነውን ነገር ከእኛ ማስወገድ ይኖርብናል። መልአከ እግዚአብሔር ለሎጥ «ራስህን አድን...በዚህም ዙሪያ አትቁም



እንዳትጠፋም።» በማለት የመከረውን ምክር ማሰብ ይገባናል። ዘፍ.፲፱፥፲፯።

በዚሁ መሠረት አባታችን አብርሃም ከካራን ወጥቶ እንደዳነ:- ጻድቁ ዮሴፍም ከምታሳድደው ኃጢአት ሸሽቶ እንደዳነ እኛም ደግሞ ተሰናክለን ከመውደቅ ለመዳን የተቻለንን ሁሉ ማድረግ ይገባናል። ከመሰናክልና ከኃጢአት መሸሻችን ኃጢአትን መቃወማችንን የሚያስረዳ ነው። ይህም ልቡናችን ኃጢአትን የማይፈልገው መሆኑን ይገልጣልና ከኃጢአት መሸሽን እንደደካማነት ልንቆጥረው አይገባም ይልቅ እንደ አሸናፊነት ነው እንጂ። ኃጢአትን የሸሸ ኃጢአትን የጠላ ነውና ድል የነሣው እርሱ ነው። ከመሰናክል መሸሽ እንጂ ራስን ለፈተና ማጋለጥ ጥበብ አይደለም። አባቶችም ከኃጢአት መሸሽ እንዲገባ እንዲህ ብለው ይመክራሉ።

«ወደ ኃጢአት የቀረበ ሁለት ውጊያ አለበት:- ከውስጥም ከውጭም:- ከኃጢአት የራቀ ግን ውጊያው አንድ ብቻ ነው ከውጭ።»

በቅዱስ መጽሐፍም

«ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ሽሽ።» ፪ጢሞ.፪፥፳፪።

«አትሳቱ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋልና» ፩ቆሮ.፲፭፥፴፫።

«በክፉዎች ምክር ያልሄደ:- በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ:- በዋዘኞች ወንበር ያልተቀመጠ ምስጉን ነው» የሚሉ ምክሮች ተጽፈዋል። መዝ.፹፩፥፩። ይህ የተባለበት ምክንያትም በእነዚህ ክፉ ፍላጎቶችና ተግባራት መጠመድ ያሰናክላልና ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ቀኝ እጅህ ብታሰናክልህ ከአንተ ቆርጠህ ጣላት» በማለት በተራራው ስብከቱ አስተምሯል። ማቴ.፩፥፳፱—፴። ማቴ.፲፰፥፰—፱። ይህ ቃልም የሚያመለክተው ጌታችን መሰናክልን ወይም ማሰናከያን በማስወገድ ላይ ከፍያለ ትኩረት ማድረጉን ነው። በጌታችን ትምህርት ዓይን:- እጅ፣ የተባሉት አብዝተን የምንወደውን:- የምናከብረውን:- የሚረዳንን:- የምንመካበትን ሰው ሥልጣን:- ሀብት:- ክብር ወዘተ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሁሉ የሚያሰናክሉን ከሆነ ከእኛ አውጥተን ልንጥላቸው ያስፈልጋል። በእነዚህ ተመክቶ በዘለዓለም ፍዳ ከመሰቃየት ትምክህቱንና ክብሩን አጥቶ የዘለዓለምን ሕይወት ማግኘት ይሻላልና።

www.ethiopianorthodox.org

## የመሰናከል (ማሰናከያ) ምንጭ

መሰናከል ከሰውየው ከራሱ ውስጣዊ ጠባይ ሊመነጭና ሊመጣ ይችላል:- ይህም ውስጣዊ መሰናከል ነው። በመጽሐፍ «ከልብ ክፉ መዝገብ ክፉ ይወጣል» ሲል ይናገራልና። ሉቃ.፮፥፵፭። ሰው በልቡ የሚያስበውና የሚመኘው ነገርና በኅሊናው የሣለው ሥዕል ማሰናከያ ሊሆንበት ይችላል። በእርግጥም ሰው ከራሱ ውስጣዊ ሃሳብ የተነሣ የተሰናከለ እንደሆነ ጌታችን «ለሰው ቤተሰቦቹ ጠላቶች ይሆኑበታል» እንዳለው ቤተሰብ የቸባለ የልቡ ልዩ ልዩ ሃሳብ ለውድቀቱና ለመንፈሳዊ ሞቱ ምክንያት ሊሆንበት ይችላል። እንዲህ ከሆነ ራሳችንን ለመቆጣጠር መጣር ይኖርብናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ራስን መመርመርና ለጽድቅ ማስገዛት እንደሚገባ ሲናገር «ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን» ያለውን በአንክሮ ማስተዋል ይገባናል። ፪ቆሮ.፲፥፭።

በዚህ ተቃራኒ ደግሞ ከሰዎችና ከአጋንንት የሚመጡ መሰናክሎችም አሉ። እነዚህ አፍአዊ (ውጫዊ) መሰናክሎች ናቸው። ዲያብሎስ በቀጥታ ሰዎችን ተጠቅሞ ሊያሰናክል ይችላል:- ሔዋንን ተጠቅሞ አዳምን እንደአሰናከለ። ዘፍ.፫፥፩። በተዘዋዋሪ ደግሞ ባሕርዩን ደብቆ የብርሃን መልአክም መስሎ በመታየት ሊያሰናክል ይችላል። አፎምያን ሊያሰናክላት እንደሞከረ። ፪ቆሮ.፲፩፥፲፬–፲፭። ከዚህ ጋር የተያያዘ አንድ ታሪክ ብንጠቅስ ትምህርት ይሆነናል።

ሰይጣን በገዳም ለሚኖር አንድ ባህታዊ እኔ ሊቀመላእክት ቅዱስ ገብርኤል ነኝ – የመጣሁትም እግዚአብሔር ወደአንተ ልኮኝ ነው አለው። መነኩሴውም መልሶ–ምናልባት ተሳስተህ ይሆናል–የተላከኸው ወደእኔ አይደለም:- እኔ ከኃጢአቴ የተነሣ ቅዱሳን መላእክትን ለመቀበል የበቃሁ አይደለሁምና አለው። ሰይጣንም ከዚያ በንኖ ጠፋ።

ዲያብሎስ በሞተ ሰው ተመስሎ በመገለጥ ሊያሰናክል ይችላል። በቅዱሳን ተመስሎ በመገለጥም ለማሰናከል ሊሞክር ይችላል። በሕልም በመገለጥም ሊያሰናክል ይችላልና በጅምላው በሕልም መመራት ተገቢ አይደለም። ይህ ማለት ደግሞ ከእግዚአብሔር የሆነ ሕልም የለም ለማለት አይደለም። በቅዱስ መጽሐፍ እንኳ የተመዘገቡ የዳንኤል:- የቅዱስ ዮሴፍ:- የአናጢው ዮሴፍ የመሳሰሉ ሕልሞች አሉና። ይሁን እንጂ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ስለዚህም በሰይጣን ከመታለል እንጠንቀቅ። አታላይነቱንም እንወቅበት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በሰይጣን እንዳንታለል የእርሱን



ሃሳብ አንስተውምና» እንዳለው። ፪ቆሮ.፪፥፲፩። ዲያብሎስ የሚያመጣውን ሃሳብ ሁሉ በመቃወም ከመሰናከልና ከመውደቅም ልንጠበቅ ይገባል። እርሱ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይቀር የተፈታተነ ነውና እንደጌታችን እኛም ደግሞ ልንቃወመውና ልንቋቋመው ያስፈልጋል። እንኳን ከሰይጣን ከሰውም ቢሆን የማያንፀንንና መንፈሳዊ ሕይወታችንን የማይለውጥልንን–ወደ መልካምም የማይመራንን ሃሳብ ሁሉ መቀበል የለብንም።

አብረናቸው የምንሠራ ወይም በጠባይ የሚመስሉን ሰዎች ወዳጅም ይሁኑ ጠላቶቻችን ለእኛም ሆነ ለሌሎች ሰዎች መሰናክል ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህም አንፃር መሰናክል ክተለያዩ አቅጣጫዎችና ከተለያዩ ሰዎች ሊመጣ ይችላል።

### መሰናክል ከምንወዳቸውና ከምናከብራቸው ሰዎች ሊመጣ ይችላል

ሶምሶን በሚያፈቅራትና በወደዳት ደሊላ ተሰናከለ።

ንጉሡ አክዓብ በሚስቱ በኤልዛቤል ተሰናከለ:-

አባታችን አዳምም በሔዋን ተሰናከለ። የብዙ ወጣቶች ማሰናከያ ከቤተሰብ የሚመጣ ሊሆን ይችላል። ቤቱ መንፈሳዊ ቤተሰቡም ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ያልሆነ እንደሆነ ወጣቶቹ ከቤተሰባቸው አሉባልታንና ጭቅጭቅን ያደምጣሉ–ይህንኑ ይለምዳሉ:- በእነዚህ የማይጠቅሙና ክፉ ልምዶችም ያድጋሉ። አባታችንን ያዕቆብን እናቱ አሰናክላዋለች:- ወንድሙን መስሎ አባቱን በማታለል የማይገባውን የወንድሙን በረከት እንዲወስድ አድርጋለችና። ዘፍ.፳፯፥፳–፲፫። ቅዱስ ጴጥሮስም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማሰናከያ አምጥቶበት ነበር–ነገር ግን ተገሠፀ። ይህም ለጌታ ያቀረበው የተሳሳተና የማይገባ ምክር ነበር። ማቴ.፲፮፥፳፩–፳፫።

ከምንወዳቸውና ከምናከብራቸው የሚመጣውን ማሰናከያ አጥብቀን ልንቃወመው ይገባል። ንጉሥ ሳኦል በልጁ በዮናታን ላይ መሰናከል አምጥቶበት ነበር። ነገር ግን ዮናታን የአባቱን ትእዛዝ አልተቀበለውም። የታዘዘው ዳዊትን እንዲጠላውና እንዲነሣበት ነበር። ፩ነገ.፲፱፥፳። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ከእኔ ይልቅ ቤተሰቦቹን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም።» ብሏል። ማቴ.፲፥፴፯። እግዚአብሔርን ከማፍቀር ሌሎችን ሰዎች ማፍቀር:- እንዲሁም ደግሞ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ለሌሎች ሰዎች መታዘዝ ይገኛልና – መጽሐፍም – «ልጆች ሆይ –

www.ethiopianorthodox.org

ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ።» ይላል። ኤፌ.፮፥፩። የሳኦል ትእዛዝ «በጌታ» ስላልነበረ ዮናታን አልተቀበለውም – ለሕይወቱ መሰናክል ሆኖበታልና።

ትእዛዝን መቀበል መሰናክል የማይሆንና ለኃጢአት በር የማይከፍት እስከሆነ ድረስ ብቻ መሆን አለበት። በመጽሐፍ «ፍሬ ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ ይልቁንም ግለጡት እንጂ» የተባለው ለዚህ ነው። ኤፌ.፭፥፲፩።

እንግዲህ እኛም ራሳችን መሰናክል እንዳንሆንና በሰዎች ሕይወት ላይ ማሰናከያ እንዳናመጣ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል። መሰናክል ብንሆን ማሰናከያም በሰዎች ብናመጣ የኀሊና ፍርድ:- በእግዚአብሔርም ፊት ፍርድ:- ምናልባትም በሰዎች ዘንድ ፍርድ ሊጠብቀን ይችላል። ለሰው ሕይወት መውደቅ ምክንያት ሆነናልና።

## የአሰናካዩ ተጠያቂነት

አንድ ወጣት የአንዲትን ሴት ውበት ዓይቶ ቢፈተንና ቢወድቅ ለእርሱ መውደቅ ተጠያቂዋ እርሷ አይደለችም። ምክንያቱም የተሰናከለው በራሱ ፍላጎት እንጂ በእርሷ በኩል የተደረገ ምንም ነገር የሌለ ስለሆነ ነው።

በተፈጥሮ ውበታቸው የተነሣ ሰዎች የሚሰናከሉባቸው ሴቶች አሉ። ይህን በመሰለው ሁኔታ በእነዚህ ሴቶች ዘንድ ምንም ዓይነት ተጠያቂነት አይኖርም:- የሚጠየቀው እነርሱን በማየትና የማይገባውን በመፈለግ የተሰናከለው ሰው ነው እንጂ እነርሱ አይደሉም። ለምሳሌ የአባታችንን የአብርሃምን ሚስት ሣራን ከውበቷ የተነሣ በመጀመሪያ ፈርዖን:- (ዘፍ.፲፪፥፲፬-፲፭) በኋላም ንጉሥ አቤሜሌክ (ዘፍ.፳፥፪) ተሰናክለውባት ወደ ቤተ መንግሥቶቻቸውም ወስደዋት ነበር። በሁለቱም ጊዜያት እርሷ የምትጠየቅበት ምክንያት አልነበረም። ነገሥታቱ ከገዛ ፍላጎታቸው የተነሣ ተፈትነው ተሰናከሉ እንጂ እርሷ ያደረገችው አንዳችም አስተዋጽኦ አልነበረም።

አንዲት ሴት አንድን ወንድ የራሷ ለማድረግ የሞከረችና እርሱንም ለመሳብና ለማስጎምዠት ጥረት ያደረገች እንደሆነ:- ከዚህም የተነሣ እርሱ ቢሰናከልና ቢወድቅ ተጠያቂዋ እርሷ ናት። የምታሳየው ሁኔታ:- ንግግሯ:- አለባበሷ ሁሉ ሆንብላ ሰውየውን ለመማረክ ያደረገችው ከሆነ እርሱን በማሰናከሏ በዚህ ምክንያት ተጠያቂ ትሆናለች።

ሰው በራሱ ድካም ከተሰናከለ በኋላ በሌሎች ሰዎች ላይ ለማመካኘት ቢሞክር እንኳ ራሱን ከተጠያቂነት ሊያድን አይችልም። ከማመካኘት



በፊትም ራስን አጥርቶ ማየት ያስፈልጋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በወንጌል – «ዓይንህ ጤናማ ብትሆን ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል:- ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል» በማለት ተናግሯል። ማቴ.፮፥፳፪-፳፫። ብዙዎች የሚሰናከሉት ዓይናቸው ብሩኅ ስላይደለ ነው። ኃጢአት በዓይናቸው ውስጥ በመሆኑ የሚያዩት ሁሉ ለኃጢአት ይቀሰቅሳቸዋል። ስለዚህ የሚከተሉትን ሁለት ዓይነት ማሰናከያዎች መቃወምና ከራስ ማራቅ ይገባል።

ሀ. ከሰዎች ጋር ወደ መዳራትና ሌሎችንም በመፈተን ለመውደቅ ከሚያበቃ መሰናክል ራስን ማራቅ

ለ. በተፈጥሮ ንጹሐን ሆነው ነገር ግን ለመሰናክል አመቺ ከሆኑ አጋጣሚዎች ራስን ማራቅ – ከደካማ ባሕርይ የተነሣ መውደቅ ሊመጣ ይችላልና።

የምንናገረው ንግግርም ሰው ሊያሰናክልና እኛ ያላሰብነውን ትርጉም ሊይዝብን ስለሚችል ንግግራችን የተመጠነና የተስተዋለ ይሁን። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «መሰናክል ሊመጣ ግድ ነው» ብሎአልና። ማቴ.፲፰፥፯። የምንኖረው በማሰናከያና በፈተና በተሞላ ዓለም ውስጥ:- እንክርዳድና ስንዴም ተደባልቀው በአንድነት በሚኖሩበት ዓለም ውስጥ በመሆኑ ያኔ የእኛ መቆሚያ የት ሊሆን እንደሚችል ከአሁኑ በማሰብ መዘጋጀት ተገቢ ነው። ማቴ.፲፫፥፴። ከዚህ የተነሣም ራሳችንን ከማዳንና ከመሰናከሉ ከማምለጣችን ባሻገር ለመሰናከሉ ተጠያቂውን ስንፈልግና ሰናመካኝ እንዳንገኝ እንጠንቀቅ። ማመካኘትና ሌሎችን ጥፋተኛ አድርጎ መፍረድ በራሱ ሌላ ኃጢአት ነውና።

ከመሰናክል የተነሣም ውስጣዊ ንጽሕናችንን ልናጣ አይገባንም። በመሰናክል ምክንያት የልባችንን ሰላም እንዳናጣ ያስፈልጋል። የምንኖረው በምድር ላይ እንጂ በገነት ስላይደለ በሰው ዘንድ ስህተት መኖሩ የታወቀ ነው። ዋናው ነገር ግን ከዚህ ስህተትና ከመሰናክል ማምለጥና ራስንም ማራቅ ነው። ይህንንም በማድረግ ራሳችንን እናድናለን ሌሎችንም አናሰናክልም።

ውስጣዊ ጥንካሬና መንፈሳዊ ሰላም በልባችን ያለ እንደሆነ በማንኛውም መሰናክል ልንጎዳ አንችልም:- በዓለት ላይ እንደተመሠረተው ቤት የመጣውን እንቅፋት አልፈን ጸንተን እንገኛለን። ማቴ.፯፥፳፬-፳፭።

አንዳንድ ጊዜ በሌሎች ሰዎች ጣልቃ መግባት የተነሣ የሚመጡብን መሰናክሎች አሉ። በሰዎቹ ምክንያት የምንፈተን ከሆነ ከእነርሱ ራሳችንን ማራቅ ይገባል። ከዚህ መሰናክል በመሸሽም ማምለጥና ራስን ማዳን

www.ethiopianorthodox.org

ይገኛል። አባታችን ቅዱስ እንጦንስ የዲያብሎስ ወጥመድ በከበበው ጊዜ «አቤቱ ጌታዬ ሆይ ከዚህ ወጥመድ ማን ያመልጣል?» በማለት ወደፈጣሪው ጮኸል። ስለዚህ ወደ ወጥመድና መሰናከል እንዳንገባ በእጅጉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። መሰናከል የመጀመሪያ ደረጃ በመሆኑ ከአቅም በላይ ሆኖብን ብንሰናከል እንኳ ከሚቀጥለው ደረጃ ከመድረስ በፊት ራሳችንን ለማዳን መጣር እንጂ በዚያው መቀጠል ተገቢ አይደለም።

የመሰናከል መኖር ከሠራነው ኃጢአት የተነሣ ከሚፈረድብን መለኮታዊ ቅጣት ያድነን ዘንድ ምክንያት ሊሆነን እንደማይችል መረዳት ተገቢ ነው። ምክንያቱም የሚመጣውን ፈተና ለመቋቋም የሚያስችለው የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችን ነውና–እርሱም ከሥላሴ በተወለድን ጊዜ የተሰጠን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት የመጣብንን መሰናከል ልንወጣው ይገባናል። በመሰናከሉ በወደቅንና ኃጢአትን በፈጸምነው ጊዜ ይህ መለኮታዊ ኃይል ከእኛ ስለሚለይ ደካሞች እንሆናለን። ጻድቁን ዮሴፍን ዘወትር በማስታወስ እርሱን አብነት ማድረግ ይገባል። እርሱ ምንም እንኳ ፈተናውና ከፊቱም የተደቀነበት ፈተና ኃይለኛ ቢሆንም በጽናትና በትዕግሥት መሰናከሉን በድል ተወጥቶታል። መሰናከል ለተወሰነ ጊዜ የሚ ያጋጥም ነው:- ከታገሡት ወዲያው ሊያልፍ ይችላልና ከትዕግሥት እጦት የተነሣ ተሰናክሎ ላለመውደቅ ጸንቶ ራስን መጠበቅና መጠንቀቅ ይገባል።

## የመሰናከል ዓይነቶች

### ከፈቃደ ዝሙት የሚመጣ

ይህ በብዙ መልክ የሚመጣ መሰናከል ነው። ለምሳሌም በመነካካት፣ በመዝናናት፣ የዝሙት ሥዕሎችን በማየት፣ በመዝፈን፣ የዝሙት ቀልዶችን በማውራት፣ በወሲባዊ ተራክቦ ላይ የተጻፉ ታሪኮችን በማንበብ፣ በመስማትና በፊልም በማየት ወዘተ ይህ ዓይነቱ መሰናከል ሊያጋጥም ይችላል። ስለዚህ ለእንዚህ ሁኔታዎች ከተመቻቹ ሥፍራዎችና ሰዎች መራቅ ጠቃሚ ነው።

### ከሚታይና ከሚደመጥ ነገር የሚመጣ

ማየትና መስማት ስለሚታየው ነገር ማሰብን – ከዚያም ያንን ነገር መፈለግና መመኘትን ያስከትላሉ። ምኞትም በተግባር ኃጢአትን ወደመሥራት ያደርሳል። ስለዚህ ከማየትና ከመስማት የተነሣ መሰናከል እንዳይመጣ የምናየውንና የምንሰማውን ነገር መምረጥና መለየት



ያስፈልጋል። በድንገት ስለአየነውና ስለሰማነው ነገር አንጠየቅም። አስበን ያደረግነው እንደሆነ ግን ከመሰናከሉ ለሚከተለው ፈተናና ኃጢአት ከመጠየቅ አናመልጥም። ስለዚህ ክፉ ነገርን ከማየትና ከመስማት መራቅ አስፈላጊ ነው። ለማየትና ለመስማት የሚያስገድድ ሁኔታ እንኳ ቢያጋጥመን ሃሳባችንን እንዳንሰጠው ይገባል።

### የሰይጣን መጠቀሚያ ከሆኑ ሰዎች የሚመጣ

የሰይጣን ማደሪያ ከመሆኑ የተነሣ ሰዎችን ከሚያሰናክል ሰው ጋር ብዙ ጊዜ መቆየት አይገባም። አብሮ በመቆየትም የልብ ጥንካሬ የሚፈተንና የሚደክም ከሆነ እንዲህ ካለው ሰው ፈጥኖ መለየት ተገቢ ነው። ይህን ከመሰለ ሰው ጋር በምንገናኝበት ጊዜም ልባችን በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መሆን አለበት:- ስለዚህ ሰው ከማሰብም ልቡናችን የጸዳ ሊሆን ያስፈልጋል።

### ከአመለካከትና ከአስተሳሰብ የተነሣ የሚመጣ

በዚህ ሥር የሚካተቱት የመሰናከል ዓይነቶች የተለያዩ የፍልስፍና ሃሳቦችና አመለካከቶች ናቸው። በምናነባቸው ጊዜም ሃሳባችን የተምታታ እንዲሆንና ስለምናውቀው ነገር እንኳን በጥርጥር እንድንሞላ ያደርጉናል። በመጨረሻም ወደመናፍቅነትና ብሎም ወደክህደት ሊያደርሱ ስለሚችሉ አስቀድመን በማናውቀው ነገር ላይ የተጻፉ የፍልስፍና መጻሕፍትን ከማንበብ የተነሣ ከሚመጣ መሰናከል መጠንቀቅ ይኖርብናል።

### ስለሃይማኖት ከሚሰጥ የሐሰት ትምህርት የሚመጣ

አንዳንድ ሰዎች ከሚያስተምሩት የተሳሳተ ትምህርተ ሃይማኖት የተነሣ መሰናከል ሊመጣ ይችላል።

- ኢዮርብዓም እሥራኤልን እንደአሳሳተ:- ፩ነገ.፲፪፥፲፰።
- የገሊላው ይሁዳ ብዙዎችን እንደአሳሳተ:- የሐዋ.፭፥፴፮—፴፯
- በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን ሥጋዊ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ብዙ አይሁድ በክርስቶስ እንዳያምኑ–ትምህርቱንም እንዳይቀበሉ አሰናክለው ነበር።

### ከእንግዳ የኑፋቄ ትምህርት የተነሣ የሚመጣ

ይህ ዓይነቱ ደግሞ አባቶች ሐዋርያት ካስተማሩትና ቤተ ክርስቲያን ከተቀበለችው ትምህረተ ሃይማኖት ውጭ በሆነ አዲስ ትምህርት የሚመጣ ነው። የዚህ ዓይነቱ ትምህርት በምእመናን ልቡናም ውስጥ ጥርጥርን

www.ethiopianorthodox.org

ይጨምራል — ያሰናክላልም። ስለዚህ ይህን የመሰለውን ትምህርት መቀበል አይገባም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «የሚያናውጡአችሁ:- የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ:-...ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።» ከማለቱም በላይ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ «ወዳጅ ሆይ በጎ የሆነውን እንጂ ክፉ የሆነውን አትምሰል። በጎ የሚያደርግ ከእግዚአብሔር ነው:- ክፉ የሚያደርግ ግን እግዚአብሔርን አላየውም።» በማለት ክፉ ከሆነ እንግዳ ትምህርት በመራቅ ራሳችንን እንድንጠብቅ መክረውናል። ገላ.፩፥፯—፰። ፫ዮሐ.፲፩።

የምንገኝበት ዘመን ዘመነ ንስሐና ወደ ድኅነት የሚኬድበት ዘመን ስለሆነ የተለያዩ የፍልስፍና መጻሕፍትን በማንበብ ከሚመጣ መሰናክል መለየትና ራስንም ማራቅ ተገቢ ነው። ስለዚህም ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ በእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር መጨመርና ልባችንንም በፍጹም ንጽሕና ወደእርሱ የቀረበ ማድረግ መልካም ነው።

## ምሥጢር በሚያባክኑ ሰዎች የሚመጣ

አንዳንድ ሰዎች እንኳን የሌላውን የራሳቸውንም ምሥጢር መጠበቅ አይቻላቸውም። እነዚህ ሰዎች በሚያባክኑት ምሥጢርና በሚያወሩት ወሬም ሌሎች ደግሞ ሊሰናከሉ ይችላሉ። ይህን በመሰለ መሰናክል እንዳንወድቅ ራሳችንን መጠበቅ የሚገባ መሆኑን እንዳንዘነጋ ያስፈልጋል።

## ከክፉ ምክር የሚመጣ

የአንዳንድ ሰዎች ምክር ለሕይወት መሰናክል ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ — አቤሴሎም የአኪጦፌልን ምክር ተቀብሎ በአባቱ በዳዊት ላይ ተነሣ:- ተሰናክሎም ከፉኛ ወደቀ። ፪ሳሙ.፲፭፥፴፩። የበለዓም ምክርም ለእሥራኤል አልጠቀማቸውም—ተጎዱበት እንጂ። ዘኁ.፳፪። ይሁ.፲፩። ራእ.፪፥፲፬። ስለዚህ ይህን ከመሰለ ክፉ ምክር የተነሣ እንዳንሰናከል ሕይወታችንን በሚገባ እንጠብቅ። የምንሰማቸው ምክሮች ብዙ ቢሆኑም የምንቀበለውን ግን እንምረጥ።

በሕይወት ዘመናችን የሚያጋጥሙንን መሰናክሎች ልንመረምርና ምንጫቸውን ልናውቅ—ከዚያ በኋላም ፈጽሞ ከእኛ ልናስወግዳቸው ያስፈልጋል። ንስሐ ለመግባት የመጀመሪያው እርምጃ አስቀድሞ መሰናክሉን ከፊታችን ማስወገድ ነውና ዘወትርም «አቤቱ ወደፈተና አታግባን ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ» በማለት በብርቱ ልንጸልይ ይገባል።



## ፮. ለኃጢአት ጊዜ አለመስጠት

ሰው ለኃጢአት ጊዜ ከመስጠት የተነሣ ደጋግሞ ይወድቃል። ይህም ቀስ በቀስ በልቡና አድሮ ለመንሠራፋት ከሚሻ ውጫዊ ውጊያ ይጀምራል። ጊዜ ከተሰጠው ደግሞ ውጊያው ውጫዊ መሆኑ ቀርቶ ውስጣዊ ጦርነቱን በልቡና ውስጥ ይከፍታል። ውጫዊው ኃጢአት በሚታይና በሚያስጎመጅ፥ ወይም በመጻሕፍት ባለ ሥዕል:- ወይም በአንድ ሰው ንግግር ወይም በማንኛውም የሚደነቅ ነገር መልክ ሊሆን ይችላል። በማየት:- በመስማትና በማድነቅ ጊዜ የሰጠነው እንደሆነ ስሜቱ ወደልቡናችን መዝለቅ ይጀምራል። «ከነቃንና ሃሳባችንን ከዚህ የኃጢአት ስሜት የለየን እንደሆነ በፍቅረ እግዚአብሔር ጸንተን ልንቆይ እንችላለን። ካለበለዚያ ግን ከእግዚአብሔር ፍቅር መለየታችንና በኃጢአት መውደቃችን የማይቀር ይሆናል። የተሳሳተ ስሜት በራሱ ኃጢአት ነው ምንጩም ንጹሕ ያልሆነ ልቡና ነው።

ለስሜት ጊዜ ከተሰጠው ደግሞ ፍላጎት ወደመሆን ይለወጣል። በዚህ ጊዜ የስሜታችን ተገዥ በመሆን በውስጣችን ባለ ፍላጎትና በኀሊናችን መካከል ውጊያ ይጀመራል። ፍላጎት አሸንፎ የበላይ ለመሆን ይጥራል — ነገር ግን ኀሊናችን በጽኑ ከተቃወመው የነደደው የኃጢአት ፍላጎት ሊከስም ይችላል።በሰው ልቡና ውስጥ ኃጢአትን ለመሥራት ለተቀሰቀሰው ፍላጎት ጊዜ የተሰጠው እንደሆነ—ይህ የኃጢአት ፍላጎት ሃሳብን:- ስሜትን:- ውስጣዊ ማንነትን:- አካልንም ጭምር ለመቆጣጠር ወደመቻል ሊያድግ ይችላል። ይህም በሰው ዘንድ ጊዜ ከተሰጠው በተግባር ወደመተርጐም ያድጋል። ይህ ደግሞ በድርጊት ለመርካት ወደመቻል ያድጋል — ይህ ጊዜ ከተሰጠው ኃጢአቱ በድርጊት ይፈጸማል:- ኃጢአትም እውን ይሆናል።

ኃጢአት በዚህ አይበቃውም። አንዴ ከተፈጸመ በኋላ ድገሙኝ ድገሙኝ — አጣጥሙኝ ይላል። ታዲያ ሰው ወይ በመጀመሪያ ውድቀቱ ተፀፅቶ ንስሐ ይገባል ወይም ደግሞ በኃጢአቱ ይቀጥላል። ኃጢአት መሥራቱን የቀጠለ እንደሆነ ደግሞ ኃጢአትን እንደልማድ ያደርገዋል — ደጋግሞ ኃጢአትን በመሥራትም የኃጢአት ባሪያ ይሆናል።

የእግዚአብሔር የሆኑት ጻድቃን ግን ጥብቅ ናቸው። በውስጣዊ ስሜታቸው የሚነሣውን ማንኛውንም ሃሳብና ፍላጎት በጥልቅ ይመረምራሉ:- ከአንደበታቸው የሚወጣው ቃልና ምግባራቸው ሁሉ ከፍጹም መንፈሳዊ ጥንቃቄ የመነጨ ነው። ልባቸውም «የተቆለፈ ገነት:- የተዘጋ

www.ethiopianorthodox.org

ምንጭ የታተመም ፈሳሽ ነው።» መኃ.፬፥፲፪። እነዚህም ዘወትር በጸጋ እግዚአብሐር የሚገበኙና በረድኤተ እግዚአብሐርም የሚጠበቁ በመሆናቸው ነፍሳቸውን ወደ ድኅነት ያደርሷታል። ነፍሳቸውም እግዚአብሐርን ታመሰግናለች — እነርሱም:-

> «ኢየሩሳሌም ሆይ እግዚአብሐርን አመስግኚ:- ጽዮንም ሆይ ለአምላክሽ እልል በይ የደጆችሽን መወርወሪያ አጽንቷልና ልጆችሽንም በውስጥሽ ባርኳልና።» በማለት ይዘምራሉ። መዝ.፻፵፯፥፩–፫።

እንግዲህ የሰው ልጆች ሁላችን የልቡናችንን በር እግዚአብሐር እንዲጠብቅልን:- ሃሳባችንንም ሁሉ እርሱ እንዲባርከው ለእርሱ አሳልፈን መስጠት እንጂ በራሳችን የምንመካ መሆን የለብንም። በራስ መመካት ኃጢአት ነውና። በራስ ለመመካት ኃጢአት ጊዜ ከተሰጠው ራስን ወደማምለክ አድርሶ ይጥላልና መጠንቀቅ ይገባል። ቅዱሳን እንኳ ሳይቀሩ በመውደቅ ቅድስናቸውን እንዲያጡ በዚህ ተፈትነዋልና። በመጽሐፍም ኃጢአት «ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና — እርሷም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው ቤቷ የሲኦል መንገድ ነው።» ተብሎ መነገሩን ማስታወስ ያስፈልጋል።

በሕይወቱ የማይጠነቀቅ:- ከመሰናክል የማይርቅ ነፍሱንም የማያሸሽና የማያድናት:- የእግዚአብሐርንም ዕርዳታ በጠዋትና በማታ የማይጠይቅ:- ከእርሱ በፊት የነበሩት ብዙ ጠንካራና ታላላቅ ሰዎች ተፈትነው እንደወደቁት ሁሉ መውደቁ የማይቀር ነው። ኃጢአትን በመታገሥ ጊዜ የሚሰጠው ሰው ሳያስተውለውና ሳያውቀው ቀስ በቀስ ወደ ውድቀት እንደሚደርስ ዐውቀን ራሳችንን ከጥፋት ማዳን ይገባል — ለኃጢአትም ጊዜ መስጠትን ከእኛ ልናርቀው ያስፈልጋል።

ለኃጢአት ጊዜና የሚበረታበትን ዕድል በሰጠነው ቁጥር የሚያጋጥመንን አደገኛ ሁኔታ ማሰብና ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ለኃጢአት በልባችን ውስጥ ሥፍራ እስኪያገኝ ድረስ ጊዜ የሰጠነው እንደሆን ማስተዋላችን ይቀንሳል፤ መንፈሳዊ ፈቃዳችን ደካማ ይሆናል:- ለእግዚአብሐርም ያለን ፍቅር ይቀዘቅዛል ቀስ በቀስም ውስጣዊና ውጫዊ ማንነታችን ይለወጣል። በውስጣችንም የኃጢአት ተጽእኖ እያየለ የነበረን መንፈሳዊ ጸጋና በረከት ጥንካሬአችንም እየቀነሰ ይሄዳል። በመቀጠልም ኀሊናችን ለኃጢአት በመገዛቱ የተነሣ ኃጢአት በውስጣችን መኖሪያውን ይሠራል—ያኔ ደግሞ አደጋው ቢታየንም የማንወጣው ስለሚመስለን



እንጨነቃለን። ጊዜ በመስጠታችን ልናሸንፈው የማንችለውን ጠላት በውስጣችን እንፈጥራለን። ለኃጢአት ታጋሾች በሆንን መጠንም በውስጣችን የነበረውን የእግዚአብሐር መንፈስ እናሳዝናለን:-

> «የእግዚአብሐር ፈቃድ...ወደ እናንተ ነውና መንፈስን አታጥፉ።» «የእግዚአብሐርን መንፈስ አታሳዝኑ።» እንደተባለው። ፩ተሰሎ.፭፥፲፱። ኤፌ.፬፥፴።

ለኃጢአት ጊዜ መስጠት የእግዚአብሐርን ጸጋ መቃወም፣ መንፈሳዊውን ትጥቅ መፍታት፤ ለእግዚአብሐር ጠላቶችና ተቃዋሚዎቹ ለሆኑ አጋንንት የልቡናን በር መክፈትና ከኃጢአት ጋር ወዳጅነት መጀመር ነው።

ለኃጢአት ጊዜ መስጠታችንን የቀጠልን እንደሆነ በመንፈሳዊ ፈቃዳችንና ሃሳባችን መናወጥ እንጀምራለን። በአርአያ ሥላሴ መፈጠራችንን ከንቱ በማድረግ በልቡናችን ከሰይጣን ጋር መደራደር እንጀምራለን። በዚህም አጋጣሚ ጥንካሬአችንን ለመገመት ሰይጣን ይፈትነናል። ከሕይወታችንም ግማሹን ጊዜ የሰጠነው እንደሆነ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ሃሳቦችን በመደጋገም ወደእኛ ማምጣትና በልቡናችን በማሳደር ቀስ በቀስ ሊያታልለን ይሞክራል:- ጊዜ የሰጠነው እንደሆነም በደካማ ጎናችን ገብቶ በመጨረሻ ይረታናል።

ኃጢአትን የምንቃወም የሆንን እንደሆነ ግን ሰይጣንም ይፈራናል። ሰይጣን የእግዚአብሐር እውነተኛ ልጆች ወደሆኑት ሊቀርብ አይችልም። ያሸንፉታልና ይፈራቸዋል። እነርሱ በእግዚአብሐር ጸጋ የተሞሉ የእግዚአብሐር አብያተ መቅደስ መሆናቸውን ያውቃልና።

ሰው መጀመሪያ ለኃጢአት ጊዜ ሰጥቶ በኋላም የፈጸመው እንደሆነ በዚያው በመቀጠል እያጣጣመው ደግሞ ደጋግሞ ይሠራዋል።

ሰሎሞን መጀመሪያ በደለ—የማትገባውን ቤት አገባ:- ቀጠለና ለምታ መልከው ጣዖት ቤት ሠራላት፤ ቀጥሎም እርሱ ራሱ ጣዖቱን ወደማምለክ አዘነበለ:- እንዴ እግዚአብሐር ያዘዘውን ተላልፏልና። ፩ነገ.፲፩፥፩–፱። ቀድሞ የእግዚአብሐርን ትእዛዝ ቢያስብና ለሥጋዊ የኃጢአት ፍላጎት ጊዜ ሳይሰጥ ወደልቡ ቢመለስ ኖሮ ለውድቀትና ለውርደት ባልበቃም ነበር።

እንግዲህ ጥበበኛ የነበረው ሰሎሞን ኃጢአትን በመታገሡ እንዲህ ከወደቀ ደካሞች የምንሆን እኛማ እንዴት? ስለዚህ ትንሽ ነው ብለን የምንንቀው ሳይኖር ለኃጢአት ጊዜ መስጠትንና መታገሥን ከእኛ ልናርቀው ይገባል። ትንሽ ነው:- ቀላል ነው በማለት ራስን ማጽናናት በራሱ

www.ethiopianorthodox.org

ለኃጢአት ዕድል መስጠት ነውና ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል። በትንሹ ያልነቃና ለመጠንቀቅ ያልቻለ በትልቁና በከፋው ኃጢአት መዘፈቁ አይቀርም።

ማንኛውም ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ማመፅና ከእርሱ መለየት ነው። የሚያስኩንነው ከባድ ኃጢአት ነው ብለን ራሳችንን ማምኘትና በኃጢአት መኖር የለብንም። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ «ማንም ወንድሙን ደንቆሮ የሚለው ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል» በማለት አስገንዝቦናል። ማቴ.፭፥፳፪። ሳያስቡና ስለሚናገሩት ነገርም ሳይጨነቁ የሚወረወር ቃል ለገሃነም የሚያበቃ መሆኑን አስረድቶናል። በወንጌልም «ሰውን የሚያረክሰው ከአፍ የሚወጣ ነው» ተብሎአል። ማቴ.፲፭፥፲፩። በአንደበታችን ተናግረን ለምንፈጽመው ኃጢአት ጊዜ መስጠት እንደማይገባ ሲመክር ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ – «አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው።» ብሏል። ያዕ.፩፥፳፮። ስለዚህ «ሰው ከቃሉ የተነሣ ይጸድቃል:- ከቃሉም የተነሣ ይኩነናል» ተብሎ ስለተጻፈ ማቴ.፲፪፥፴፯። ከፍርድና ከዘለዓለማዊው ኩነኔ ለመዳን በመናገርም ለምንፈጽመው ኃጢአት ጊዜ መስጠት የማይገባ ነው። በዚህ መሠረት ቅዱሳን አበው ለጽድቅ ካልሆነ በቀር አንደበታቸውን ከመናገር ከልክለው በአርምሞ ይኖራሉ። ኃጢአትን ከመናገር ሊታገሥ ያልቻለ ከመሥራትም ሊታገሥ አይችልምና።

ስለዚህ የኃጢአት ትንሽ የለውምና በዚህ ሃሳብ የራሳችንን አእምሮ መደለል የለብንም። የሎጥ ሚስት የጨው ሐውልት ሆና የቀረችው ወደኋላ ዞራ በመመልከቷ ነው። ዘፍ.፲፱፥፳፮። የዋሹት ሐናንያና ሰጲራም ወዲያው በሞት ተቀጥተዋል። የሐዋ.፭፥፩–፲። ጌታችንም ዝሙትን ብቻ ሳይሆን አይቶ መመኘትንም ከልክሏል ኃጢአት ስለሆነ። ማቴ.፭፥፳፰። በመጀመሪያ ደረጃ ለኃጢአት ጊዜ የሰጠ ለሁለተኛው ደረጃ መድረሱ አይቀርምና ለኃጢአት ጊዜ እንዳንሰጥ ኅሊናችንን እንቆጣጠረው። ለሁለተኛው ደረጃ ጊዜ የሰጠ በሦስተኛው ደግሞ መውደቁ የማይቀርና እንዲህም እያለ ኃጢአትን ልማድ ወደማድረጉ መድረሱ አይቀርም። ይህን የሚያውቅ ሰይጣን ደግሞ ለመጣል ወጥመዱን ከመዘርጋት ጨርሶ የማይቦዝን በመሆኑ ምን ጊዜም በእርሱ ወጥመድ ላለመያዝ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።



በአንዱ በኩል ጠንቃቃ የሆንን እንደሆነ ደግሞ ሰይጣን በሌላ አቅጣጫ ሊፈትነን ይዘጋጃል። በሰዎች ዘንድም አታላዮች:- የሌለውን ነገር ፈጥረን የምንዋሽ:- ነገረ ሠሪዎች ወዘተ አድርጎ ሊያቀርበን ይችላል:- እኛ ይህን ክስ በመጥላት ለእርሱ ዓላማ ዕድል እንድንሰጠው ይፈልጋልና። እኛ ደግሞ የበለጠ ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባው የመዳናችንንና የትእዛዛተ እግዚአብሔርን ጉዳይ እንጂ የኃጢአትን ነገር አይደለም። ስለዚህም የእግዚአብሔርን ሕግ ተላልፎ ኃጢአትን ልሥራት ልሥራት ለሚለው ሥጋችን ዕድል መስጠት የለብንም። በኃጢአት ብንወድቅ እንኳ ንስሐ ከመግባት መዘግየት አይገባንም:- የዘገየንና በጊዜው ራሳችንን በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ያልቀጣን እንደሆነ ግድየለሾችና ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለን ደካሞች እንሆናለን። እግዚአብሔር መሐሪ ነው ብለንም ስለምናስብ ኃጢአትን ደጋግመን የምንሠራ የኃጢአት ባሮች እንሆናለን። መዝ.፶፪፥፲። ስለሆነም በውስጣችን የሚያድገውን እኛ የምንሠራውን ኃጢአት ወዲያው በንስሐ ከራሳችን እናስወግድ እንጂ በእኛ ላይ እንዲሠለጥንና ባሪያ እንዲያደርገን ጊዜ አንስጠው። ዘወትርም ራሳችንን በመመርመር በንስሐ ሕይወት መኖር ይጠበቅብናል። መዝ.፶፥፫። ስለኃጢአታችን ሁል ጊዜ መቀጣት እንዳለብንም እንቁጠር። ሮሜ.፲፪፥፲፩። ከዚህ አንፃርም እግዚአብሔር የሚወደውንና የሚደሰትበትን ሥራ በትጋት እንሥራ። በመጽሐፍ «የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚያደርግ ርጉም ይሁን።» ተብሎ ተጽፏልና። ኤር.፵፰፥፲።

ሌሊቱን ሙሉ ነቅቶ በጎቹን በትጋት እንደሚጠብቀው እረኛና ሌሊቱን በሙሉ በጸሎት እንደሚተጋው ባህታዊ እንቅልፍን አጥቶ እግዚአብሔር የሚወደውን ሥራ ለማከናወን ራስን መስጠት ጊዜንም መሰዋት ያስፈልጋል። በሌሊት ጸሎታችን ወቅት ፈተና ቢበዛብን አብዝተን እንጸልይ:- የምንደግመውን ዳዊትም እንጨምር እንጂ አንሰልች – አንሸነፍም። በጾምም ጊዜ እንዲሁ ጥብቅና ጠንካራ ልንሆን:- አብዝተንም በመጾምና የምንመገበውን በመቀነስ ራሳችንን በመግዛት መንፈሳዊ ሕይወታችንን በንቃትና በጥንቃቄ በመጠበቅ መኖር አለብን። ጌታችን «ባለቤቱ መቼ እንዲመጣ አታውቁምና ድንገት መጥቶ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ ስለዚህ ትጉ።» እንዳለው ከመትጋት በቀር ማንቀላፋትን ከእኛ ዘንድ እናርቀው።

አንተኛ – ከተኛን ደግሞ ፈጥነን የምንነቃ እንሁን። ሶምሶን በተኛ ጊዜ ቀለበቱ ከተወሰደበት በኋላ በኀንቃቱ ከመውደቅ አላመለጠም። አምስቱ ሰነፎችም በሩ ከተዘጋ በኋላ ቢደርሱ ለመግባት ሳይችሉ በውጭ ቀርተዋል።

www.ethiopianorthodox.org

እኛም እንግዲህ ኃጢአት በእኛ ላይ ቤቱን ከሠራ በኋላ ሳይሆን የኃጢአትን የመጀመሪያ እርምጃ ስንራመድ እንንቃ ዘንድ – ወዲያውም ጊዜ ሳንሰጠው ከእኛ እናስወግደው ዘንድ ይገባናል።

## ፰. ጠባይን መመርመር:- ከድብቅ ኃጢአቶችም መጠንቀቅ

ኃጢአት መገለጥን ስለማይሻ ራሱን ይደብቃል። ለሚያፈቅረው ግድየለሽ ግን ራሱን መግለጡ አይቀርም። ኃጢአት የሚደበቅበት ምክንያት የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት እንዳያውቁትና ከእርሱም ከፋት እንዳይሸሹ ለማድረግ ነው። እንዲህም በድብቅ የሚመጣ ኃጢአት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የበግ ለምድ ለብሰው የሚመጡ በውስጣቸው ነጣቂ ተኩላዎች» ያላቸውን ይመስላሉ። ማቴ.፯+፲፭። ሐሰተኛ መምህር ማንነቱን ሳይገልጥ በድብቅ በሐሰት ትምህርቱ እንደሚያሳስት ኃጢአትም በላይ መልካም በመምሰል ሰዎችን ያሳስታል። ሰዎችን በኃጢአት የሚፈትነው ዲያብሎስም ክፉ ሥራውን መልካም አስመስሎ በማሳየት ነው፤ ቅዱስ ጳውሎስ «የብርሃን መልአክ እስኪመስል ራሱን ይለውጣልና» በማለት እንዳስተማረው። ፪ቆር.፲፩+፲፬–፲፭።

ስለዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር የሆነውንና የሰይጣን የሆነውን ለይተን ለማወቅ የሚያስችለንን ማስተዋልና ጥበብ ከእግዚአብሔር እንለምናለን ምክንያቱም የእግዚአብሔር እየመሰለን ባለማወቅ በሰይጣን መንገድ ልንሄድ እንችላለንና ነው። በመጽሐፍም «ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው።» በማለት ተነግሯል። ምሳ.፲፬+፲፪። ምሳ.፲፮+፳፭።

ይህን የመሰለ የሐሰትና የጥፋት መንገድ ስላለ ሰዎች በመታለልና ባለማወቅ ሊጠፉ ይችላሉ። እግዚአብሔርም «ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቷል» ብሏልና:- ሆሴ.፬+፮። ጠቢቡ ሰሎሞንም ደግሞ ከዚህ በመነሣት «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን በራስህም ማስተዋል አትደገፍ» በማለት መክሯል። ምሳ.፫+፭። እንዲሁ ሁሉ ደግሞ ቅዱስ ዳዊት «አቤቱ ፍለጋህን ሁሉ አሳየኝ መንገድህንም አስተምረኝ» በማለት ደጋግሞ ጸልዮአል። መዝ.፳፲፭። የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ያደረባቸውና የእርሱ ምርጦች የሆኑት እንዲህ በማለት የሚጸልዩ ከሆነ:- እኛ ደግሞ እግዚአብሔር ጥበብና ማስተዋልን እንዲሰጠንና ሳናውቅ ተደብቆ ሊጥለን ከሚመጣብን ኃጢአት እንዲያድነን አብዝተን መጸለይ ይገባናል።



ጥበበኛ ሰው ፍጹም አለመሆኑን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ምን ጊዜም ራሱን ይመረምራል። በመጽሐፍም «የጠቢብ ዓይኖች በራሱ ላይ ናቸው:- ሰነፍ ግን በጨለማ ይሄዳል» ተብሏል። መክ.፪+፲፬። ስለዚህም ራሳችንን እንድንመረምርና ከድብቅ ኃጢአቶች እንድንጠነቀቅ የሚመክርና የሚያስተምር ያስፈልገናል። መጽሐፍ «የሰነፍ መንገድ በዓይኑ የቀናች ናት:- ጠቢብ ግን ምክርን ይሰማል» ተብሎ ተጽፏልና ምክርንና ትምህርተ አበውን በጽኑ የምንከታተል ልንሆን ያስፈልጋል። ምሳ.፲፪+፲፭።

ይህም ሲባል ከእግዚአብሔር ያልሆነውን:- መልካም ያይደለውን ምክር እንስማ ማለት አይደለም። ብዙዎች በሐሰተኛና የተሳሳተ ምክር ጠፍተዋልና እኛም እንጠንቀቅ ለማለት ነው። ኢሳ.፫+፲፬። ለምሳሌም የበለዓም ምክር የሐሰትና ክፉም ነበር። መሳ.፳፪። የሮብአም አወዳደቅም ከክፉ ምክር የመነጨ ነበር። ፩ነገ.፲፪+፲። ስለዚህ ነገር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሐፍት ፈሪሳውያንን «ዕውሮች መሪዎች» በማለት ዘልፏቸዋል:- ምክራቸው ክፉ ነበርና። ማቴ.፳፫+፲፫–፲፮። በሌላው ትምህርቱም «ዕውር ዕውርን ቢመራው ሁለቱም ወደ ጉድጓድ ይወድቃሉ» ሲል ተናግሯል። ማቴ.፲፭+፲፬። እንግዲህ በስህተት የሚመሩት እነዚህ ከእግዚአብሔር ስላይደሉና የተቀደሱም ስላልሆኑ ከእነርሱ ምክር መራቅ ተገቢ ነው።

በዚያው አንፃር ደግሞ የቅዱሳንን ምክር መስማት:- በሕይወትም ሆነ በምግባር እነርሱን መከተል ይጠቅማል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ:- የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው።» በማለት ይህንኑ እንድናደርግ ይመክረናል። ዕብ.፲፫+፯። ከዚሁ ጋር በማያያዝ ስለእነዚህ ቅዱሳን አበው «እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጥ አድርገው... ስለነፍሳችሁ ይተጋሉ።» ሲል አስገንዝቧል። ዕብ.፲፫+፮–፯። ስለዚህም ከእግዚአብሔር የሆነውንና ከሰይጣን የሆነውን ለመለየት የሚያስችል ማስተዋል እንድናገኝ ወደቅዱሳን ተጠግተን ስለእኛ የሚነግሩንን ምክር መስማት ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ደግሞ ምክር ሁሉ መልካም አይደለምና መንፈስን ሁሉ መፈተንና መመርመር እንደሚገባ ተጽፏል። ፩ዮሐ.፬+፩።

በዚህም የእግዚአብሔርን መንፈስ ያገኘን እንደሆነ እርሱ ይመራናል:- ነቢዩ ኢሳይያስም «የእግዚአብሔር መንፈስ የጥበብና የማስተዋል:- የምክርና የኃይል:- የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ» እንደሆነ ተናግሯል። ኢሳ.፲፩+፪። ስለዚህ ነው እግዚአብሔር ማስተዋልን ሰጥቶ ከስህተትና ከውድቀት እንዲጠብቀን ዘወትር የምንጸልየው።

www.ethiopianorthodox.org

ራስን ቅዱስ አድርጎ በመቁጠር ከሚያሳስት የኃጢአት ሃሳብም እግዚአብሔር እንዲጠብቀን መጸለይ ያስፈልጋል። እንዲህ ራሳቸውን የሚያመጻድቁ ሰዎች የቅርብ አባቶች መክረው ካልመለሷቸው ድርጊታቸው ኃጢአት ስለማይመስላቸው ራሳቸውን ሲክቡ ቆይተው በንሥሐ መመለስ ይከብዳቸውና ሊጠፉ ይችላሉ። በራሳቸው ዓይኖች እነርሱ ቅዱሳንና ፍጹማን የሆኑ ይመስላቸዋል። ስለዚህ ኃጢአታቸውን መናገርና መግለጥ ስለማይፈልጉ ጥፋታቸውንና ስህተታቸውን ሸፋፍነው ለማለፍ ይጥራሉ። ኃጢአታቸውን የሚሸፋፍኑ ሰዎች ደግሞ «በበግ ለምድ የተከናነቡ» ስለሆኑ ኃጢአት እንደሠሩ ካለማሰባቸውም በላይ ራሳቸውን በማታለልና በመጽናናት ስለሚረጋጉ ንስሐም አይገቡም።

የተገለጠውን ኃጢአት ግን ለመተው አይከብድም። ከፋው ሰይጣንም ይህን ስለሚያውቅ ኃጢአታችንን ሸፍነን ራሳችንን በማታለል ያለንስሐ እንድንኖር በረቀቀ ጥበቡ ሊያሞኘን ይጥራልና መጠንቀቅ ተገቢ ነው።

ለሠራው ኃጢአት ሌላ ትርጉም የሚሰጥ ወይም ሌላ ስያሜ በመስጠት ኃጢአቱን እንደመልካም ሥራ የሚያስብ ሰው ራሱን ጻድቅ አድርጎ ስለሚቆጥር ንስሐ አይገባም። ለምሳሌ ያዕቆብ ወንድሙን አታልሎ ብኩርናውን በመውሰዱ:- አባቱንም አታልሎ በመባረኩ:- እኅቱን ለባንም አምኝቶ በኅቹን በመውሰዱ ጠቢብ እንደሆነ ካሰበ የሠራውን ኃጢአት እንደጽድቅ ስለሚቆጥረው ንስሐ አይገባም። ዘፍ.፳፭፥፴–፴፬። ዘፍ.፳፯። ዘፍ.፴፥፴፩–፵፫። እንዲሁም ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግ የጠበቁ መስሏቸው ወግ ያጠብቁ የነበሩት ፈሪሳውያን የሚሠሩትን ኃጢአት እንደጽድቅ ስለሚቆጥሩ ንስሐ አይገቡም። ሳውልም ክርስቲያኖችን ማሳደዱን እንደመልካም ገድል ይቆጥረው ስለነበረ ንስሐ አልገባም ነበር። ማቴ.፳፫። የሐዋ.፳፮፥፩።

ለኃጢአት በምንም መንገድ ቢሆን ሽፋን የሚሆነው ስያሜ ሊሰጠው አይገባም። ኃጢአት በኃጢአትነቱ ልናውቀውና ልንሸሸው የሚገባ ጠላታችን ነው እንጂ ለአእምሮአችን እንዲመች የቅድስና ስም እየሰጠነው ራሳችንን የምንሸነግልበት መሆን የለበትም። እውነቱን እንናገር ከተባለ ማንኛውም ኃጢአት በሚሠራው ሰው ዘንድ የመሸፈኛ ሌላ ስያሜ አለው። በዚህም የተነሣ ኃጢአተኛው ንስሐ አይገባም በዚህ የመጽናኛና የሽፋን ስያሜ ራሱን እያታለለ በኃጢአት ይኖራል እንጂ።

ሲጃራ የሚያጨስ ሰው በማጨሱ የሚደሰትበት መሆኑን እንጂ ኃጢአት እየሠራ መሆኑን ስለማያስብ:- ማጨስም ደግሞ «የደስታ ምንጭ» የተሰኘ



የተሳሳተ ስያሜ ስለተሰጠው የሚያጨሰው በዚህ ራሱን እያታለለ ማጨሱን ይቀጥላል እንጂ ንስሐ አይገባም። ጭፈራም ‹ጥበብ› ወይም «አርት» ስለተባለ:- ዝሙትና ማመንዘርም ‹ፍቅር› ስለ ተሰኘ:- የሚፈጽሙት ሁሉም ኃጢአት እንደሠሩ ስለማያስቡ ንስሐ አይገቡም።

ሰዎችን ለማሳሳቅ ብለው አንዳንድ ሰዎች በቀልድ ሽፋን በሌሎች ሰዎች ያሾፋሉ—በዚህም የሰውን ኅሊና ይጎዳሉ፣ ይዋሻሉ፣ የኃጢአት ቃላትን ይጠቀማሉ፣ በዚህም የተነሣ ብዙ ሰዎች ኃጢአት ይሠራሉ:- በእነዚህ ሰዎች አመለካከት በሃሳባቸው እየቀለዱ እንጂ ኃጢአት እየሠሩ ስላልሆነ ንስሐ አይገቡም።

ከዚህ ሁሉ በተቃራኒ ደግሞ ጭካኔም «የበግ ለምድ ለብሶ» የሚቀርብበት ወቅት አለ። ለምሳሌ ጨካኝ አባት ልጁን በሥነ ሥርዓት እንደአሳደገ ራሱን ይቆጥራል እንጂ ጭካኔው ኃጢአት መሆኑን አያስብም:- ለዚህም በራእይ ፪፥፳፯ የተጻፈውን አብነት አድርጎ ሊጠቅስ ይችላል። በቁጡነቱም ጽድቅ የሠራ ይመስለዋል። ነገር ግን ቅዱስ ዳዊት «አቤቱ በቁጣህ አትቅሰፈኝ» ያለውን ዘንግቶታል። መዝ.፮፥፩። ይህን ሥራውንም እንደ ኃጢአት ላይቆጥረው ይችላል።

ክርስቲያኖችን ከምድረገጽ ለማጥፋት ያሳድድ የነበረው ሳውል በዚያ ሁሉ ጭካኔው ጽድቅን እንደሚሠራ ያስብ ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በወንጌል «የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል» ብሏልና። ዮሐ.፲፮፥፪። የሐዋ.፳፮፥፱–፲፩። በንስሐ ከተመለሰና የሚያሳድዳትን ወንጌልንና ክርስትናን መስበክ ከጀመረ በኋላ ስለቀደመ ኑሮው ሲናገር ቅዱስ ጳውሎስ «ለሕግ ስለመቅናት ብትጠይቁ ቤተ ክርስቲያንን አሳዳጅ ነበርኩ» ብሏል። ፊል.፫፥፮። ይህ ሁሉ ጭካኔውና በክርስቲያኖች ላይ ያደረሰው መከራ ለእግዚአብሔር ቤት በመቅናትና በመቆርቆር ለሚፈጸም ተግባር የተሰጠውን ስያሜ ወስዶ ነበር። ስለዚህም ይህን ሲፈጽም የነበረው ሰው ንስሐ እንዲገባ አይጠበቅበትም በእርሱ አእምሮ ኃጢአትን አልሠራምና። ከዚህም ሌላ ብዙ በቅድስና ሽፋን በተቀደሰ ሥራ ስም የሚጠሩ ኃጢአቶች አሉ።

በአጠቃላይ ኃጢአት በራሱ እውነተኛ ስም እንዲጠራ አይፈልግም:- ፈጻሚዎቹ ይቸገራሉና።

በሃይማኖት ረገድ ኑፋቄ አስተምረዋል ተብሎ የተነገረባቸው ሰዎች ሲጠየቁ ስህተታቸውን አምነው አይቀበሉም። «ለማሰብ መብትና ነፃነት

www.ethiopianorthodox.org

አለን» ነው የሚሉት። በእርግጥ ነፃነት አላቸው:- ነገር ግን በተሳሳተ ትምህርታቸው እንዲያሳስቱ ነፃነት የላቸውም። ነፃነት አለን በማለት በማሳሳታቸው የቀጠሉ እንደሆነ ግን በፍርድ መጠየቃቸው አይቀርም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ከሰበክንላችሁ ወንጌል የተለየ የሚሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን» ብሎ አስትምሯል። ገላ.፩፥፯–፱። እነዚህን የመሰሉ የሚያሰናክሉ ሰዎች ተዉ ቢሏቸው እንኳ በጀ አይሉም – ሕይወትን አስተማርን እንጂ አሰናክለናል ብለው አያምኑምና።

በእኛ በኩል ግን ለኃጢአት ከሚሰጥ የሽፋን ስያሜና ትርጉም ራሳችንን ማራቅና ኃጢአትን በኃጢአትነቱ መሸሽ ያስፈልገናል። የእግዚአብሔርን ቃል መሪ ማድረግና በያዝነው ሃይማኖት ጸንተን መገኘት:- በቅድስናና በንጽሕና የራስን ሕይወት መጠበቅ፤ ኃጢአትን መግለጥና በእርሱም ላይ መናዘዝ:- ንስሐ መግባትና የእግዚአብሔርን ይቅርታና ምሕረት መጠየቅ ያስፈልገናል። ይህም ራሳችንን መመርመርና ከኃጢአት ሽንገላ መራቅ ነው። ማንም ለኃጢአቱ የሽፋን ስያሜ እየሰጠ ራሱን የሚሸነግል ሰው ንስሐ አይገባም በመንፈሳዊ ሕይወትም ለመኖር አይችልም። ራሱን የሚመረምር:- ኃጢአቱን የማይሸፍን:- በልቡናው መታደስ የተለወጠው ሰው ግን ንስሐ ይገባል – ሕይወትንም ያገኛል። ሮሜ.፲፪፥፪።

## ፱. ከሚወዱት ኃጢአት መሸሽ ደካማ ጎንን ማረም

ኃጢአተኛ የሚያሰኘው በብዙ ወይም በሁሉም ኃጢአት መውደቅ ብቻ አይደለም። አንድም ኃጢአት ቢሆን ከፈጣሪው ስለሚያጣላው ኃጢአተኛ መሆኑ አይቀርም። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ኃጢአት የሆነውን ሁሉ ከመሥራትና ኃጢአትንም ከመውደድ መለየት አለበት። ኃጢአት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሰናክል ታላቅ እንቅፋት ነው።

ስለዚህ ሰው የሚወደውን ኃጢአት የተቋቋመ እንደሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ባለድልና አሸናፊ ይሆናል። ኃጢአትን መቋቋም አሸናፊ የሚያደርግ ከሆነ ብዙውን ኃጢአት ተቋቁሞ በአንዱ መውደቅ ረብ የሌለውና የማይጠቅም ስለሆነ በኃጢአት ሁሉ ላይ አሸናፊነትን ለመቀዳጀት መጣር ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሰይጣን ልንቋቋመው ባልቻልነው ኃጢአት ገብቶ በልቡናችን ግዛቱን ከአስፋፋ በኋላ ከፈጣሪአችን ሊለየን ይችላልና ነው። አንዲት የመርፌ ቀዳዳ የምታክል ቀዳዳ ግዙፉን መርከብ ለመስጠም ታበቃዋለች፤ አንዲትም ነቁጣ ዕድፍ ያማረውን ሸማ



ታቆሽሽዋለች፤ አንዲት ጠብታ ቀለም በብርጭቆ ውስጥ ያለውን ንጹሕ ውኃ እንዳይጠጣ ታደርገዋለች:- በሌሎች ትምህርቶች ሁሉ ጥሩ ውጤት ያመጣ ተማሪ በአንዱ ቢወድቅ ከኮሌጅ ሊመረቅ አይችልም። በመሆኑም የወደቀበትን ትምህርት እስኪያልፍና ጥሩ ውጤት እስኪያመጣ ድረስ መማርና ማጥናት አለበት:- ውጤቱ በተሻሻለ ጊዜ ለመመረቅ ይችላል። የታመመ ሰው ከመላ አካሉ አንዱ በሽተኛ ቢሆን የታመመውን የአካሉን ክፍል ተመርምሮ መታከም አለበት። ኃጢአትም እንዲሁ ነው መንፈሳዊ በሽታ– የነፍስ ደዌ ነውና – ትንሽም ቢሆን– አንድም ቢሆን መታከም ያስፈልጋል። ጾመኛ ሰው ምግቦችን ሁሉ ቢተው ነገር ግን የሚወደውን ምግብ መመገቡን ባያቆም አልጾመም:- የሚወደውን እያደረገ ነውና። መጽሐፍም – «ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል።» በማለት ያስገነዝባል። ያዕ.፪፥፲። ከእግዚአብሔር አብልጠን የምንወደው ነገር መኖር የለበትም– በእግዚአብሔር ስላለን ፍቅር ሁሉን መተው ይገባናል እንጂ። ከእግዚአብሔር አብልጠን የምንወደውና ከእግዚአብሔር የምናወዳድረው ነገር ካለ ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር ግን በልባችን ከእርሱ በቀር ማንም እንዳይኖር ስለሚሻ «ልጀ ሆይ ልብህን ስጠኝ» ይለናል። ልባችንን ለእግዚአብሔር የሰጠን እንደሆነ ኃጢአት ከእኛ ይርቃል። ልባችን ከእግዚአብሔር የራቀ እንደሆነ በእኛና በእርሱ መካከል እንቅፋት የሆነ ፈቃደ ሰይጣን – ኃጢአት ይገባል:- በልባችንም ያለውን ፍቅረ እግዚአብሔር ይከፍልብናል – ይቀንስብናል – ከእግዚአብሔር የበለጠም ኃጢአትን እንድንወድ ያደርገናል – ከአምላካችንም ያጣላናል። አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን ንጽሕናቸውን አጥተው ከእግዚአብሔር ጋር ለመጣላት የበቁት ልባቸውን ለምክረ ከይሲ ለእባብ ሰጥተው ዕፀ በለስን ወደው ነው። በልባቸው ያደረ የመብል ፍቅር ነበርና በዚያ የገባ ፈቃደ ሰይጣን ደካማ ጎናቸውን ተጠቅሞ ረታቸው። እኛም እንግዲህ የምንወደው ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር የሚነፃፀር–የሚወዳደር እንዳይሆንና በድካማችንም ከፈጣሪአችን ጋር እንዳንጣላ ደካማ ጎናችንን ማረም ይኖርብናል። ለሰይጣን መግቢያ በር እንዳንከፍትለት።

ብዙ ሰዎች በሠሩት መልካም ምግባር ይመጻደቃሉ። በዚህ ጥቂት ምግባራቸውም ኃጢአታቸውን ያካክሳሉ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አምላክ ይህን የመሰለውን የኃጢአት ማካካሻ አይቀበለውም። በመጽሐፍ እንደተጣፈ በቤተ መቅደስ ሲመጻደቅ የነበረው ፈሪሳዊ በጌታ ዘንድ ተቀባይነት ማጣቱ በቂ መረጃና ምሳሌ ነው። ሉቃ.፲፰፥፱–፲፬።

www.ethiopianorthodox.org

እሥራኤልም በመስዋዕታቸው፣ በጸሎታቸውና ሰንበትን በማክበራቸው ይመጻደቁ ነበር:- እግዚአብሔር ግን አልተቀበላቸውም። ኢሳ.፩፥፲፩–፲፯። እግዚአብሔር ፈሪሳዊውንም ሆነ እሥራኤላውያንን ያልተቀበላቸው በልቡናቸው የነበረውን ክፉ ሃሳብ ለበረከትና ለጸጋ ብለው ሳይሆን በልማድ በፈጸሙት መልካም ምግባር ለማካካስ በመሞከራቸው ነው። ምክንያቱም ዛሬ የተሠራ ኃጢአት የሚወገደው ንስሐ በመግባት ነው እንጂ ትናንት በተኖረ የቅድስና ሕይወት ወይም በተሠራ በጎ ምግባር ተጣጥቶ ወይም ተካክሶ አይደለም። ስለዚህ ምን ጊዜም ቢሆን ኃጢአት የሆነውን ሁሉ መዋጋት ያስፈልጋል። በልቡናችን ኃጢአትን እያሰብንና እየሠራን በቀደመ ማንነታችን ከመመጻደቅ ይልቅ በግልጽ ከራሳችን ጋር ልንዋጋ – ደካማ ጎናችንን ልንጠግንና ከኃጢአትም ልንለይ ይገባል።

የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ የፈጸመው ወጣት የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርስና ዘለዓለማዊ ሕይወትንም እንዳያገኝ እንቅፋት የሆነበት ገንዘብ መውደዱ ነበር። ማቴ.፲፱፥፲፮–፳፪። የዚህ ወጣት ደካማ ጎኑ በልቡናው ያደረ ፍቅረ ንዋይ ነበር። ስለዚህም «ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥና ተከተለኝ» በተባለ ጊዜ «እያዘነ ሄደ»:- ድካሙን ከእርሱ አውጥቶ ለመጣል ባለመቻሉ:- በልቡናው ያደረውን ፍቅረ ንዋይ በፍቅረ እግዚአብሔር መለወጥ ባለመቻሉ እግዚአብሔርን ለመከተልና ደቀ መዝሙሩ ለመሆን ሳይታደል ቀርቷል።

በእግዚአብሔር አንደበት ቅድስናው የተመሰከረለት አባታችን ኢዮብ እንኳ በዚህ ቅድስናው መመጻደቅ በጀመረ ጊዜ ተፈተነ። ኢዮ.፩፥፳፤ ፳፪፤ ፵፪፥፮። ከዚህም የተነሣ ያለውን ሁሉ አጣ። ሀብቱና ልጆቹ ሁሉ ተወሰዱበት። በዚህ ጊዜም ቆም ብሎ ራሱን በመመርመሩ ደካማ ጎኑን ዐወቀው:- «የማላውቀውን እናገራለሁ–አሁንም ራሴን በማዋረድ ንስሐ እገባለሁ» አለ። ኢዮ.፵፪፥፫–፮። ይህንም በማድረጉ በቀደመ ምግባር መመጻደቅን ከእርሱ አራቀ:- በደካማ ጎኑም ላይ አሸናፊ ሆነ። ንስሐ በመግባቱም የበለጠ ቅድስናን ከእግዚአብሔር ዘንድ አገኘ። ስለዚህ ደካማ ጎናችንን በመመርመር ከእኛ ልናርቀው ይገባል።

ሳይወድ በግዱ መንፈስ ቅዱስ አፉን ከፍቶ ፈቱን ጸፍቶ ስለመድኃኒታችን ትንቢት ያናገረው ነቢዩ በለዓም ለውድቀት የበቃው ገንዘብ በመውደድ ነው። ዘኍ.፳፪፥፲፪። ዘኍ.፳፪፥፴፫። ዘኍ.፳፫፥፳። ዘኍ.፳፬፥፫–፬፤ ፲፭–፲፯።

ንጉሥ ሰሎሞን የወደቀው ሴት በመውደዱ ነው። በዚህ ድካሙ የተነሣም ወደቀ፣ አባታችን አብርሃምም በፍርሃት የተነሣ በውሸት ወደቀ፣



ቅዱስ ጴጥሮስም በችኩልነቱ ወደቀ፣ ቶማስም ድካሙ ጥርጣሬ ነበር:- አባታችን ያዕቆብም ድካሙ በሰው መመራቱ ነበር።

ሊቀ መላእክት የነበረውን ሳጥናኤልንም ለውድቀት ያበቃው ትዕቢቱ ነው። ኢሳ.፲፬፥፲፪–፲፬።

ማንም ሰው ቢሆን በጊዜው ካላረመው በድካሙ የተነሣ ይወድቃል። ስለዚህ የምንወደውን ኃጢአት መሸሽና ደካማ ባሕርያችንን በመመርመር ልንቋቋመው ከእኛም ልናስወግደው ያስፈልጋል። በንስሐ ጊዜም ቢሆን በእነዚህ ነገሮች ላይ ማተኮር ይገባል። እኛነታችንን ከምንወደው ኃጢአት የለየን እንደሆን ያን ጊዜ የእግዚአብሐር ፍቅር ሕይወታችንን የሚመራው መሆኑን እናውቃለን።

## ፲. ዘለዓለማዊውን ሕይወትና የሚጠበቅብንን ማሰብ

መንፈሳዊ ጉዞአችን ረጅም ከመሆኑ የተነሣ መላ የሕይወት ዘመናችን አይበቃውም። ስለዚህ በዘመናችን ሁሉ ከእኛ ምን እንደሚጠበቅ በእርግጠኛነት ማወቅ አለብን። ከዚህ አንፃርም ጉዞውን ጀምረን በመንገዝ ላይ ነን? ወይስ ጥቂት ከተጓዝን በኋላ ቆመናል? ወይስ ገና መንገዝ አልጀመርንም? በማለት ራሳችንን መጠየቅ ተገቢ ነው።

ከእኛ የሚጠበቀው ማመን ብቻ ሳይሆን የቅድስናን ሕይወት መኖር ነው። ስለዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ «የጠራችሁ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ።» በማለት ተናግሯል። ፩ጴጥ.፩፥፲፭። እንዲሁም ደግሞ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እግዚአብሔርን በመፍራት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ።» በማለት መንገዳችን የቅዱሳንን ጉዞ አብነት በማድረግ ወደቅድስና መንዝ እንዲሆን ይጠበቅብናል። ፪ቆሮ.፯፥፩። ከዚህም በተጨማሪ «ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ:- ያለእርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።» ሲል ቅዱስ ጳውሎስ አስገንዝቧል። ዕብ.፲፪፥፲፬። ቅድስና የጉዞው ፍጻሜ አይደለም፤ ይሁን እንጂ ወደቅድስና ልንደርስ የቅድስናንም ሕይወት እየኖ ርን በውስጡ ማለፍ ያስፈልገናል። መንፈሳዊ ዕድገታችን ከፍጹምነት እስክንደርስ መቀጠል ያለበት እንጂ በተወሰነ ደረጃ ላይ የሚያቆም መሆን የለበትም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ ፍጹማን ሁኑ» በማለት አስተምሯል። ማቴ.፭፥፵፰። ቅዱስ ጳውሎስም ከዚህ በመነሣት «ፍጹማን የሆንን ሁላችን በደረስንበት በዚያ እንመላለስ» በማለት ግባችን ቅድስና እንዲሆን ይመክረናል። ፊል.፫፥፲፬–፲፭። ይህ

www.ethiopianorthodox.org

መመላለስም ከእግዚአብሔር የሚሰጠውን የፍጹምነት ጸጋ እስከማግኘት መሆን እንደሚገባው ነግሮናል። ፊል.፫፥፲፱።

ወደ ፍጹምነት የሚያደርሰውን የቅድስና ሕይወት መኖር ማለትም ዓለምን ለማዳን ሰው የሆነው ክርስቶስ ያስተማረውንና በሥራ ያሳየውን በመከተል መኖር ነው። «በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ ክርስቶስ እንደተመላለሰ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል።» ሲል ቅዱስ ዮሐንስ የተናገረው ለዚህ ነው። ፩ዮሐ.፪፥፮።

ይህ የቅድስናና የፍጹምነት ሕይወት ወሰንና ልክ የሌለው ስለሆነ ቅዱሳን እንኳ ራሳቸውን «ኃጢአተኞች ነን» እያሉ ሲያሳንሱ እናገኛቸዋለን። ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑን ከሚችሉት ብዙዎች መካከል አንዱ ቅዱስ ጳውሎስ ነው:- «ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ የሆነ ኢየሱስ ወደዓለም መጣ:- ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ።» በማለት ተናግሯል። ፩ጢሞ.፩፥፲፭። እርሱ ራሱን የኃጢአተኞች ዋና ካደረገ እኛ ደግሞ ስለራሳችን ምን ልንል እንችላለን?

ቅዱስ ጳውሎስ በተሰጠው ጸጋ ከሁሉም ሐዋርያት የበለጠ ለወንጌል አገልግሎት ደክሟል:- ፩ቆሮ.፲፭፥፲። በብዙ ሀገሮችም ሰብኳል፥ አሥራ አራት መልእክታትን ጽፏልና:- ብዙ ድንቅ ተአምራትን አድርጓል፣ የሥጋን ውጊያ ታግሦ ትዕቢትን አሸንፏል:- ፪ቆሮ.፲፪፥፯። ወደ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ዐርጎ የሚያስደንቁ ቃላትን ሰምቷል:- ፪ቆሮ.፲፪፥፬። እንግዲህ ይህ ጳውሎስ «አሁን እንዳገኘሁ ወይም...እንደሆንሁ አይደለም።...ነገር ግን ስለእርሱ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ...እኔ ገና እንዳልያዝኩት እቆጥራለሁ:- ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ:- በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ።» በማለት ስለወደፊቱ የሚያስብ ከሆነ ከቶ አንዱን ነገር እንኳ ያልያዝነው እኛ ምን ልንል ይሆን? ፊል.፫፥፲፪–፲፫።

እኛ እንደተወደዱት ልጆች ልንኖር አልቻልንም። የታመኑ ባሮችም ለመሆን አልቻልንም። «የማይጠቅም ባሪያ» ከምንባልበት ደረጃ ላይ እንኳ አልደረስንም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ በአደረጋችሁት ጊዜ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን በሉ።» እንዳለ እንዲሁ ልንል ደግሞ እንደሚገባን አስተምሮናል። ሉቃ.፲፯፥፲። ይህን በማለት የመከረን ገና በሕግ የምንመራና ሁሉንም ነገር ስለክርስቶስ አልተውንምና ነው። እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለክርስቶስ ስለጌታዬ ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቆጥራለሁ» ለማለት አልበቃንምና። ፊል.፫፥፰። ሕግን የጠበቀ



የማይጠቅም ባሪያ ከተባለ ስለኃጢአተኛው ደግሞ ምን ሊባል ይችላል? ይህ የኃጢአት ባሪያ እንጂ የክርስቶስ ባሪያ ሊባል አይችልም። የዲያብሎስ ባሪያ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ነውና።

ከዚህም የምንማረው ፍጹም ትሕትናን ነው። እነዚህ በእግዚአብሔር ጸጋ የከበሩ ቅዱሳን አበው ራሳቸውን የማይጠቅሙ ባሮች አድርገው እንደቆጠሩ ስንመለከት ገና ውዳሴ ማርያም በመድገማችን የክርስትናን ሕይወት ጉዞ ፈጽመን ከግቡ የደረስን ይመስለን የነበርን ሁሉ ያለንበትን ደረጃ እንድናውቅና ራሳችንን እንድንመረምር ይረዳናል። ስለዚህ በየትኛውም መንፈሳዊ የሕይወት ጉዞ ላይ ከምድራዊው ነገር ይልቅ ልናተኩርበት የሚገባው የመዳናችንን ነገር ነው። ያለችንን አንዲት ነፍስ ከስቃይና ከፍርድ በማዳን በዘለዓለማዊ ሕይወት ብንኖር ይበጃል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል» ያለው ለዚህ ነው። ማቴ.፲፮፥፳፮።

ይህም ስለሆነ ቆም ብለን በእርግጥ በሕይወት ጎዳና ላይ እየተጓዝን ስለመሆናችን ራሳችንን መመርመር:- በፍቅረ እግዚአብሔር ስለመኖራችን፣ ማወቃችንን ማስተዋልና መንፈሳዊ ዕድገታችንን ማጤንና መቆጣጠር ያስፈልገናል። ከዚህ አንፃር እንግዲህ የምንረዳው ዐቢይ ቁም ነገር በፊታችን ያለውን እጅግ ረጅም መንፈሳዊ ጉዞ ገና ያልጀመርነው መሆኑን ነው።

የዚህ ረጅም ጉዞ መጀመሪያው እግዚአብሔርን መፍራት ነው። «ፈሪሃ እግዚአብሔር የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው።» ተብሏልና። ምሳ.፩፥፯። ፈሪሃ እግዚአብሔር ወደ ፍቅረ እግዚአብሔር የሚያደርስ መንገድ ነው። ከፈሪሃ እግዚአብሔር የደረሰ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግጋቱን አይጥስም ትእዛዛቱንም አያፈርስም። እኛ ግን ሕጉንና ትእዛዛቱን ስንቃወምና ስንጥስ እንገኛለንና ፈሪሃ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ያለመኖሩን በዚህ እናውቃለን። ወደ ፍቅረ እግዚአብሔር የሚያደርሰንን ፈሪሃ እግዚአብሔር ገንዘብ ካላደረግን እንግዲህ ወደፍቅር የምንደርሰው መቼ ነው?

ፈሪሃ እግዚአብሔር ከሌለን – በፍቅረ እግዚአብሔር ልንኖር አንችልም:- ፍቅረ እግዚአብሔር በእኛ ዘንድ ከሌለ የእግዚአብሔር መንፈስ ሊያድርብን አይችልም። የእግዚአብሔር መንፈስ ካልመራን ወደ እግዚአብሔር ልንደርስም አንችልም። በእግዚአብሔር መንፈስ ብንመራ በሕይወታችን የመንፈስን ፍሬ እናፈራለን:- እርሱም ሰፊና ብዙ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የመንፈስ ፍሬ «ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው።»

www.ethiopianorthodox.org

በማለት ተናግሯል። ገላ.፭፥፳፪። ከእነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች የመጀመሪያ የሆነውን ፍቅርን በቀዳማዊ የቆሮንቶስ መልእክቱ በሰፊው ተንትኖታል። ፩ቆሮ.፲፫። ከእነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች በየትኛው መጓዝን ጀምረን እንደሆነ ራሳችንን ልንጠይቅ ያስፈልጋል።

እንግዲህ በዘለዓለም ሕይወት ለመኖር የሚያበቃውን የፈሪሃ እግዚአብሔርና የፍቅረ እግዚአብሔር በአጠቃላይም ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረንን ግንኙነት የመጀመሪያ እርምጃ መጀመር ይገባናል። ይህ የመጀመሪያ እርምጃም ራስን ቆም ብሎ መመርመርና ጉድለትን በማስወገድ ዘለዓለማዊውንም ሕይወት በማሰብ ንስሐ መግባት ነው። ንስሐ የእግዚአብሔርን ጥሪ የምንሰማበት ወደ እግዚአብሔርም የሚመልሰን፥ ወደንጽሕና፥ ወደቅድስና ወደጸጋ ፍጽምና የሚያደርሰን መሣሪያ ነው። በዚህ ጉዞ ሕይወትን ለመጀመር ከፈለግን የሚከተለውን መመሪያ መከተል ይገባናል።

## ፲፩. የኃጢአትን ፍቅር ለማስወገድ ፍቅረ እግዚአብሔርን ማጽናት

ሰው በልቡናው ከሁሉም ነገር ነፃ ሆኖ ለመኖር አይችልም። ወይ የመልካም አሊያም የክፉ ሃሳብ ማደሪያ ነው የሚሆነው — በፍቅረ እግዚአብሔር ወይም በፍቅረ ዓለም የተያዘ ነው የሚሆነው። ይሁን እንጂ እነዚህን ሁለቱን ተቃራኒ ነገሮች ለማስተናገድና በሁለቱም ደስተኛ ለመሆን አይቻለውም። የእግዚአብሔር ቃልም «የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚወድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኗል።» በማለት ምስክርነቱን ገልጧል። ያዕ.፬፥፬። ሌሎችን ነገሮች መውደድ ከደጉና ከቸሩ አምላክ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያጣላ ከሆነ ከፍቅረ እግዚአብሔር የበለጠ በልቡናችን ሊያድር የሚገባው ሌላ ነገር መኖር የለበትም። የእግዚአብሔር ፍቅርም ጥልቅና ጠንካራ ነው ከዚህም የተነሣ በልቡናችን ያለውን ማንኛውንም ሌላ ፍላጎት ያስወግድልናል።

እንግዲህ ፍቅረ እግዚአብሔርን በንስሐ የምናገኘው ከሆነ—በልባችን ያደረው ፍቅረ እግዚአብሔርም የሠለጠነብንን የኃጢአት ፍላጎት የሚያስወግድልን ከሆነ «ንስሐ አንዱን ፍላጎት በሌላ መለወጥ ነው» በማለት አንድ ቅዱስ አባት መናገሩ ትክክል ነው። ይህም ንስሐ የዓለምና የሥጋ ፍላጎት በሆነው የኃጢአት ፍላጎት ፈንታ መንፈሳዊውንና የጽድቅን— ከእግዚአብሔር ጋራ ለዘለዓለም የሚያኖረውን ሕይወት መተካት ነው። በመሆኑም ልቡናችን ከእግዚአብሔር ፍቅርና ከሰማያዊው የዘለዓለም ተስፋ የተለየ እንዳይሆን ጸንተን የዓለምን ፍላጎትና ኃጢአትን መቃወም



ይኖርብናል። የዓለም ፍላጎት በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ ተጽእኖ በሚያደርግብን ጊዜ ሁሉ መንፈሳዊ በሆነው መሣሪያ — በጾምና በጸሎት በመጠቀም ልንዋጋው ይገባል፡- የዚህ መንፈሳዊ ውጊያ ውጤት ደግሞ የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጣችን ጥልቅ እንዲሆን የረዳናል።

እግዚአብሔርን ፈጽሞ በሚያፈቅር ልቡና ኃጢአት ሊገባበት እንደማይችል ማወቅ አለብን። በአንድ ሰው ልቡና ውስጥ ያለው ጽኑ ፍቅረ እግዚአብሔር ያለማቋረጥ እንዲጾም፥ እንዲጸልይ፥ መንፈሳውያን መጻሕፍትን እንዲያነብ፥ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄድ— ንስሐ እንዲገባ፡- ሥጋውን ደሙን እንዲቀበል ያደርገዋል።

ሃይማኖት (እምነት) ራሱ ፍቅር ነው፡- በመሆኑም ሃይማኖት፥ ፍቅረ እግዚአብሔር፥ መልካምን ነገር የማድረግ ፍቅር፥ ሌሎችን ሰዎች ማፍቀር ነው። ይህን ፍቅር ያጣ ልቡና ግድየለሽ ከመሆኑ የተነሣ ቀድሞ የእግዚአብሔርን ፍቅር ባወቀበት ጊዜ በልቡናው የተቀጣጠለውን ፍጹም መንፈሳዊነት ያጣል — እናም ይህ ግድየለሽነቱ ወደ ኃጢአት ያድጋል።

በልቡናችን ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር ከሌለ ንስሐ ልንገባ አንችልም። እግዚአብሔርንም ካላፈቀርን ኃጢአትን ልንጠላና ልቡናችንን ልናነጻ አንችልም። ሰው እግዚአብሔር በመጨረሻው የፍርድ ቀን የሚሰጠውን የቅጣት ፍርድ በመፍራት ከሲኦልና በኋላም ከገሃነም እሳት ለመዳን ብሎ ንስሐ ሊገባ ይችላል፡- ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ሰው በፍርሃት ምክንያት ተዋት እንጂ ኃጢአትን ከልቡናው ጨርሶ አላወጣትም— አልጠላትምና። የዚህ መሰሉ ልቡና ደግሞ ከግራ ወደቀኝ ሲዋዥቅ ይኖራል እንጂ ውስጣዊ ሰላምና ዕረፍት አግኝቶ አይረጋጋም በውስጡ ፍቅረ እግዚአብሔር አልተተካምና። ልቡና በፍቅረ እግዚአብሔር ሊሞላና ወደ መልካምነት ሊለወጥ የሚችለው በንስሐ ነው። መንፈሳዊ ሕይወትም ከዚህ ፍቅረ እግዚአብሔር የሚመጣ ነው እንጂ እንደደራሽ ውሃ ድንገት የሚገኝ አይደለም።

ማንኛውም ነገር በፍቅረ እግዚአብሔር ላይ ተመሥርቶ ካልተደረገ ልማድ እንጂ መንፈሳዊ ሕይወት ነው ሊባል አይችልም። ስለዚህም በጸሎታችን «ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች» መዝ.፷፪፥፭። «አቤቱ ሕግህን እንደምን እጅግ ወደድሁ ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው» እያልን መጸለይ አለብን። መዝ.፻፲፰፥፺፯። በመጽሐፍም «ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው፡- ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ» ተብሎ ተጽፏል። መዝ.፻፲፰፥፻፫። እኛም ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደን

www.ethiopianorthodox.org

«የሠራዊት አምላክ ሆይ ማደሪያዎችህ እንደምን የተወደዱ ናቸው ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች ትወዳለች:- ትናፍቃለችም:- ልቤም ሥጋዬም በሕያው አምላክ ደስ ተሰኘ።» በማለት ልንጸልይ ያስፈልጋል። መዝ.፹፫፥፩–፪። በዚህ አኳኋን በውስጣችን ከሚፈጠረው መንፈሳዊ ስሜት የተነሣ ንስሐ በመግባታችን ደስተኞች ስለምንሆን የንስሐ ሕይወታችን የሚቋረጥ ሳይሆን ተከታታይ ይሆናል።

ፍጹሙ ፍቅረ እግዚአብሔር በልቡናችን ውስጥ ሳይኖር ኃጢአትን ብንተው እንኳ ኃጢአት ደግሞ ወደነበርንበት ወደ ራሱ መንግሥት ሊመልሰን መዋጋቱን አይተውም። ምክንያቱም ልቡናችንን ፍጹም በሆነ የንስሐ ሕይወት ሊያኖረንና ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቀን የሚችለው ፍቅር በልቡናችን ውስጥ ስለሌለ ነው። ኃጢአትንና የኃጢአት ምንጭ የሆነውን ዲያብሎስን ማሸነፍ የሚችለው ፍጹም የሆነ ፍቅረ እግዚአብሔር ነው።

በእርግጥ ንስሐን እንደምንሻ የታወቀ ነው። በልባችንም መንፈሳዊውን ሕይወት በመጀመራችን በንስሐ ጉዞ ላይ እንደሆንን ልናስብ እንችላለን:- ነገር ግን ብንጸልይና ብንጾምም በውስጣችን ሥር ከሰደደው የኃጢአት ፍቅር የተላቀቅን መሆኑ አይሰማንም ለምን? ምክንያቱም መንፈሳዊውን የሕይወት ጉዞ በመጀመራችን መንፈሳዊ እርካታም በማግኘታችንና በጽናት በመጾማችን፣ በትጋት በመጸለያችን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበባችን የመንፈሳዊውን ሕይወት ጣዕም በማወቃችን ነው። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፍቅር በልቡናችን በማሳደር ወደ ንስሐ እንድንደርስ ያደርገናል።

በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በንስሐ ሕይወት ያልኖርን እንደሆን መጥፋታችን አይቀርም። ስለዚህ ኃጢአትን ከልቡናችን ፈጽሞ ሊያስወግድልን የሚችለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ገንዘብ ማድረግ ይገባናል። በምንጩ አጠገብ እንሥራችንን ለመጣል ጌታችንን አምላካችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ አለብን። ዮሐ.፲፯። ይህን የእግዚአብሔርን ፍቅር ለማግኘትም በትዕግሥትና በጽናት መጸለይ ይገባናል። በፍጹም ልባችን — በፍጹም ሃሳባችን ሁሉ «አቤቱ ጌታ ሆይ አንተን የማፈቅር አድርገኝ፣ ከልቤም ውስጥ የኃጢአትን ፍቅር አስወግድልኝ:- የአንተን ፍቅርም ስጠኝ» በማለት በጸሎት እግዚአብሔርን ልንጠይቅ ያስፈልጋል። ከዚህም ሌላ ሁል ጊዜ ፍቅረ እግዚአብሔርን በልቡናችን የሚያሳድሩ ነገሮችን ለማድረግ፣ ለማየትና ለመስማት በጽኑ መፈለግ አለብን። ከዚሁ አንፃር ደግሞ የእግዚአብሔርን ፍቅር ከልቡናችን ሊያጠፉብን የሚችሉ ነገሮችን ከእኛ ማራቅና በጽኑ መቃወም ይገባናል።



ስለዚህ ኃጢአትን ከልቡናችን ፈንቅሎ ለጣለልን የእግዚአብሔር ፍቅር ከእኛ የሚጠበቀውን ሁሉ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። የእግዚአብሔር ፍቅር በልቡናችን ውስጥ ባደገ መጠን ልቡናችን ደግሞ ለኃጢአት ያለው ጥላቻ እያደገና እየበረታ ይሄዳል። እግዚአብሔር አምላካችንም ኃጢአትን በጠላን መጠን ፍቅሩን የበለጠ ይጨምርልናል። አምልኮአችንና አገልግሎታችንም ሁሉ በደስታ ይሆናል። የፈጣሪአችንን የእግዚአብሔርን ሕግም ለማክበርና ትእዛዛቱን ለመፈጸምም አይከብደንም። ከዚህም የተነሣ እንደፍቁረ እግዚእ ቅዱስ ዮሐንስ «ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና:- ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም» ብለን ለማመንና ለመመስከር እንችላለን። ፩ዮሐ.፭፥፫። ምክንያቱም በእነዚህ የእግዚአብሔር ሕግጋት ጸንተን ብንኖር ያለአንዳች ችግር ደስተኞች ስለምንሆንና እንዲሁም በልባችን አድሮ የሚፈትነን አንዳችም የሥጋ ፍላጎትና ኃጢአት ስለሌለ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና» በማለት መናገሩ ለዚህ ነው። ሮሜ.፯፥፳፪።

እግዚአብሔርን የሚያፈቅር ሰው ሕግጋቱን በመፈጸሙ ደስተኛ ነው። የእግዚአብሔር ሕግጋት ፍጻሜ የሆነው ፍቅር በልቡናው ያደረ በመሆኑም እግዚአብሔር ከሚደሰትበት በቀር የሚያዝንበትንም ነገር ስለማይሠራ ደስተኛ ነው። ወላጆቹን የሚወድ ሰውም ከእነርሱ በሚያገኘው ምርቃት ተስፋና ደስታ ስላለው እነርሱ የሚከፉበትን ነገር ከቶውኑ አያደርግም። እንዲህ ያለ በፍቅረ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ የቅንነትና የየዋህነት ስሜት ያለው ሰው ያለምንም ችግር ንስሐ ሊገባ ይችላል። በልቡናው ፍቅረ እግዚአብሔር ለሌለው ሰው ንስሐ መግባት ከባድ ሸክምና አስቸጋሪው ነው ምክንያቱም የኃጢአትን ፍቅር ገና ከልቡ ጠርጎ አላስወገደምና። ስለዚህ የንስሐ ሕይወታችንን አስቸጋሪ የሚያደርገውን የኃጢአት ፍቅር ከልቡናችን የሚያስወግደውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ገንዘብ ማድረግ ይኖርብናል። ይህን አማናዊና ፍጹም ፍቅር ያገኘን እንደሆን ንስሐ መግባትና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መፈጸም አይከብደንም።

ንስሐ መግባት የተራራ ያህል ገዝፎ የገደል ያህል አስቸጋሪ ሆኖ የታየን እንደሆን በልቡናችን ያለው የእግዚአብሔር ፍቅር ፍጹም አይደለም ወይም ደግሞ ምንም ፍቅረ እግዚአብሔር የለንም ማለት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ «ጽድቅን የማያደርግ...ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም» ብሏልና። ፩ዮሐ.፫፥፲። በድጋሚም «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም:-...ከእግዚአብሔር የተወለደው ራሱን እንዲጠብቅ ክፉም እንዳይነካው እናውቃለን።» በማለት የእግዚአብሔር ፍቅር ካለን የኃጢአት

www.ethiopianorthodox.org

ተቃራኒ ወደሆነው ሕይወት የሚያደርሰንን ንስሐ መግባትን ልንወደው እንደምንችል ነግሮናል። ፩ዮሐ.፫፥፱። ፩ዮሐ.፭፥፲፰። ከንስሐ ይልቅም የሚከብደንና የሚያስፈራን ኃጢአትን መሥራት ይሆናል። በልባችን ካደረው ጽኑ የእግዚአብሔር ፍቅር የተነሣም «እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» እንላለን። ዘፍ.፴፱፥፱። ኃጢአትን ከጠላን ደግሞ ንስሐን እንወዳለን:- እርሱም የልብ ንጽሕናን ለማግኘት ያበቃናል። የእግዚአብሔር ፍቅር በልቡናችን ያለውን የኃጢአት ፍቅር አውጥቶ እንደሚጥልልን ስንገነዘብ እንዴት አድርገን ወደ ፍቅረ እግዚአብሔር ልንደርስ እንደምንችል እንጨነቅ ይሆናል። ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ሊያደርሱን ከሚችሉት ዋና ዋና መንገዶች መካከል የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው:- እነርሱም:- መላ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር በመስጠት የኖሩ ቅድሳንን ታሪክና ገድላቸውን አዘውትሮ ማንበብ፣ ስለንስሐና ወደ እግዚአብሔር ስለመመለስ የተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍትን መመርመር፣ ሞትን:- የመጨረሻውን ፍርድና የእግዚአብሔርን መንግሥት ማሰብና እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍጹም ፍቅር በማስተዋል ማስታወስ ናቸው። እነዚህም እግዚአብሔር ያደረገልንን ታላቅ ቸርነትና የገለጠልንን ፍጹም ፍቅር እያሰብን እንድንወደው ያደርጉናል። ምክንያቱም እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና። ስለዚህም ለንስሐ የሚያበቃውን ፍቅሩን በልቡናችን እንዲያሳድርልንና አዲስ ልብንም እንዲሰጠን ዘወትር ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት መነጋገርን አጥብቀን መያዝ ያስፈልጋል።

## ፲፪. ከእግዚአብሔር ጋር መታገልና ዕርዳታውን ገንዘብ ማድረግ

ኃጢአታችንን ከእኛ አስወግደን ንስሐ ለመግባት እንፈልግና ይህም ይሳካልን ይሆናል። በዚህ ጊዜ ግን በኃጢአት ላይ ድልን መቀዳጀት ከሰው አለመሆኑን ልናስታውስ ይገባል። ምክንያቱም:-

ሀ. ታላላቆችን ሁሉ ያሸነፈ ኃጢአት ያለአምላካዊ ዕርዳታ በሥጋ ኃይልና ብርታት ሊሸነፍ የሚችል አይደለምና። ምሳ.፯፥፳፮።

ለ. ቀደም ብለን የወደቅንበትና የጣለን ኃጢአት ከሆነ ዛሬም በእኛ ላይ ኃይል አለውና:-

ሐ. ከውስጣችን ካለው የሥጋ ፈቃድ በተጨማሪ ውጊያው ከውጭም የሚሠነዘር በመሆኑ በእጥፍ ኃይለኛ ነውና:-



መ. በመጽሐፍም «እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል» ከመባሉም በላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» በማለት ተናግሯልና። መዝ.፻፳፯፥፩። ዮሐ.፲፭፥፭።

ሠ. የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ሳንሻ በራሳችን ብቻ በምነሠራው ሥራ ብዙ ጊዜ እንወድቃለን። ቢሳካልን እንኳ እኛው በኃይላችን ወይም በጥበባችን እንደአደረግነው በመቁጠር በራሳችን እንመካለን። ትዕቢት ደግሞ ሰይጣንን ያዋረደው በመሆኑ በሥራ ሁሉ የእግዚአብሔርን አጋዥነት መፈለግ መልካም ነውና:-

ረ. ከዚህ በፊት ባሳለፍነው የሕይወት ተሞክሮ በራሳችን ኃይል ንስሐ ለመግባት አለመቻላችንን ዐውቀናል። ብዙ ጊዜም ንስሐ ለመግባት ዝተን አልሆነልንም — በእግዚአብሔር ፊት ቆመንም ‹ይህን ኃጢአት ደግሜ ብሠራው እንዲህ ልሁን› እያልንም ምለናል። በራሳችን ስለተማመንንና የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ስላልፈለግን አልተሳካልንምና ነው።

ስለዚህም «አንተ ግን እግዚአብሔር አምላኬ ነህና መልሰኝ:- እኔም እመለሳለሁ» በማለት የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ደጅ ልንጠና ይገባናል። ኤር.፴፩፥፲፰። እግዚአብሔር ተነሳሒ ልቡና እንዲሰጠን እርሱን መጠየቅ ያስፈልጋል:- እርሱ ራሱ ደግሞ «አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ:- አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ:-...መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ:- በትእዛዜም አስኬዳችኋለሁ።» ሲል ተናግሯልና። ሕዝ.፴፮፥፳፮–፳፯። እርሱ አምላካችን የገባልንን ኪዳን እያሰብን ልቡናችንን ወደ ንስሐ እንዲመልስልን ብንጠይቀው በቃሉ የታመነ ነውና ያደርግልናል:- ተነሳሒ ልብንም ይሰጠናል:- በትእዛዛቱም የምንመራ ያደርገናል። ለዚህም ነው በቤተ ክርስቲያን ጸሎታችን «በንስሐ ሂሶጵ እርጨኝ እነጻማለሁ:- እጠበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ» እያልን የምንጸልየው። መዝ.፶፥፯። ከኃጢአት የሚያጥበንና የሚያነጻን እግዚአብሔር እንጂ እኛ ራሳችንን አጥበን ልናነጻ አንችልምና በዳዊታችን፣ በሠርክና በነግህ ጸሎታችን እንዲሁም በቅዳሴአችን ሁሉ ደጋግመን ‹አቤቱ ጌታችን ሆይ ከክፉ ነገር አንጻን ነፍሳችንንም ከሞተ ኃጢአት አድን› እያልን እንጸልያለን። በዚህም ንስሐ፣ ንጽሕናና ቅድስና ከእግዚአብሔር የሚገኙ፣ በጸሎትም እግዚአብሔር ሊለመንባቸው የሚገቡ እንጂ እንዲሁ ያለእግዚአብሔር ዕርዳታ በራስ ጥረት የሚመጡ አለመሆናቸውን ከቤተ ክርስቲያን

www.ethiopianorthodox.org

እንማራለን። ይህም ወደንስሐ ሕይወት ለመድረስ የሚያስችለው ድልድይ ጸሎት መሆኑን ያስረዳል። ቅዱስ ይስሐቅም «ከጸሎት በቀር ወደ ንስሐ ሊያደርስ የሚችል መንገድ እንዳለ የሚያስብ ማንም ሰው እርሱ በዲያብሎስ የተታለለ ነው።» በማለት የተናገረው ለዚህ ነው።

ስለዚህም ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን ‹የአንተን ዕርዳታ እሻለሁ:- ከአንተ ውጭ ምንም ልሠራ አልችልምና› በማለት ልንለምነው ያስፈልጋል። በፈጣሪአችንም ፊት ቆመን «ፈቃድ አለኝና መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም:- የማልወደውን ክፉ ነገር አደርጋለሁና:- ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም።» ...«እንደ ጠፉ በግ ተቅበዘበዝሁ ትእዛዝህን አልረሳሁምና ባሪያህን ፈልገው።» አንተም «እኔ ራሴ በጎቼን አሠማራለሁ:- አስመስጋቸውማለሁ።...የጠፉውንም እፈልጋለሁ:- የባዘነውንም እመልሳለሁ:- የተሰበረውንም እጠግናለሁ:- የደከመውንም አጸናለሁ።» ያልክ አይደለህምን? ሮሜ.፯፥፲፰–፲፱። መዝ.፻፲፰፥፻፸፮። ሕዝ.፴፬፥፲፭–፲፮። ስለዚህ እኔ የጠፋሁ፣ ሰባራ፣ ደካማና የባዘንኩ ነኝና ፈልገኝ:- መልሰኝ:- አጽናኝ:- አጠንክረኝም:- ደክሜአለሁና ንስሐ ልገባ አልተቻለኝም:- ስለዚህም ለንስሐ የበቃሁ አድርገኝ በማለት እግዚአብሔር ኃይልና ብርታቱን እንዲሰጠን መለመን ያስፈልጋል።

በተጨማሪም እግዚአብሔር አምላካችንን አንተ ከኃጢአት እንድትጠብቀኝ ቃል ገባልኝ:- ደግሞም:- «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ» ብለኸልና አሳርፈኝ። ማቴ.፲፩፥፳፰። ዳግመኛም «የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና» ያልክ አንተ ጠፍቻለሁና አድነኝ። ሉቃ.፲፱፥፲። ከመጨረሻው ቅጣት ብቻ ሳይሆን ከኃጢአትም አድነኝ — «ኢየሱስ» የተባልክ አንተ መድኃኒት ሆነህ ሕዝብህን ለማዳን መጥተኻልና። ማቴ.፩፥፳፩። በመጽሐፍም «ስለድሆች መከራ፣ ስለችግረኞች ጩኸት፣ አሁን እነሣለሁ መድኃኒት አደርጋለሁ:-» ብለኸልና በኃጢአት ደዌ የታመምኩትን እኔን አድነኝ በማለት ልንለምነው ይገባል። መዝ.፲፩፥፭።

የንስሐን ሕይወት ለማግኘት ኃይልን ከሚሰጥ ከእግዚአብሔር ጋር መታገል ያስፈልጋል። አባታችን ቅዱስ ያዕቆብም «ካልባረክኸኝ አልለቅህም» በማለት ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ በረከትን አግኝቷል። ዘፍ.፴፪፥፳፮። እንዲሁ ሁሉ እግዚአብሔር ከኃጢአት እንዲለየንና ከድካማችን እንዲያበረታን:- ለንስሐም እንዲያበቃን ከእርሱ እግር ሥር



ወድቀን በጸሎትና በጾም ልንታገለው ይገባል። ይህም ማለት እርሱ ኃጢአትን የምንጠላበትን፣ ትእዛዛቱን በሥራ ለመተርጐም የምንችልበትን፣ የሰይጣንን ፈተና የምንቋቋምበትን፣ በልቡናችን ውስጥ ያለውን ኃጢአት አውጥቶ የሚጥል ፍጹም ፍቅር የምናገኝበትን፣ እርሱን የምንወድበትን ኃይል እንዲሰጠን አብዝቶ መጸለይ ነው። ከእርሱ ጋር መታገል ማለት በፍጹም ፍቅርና ትህትና በፊቱ ቆሞ ኃይልን ለማግኘት በጽኑ ጸሎት መለመን ነው።

በጽኑ ጸሎት የሚተጋ ሰው ከሰይጣን ፈተና የተነሣ በሚመጣበት ኃጢአት አይወድቅም። ምክንያቱም በነገሩ ሁሉና በሚሠራው ሥራ ውስጥ እግዚአብሔር አለ ውጊያው ሁሉ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርጎ ነውና። ስለዚህ እኛም ዘወትር በምንሠራው ሥራና ከኃጢአት ጋርም በምናደርገው ረቂቅ መንፈሳዊ ውጊያ ሁሉ የእግዚአብሔርን ኃይልና አጋዥነት መከታ ልናደርግ ይገባል እርሱ ሁሉንም ያደርግልናልና። የጸሎት ሰዎች የሆንን እንደሆነም በኤርምያስ «ከአንተ ጋር ይዋጋሉ:- ነገር ግን አድንህ ዘንድ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና ድል አይነሡህም ይላል እግዚአብሔር» ተብሎ እንደ ተጻፈ ድል የሚነሣን ኃጢአት አይኖርም እግዚአብሔር ይዋጋልናልና። ኤር.፩፥፲፱። ደግሞም «በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ ወደ አንተ ግን አይቀርብም» ተብሏል። መዝ.፺፥፯። ስለዚህም «እግዚአብሔር ስለእናንተ ይዋጋል:- እናንተም ዝም ትላላችሁ» በማለት ተነግሯልና እርሱ የውስጡንም የውጭውንም ውጊያ ስለሚዋጋልን የእርሱ ዕርዳታ እጅግ ያስፈልገናል። ዘጸ.፲፬፥፲፬።

ስለዚህ በማንኛውም ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ በሚመጣብን ውጊያ እግዚአብሔርን ከፊት አድርገን «ሰልፉ ለእግዚአብሔር ነው» የሚለውን የቅዱስ ዳዊትን መርሕ መከተል ይገባል። ፩ሳሙ.፲፯፥፵፯። ምክንያቱም «በትንሽ ወይም በብዙ ማዳን እግዚአብሔርን አይቸግረውምና።» ፩ሳሙ.፲፬፥፮። ሕዝቡ ከአማሌቃውያን ጋር ሲዋጉ «በአማሌቅ ላይ የእግዚአብሔር ሰልፍ» ተብሏልና በኃጢአታችን ሁሉ ላይም የእግዚአብሔር ሰልፍ ይሆናል። ዘጸ.፲፯፥፲፮። ከኃጢአታችንና ከሚያታልለን የዓለም አምሮት የሚያድነን እርሱ ነው «እኔ ዓለሙን አሸንፌዋለሁ» በማለት ተናግሯልና። ዮሐ.፲፮፥፴፫። ያለ እግዚአብሔር ዕርዳታ ኃጢአትን ማሸነፍ:- ንስሐም መግባት እንደማይቻል በዚህ ሁሉ እናውቃለን።

www.ethiopianorthodox.org

ስለሆነም እንደ ቅዱስ ዳዊት:- «እግዚአብሔር ግን አገዘኝ:- ኃይሌም ዝማሬዬም በእግዚአብሔር ነው» መዝ.፻፲፯፥፲፬። እንደ ቅዱስ ጳውሎስም «በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።» ሮሜ.፰፥፴፯ በማለት አሸናፊነታችን ሁሉ በእግዚአብሔር ዕርዳታ መሆኑን እንናገራለን። ይህን የሚያብራሩልን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔር «ሁል ጊዜ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ (ሰው በመሆኑና ስለእኛ በመስቀል ላይ በመሞቱ) ድል መንሣትን ይሰጠናል።» ፩ቆሮ.፲፭፥፶፯። ፪ቆሮ.፪፥፲፬። ካለ በኋላ ቀጥሎ ደግሞ «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» በማለት የተናገራቸው ቃላት ናቸው። ፊልጵ.፬፥፲፫። እኛም ይህን እንመሠክራለን።

ስለዚህ ኃጢአትን ለመታገል ከመጀመር አስቀድሞ ኃይል መንፈሳዊን ለማግኘት ከእግዚአብሔር ጋር መታገል ያስፈልጋል:- ኃጢአትን ድል መንሣት የሚቻለው በእግዚአብሔር አጋዥነት ነውና። አባታችን ያዕቆብ ወደ ዔሳው ከመሄድ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ—በረከትንም አገኘ:- ወደዔሣው ዘንድም በሄደ ጊዜ ሁሉ መልካምና ያማረ ሆነለት፤ የጦር አዛዡ ባርቅ ነቢይት ዲቦራን ሳይዝ ወደውጊያ እንዳልሄደ:- መሳ.፬፥፰ ዕርዳታዋንም እንደፈለገ ሁሉ እኛም ጠላታችንን ሰይጣንንና ኃጢአትን እንዴት እንደምንዋጋ የማናውቅና ኃይልም የሌለን ደካሞች ነንና እግዚአብሔርን አንተ ተዋጋለን:- ኃጢአትን ድል ነሥተን ወደንስሐ እንድንመጣ እርዳን ብለን መለመንና እርሱን ረዳታችን ማድረግ ይኖርብናል። «አቤቱ ከእሳት እንደተነጠቀው ትንታግ እንደ ኢያሱ» እኛንም ከኃጢአት ትንታግ ነጥቀህ አውጣን ልንለው ያስፈልጋል። ዘካ.፫፥፪። ኢያሱን ለማዳንና ለንስሐም ለማብቃት የእግዚአብሔር መልአክ ከሰይጣን ጋር እንደተዋጋ — ለእኛም ይዋጋልን ዘንድ እግዚአብሔር ተራዳኢ መልአኩን እንዲልክልን መለመን አለብን።

ብዙ ጊዜ በመደጋገም የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ለማግኘት ጸልየን ንስሐ ለመግባት አልቻልን ይሆናል። ልናስተውለው የሚገባን እውነታ የምንጸልየው ጸሎት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ከተስማማ ያለጥርጥር መልስ የምናገኝ መሆኑን ነው። ብዙ ጊዜ ጸልየን መልስ ካላገኘን ግን:-



ሀ. ምናልባት የጸለይነው ንስሐን ከልብ በመፈለግ ላይሆን ይችላል:- ወይም

ለ. ምናልባት ለጸሎት በምንቆምበት ጊዜ ጽናት የሌለንና ወዲያው የምንሰለች ሆነን ይሆናል:- ኤልያስ የሚፈልገውን እስኪያገኝ ድረስ አልሰለቸም — በሰባተኛው ጊዜም አገኘ:- ፩ነገ.፲፰፥፵፬። ያዕቆብ እስኪባረክ ታገለ—ተባረከም። ዘፍ.፴፪፥፳፬።

ሐ. ምናልባት የምንጸልየው ጸሎት ያለእምነትና ያለመፀፀት ይሆናል:-

መ. ምናልባት ለጸለይነው ጸሎት ፈጣን ምላሽ ቢሰጠን እኛን የማይጠቅመን ሊሆን ይችላል:- ምክንያቱም ቅዱስ ባስልዮስ እንዳለው — «እግዚአብሔር ወዲያው ያገኘነውን ነገር እንደም ናቃልለው ስለሚያውቅ ጥያቄአችንን ሳይመልስ ሊዘገይ ይችላል። የኃጢአትን መራራነት እንድናውቅና ዳግመኛም እንዳንመለስበት ለማድረግም ዝም ሊለን ይችላል።»

ሠ. ምናልባትም እግዚአብሔር ምን ያህል ንስሐን እንደምንፈልገው ለማወቅና በጥያቄአችን የቱን ያህል እንደምንጸና ሊፈትነን:- ሲል ሊዘገይ ይችላል።

ረ. ምናልባትም መልሱ ለመዘግየቱ ራሳችን ምክንያት ልንሆን እንችላለን። በአንደበታችን ተናግረን እንጠይቅና በልባችን ግን ንስሐን የማንፈልግ ልንሆን እንችላለን:- በመጽሐፍም «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት...ልባችሁን እልከኛ አታድርጉት» በማለት የተነገረውን በመዘንጋት ንስሐችንን ልናዘገየው እንችል ይሆናል።

ስለዚህ እኛ ራሳችን ተዘናግተንና እያንቀላፋን ሳለ እግዚአብሔርን ዕርዳን ብለን መጠየቅ የለብንም። እኛ እየሠራን የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ልንጠይቅ እንጂ እኛ ተኝተን እግዚአብሔር እንዲሠራልን መጠየቅ አይገባንም። መጀመሪያ መሻቱ ሊኖረን:- ከዚያም የእግዚአብሔር ዕርዳታ እንደሚያስፈልገን ልናምን:- በመጨረሻም የአቅማችንን ያህል በመሥራት እግዚአብሔርም ከእኛ ጋር እንዲሠራ መለመን ያስፈልገናል።

ምናልባትም ደግሞ አቅማችን ውሱን ሆኖ ምንም ማድረግና መሥራት ባንችል — ምንም ባለመሥራታችን ተስፋ መቁረጥ የለብንም። ጌታችን ምንም ለመሥራት ያልቻሉትን ረድቶ አድኗቸዋልና። ደም ይፈሳት

www.ethiopianorthodox.org

የነበረችውን ሴት:- እጁ የሰለለውን ሰው:- ዕውሩን ሰው ዮሐ.፱፥፯። በጣራ የገባውን በሽተኛ –ማር.፪፥፬። በመንገድ የወደቀውን ሰው – ሉቃ.፲፥፴። መጻጉዕን – ዮሐ.፭፥፭። ሁሉንም እርሱ ረድቶ አድኗቸዋል። እርሱ ሙታንን እንኳ አንሥቷል። ኃጢአተኛም ስለመተላለፉ የሞተ ነው። ኤፌ.፪፩፥፭። በሥጋው ሕያው ነው ሲባል በነፍሱ ግን የሞተ ነው። ራእ.፫፥፪። እንግዲህ አምላካችን እግዚአብሔር የሞተውን የሚያነሣ ከሆነ መሥራት አልቻልንም ብለን ተስፋ መቁረጥና መረበሽም አይገባንም። እርሱ የመጣው–ሰው የሆነውና በመስቀል ተሰቅሎ የሞተው የኃጢአተኞችን ድኅነት ሽቶ ነው። ወደ እርሱ መመለስ የቻሉት የጠፋውን ልጅ ይመስላሉ:- መመለስ ያልቻሉት ደግሞ የጠፋውን በግና የጠፋውን ድሪም ይመስላሉ። ሉቃ.፲፭።

እኛ ስለድኅነታችን ባንጠይቅ እንኳ ሌሎች ሰዎች ስለእኛ ባቀረቡት ጥያቄ ሊያድኑን ይችላልና ተስፋ መቁረጥ የለብንም። ሎጥ የዳነው በራሱ ጥያቄ ሳይሆን በአብርሃም ምልጃ ነው። ዘፍ.፲፱፥፲፭–፲፮። ስለእነዚህ ያሰበና ያዳናቸው እግዚአብሔር ለእኛም ደግሞ ያስብልናል። ተነሳሒ ልቡናም ይሰጠናል ወደእርሱም ይመራናል። አዲስም ልብ ይሰጠናል። ሕዝ.፴፮፥፳፮።

ክፍል አራት

# የንስሐ ምልክቶች

መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ።» ...«ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ» እያለ በበረሃ ይሰብክ ነበር። ማቴ.፫፥፪። ማቴ.፫፥፰። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ንስሐ ትገቡ ዘንድ ለንስሐ የሚገባ ነገር አድርጉ:- ወደ እግዚአብሔርም ዘወር በሉ» እያለ ወንጌልን ለአሕዛብ ይሰብክ ነበር። የሐዋ.፳፮፥፳። ስለዚህ ንስሐ የልቡና ብቻ ሥራ አይደለም:- ምክንያቱም ሌሎች ለንስሐ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ተግባራትና ንስሐን የሚያመለክቱ ምልክቶች ስላሉ ነው። መጽሐፍ የእግዚአብሔር የሆኑትን «ከፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ» እንዳለው የንስሐን ሕይወት የሚኖሩም እንዲሁ በመንፈሳዊ ኑሮአቸው በሚያሳዩት ፍሬ ይታወቃሉ። ማቴ.፯፥፲፮፣፳። እነዚህ የንስሐ ምልክቶችም ቀጥሎ በየተራ የምንመለከታቸው ናቸው።

## ፩. ኃጢአትን መናዘዝ

ኑዛዜ አራት ዋና ዋና ነጥቦችን ያጠቃልላል። እነርሱም:-

ሀ. ኃጢአትን ለራስ ኀሊና መናዘዝ:-

ይህ ዝቅ ብለን ከምንጠቅሳቸው ሁሉ የሚቀድም ነው። በመጀመሪያ ኃጢአት የሠራን መሆኑን ኀሊናችን ሳያውቀውና መበደሉን ሳያምን ለእግዚአብሔርና ለካህኑ ለመናዘዝ እንዴት ይቻላል? ስለሠራነው ኃጢአት ጥልቅ የሆነ ኀዘን ሊሰማን ይገባል። እንደበደልን ካላመንንና በበደላችን ካላዘንን በኃጢአታችን ላይ ልንናዘዝና ንስሐም ልንገባ አንችልም። ስለዚህ ስለበደላችን ሰዎች በእኛ ላይ ከመፍረዳቸው በፊት እኛ በራሳችን ላይ ልንፈርድ ይገባናል። ስለሠራው ኃጢአትና ስለፈጸመው በደል ራሱን በራሱ ከሚተችና ከሚከስስ ሰው የበለጠ ታላቅ ሰው የለም። በልባችን ራሳችንን የኰነንን እንደሆን በእግዚአብሔርና አገልጋዩ በሆነ በካህኑ ፊት ራሳችንን ለመክሰስ አንቸገርም።

www.ethiopianorthodox.org

ለ. በጸሎት በደልን ለእግዚአብሔር መናዘዝ:-

ለዚህ ዋናው ምክንያት ኃጢአትን መሥራት በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔርን መበደል ስለሆነ ነው። ቅዱስ ዳዊትም በኃጢአት በወደቀ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ «አንተን ብቻ በደልሁ» ያለው:- ዳንኤልም «አምላክ ሆይ ኃጢአትን ሠርተናል:- በድለንማል:- ክፋትንም አድርገናል:- አምፀንማል:- ከትእዛዝህና ከፍርድህም ፈቀቅ ብለናል» ማለቱ:- ነህምያ ደግሞ «እኔና የአባቴም ቤት በድለናል:- እኛም በአንተ ላይ ሠርተናል።» በማለት መናገሩ:- ዕዝራም «አምላክ ሆይ ኃጢአታችን በራሳችን ላይ በዝቷልና።» ሲል መናገሩ ስለዚህ ነው። መዝ.፶። ዳን.፱፥፭። ነህ.፩፥፮-፯። ዕዝ.፱፥፮። ኃጢአትን መሥራታችን በእርሱ ላይ በማመፃችን በመሆኑ:- የሚወደንን እርሱን:- የቅዱስ መንፈሱ ማደሪያዎችና ቤተ መቅደሶቹ ያደረገንን እርሱን በመበደላችን የመጀመሪያ ኑዛዜአችን ወደ እግዚአብሔር መሆን አለበት። በእርሱ ፊት ኃጢአትን በመሥራታችን ልናዝንና ልንፀፀት ይህንንም ፍጹም በተሰበረ ልብ ልንነግረው ይገባናል።

ሐ. በደልን ለካህን መናዘዝ:-

ይህ መሆን ያለበት ካህኑ የእግዚአብሔር እንደራሴና አገልጋይ ስለሆነ ነው። በካህኑ ፊት የሚናዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ይናዘዛል። ነቢየ እግዚአብሔር ኢያሱ አካንን – ልጄ ሆይ ለእሥራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ክብርን ስጥ:- ለእርሱም ተናዘዝ:- ያደረግኸውንም ንገረኝ:- አትሸሽገኝ።» ማለቱ ለዚህ ማረጋገጫ ነው። ኢያ.፯፥፲፱። በሐዲስ ኪዳንም ሆነ በብሉይ ኪዳን ለካህን መናዘዝ የታወቀና የነበረ ያለም ነው። ወደመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ የመጡ ሁሉ ንስሐ እየገቡ ተጠምቀዋል። ማቴ.፫፥፮። በብሉይ ኪዳንም ኃጢአትን የሠሩ ኃጢአታቸውን ተናዝዘው የኃጢአት ማስተሥረያ ማቅረብ ነበረባቸው። ዘሌ.፭፥፭-፮። በሐዲስ ኪዳንም በወንጌል ያመኑ ብዙ ሰዎች ኃጢአታቸውን ይናዘዙ ነበር። የሐዋ.፲፱፥፲፰።

ተነሳሒው የሠራውን ኃጢአት ለካህኑ በመናዘዝ የንጽሕና ማረጋገጫና ሥጋወደሙን ለመቀበል የሚያስችለውን ፈቃድ ያገኛል። የሠራውን ኃጢአት በካህኑ ፊት የገለጠና የተናዘዘ ሰው ዳግመኛ ያንን ኃጢአት እንዳይሠራ የሚያደርገው መንፈሳዊ ኃይልና በረከት ያገኛል። ኑዛዜና ንስሐ ስለማይነጣጠሉና ንስሐ ደግሞ ኃጢአትን መጥላት በመሆኑ የቀደመ ኃጢአቱን አይሠራም። ስለዚህም መናዘዝ የንስሐ አንዱ ምልክት ነው።



ተነሣሒው ሰው በአንደበቱ የቀደመ ኃጢአቱን ለካህኑ መናገሩ ወይም መናዘዙ ብቻ የንስሐ ምልክት ሊሆን አይችልም:- ነገር ግን ሥለሠራው ኃጢአት ከልቡ ማዘንና ማልቀስ – ስለበደሉም መቀጣት እንደሚገባው በማመን የተናዘዘ እንደሆነ ነው።

መ. ኃጢአትን ለበደሉት ሰው መናዘዝ

ይህን ማድረግ የራስን ልብ ለማስተካከልና ለማረጋጋት – ከተበደለው ሰው ጋራም እርቅን ለመመሥረት ይጠቅማል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «በመሠዊያው ፊት መባህን አስቀምጠህ ሂድ:- አስቀድመህ ከወንድምህ ታረቅ:- ከዚያ በኋላ መሥዋዕትህን ታቀርባለህ።» በማለት ማስተማሩ ስለዚህ ነው። ማቴ.፭፥፳፬። በመሆኑም ወደበደልነው ሰው በመሄድ ‹በድዬኻለሁና ይቅርታ አድርግልኝ» ልንለው ይገባል። ይህን የምናደርገው በመጽሐፍ ሰባ ጊዜ ሰባ ብንበድለው እንኳ ይቅር እንዲል ስለታዘዘ – ይቅር ይለናልና ነው። ሉቃ.፲፯፥፬።

ስለሠራው ኃጢአት በራሱ ለመፍረድ ያልቻለ ማንም ሰው ንስሐ ሊገባ አይችልም። ወደመቅደስ ሄዶ «አምላክ ሆይ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን እየደቃ» ቀራጩ የጸለየው ጸሎትና:- «ራሱን የሚያዋርድ ከፍ ይላል» በማለት ጌታ የተናገረው ቃል ይህን የሚያረጋግጡ ናቸው። ሉቃ.፲፰፥፲፫-፲፬። እንዲህ ሁሉ በራሱ ላይ ከመፍረድ ባሻገር በሠራው ኃጢአት ላይ የማይናዘዝ ሰውም ንስሐ ለመግባት አይችልም። ነቢዩ ዳዊት ኃጢአቱን ባልተረዳበት ጊዜ ንስሐ ለመግባት አላሰበም ነበር:- ነገር ግን እግዚአብሔርንና ሰውን መበደሉ በነቢዩ ናታን በተነገረው ጊዜ ንስሐ ገብቷል። ፪ሳሙ.፲፪፥፲፫። ኢዮብም በራሱ ዓይን ራሱን ጻድቅ አድርጎ ከመመጻደቅ በቀር በደሉን አላወቀም ንስሐም አልገባም ነበር። ኢዮ.፲፥፯፤ ፳፫፥፲፤ ፴፪፥፩። እግዚአብሔር ኃጢአቱን ባሳወቀው ጊዜ ግን ተፀፅቶ ንስሐ ገብቷል። ኢዮ.፵፥፬፤ ፵፪፥፫።

ሰው ኃጢአቱን እንዳይናዘዝና ንስሐም እንዳይገባ የሚያደርጉት ሁለት ታላላቅ ምክንያቶች:-

ሀ. ኃጢአትን በተለያዩ ሁኔታዎችና ምክንያቶች መሸፋፈንና ማካካስ:- እና

ለ. ራስን ጻድቅ አድርጎ መመጻደቅ ናቸው። ስለሠራው ኃጢአት በተለያዩ ሁኔታዎች የሚያመካኝ፣ መሰናከል የሚደረድር፣ ወይም ቤተክርስቲያንን አላስተማረችኝም የሚል:- ወይም እግዚአብሔር አልረዳኝም ወዘተ የሚል ሰው ኃጢአቱን አይናዘዝም:- ንስሐም አይገባም።

www.ethiopianorthodox.org

በእውነት ንስሐ የሚገባ ሰው ግን በማንም ላይ አያመካኝም:- ስለኃጢአቱ ራሱን ይከሳል እንጂ። «ስለአደረግነው የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው።» በማለት እንደተናገረው ፈያታዊ ዘየማን። ሉቃ.፳፫፥፵፩። ምክንያት መደርደርና ማካካሻ መስጠት ኃጢአትን በመሸፋፈን ቅጣትን ለመቀነስና ለማቅለል መጣር ነው። ራስን በማጽደቅ መመጻደቅ ግን በጣም አደገኛ ነው። ኃጢአት እንደሌለና ፈጽሞ እንዳልተሠራ ያስቆጥራልና። ማመካኘት ኃጢአት መኖሩን ተናግሮ ከቅጣቱ መሸሽ ነው። ራሱን የሚያጸድቀው ግን ከቶውኑ ኃጢአት እንደሠራ አያስብም። ለዚህ ነው ጌታችን ፈሪሳዊውን ሰው የገሠፀው። «ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳልና።» ሉቃ.፲፰፥፲፬። «ኃጢአተኞችን ወደንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና።» ማቴ.፱፥፲፫። በማለት መናገሩ ራሳቸውን ንጹሐን አድርገው የሚቆጥሩ ንስሐ የማይገቡ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነው። ራሳቸውን ጻድቅ እንደሆኑ በሚቆጥሩ:- «ራሱን ጻድቅ የሚያደርግ በጽድቁ ይጠፋል» የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይፈርድባቸዋል። መክ.፯፥፲፮። እነዚህ ሰዎች ፈጽመው ከንስሐ የራቁ ናቸው ስለኃጢአታቸውም ሲነገራቸው አያምኑም:- ይከራከራሉ እንጂ – እናም ንስሐ አይገቡም። በመጽሐፍ እንደ ተነገረ «ንስሐ እንደማያስፈልጋቸው ዘጠና ዘጠኙ ጻድቃን» ራሳቸውን በሚቆጥሩ በእነዚህ፣ሳይሆን «ንስሐ በሚገባ አንድ ሰው» ኃጢአቱን በሚናዘዝ በእርሱ የተነሣ «በሰማይ ታላቅ ደስታ ይሆናል።» ሉቃ.፲፭፥፯።

በምናውቀውና በሠራነው በየጊዜውም በተለያዩ ሁኔታዎች በምናስታውሰው ኃጢአታችን ሁሉ ላይ ልንናዘዝና ንስሐ ልንገባ ያስፈልጋል። በዚህም የንስሐ ሕይወታችንን እናጎለምሳለን:- ንስሐን እንደመድኃኒተ ነፍስ በመቁጠርም ኃጢአትንና ውጤቱን እንጠላዋለን። ያለንበትንም የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃ በእርግጠኛነት ልናውቅ እንችላለን።

በደሉን በመናዘዝ ሰው ይቅርታ ሊደረግለት የሚገባና ይቅርታን ለማግኘት የበቃ ይሆናል። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን:- እውነትም በእኛ ውስጥ የለም:- በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው» በማለት ይህንኑ አረጋግጦልናል። ፩ዮሐ.፩፥፰–፱።



መናዘዝ ማለት ኃጢአት ሠርቻለሁ ወይም በድያለሁ ብሎ መናገር ብቻ አይደለም። ምክንያቱም አካን ዕድሉን ከአጣ በኋላ በግድ ሲያዝ በድያለሁ ብሎ ቢናገርም ይቅርታን አላገኘም:- ሕዝቡ ሁሉ ወገሩት እንጂ። ኢያ.፯፥፳። የአስቆሮቱ ይሁዳም «በድያለሁ» ብሎ ተናግሮ ነበር። ንስሐ በመግባት ፈንታ ግን ታንቆ ሞተ። ማቴ.፯፥፬። ፈርዖንም ከልቡ ሳይሆን በብልጠት በምላሱ ብቻ «በድያለሁ» አለ። ነገር ግን በባሕረ ኤርትራ ከመስጠምና ከመጥፋት አልዳነም። ዘጸ.፱፥፳፯። ዘጸ.፲፥፲፮። ስለዚህ ኃጢአትን ሠርቻለሁ ብሎ ከመናገርና በደልን ከመግለጥ ጋራ የልቡና መለወጥ መኖሩ ኑዛዜን ፍጹም ያደርገዋልና ኑዛዜአችን ልባዊ መሆን ይገባዋል።

በእርግጥም ትክክለኛ ኑዛዜ የሚባለው ከእውነተኛ ንስሐና ፀፀት የመነጨ እንደሆነ ነው። ልባዊ የሆነ ፀፀት የሌለበት ንስሐም ለማንም አይጠቅምም። ስለዚህ በሩ ሳይዘጋብን ራሳችንን በማስመርመር በኃጢአታችን ልንናዘዝና ንስሐም ልንገባ ያስፈልጋል።

## ፪. ስለሠሩት ኃጢአት መጨነቅና ማፈር

ሰው የኃጢአትን መጥፎነትና የሚያስከትለውንም አስፈሪ ውጤት ባወቀ ጊዜ ስለሠራው ኃጢአት ይጨነቃል ያፍራልም። ይህም ለዚህ ሰው ወደንስሐ መምጣት መግለጫ ምልክት ነው። ይህ ሰው ራሱን በእጅጉ ይኰንናል። ዘወትር በፊቱ በሆነውና በኀሊናው በሚመላለሰው ኃጢአቱ ያፍራል። «ኃጢአቴ ሁል ጊዜ በፊቴ ነውና» ሲል ቅዱስ ዳዊት እንደተናገረው። መዝ.፶፥፫። ከዚህም የተነሣ ኃጢአትን ዳግመኛ እንዳያያት – እንዳይሠራትም ፊቱንና ዓይኖቹን ይሸፍናል ወይም ራሱን ይቆጣጠራል። ከእፍረቱም የተነሣ ቀና ብሎ ለማየት ዓይኖቹን ወደ እግዚአብሔር አያነሣም። እንደ ቀራጩ አንገቱን ይደፋል። ሉቃ.፲፰፥፲፫። አንገቱን ይድፋ እንጂ ደረቱን እየደቃ ምሕረትን ይጠይቃል – የጠፋው ልጅ «ልጅህ እባል ዘንድ አይገባኝም» እንዳለ። ሉቃ.፲፭፥፲፱። ሁል ጊዜም ኃጢአቱን እያስታወሰ ባለቅኔው እንዳለው «ጕስቁልናዬ ሁልጊዜ በፊቴ ነው:- የፊቴም እፍረት ሸፈነኝ» በማለት ይጸልያል። መዝ.፴፯፥፲፯። እንደዳንኤልም «አምላክ ሆይ ጽድቅ ለአንተ ነው:- ለእኛም የፊት እፍረት ነው» በማለት ያለቅሳል። ዳን.፱፥፯። በሠራው ኃጢአት የተነሣ ጸጋውን በመገፈፉ ተጋልጧልና:- ንጽሕናውን በማጣቱ ረክሷልና:- ጽናቱን በማጣቱ ተማርኳልና ያፍራል።

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ፍቅርና የእራሱን ኃጢአት:- የእግዚአብሔርን ቅድስናና የእራሱን ርኵሰት እያሰበ ያፍራል። ንስሐ እስከገባበት ድረስ የተደረገለትን የእግዚአብሔርን ትዕግሥትና የእራሱን በደል እያሰበ ይጨነቃል—ያፍራል። ስለእርሱ የሚያማልዱትን ቅዱሳንን:- የሚጸልዩለት ወገኖቹንና የሚጨነቁለትን ዘመዶቹን ሁሉ እያሰበ በሠራው ኃጢአት ያፍራል። በእርሱ መውደቅ የሚደሰቱትን ጠላቶቹንም እያሰበ ስለእነርሱ ያፍራል። በቤተ ክርስቲያንና በቅድስናዋ:- በታቦቱ ፊት:- በሥጋውና በደሙ ፊት ከእፍረቱ የተነሣ ይጨነቃል – ይሸማቀቃል። በጸሎቱ ጊዜ ከእግዚአብሔር ፍቅር መለየቱን እያሰበ ይጨነቃል። በእግዚአብሔር ፊት ከመበደሉ በፊት የገባውን ቃል እያሰበ ይሸማቀቃል። በራሱ ዘንድም ማንነቱን ኢምንት አድርጎ ይቆጥራል።

ካለፈው ሕይወቱ የተነሣም በኃጢአት በመኖሩ መዋረዱን ያስባል። በኃጢአት የተነሣ እንደተዋረደ ማወቁ ራሱ ጤናማ የንስሐ ምልክት ነው። ይህም የልቡና ንጽሕናን ያሳያል:- ኃጢአትን ሲሠራት እንዳልተደሰተባት ሁሉ ይጠላታልና – እንደአዋረደችውም ይንቃታል።

አንዳንድ በኃጢአታቸው የተነሣ እፍረት የማይሰማቸውና በእግዚአ ብሔር ዘንድ መዋረዳቸውን የማያስተውሉ:- ነገር ግን ከዚህ ራሳቸውን ለመደበቅ የሚሹ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰይጣን በኃጢአት መኖርን እንዲወዱ በንስሐ ሕይወትም እንዳይጠቀሙ ተስፋ ያስቆረጣቸው ናቸው።

## ፫. መፀፀት:- መከራን መቀበልና ዕንባ

ከኃጢአት የተነሣ መከራ መቀበል የእውነተኛ ንስሐ አንዱ ምልክት ነው። ቅዱስ ዳዊትም «አጥንቶቼ ታውከዋልና ፈውሰኝ:- ነፍሴም እጅግ ታወከች።» በማለት ዘምሯል። መዝ.፮፥፪–፫። ጌታችንም ስለእኛ ኃጢአት እኛ ልንቀበለው የሚገባውን መከራ ስለእኛ ራሱን ለውጦ ተቀብሎታል። እኛ ደግሞ የክርስቶስ የመከራው ተካፋዮች ልንሆን ያስፈልጋል። ፊል.፫፥፲። ተነሳሒው ሰው ስለሠራው ኃጢአት የሚቀበለው መከራ ቀደም ብሎ ከኃጢአቱ ስለአገኘው ደስታ ማካካሻ ነው:- ይህም ስለኃጢአቱ የሚሰጠው ቅጣት ነው።

ንስሐ የሚገባ ሰው ሁለት ዓይነት ቅጣቶች ይቀበላል። የመጀመሪያው የሚወደውን ዓለም በመናቅ – የሚወደውንም ነገር በመተው በራሱ ላይ የሚወስነው ቅጣት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከውጭ የሚመጣ ቅጣት ነው:-



ይህም ስለተሠራው ኃጢአት እግዚአብሔር የሚያመጣው ወይም ኀብረተ ሰቡ የሚያመጣው ቅጣት ነው። ተነሳሒው ሰው እነዚህን ቅጣቶች ያንሱኛል እንጂ በዝተውብኛል በማለት ሳያንጐራጕር በአኮቴት ይቀበላቸዋል። ያለአግባቡ እንኳ ቢቀጣ ይቀበላል እንጂ አይቃወምም። ዳዊትም ያለአግባብ በሕዝብ ፊት በተረገመ ጊዜ «እግዚአብሔር አዝዞታል» አለ እንጂ አልተቃወመም ነበር። ፪ሳሙ.፲፮፥፭–፲።

በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ስለኃጢአታቸው የሚሰጣቸውን ቅጣት ለመቀበል ራሳቸውን ያላዘጋጁ ሰዎች ከንስሐ እጅግ የራቁ ናቸው። በተቃራኒው ግን ንስሐ የሚገቡ ሰዎች ስለኃጢአታቸው በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት የሚመጣባቸውን ቅጣት በፈቃደኛነት ይቀበሉታል። መከራ ወይም ቅጣት የኃጢአት ቀጥተኛ ውጤትና ዋጋውም በመሆኑ እንደ አዳምና ሔዋን ሁሉ ኃጢአት ከሠራን ከመከራው ልናመልጥ አንችልም። ዘፍ.፫፥፲፮–፲፯።

ከኃጢአት የተነሣ የሚሰጠው ቅጣት በረዘመ መጠን የተነሳሒው ልብ ንጹሕ እየሆነ ይሄዳል። ለብዙ ጊዜ የተዘፈዘፈ ልብስ እንዲጠራ። ወዲያው ይቅርታን ያገኘ ሰው ወደ ኃጢአት ለመመለስ ጊዜ አይፈጅበትም የኃጢአትን መራራ ውጤት አልቀመሰምና።

አንዳንድ የዋሆች እንደሚያስቡት ክርስቶስ ስለእኔ መከራውን ሁሉ ተቀብሎልኛልና እኔ ማረፍ እንጂ ንስሐ መግባት አይገባኝም በማለት ራስን ማሞኘት አይገባም። እሥራኤል የበሰለውን ሥጋ ከመራራ ቅጠል ጋር እንዲበሉ ታዝዘው ነበር። ዘጸ.፲፪፥፰። ስለዚህ የክርስቶስ ተከታዮች የሆንን ሁሉ ንስሐ በመግባት ስለሠራነው ኃጢአት በምንቀበለው ቅጣትና መከራ የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች ልንሆን ይገባል። እንደቀሬናዊው ስምዖን መስቀሉን መሸከም ያስፈልጋል። ሉቃ.፳፫፥፳፮። ወይም ደግሞ እንደቅዱስ ጳውሎስ ከእርሱ ጋር እንገደላለን ማለት አለብን። ገላ.፪፥፳።

ዕንባ:- በዚህ መጽሐፍ የምንነጋገረው ሰው ስለኃጢአቱ የሚያለቅሰውን ለቅሶና የሚያፈሰውን ዕንባ ይመለከታል። ወጣንያን ስለኃጢአታቸው ማልቀስ ላይጠበቅባቸው ይችላል:- ወጣንያንም ስለኃጢአታቸው ያለቅሳሉ ብለን እንደመስፈርት ማሰብ የለብንም። ይህ የታላላቅ ገዳማውያንና የቅዱሳን አባቶች ሀብት ነውና።

በኃጢአታቸው ላይ ከአለቀሱት አባቶች መካከል በዋነኛነት ልንጠቅሰው የምንችለው ነቢዩ ቅዱስ ዳዊትን ነው። እርሱ «ሌሊቱን ሁሉ

www.ethiopianorthodox.org

አልጋዬን አጥባለሁ:- በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ።» በማለት ከመናገሩም ሌላ «ዕንባዬ በቀንና በሌሊት ምግብ ሆነኝ» ብሏል። ከዚህም ሌላ ምግብ ሲመገብ እንኳ «አመድን እንደእህል ቅሜአለሁና:- መጠጤንም ከዕንባዬ ጋር ቀላቅያለሁና።» በማለት ዘወትር በዕንባ ይኖር ነበር። መዝ.፮፥፮። መዝ.፵፩፥፫። መዝ.፻፩፥፱። እርሱ ከነበረው ክብር አንፃር ማልቀስ የማይገባው ቢሆንም የዕንባ ሰው ነበር።

እርሱ የእሥራኤል ንጉሥ፣ የጦር መሪ፣ አስተዳዳሪ ሲሆን በዚህ ሳይኮራ ፈጣሪውን «አቤቱ ጌታዬ ሆይ ልቅሶዬን ስማ» እንዲሁም ደግሞ «ዕንባዬን እንደ ትእዛዝህ በፊትህ አኑር» በማለት ይጸልይ ነበር። መዝ.፴፰፥፲፪። መዝ.፶፭፥፰። ከዚህ የዕንባ ጎርፍ በኋላም ይቅርታን አግኝቷል። ፪ሳሙ.፲፪፥፲፫።

ባርያ ወይም አገልጋይ ባጠፋው ጥፋት የተነሣ የሚቀጣውን ቅጣት እያሰበ ሊያለቅስ ይችላል። ልጅ ደግሞ አባቱን በማሳዘኑ ከልቡ በመፀፀት ሊያለቅስ ይችላል። ስለኃጢአታቸው የሚያለቅሱ ተነሳሕያንም እንዲህ ናቸው። ቅዱሳኑ ዘወትር ስለኃጢአት ማልቀስን ሥርዓታቸው ከአደረጉት:- ኃጢአታችን ከብዛቱ የተነሣ ተቆጥሮ የማያልቀው እኛማ እንዴት ማልቀስ ይኖርብን ይሆን። እንዴት ያለ ዕንባ እናፈስስ ይሆን? ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታውን መካዱን ባመነና በሠራው ሥራ ባዘነ ጊዜ «ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ።» ማቴ.፳፮፥፸፭። እኛም ኃጢአታችንን እያሰብን በመረረ ዕንባ ልናለቅስ ይገባል።

ዕንባ የተሰበረ ልብና የንጹሕ ኅሊና ፍሬ ነው። ቅዱሳን እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ፍቅር እርሱንም መበደላቸውንም እያሰቡ ዘወትር ያለቅሳሉ። ቤተ ክርስቲያንም ስለኃጢአታችን በየቀኑ እንድናለቅስ በጽኑ ታስተምራለች። በምንጸልይበት ጊዜም በእንባዋ የክርስቶስን እግር እንደአጠበችው ሴት የንስሐን ዕንባ ስጠን እያልን ልናለቅስ ያስፈልጋል። ሉቃ.፯፥፴፮–፶።

ስለበደልነው በደል ዕንባችንን እያፈሰስን ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ዕንባችን ለእግዚአብሔር ያለን የንጹሕ ፍቅር ምልክት ይሆናል። ዕንባን ለማፍሰስ የታደለ ገር ልብ ነው። ጨካኝ ልብ ስለኃጢአት ማልቀስ አይችልም። ገርና የተሰበረ ልብ ንስሐ ለመግባት አይቸገርም። በኃጢአቱ ላይ በደሉን እያሰበ የሚያለቅስ ሰው ወደቀደመ ኃጢአቱ በቀላሉ አይመለስም። የኃጢአትን ውጤትና መከራ በሚገባ ቀምሷልና። እግዚአብሔርም ሁል ጊዜ ለንስሐ ዕንባ እንድንበቃ ይጋብዘናል። ለዚህ ነው



በነቢዩ ኢዮኤል «በፍጹም ልባችሁ:- በጾምም:- በልቅሶና በዋይታ ወደእኔ ተመለሱ:- ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ። አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ...ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ።» በማለት የሚመክረው። ኢዩ.፪፥፲፪። ከዚህም ሌላ በሚልክያስም «የእግዚአብሔርን መሰዊያ በዕንባና ብልቅሶ በኀዘንም ትከድናላችሁ።» ብሏል። ሚል.፪፥፲፫። በወንጌልም «እናንተ አሁን የምታለቅሱ ብፁዓን ናችሁ።» «የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው መጽናናትን ያገኛሉ» ሉቃ.፮፥፳፩። ማቴ.፭፥፬። ተብሏልና ስለኃጢአታችን ብናለቅስ «እግዚአብሔር የልቅሶዬን ቃል ሰምቷልና እግዚአብሔር ልመናዬን ሰማኝ» በማለት ቅዱስ ዳዊት የተናገረው ይሆንልናል። መዝ.፮፥፰።

ዕንባ የንስሐ ምልክት ነውና እግዚአብሔርም ከንስሐ የተነሣ ለሚፈስ ዕንባ መልስ ይሰጣል። ዕንባ የእግዚአብሔር ጆሮዎች ብቻ የሚሰሙት ድምፅ አለው። ለዚህ ነው ቅዱስ ዳዊት «በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ያጭዳሉ።» ያለው። መዝ.፻፳፭፥፭።

ምናልባት ዕንባችን የሚፈስ ከሆነ ስለኃጢአት በማዘን የሚፈስ ዕንባ ወይም በመመጻደቅ የሚፈስ ዕንባ ስለመሆኑ መመርመር ይገባናል። የሚፈሰው ዕንባችን ምንጩ ወይም ምክንያቱ የሠራነው ኃጢአት መሆኑን ማረጋገጥ አለብን። ባለቀስን ጊዜ ኃጢአተኛነታችንን እያሰብን ራሳችንን ዝቅ ከማድረግ ይልቅ በመመጻደቅ ከፍ እንላለን ብለን እንዳንወድቅ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

የልብ ጭካኔ፣ በሰው መፍረድ፣ በሰው መናደድ፣ ከመጠን ያለፈ ደስታና መዝናናት፣ መቀለድና መሳቅ፣ ብቸኝነት:- ወዘተ የመሳሰሉት የሰው ልብ ገር እንዳይሆንና ስለኃጢአቱ እንዳያለቅስ ያደርጉታልና በንስሐ ጊዜ ከእነዚህ መራቅና የሠሩትን ኃጢአት እያሰቡ መፀፀት ያስፈልጋል።

ሰው ዘለዓለማዊ ሕይወትን፣ የመጨረሻውን ፍርድና ዘለዓለማዊ ሞትን የሚያስብ ከሆነ ስለኃጢአቱ ማልቀሱ የማይቀር ነው። ስለሠራው ኃጢአት የሚያለቅስ ከሆነ ደግሞ ንስሐ ለመግባት አይቸገርም:- ዕንባ ራሱ የንስሐ ምልክት ነውና።

## ፬. ጥልቅ ኀዘንና ራስን ማዋረድ (ትህትና)

እውነተኛ ተነሳሒ ስለሠራው ኃጢአት በማፈሩና በመፀፀቱ የተነሣ ያዝናል:- ራሱንም በማዋረድ በትሕትና ይኖራል። በራሱ እና በእግዚአብሔር ዘንድ ራሱን በማዋረድ ይኖራል። ስለሠራው ሥራ ሁል

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ራሱን ይገሥፃል — ራሱን ይወቅሳል። ይህ ሰው ያለምንም ፍሬ ስለአባ ከነው የሕይወት ዘመኑ:- ስለደካማነቱ፣ ስለመውደቁ፣ እግዚአብሔርንም ስለከዳባቸው ቀናት እያሰበ ራሱን ይወቅሳል። ብዙዎች ከእኔ ቀድመው ከፍጹሙ ፍቅረ እግዚአብሔር ደርሰዋል:- እኔ ግን ገና ንስሐ ለመግባት ከራሴ ጋር እየታገልሁ ነው:- ለመሆኑ የእኔ ግድየለሽነትና ስንፍና እስከመቼ ሊዘለቅ ነው? እያለም ከራሱ ጋር ይሟገታል። እንዲህ ዓይነቱ ተነሳሒ በራሱ ላይ ያዝናል፤ ቅዱስ ይስሐቅም «ስለሠራው ኃጢአት እያሰበ በየቀኑ በሠራው ሥራ የማያዝን ተነሳሒ ምንም እንኳ በዚያ ጊዜ መልካም ሥራዎችንም ቢሠራ እነዚያን በኃጢአት የኖረባቸውን ቀናት እንደአጣቸው ማወቅ አለበት።» በማለት ተናግሯል። ስለዚህ ይህ ሰው በንስሐ ዘመኑ መልካም ሥራን ቢሠራም የቀደመ ኃጢአቱን እያሰበ ስለአሳለፈው ከንቱ ሕይወቱ ማዘኑ አይቀርም። ሰው ሁል ጊዜ ኃጢአቱን የሚያስብ ከሆነ በሠራው መልካመ ሥራ ራሱን ከፍ ከፍ ሲያደርግ አይገኝም። በመሆኑም ለንስሐ የሚገባ ፍሬ በማፍራት ወደክብር ይደርሳል።

ትሑቱ ተነሳሒ ስለሠራው ኃጢአት ቅጣት የሚገባው መሆኑን ያምናል:- ስለዚህም እንደዳዊት «ያስጨነቅሽኝ መልካም ሆነልኝ:- ሥርዓትህን እማር ዘንድ» በማለት ይናገራል። መዝ.፻፲፰፥፸፩። ተነሳሒው ስለ ሠራው ኃጢአት ኀዘኑ በበዛ መጠን ንስሐው ደግሞ ጥልቅ ይሆናል። ምክንያቱም በዚህ ጊዜ ከኃጢአት የተነሣ መዋረድን፣ የኃጢአትን መጥፎነትና በሕይወቱ ውስጥ ያስከተለበትን ውጤት በሚገባ ስለሚረዳ ነው።

ንስሐ ከገባ በኋላ ሕይወቱ በፍጹም የተለወጠ መስሎት የቀደመ ደካማነቱን እያሰበ ከመጠንቀቅ የሚዘናጋ ሰው ሞኝ ነው። ስለኃጢአት ማዘንን ወዲያው በደስታ መለወጥ ለተነሳሒው ሕይወት በጣም አደገኛ ነው። ንስሐ በመግባቱ እንደጻድቅ ራሱን ከመቁጠር ይልቅ ከንስሐ በኋላም ኃጢአተኛ እንደሆነ ራሱን መቁጠር ለተነሳሒው መልካም ነው። ቅዱስ ጳውሎስም ከቀደመ ሕይወቱ ተመልሶ የወንጌል ሐዋርያ ከሆነ በኋላ «ከኃጢአተኞች እኔ ዋነኛ ነኝ» በማለት መናገሩን ማስታወስ ይጠቅማል።

ትናንት የነበረን ማንነት ወይም ትናንት የኖርነው ኑሮ ኃጢአታችንን ያላስተዋልንበት በኃጢአት የነበርንበት ነበር:- ዛሬ ደግሞ ኃጢአታችንን ዐውቀን ንስሐ ለመግባት በመታገል ላይ እንገኛለን:- ትናንትናም ዛሬም ከኃጢአት አልተለየንም። ንስሐ ደግሞ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ከእኛ ጋር ትኖራለች:- ለንጽሕና የበቃን እስከምንሆን ድረስ። ኃጢአተኛ መሆኑን የማያስብና የማይረዳ ሰው ታላቅ ኃጢአት እየሠራ ነው።



የሕይወት ዘመኑ አንዲት ቀንም ብትሆን ከእመቤታችን በቀር ከኃጢአት ንጹሕ የሆነ ሰው የለም። በየእለቱ እንበድላለንና ኃጢአተኞች ሆነን በየቀኑ በእግዚአብሔር ፊትም እንመላለሳለን:- ስለዚህ ነው በጸሎታችን «በደላችንን ይቅር በለን» በማለት የምንለምነው። ጻድቅ እንኳ ቢሆን ይህን ጸሎት በመደጋገም ይጸልየዋል:- በመጽሐፍም «ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ይነሣማል» ተብሎ ተጽፏልና። ምሳ.፳፬፥፲፮።

በሠራው ኃጢአት የማያዝን ሰው ንስሐ ገብቻለሁ ሊል አይችልም ራሱን አያውቅምና። ስለዚህ ሁል ጊዜ ስለኃጢአታችን በማዘን በተሰበረ ልቡና እንድንኖር ያስፈልጋል «እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነውና።» መዝ.፴፫፥፲፰።

ሰው ከነበረበት የኃጢአት ሕይወት እግዚአብሔርን ለማገልገል የተጠራም ቢሆን ኃጢአቱን እያሰበ ማዘኑንና ስለኃጢአተኛነቱም ራሱን እየወቀሰና በትሕትና አገልግሎቱን መፈጸም እንዳለበት መዘንጋት አያስፈልገውም። በአገልግሎቱ ጥሩ ውጤት ያለው እንኳ ቢሆን እግዚአብሔርን ለማገልገል የተጠራሁ እኔ ማነኝ በማለት ራሱን መመርመርን መዘንጋት የለበትም። ሥጋዊ ዕውቀቱና አካላዊ አገልግሎቱ ብቻ ነፍሱን ለማዳን ስለማይበቃ መልካም እንኳ እየሠራ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ «እንደ ጭንጋፍ ለምሆን...ከሁሉ የማንስ ነኝና የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንኩ ነኝ» ማለት እጅግ ያስፈልጋል። ፩ቆሮ.፲፭፥፰—፱። ፩ጢሞ.፩፥፲፭።

ቅዱስ ጳውሎስ ቀድሞ የሠራው ኃጢአት በንስሐ ቅጣት ተወግዶለታል — ከኅሊናው ግን አልጠፋም። ከአእምሮው አለመጥፋቱ ደግሞ በሠራው በደል ላይ ጥልቅ ኀዘንና ራሱን በማዋረድ ትሕትናን ገንዘብ እንዲያደርግ ረድቶታል የማይገባኝ ነኝ ለማለትም አብቅቶታል። ለብዙ ዓመታት ያገለገለ ሲሆን እንደጀማሪ ወይም ወጣኒ የማይገባኝ ነኝ እንዲል አግዞታል — ስለዚህም ከሐዋርያት የማንስ ከኃጢአተኞች ዋነኛ ነኝ በማለት ተናግሯል።

እኛም እንደዚሁ እንደወጣንያን ራሳችንን በመቁጠር በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ‹የማይገባኝ ነኝ› በማለት መኖር አለብን። ራሳችንን በመንፈሳዊ ሕይወት እንደ ሕፃን ልንቆጥረው ይገባል:- በመጽሐፍ — «እግዚአብሔር ሕፃናትን ይጠብቃል» ተብሎ ተነግሯልና። መዝ.፻፲፭፥፮። ራሳችንም ከሚያስፈልገው መንፈሳዊ ግብ የደረስን እንዳይመስለን መጠንቀቅ አለብን:- ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ እንኳ «አሁን ፍጹም እንደሆንሁ አይደለም:...እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቆጥራለሁ — ነገር ግን አንድ

www.ethiopianorthodox.org

ነገር አደርጋለሁ።» ፊልጵ.፫፥፲፪—፲፫። በማለት ራሱን በትሕትና ገልጧል። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ አርሳንዮስም ራሱን ገና መንፈሳዊ ሕይወትን እንዳልጀመረ በመቁጠር «አቤቱ ጌታዬ ሆይ መጀመርን ስጠኝ» በማለት ጸልዮአል። ጥልቅ ኀዘንና ራስን ማዋረድ ወይም አትሕቶ ርእስ የንስሐ ሕይወት ምልክቶች ናቸውና ገንዘብ ልናደርጋቸው ይገባል።

## ፭. የኃጢአትን ውጤት ማስተካከል

የኃጢአት ውጤቱ ከእግዚአብሔር መጣላትና ሰውንም መበደል ነው። ስለዚህ በንስሐ ጊዜ ኃጢአትን መናዘዝና ኃጢአትን መተው ብቻ በቂ ሳይሆን በተሠራው ኃጢአት የደረሰውን ጉዳት መካስ — የተበላሸውን መጠገን — የተጣመመውን ማስተካከል:- የተቀማውን መመለስ ጭምር ይገባል። የኃጢአትን ውጤት ማስተካከል ማለትም ይህ ነው።

የሰረቀ ሰው ሰርቄአለሁ ብሎ መናዘዙ ብቻ በቂ አይደለም የተሰረቀውን ንብረት ለባለቤቱ መመለስ አለበት:- የበደለ ሁሉ በድያለሁ ብሎ መናዘዙና ይቅርታ መጠየቁ ብቻ በቂ አይደለም የበደለውን በመካስ ከኃጢአቱ የተነሣ የደረሰውን ጥፋት ማስተካከል ይገባዋል እንጂ — ይህም ለበደላቸው ሁሉ የበለጠ መልካም በማድረግ ይታወቃል።

ለዚህ በቂ ምሳሌ የሚሆነን ቀራጩ ዘኬዎስ ነው። ዘኬዎስ ንስሐ በገባ ጊዜ በጌታ ፊት በሕዝብ መካከል ቆሞ — «ጌታ ሆይ ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ:- ማንንም በሐሰት ከስሼ ብሆን አራት እጥፍ እመልሳለሁ።» በማለት ተናግሯል:- የበደለውን መካስ እንደሚገባው ዐውቋልና። ሉቃ.፲፱፥፰።

ያማነውንና ስሙን ያጠፋነውን ሰው ስም እንደገና በማክበር ንጽሕናውን መመስከር ይኖርብናል። እንዲህ በማድረግ የንስሐን መልካምነት ማጣጣም ይቻላል። ስለዚህ በኃጢአት የሰበሩትን መጠገን:- ያጎደፉትን ማንጻት:- የኃጢአትን ውጤት ማስተካከል የንስሐ ምልክት ነው።

## ፮. ለኃጢአተኞች ማዘን

ስለ ራሱ ኃጢአት የማያዝን ሰው ስለሌሎች ኃጢአት ሊያዝን አይችልም። የራሱን ኃጢአት ሊመለከት የማይችልም እንዲሁ ስለሌሎች ሰዎች ኃጢአት ሊያስብ አይችልም ቢያስብም ደግሞ ራሱን ንጹሕ አድርጎ ነው። ዘማዊቱን ሴት በጌታ ፊት አቁመውና ኃጢአቷን በመዘርዘር በከሰሷት ጊዜ «ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት እርሱ ይውገራት» ሲባሉ ከዚያ አፍረው



እንደሄዱት ሰዎች ዮሐ.፰፥፩—፲፪። በእርግጥም በራሱ ዓይን ያለውን ምሰሶ አውጥቶ መጣል ያልቻለና የማያይ በሌላው ያለውን ጉድፍ እንዴት ማየት ይችላል። ማቴ.፯፥፭። ስለኃጢአቱ የሚያስብ ሰው እኔ ብዙ ጊዜ በኃጢአት ወድቄአለሁና ሌላው ሰው ከእኔ የተሻለ ቅዱስ ነው:- ይላል።

ስለራስ ኃጢአት ማዘን ከልቡና ክፋትን ያጠፋል:- ለማንም ቢሆን ምንም እንኳ ኃጢአተኛ ቢሆን የሚራራ ርኅሩኅ ያደርጋል። የራሱን ኃጢአት የሚያስታውስ ሰው ለሌሎች ኃጢአተኞችም ደግሞ ያዝናል። ቅዱስ ዮሐንስ የተባለ የቤተ ክርስቲያን አባት ማንንም በኃጢአት ያየ እንደሆን «ሰይጣን ዛሬ ወንድሜን ከጣለው:- ነገ እኔን ይጥለኛል:- ወንድሜን ጌታ ይቅር ብሎት ንስሐ ይገባ ይሆናል:- እኔ ግን ንስሐ የምገባ ሰው አይደለሁም» እያለ አምርሮ ከልቡ ያለቅሳል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ከእነርሱ ጋር እንደ ታሠረ ሆናችሁ እሥሮችን አስቡ» በማለት የተናገረው ቃል ንስሐ የገባ ሰው ንስሐ እንዳልገባ ራሱን በመቁጠር በኃጢአት ላሉት ማሰብና ማዘን የሚገባው መሆኑን ያመለክታል። ዕብ.፲፫፥፫። ኃጢአትን የማያውቅ ሰው በትዕቢት ይፈርዳል ኃጢአትን የሚያውቅ ደግሞ የሰውን ድካም ያውቃልና በኃጢአት ለወደቁት ያዝንላቸዋል።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን የሙሴ ፀሊም ሕይወት ነው። በአንድ ወቅት የገዳሙ ጉባኤ በሚሰበሰብበት የአንድ መነኩሴ ጉዳይ ሲታይ እርሱም እንዲሳተፍ ተጋበዘ። እርሱም በአንድ ጆንያ አሸዋ ሞልቶ በመሸከም ወደጉባኤው ሄደ። የገዳሙ አባቶች ስለምን ይህን እንደአደረገ ቢጠይቁት:- «ይህ ከእኔ ጀርባ የሚከተለኝ ኃጢአቴ ነው — እኔ ላየው አልችልም ነገር ግን እነሆ በወንድሜ ልፈርድ መጥቻለሁ» አላቸው።

ተነሳሒ ልቡና ያለውና ሕይወቱን በንስሐ የሚመራ ሰው ለእርሱ አደገኛ እንኳ ቢሆን ስለሌላው ሰው ኃጢአት አይናገርም። ቅዱስ አሞጽ የተባለ የቤተ ክርስቲያን አባት ሲናገር — «ለባልንጀራ ይቅርታ ማድረግ፣ በሌሎች መፍረድን መተውና የልብ ትሕትና የንስሐ ምልክቶች ናቸው» ብሏል። ቅዱስ ይስሐቅም «ተነሳሒው ሰው ስድብንና አሉባልታን ፈጽሞ መታገሥ አለበት» ይላል። ሰዎች ከውጭ ቢያሙትና ቢሰድቡት እርሱ ደግሞ በልቡ ራሱን የሚያማና የሚሰድብ መሆን አለበት። ከዚህም ሌላ ክርስቶስ እርሱን ይቅር እንዳለው ሁሉ እርሱ ደግሞ ሌሎችን ይቅሬ የሚል መሆን አለበት። ጌታም በአምላካዊ ቃሉ — «ይቅር በሉ ይቅርም ትባላላችሁ» በማለት ተናግሯል። ሉቃ.፮፥፴፯። ከዚህም ሌላ «ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማይ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና:- ለሰዎች ግን

www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።» በማለት ጌታችን አስተምሯል። ማቴ.፮፥፲፬–፲፭። ይህ ይቅርታም በፍጹም ፍቅር ሊሆን ይገባል። በፍጹም ፍቅር ማለትም «ጠላቶችህን ውደድ» የሚለውን ትእዛዝ መፈጸም ነው። ሉቃ.፮፥፳፯። ይህም የንስሐ ምልክት በሆነ ፍጹም ትሕትና ሊደረግ ይገባዋል።

### ፮. ሌሎች ስሜቶች

ንስሐ የገባና ስለኃጢአቱ የሚያዝንና የሚያለቅስ ሰው ዘወትር ጭምትና ሰላማዊ:- የማይከራከር ዝምተኛና ድምፁም የማይሰማ ይሆናል። ኢሳ.፵፪፥፪። በንስሐ የሚኖር ሰው ስሜቱ ከመናገር ይልቅ ዝምታንና ማዳመጥን ይመርጣል። መናገርን – ማስተማርን ጭምር አይሻም – ይልቁኑ መማርን ይፈልጋል – ቅዱስ ያዕቆብ:- «ወንድሞቼ ሆይ:- ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ:- የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁና:- ሁላችን በብዙ ነገር እንሰናከላለንና» ሲል የተናገረውን ስለሚያስብ እናገር ዘንድ እኔ ማንኝ – ማስተማርም ከእኔ እጅግ ለሚበልጡ የተሰጠ ነውና – ሌሎችንም አስተምር ዘንድ የእኔ መንፈሳዊ ልምድስ ምንድን ነው? ይላል። ያዕ.፫፥፩–፪።

ለእርሱ የሚሰማው እግዚአብሔር ያዘጋጀለት መንፈሳዊ የበላይነት ስለሆነ – ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባትንም ስለሚሻ ራሱን የማይጠቅም አድርጎ ስለሚቆጥር ዝም ማለትን ይመርጣል። ለዚህም ነው ንስሐ በሚገቡ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ብዙ ጊዜ መንፈሳዊ ጥንካሬን የምናየው።

### ፯. መንፈሳዊ ጽናት (ጥንካሬ)

ንስሐ ሰው ሕይወቱን ወደተሻለ ደረጃ ለመለወጥ የሚያስችለው መንፈሳዊ ጥንካሬ (ኃይል) ነው። ንስሐ በልቡናችን ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ፍቅረ እግዚአብሔር እንዲወለድ ያደርጋል። ምክንያቱም በንስሐ ሕይወት የምንኖር ከሆነ እግዚአብሔር ስለእኛ ብሎ የተሸከመልንን ሸክምና ይቅር ያለንን እጅግ የከፋ ኃጢአት እንድናስብ ስለሚያደርግና ለእግዚአብሔርም ያለን ፍቅር እያደገ ስለሚሄድ ነው። በወንጌል ታሪኳ እንደተነገረላት ሴት:- እርሷ በዕንባዋ የጌታን እግር አርሳው – በጠጉርዋም አብሳው ነበርና የበደለችውን ሁሉ አስባ – ጌታም ስለዚህ – «እጅግ ወዳለችና ብዙ ኃጢአትዋ ተሠርዮላታል» በማለት ተናግሯል። ሉቃ.፯፥፵፯። እግዚአብሔር የበዛ ኃጢአቱን ይቅር ያለው ሰው የተደረገለትን ይቅርታ እያሰበ በልቡ



የእግዚአብሔር ፍቅር እየጨመረ ይሄዳል። እነዚህ የኃጢአታቸውን ብዛት የእግዚአብሔርን ምሕረት እያሰቡ የሚኖሩ ሰዎች ፍቅረ እግዚአብሔር የገባቸው የመስቀሉን ዋጋና የተፈጸመላቸውን የማዳን ምሥጢር የተረዱ ናቸው።

ከዚህ ጽኑ ፍቅር የተነሣም ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ክብር ብለው እስከመሰዋት የሚያደርሳቸው መንፈሳዊ ብቃትና ጥንካሬ ይኖራቸዋል። ይህ መንፈሳዊ ጥንካሬም በሕይወታቸው ዘመን ራሳቸውን ወስነው ለቅድስና እንዲበቁም ሊያደርጋቸው ይችላል። ብዙ ኃጢአተኞች ከንስሐ ባገኙት መንፈሳዊ ብቃት ለቅድስና በቅተዋል። ለምሳሌ ማርያም ግብፃዊት አንዷ ቅድስት ናት።

የብዙ ሰዎች ችግር በንስሐ ጊዜ የነበራቸውን መንፈሳዊ ጥንካሬ ማጣት ነው። በኃጢአት ወድቀው በነበረ ጊዜ የፈጸሙትን በደል ሁሉ ለመካስ ያነሣሣቸው የነበረው መንፈሳዊ ኃይል ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ከልቡናቸው ፈጽሞ ይጠፋል። አንድ ሰው ደግሞ በንስሐ ያገኘውን መንፈሳዊ ጥንካሬ ይዞ ለመቆየትና ለመጽናት ካልቻለ ያገኘውን ከማጣት ሌላ አማራጭ ሊኖረው አይችልም። ኃጢአቱን ከዘነጋና ስለኃጢአቱም ማሰብን ከተወ በልቡናው ግድየለሽነት እያደገ ይሄዳል። ይህ ደግሞ አደገኛ ስለሆነ መንፈሳዊ ጥንካሬአችንን እንዳናጣ መጠንቀቅ ነው።

በፍጹም ንስሐ የገባው ሰው የሚመለከተው ቀድሞ በኃጢአቱ ምክንያት ሊያየው ያልቻለውን የተከፈተ የገነት ደጅና አዲስ የመንፈሳዊ ሕይወት ምዕራፍ ነው። ይህ አዲስ መንፈሳዊ ዓለም እጅግ ስለሚማርከው መንፈሳዊ ተመስጦው ለንስሐ አባቶቹ እንኳ እስኪያስፈራ ድረስ ጥልቅ ይሆናል። በንስሐ ጊዜአቸው ያገኙትን መንፈሳዊ ጥንካሬ በማጽናት ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ፈጽመው ያስገዙ ብዙ ናቸው። እነዚህ ኃጢአታቸውን በማሰብ ዓለምን በመናቅ ከእግዚአብሔር ፍቅር የበለጠ ሊጠመዱበት የሚገባ ምንም አለመኖሩን ያረጋገጡ ናቸው።

ከንስሐው ጋር በሚመጣው መንፈሳዊ ጥንካሬ ውስጥ ተነሳሒው ቀድሞ የሌለውን መንፈሳዊ ኃይል ገንዘብ ያደርጋል። በኃጢአት በነበረ ጊዜ ከሰይጣን ጋር በነበረው ውጊያ ደካማ ነበር ንስሐ ሲገባ ግን የተለየ ጸጋና መንፈሳዊ ኃይል ያገኛል። በዚህም የተነሣ በአዲስ መንፈሳዊ ኃይልና ፍቅረ እግዚአብሔር ሕይወቱ ይመራል «እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ...ኃይላቸውን ያድሳሉ:- እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ – ይሮጣሉ:- አይታክቱም:- ይሄዳሉ አይደክሙም።» በማለት ነቢዩ ኢሳይያስ

www.ethiopianorthodox.org

እንደተናገረው። ኢሳ.፵፥፴፩። ከዚህም ሌላ ይህ ነቢይ እግዚአብሔር «ለደካማ ኃይልን ይሰጣል – ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምርለታል» ሲል ተናግሯል። ኢሳ.፵፥፳፱። እንግዲህ የሚደነቀው በንስሐ ሕይወታችን ይህን ኃይል እስከማግኘት ደርሰን እንደሆን – የእግዚአብሔርም ቀኝ እጅ ለብሩኀ ሕይወት እንዳበቃን የተረዳን እንደሆን ነው። እርሱ «ኀልማሳነትን እንደንስር ያድሳል» ተብሏልና። መዝ.፻፲፯፥፲፮። ስለዚህ ይህን ለማስተዋል በቻልን ጊዜ እንደ ቅዱስ ዳዊት:- «የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ:- የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች:- አልሞትም በሕይወት እኖራለሁ እንጂ – የእግዚአብሔርንም ሥራ እናገራለሁ» እያልን ከንስሐ የተነሣ ስለአገኘነው መንፈሳዊ ኃይልና ጥንካሬ እንናገራለን። በዚህ መንፈሳዊ ኃይልም የተቀደሰውን ሕይወት እንኖራለን።

## ፱. በተቀደሰ ሕይወት መኖር

በሕይወት ውስጥ መንፈሳዊ ለውጥ ከሌለ ንስሐም የለም። ንስሐም መናዘዝና ሥጋወደሙን መቀበል ብቻ አይደለም ኃጢአትን ፈጽሞ በመተው በተቀደሰ የሕይወት ጎዳና መኖርም ነው እንጂ። በዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ «ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አንድነት አለን:- የኢየሱስ ክርስቶስም ደም ከኃጢአት ያነጻናል» እንዳለው ተነሳሒው ይቅርታን ይቀበልበታል። ፩ዮሐ.፩፥፯። በመሆኑም በብርሃን መመላለሳችን ከኃጢአት ለመንጻታችን እጅግ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ነው ከንስሐ ምልክቶች አንዱ ነውና። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ከኃጢአት ስለሚያነጻውና ከፍርድም ስለሚያድነው መመላለስ ሲናገር – «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት...እንደመንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደሥጋ ፈቃድ ለማይመላለሱት...አሁን ኩነኔ የለባቸውም።» ብሎአል። ሮሜ.፰፥፩—፬። በዚህ አባባልም ለዚህ አዲስ ሕይወት ከሚያስፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች መካከል ታዲያ በብርሃን መመላለስና በመንፈስ መመላለስ ዋነኞቹ ናቸው። ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ሊያጠናክር «በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ።» ብሏል። ኤፌ.፬፥፩። በሌላ ሥፍራም «በበጎ ሥራ ሁሉ እያደጋችሁ...ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን።» ከማለቱም በተጨማሪ «እንደተወደዱና እንደብርሃን ልጆች ተመላለሱ» በማለት ተናግሯል። ቆላ.፩፥፲። ኤፌ.፭፥፩፤ ፰።

ንስሐ ከክርስቶስ እግር በታች ራስን መጣል ብቻ አይደለም:- በመንፈሳዊ ሕይወት መኖርና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመፈጸም መኖርም



ጭምር ነው እንጂ። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም በዚህ ረገድ «በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም:- ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም:- አላወቀውምም።» ፩ዮሐ.፫፥፮። ካለ በኋላ «በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል።» ፩ዮሐ.፪፥፮። እንዲሁም ደግሞ «ዐውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው:- እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም።» በማለት ተናግሯል። ፩ዮሐ.፪፥፬። ስለዚህ ከእርሱ ዘንድ ዕርዳታውንና ጸጋውን ለማግኘት ራሳችንን ከክርስቶስ እግር በታች ማዋረድ ይገባናል። ጸጋውም በኃጢአትና በስንፍና መኖር ሳይሆን እርሱ ክርስቶስ በብርሃን እንደተመላለሰ በብርሃን መመላለስና ትእዛዛቱን በመጠበቅ መኖር ነው። በብርሃን እየተመላለስን ትእዛዛቱንም እየፈጸምን ብንኖር ከመጨረሻው የንስሐ ምልክት እንደርሳለን።

## ፲. ንጽሕና

ንጽሕና በንስሐ ከተለወጠ ሕይወት የሚገኝ መንፈሳዊ ፍሬ ነው። በንጽሕና የዓለም ፍላጎት:- የሥጋ ፈቃድና ኃጢአት ተወግደው የልብ መሻትም የቅድስና ሕይወትና የእግዚአብሔር ፍቅር ይሆናል። ተነሳሒውም ዳግመኛ በኃጢአት ፍቅር አይፈተንም። ሰው ያለትግል:- ያለድካም:- ያለጦርነት የተቀደሰውን ነገር ሁሉ ማድረጉ የንጽሕና ምልክት ነው፤ ፈተናውንና ጦርነቱን አልፎታልና ቅድስናውን ሊቋቋመው የሚችል ነገር የለም።

በውስጣችን የመልካምና የክፉ ሃሳብ ግጭት ካለ ወደንጽሕና ለመድረስ እየሞከርን እንጂ ከንጽሕና ያልደረስን መሆናችንን እናውቃለን። በቅድስና ለመኖር በምናደርገው ጥረትም ገና ወደንጽሕና ለመድረስ የምንጥር እንጂ ንጽሕናን ገንዘብ ያላደረግን መሆኑን እናውቃለን።

በንጽሕና ሰላም በልብ ውስጥ ይሰፍናል – ፈተናውና ጸሩ ሁሉ በመልካሙ አሸናፊነት የተጠናቀቀ በመሆኑ ውጊያ የለም። በንጽሕና ሰላማችን:- ፍላጎታችንና ደስታችን ሁሉ በእግዚአብሔር ይሆናል። ንጽሕናም – አነጋገራችንን፣ ሕዋሳቶቻችንን፣ አካላችንን:- ልቡናችንንና አመለካከታችንን:- በአጠቃላይ መላ ሕይወታችንን የሚሸፍን ስለሚሆን መንፈሳዊ ፍሬ የሚገኝብን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች እንሆናለን። ስለዚህ የንስሐ አንዱ ምልክት ወደሆነው የንጽሕና ደረጃ ለመድረስ የተቻለንን ያህል ራሳችንን ማዘጋጀት ይገባል።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል አምስት

# የልብ ንጽሕና

ፍጹም ንስሐ ኃጢአትን ጨርሶ መጥላት – ልብንም ፈጽሞ ከኃጢአት ማጥራት ሲሆን የልብ ንጽሕና ደግሞ ከፍጹም የንስሐ ምልክቶች አንዱ ነው።

የልብ ንጽሕና፡- ፍጹሙ ንስሐ – ማለትም ሰው ኃጢአትን ጨርሶ መጥላቱ እንዴት ሊታወቅ ይችላል? ቀጥሎ የዚህን ጥያቄ መልስ እንመረምራለን።

### ፩. ከኃጢአት መንጻት

ሀ. ሰው አእምሮውን በመፈተን የሚያስጨንቁትን ከባድ ኃጢአቶች በመተውና ዳግመኛም ወደእነርሱ ባለመመለሱ በንስሐ የሚኖር ሊመስለው ይችላል። ለምሳሌ ዳግመኛ ዝሙት አልሠራ፣ አልሰረቀ፣ ወይም አላታለለ ወይም ደግሞ አልሰከረ ይሆናል። በዚህ ደረጃ ያሉትን ኃጢአቶች አልፈጸመ ይሆናል። በዚህ የተነሣ አእምሮው እረፍት ስለሚኖረው ንስሐ የገባ ሊመስለው ይችላል። ለዚህ ምክንያቱ እርሱ ያተኮረባቸው ዐበይት ኃጢአቶች ጥቃቅኑንና ሊያስተውላቸው ያልቻለውን ኃጢአቶች ስለሚሸፍኑበት ነው። ምናልባትም ራሱን ተነሳሒ አድርጎ በሚቆጥርበት ጊዜ በብዙ ሊያስተውላቸው ባልቻላቸው ወይም ኃጢአቶች ናቸው ብሎ ባላሰባቸው ብዙ ኃጢአቶች ተዘፍቆ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ስለራሱ በመናገር፣ በውዳሴ ከንቱ በመደሰት፣ ራስን በማምካሸት፣ በራስ ፍላጎት በመጓዝ:- ለግትርነት በሚያበቁ ሃሳቦች ላይ በመመርኮዝ፣ የተወሰኑ ጸሎቶችን ንቆ በመተውና ለመንፈሳዊ ንባቦች ግድየለሽ በመሆን፣ ምናልባትም ስድብን ባለመታገስ፣ ሰንበትን ባለማክበር፣ ይህን ሁሉ በማድረጉ ራሱን አይወቅስም:- በዚህ የተነሣ ራሱን ሊወቅስ ከሚችልበት ደረጃ አልደረሰምና። ታዲያ ይህን ሰው በእውነተኛ ንስሐ ውስጥ እየኖረ ነው ማለት እንችላለን?

ስለዚህ ይህ ሰው የንስሐ እርምጃውን ማጠናከር አለበት:–ብናቃቸው ኃጢአቶች ሁሉ ላይ ንስሐ መግባት አለበት:- በንስሐ ይኖራል ለማለት የሚቻለውም በእርሱ ሃሳብ ጥቃቅን ከሚመስሉት ጀምሮ ኃጢአትን ሁሉ ሲተውና ከልቡናው ፈጽሞ ያጠፋው እንደሆነ ነው። በዚህ ጊዜም በንስሐ አንድ ርምጃ በመጨመሩ በመንፈሳዊ ብስለት እያደገ ነው ሊባል ይችላል። አእምሮውም ምንም ነገር ሳይንቅ ለሁሉም ኃጢአት ትኩረት መስጠት ስለሚጀምር በንስሐ ሕይወት እየኖረ ነው ለማለት ይቻላል።

ለ. ምናልባትም ሰይጣን ለተወሰነ ጊዜ ከእርሱ በመለየቱ ኃጢአትን ላይሠራ ይችላል። ሰይጣን ለክፉ ሥራው ጠቢብ ነው። መቼ:- እንዴትና በምን ኃጢአት ሰውን እንደሚጥል ያውቃልና – ሰውየው በራሱ በመተማመን ከኃጢአት መጠንቀቁን እስኪተውና ስለሕይወቱ ግድየለሽ እስኪሆን በትዕግሥት ይጠብቀዋል። በሕይወቱ በደከመ ጊዜ በቀላሉ ሊጥለው እንደሚችል ስለሚያውቅ ያኔ ይመጣበታል። ይህ ሰይጣን ከሰውየው ገለል ብሎ የቆየበት ጊዜ ኃጢአትን የማሸነፍያ ጊዜ አይደለም ጦርነት የሌለበት ጊዜ ነው። ከመንፈሳዊ ጦርነት የማረፊያ ጊዜ እንጂ የድል ወይም የንጽሕና ጊዜ አይደለም።

ምናልባት በኃጢአት ያልወደቅንበት ጊዜ ቢኖር ከኃጢአት ፈጽመን ስለንጻን አይደለም ነገር ግን በዚያ ጊዜ ሰይጣን ስላልተዋጋን ወይም ደግሞ ኃጢአት ለመሥራት የተመቻቸ ሁኔታ ስለሌለ ነው።

ሰይጣን በተወሰነ ጊዜ ላይዋጋን ይችላል:- የእኛን እረፍት ሽቶ ሳይሆን እኛን የሚጥልበት ሌላ ወጥመድ እያዘጋጀ ስለሆነ ነው። ምናልባትም ከኃጢአት የነጻንና የተቀደስን እንደሆንን የሚያሳስብ ሰይጣን ወደ እኛ ሊመጣና ንጹሐን መሆናችንን ያለፈው በደል ሁሉ ከእኛ መወገዱን ሊያበሥረን ይችላል:- በዚህ ጊዜ ምንም እንኳ በኅሊናችን የአሸናፊነት ስሜት ቢሰማን ደካማ መሆናችንንና በሥጋ የምንኖር እስከሆንን ድረስ ልንወድቅ የምንችል እንደሆንን መዘንጋት የለብንም። ስለዚህ ከንጽሕና ደረጃ ደርሻለሁና ዳግመኛ አልወድቅም ማለት የለብንም:- ይልቅ ግን እንደ ዳዊት «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን...ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር» ማለት ይገባናል። መዝ.፻፳፫፥፪–፫። የሚጠብቀንን እግዚአብሔርንም ልናመሰግን ይገባል።

ሐ. ምናልባትም እግዚአብሔር ከኃጢአት ሸክም እንድናርፍና ነፍሳችንንም ተስፋ ከመቁረጥ ሊያድናት አስቦ የእረፍት ጊዜ ሰጥቶን ይሆናል። ያለማቋረጥ በኃጢአት ተዘፍቆ መቆየት ከተስፋ መቁረጥ ሊያደርስ ስለሚችል – እግዚአብሔር በጸጋው ከልሎ በቸርነቱ ጠብቆ ከኃጢአት ሊያሳርፈን ይችላል:- ይህም ንጹሐን ስለሆንን አይደለም።

www.ethiopianorthodox.org

መ. ምናልባት ብዙ ጸሎቶች ስለእኛ ቅድመ እግዚአብሔር በመድረሳቸው ሰላም አግኝተን ይሆናል:- ቅዱሳን ስለጸለዩልን ጸሎት ወይም ወዳጆቻችን ስለአቀረቡት ልመና ከኃጢአት ሸክማችን ልናርፍ እንችላለን። ይህም ከንጽሕናችን የተነሣ አለመሆኑን ጠንቅቆ መረዳት ይገባል። ይህ ጊዜም ከሰይጣን የማንዋጋበት በሰላምና በዝምታ የምናሳልፈው ጊዜ ነው እንጂ ከንጽሕና ደረጃ የደረስንበት አይደለም።

በሕፃናትና በዕድሜና በመንፈስ ትልቅ ዐዋቂ በሆኑ ሰዎች ንጽሕና መካከል ልዩነት አለ። ሕፃናት ወደዚህ መንፈሳዊ ጦርነት አልገቡም – አልተፈተኑምም። ትላልቆቹ ግን በጦርነቱ ውስጥ ናቸው:- ተዋግተውም አልፈዋል። የኃጢአትንም ኃይል ተቃውመዋልና የድል አክሊል ያገኛሉ። ሕፃናት ግን እንደእነዚህ አይደሉም – ገና ናቸው።

ሕፃናት ከማያውቁት ከዚህ ውጊያ በኋላ የሕፃናትን ንጽሕና ገንዘብ ያደረጉ ሰዎች ግን እጅግ የሚደነቁ ናቸው። ይህ የልብ ንጽሕና በቀላሉ የሚደረስበት አይደለም:- ከዚህ ደረጃ የሚደርሱት ብዙ ውጊያዎችንና ፈተናዎችን በድል አልፈው ነው። የልብ ንጽሕና እጅግ ከፍተኛ የሆነ የንጽሕና ደረጃ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው በተወሰነ ኃጢአት ተፈትኖ ራሱን ከዚህ ኃጢአት ቢያነጻ ይህ ፍጹም ንጽሕና ነው ለማለት አይቻልም።

ፍጹም ንጽሕና ከኃጢአት ሁሉ መንጻት ነው። ይህም በማንኛውም ጊዜና መንገድ ከሚመጣ ከማንኛውም ኃጢአት መንጻት ማለት ነው። ከተወሰኑ ኃጢአቶች ብቻ መንጻት ፍጹም ንጽሕና አይባልም። በመቅደስ ከቀራጩ ጋር ቆሞ ይጸልይ የነበረው ፈሪሳዊ ቀማኛ፣ ዓመፀኛና አመንዝራ ባለመሆኑ በሳምንትም ሁለት ቀን በመጾሙ ንጹሕ እንደሆነ አስቦ ነበር። ሉቃ.፲፰፥፲፩–፲፪።.ነገር ግን ከኩራትና በሌሎች ከመፍረድ ራሱንም ከፍ ከፍ ከማድረግና ከመመጻደቅ ራሱን አላነጻም ነበር። ስለዚህ ከተወሰኑ ኃጢአቶች በነጻን ጊዜ ከንጽሕና የደረስን ሊመስለን አይገባም። ለንጽሕናችን መለኪያ የሚሆነው ከኃጢአት ወገን የትኛውም ቢሆን በላያችን ሥልጣን የሌለው እንደሆነ ብቻ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን እንመልከት:- «ከእናንተ ስለኃጢአት የሚወቅሰኝ ማነው?» ማለቱ ስለየትኛውም ኃጢአት ቢሆን ማለቱ ነው። ዮሐ.፰፥፵፮። በሌላ ሥፍራ ደግሞ «የዚህ ዓለም ገዥ ይመጣልና በእኔ ላይም አንዳች አይኖረውም» በማለት ፍጹም ንጹሕ የባሕርይ አምላክ መሆኑን ተናግሯል። ዮሐ.፲፬፥፴። እንግዲህ ከሰው ወገን ማን ከዚህ ደረጃ ደርሷል?



እውነተኛው ንጽሕና ኃጢአትን ፈጽሞ ከመጥላት ይጀምራል። ይህም ማለት መልካሙንና ክፉን ለመለየት የሚቻልበት የፍጹምነት ደረጃ መጀመሪያ ነው። ዕብ.፭፥፲፬። ንጽሕና ከልብ የሚመነጭ እንጂ ከውጭ የሚመጣ አፍአዊ አይደለም። ውስጡ ያልጸዳ ውጭው ግን አምር የታየ ሁሉ ንጽሕ ነው ሊባል አይችልም። ማቴ.፳፫፥፳፭–፴፩። ይህም ንጽሕና ማለት የውጫዊ አካላችን ሳይሆን የልቡናችን ከኃጢአት ንጹሕ መሆን ነው ማለት ነው። በመጽሐፍም «በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና» በማለት ቀዳሚውና ዋነኛው የልብ ንጽሕና መሆኑ ተነግሯል። ማቴ.፲፪፥፴፬። ስለዚህ ከውጫዊው ንጽሕና በተጨማሪ ልናተኩርበት የሚገባው የልብ ንጽሕና ነው። መልካሙና ንጹሑ ሥራ የሚመነጨው መልካም ሃሳብ ከሚገኝበት ንጹሕ ልብ ነው። ይህ ደግሞ ንጹሕ ዓላማና ንጹሕ የአሠራር ዘዴ እስካለ ድረስ ነው። ይህ የልብን ንጽሕናም ወደፍጹም ንጽሕና ሳይሆን ከኃጢአት ንጹሕ ወደመሆን ያደርሳል።

፪. ንጽሕናን መፈተን

ሰው ንጹሕ ሊባል የሚችለው እጅግ ከባድ የሆነ የኃጢአት ፈተና ቢደርስበት እንኳ ሳይናወጥ የኃጢአትን ኃይል የተቋቋመ እንደሆን ነው። በኃጢአት አለመውደቅ ብቻ ሳይሆን በዚህ የኃጢአት ኃይል የማይንገዳገድ ጽኑ የሆነ እንደሆነም ነው። የሰው የልብ ንጽሕናም የሚፈተነው በከባድና በአስፈሪ የኃጢአት ጦርነት ነው። ሰይጣን ታላላቆችን እንኳ ሳይቀር የሚያዋርድ ስለሆነ እኔ ጠንካራ ነኝ ከማለት ይልቅ ደካማነትን ማወቅና እኔም ንጹሕ አይደለሁም ማለት ይገባል። ምሳ.፯፥፳፮።

ከባዱ ውጊያ ሰውን ያለእረፍትና ያለፋታ ይፈትነዋል። አንዱ በመራራው ውጊያ ሊያሸንፍ ይችላል – ውጊያው እየቀጠለ በሄደ ቁጥር እየደከመ ሄዶ ከመሸነፍና ከመውደቅ ሊደርስ ይችላል። ለምሳሌ እንደ ሶምሶን። መሳ.፲፮፥፲፮–፲፯። ይህ ከባድ ጦርነት መልኩን እየለዋወጠ ሰውን ሊፈትን ይችላል። የሰውየውን ደካማ ጎን በማጥናትና የውጊያ ስልቱን በመቀየር ሊረታውም ይችላል።

ታዲያ ንጹሕ ልብ አለው የሚባለው እንዴት ያለው ሰው ነው? ሰው ንጹሕ ልብ አለው የሚባለው በሃሳብ፣ በስሜት፣ በመናገር፣ በአካል እንዲሁም በማድረግ ከሚሠሩ ኃጢአቶች ሁሉ ልቡናውን ያነጻ እንደሆነ ነው። ንጹሕ የሚባለው እግዚአብሔር በሰጠው ጸጋ ታግዞ እነዚህን ሁሉ ኃጢአቶች ተዋግቶ ያሸነፈ ሰው ነው። ይህ ንጽሕና የመጨረሻው የንስሐ ጉዞ ምዕራፍ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ለመተያየት የሚያበቃ ጸጋ

www.ethiopianorthodox.org

ይገኝበታልና መድኃኒታችን «ልበ ንጹሐን ብፁዓን ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና።» በማለት እንደ አስተማረ። ማቴ.፭፥፰።

## ፫. ከኃጢአት ሃሳብና ሕልም መንጻት

ከኃጢአት ከመንጻት በተጨማሪ ከሃሳብና ከግምት፣ ከመላ ምትም መንጻት ይገባል። አንድ ቅዱስ «የአንተነትህን እውነተኛ ገጽታ የሚገልጠው ውጫዊ ሥራህ ብቻ ሳይሆን የምታስበው ሃሳብና የሚኖርህ መላምታዊ (ግምታዊ) አስተያየትም ጭምር ነው» ብሏል። የተለያዩ ሦስት ሰዎች በጨለማ ውስጥ ያዩትን ሰው — «ሌባ ነው:- ወንበዴ ነው:- ማንም ሳያየው ለመጸለይ የመጣ ክርስቲያን ነው።» ቢሉት — የሦስቱም ሃሳብና መላምት ከልባቸው የመነጨ ነው። ጌታችንም «መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካምን ያወጣል:- ክፉም ሰው ከልቡ ክፉ መዝገብ ክፉውን ያወጣል።» በማለት ልብ የመልካምም የክፉም ሃሳብና ግምት ምንጭ መሆኑን ተናግሯል። ሉቃ.፮፥፵፭።

ስለዚህ ሃሳባችን ክፉ ከሆነ ልባችን ገና አልነጻም:- ልቡ ንጹሕ የሆነ ሰው ምን ጊዜም ቢሆን የሚያስበው መልካም ነገርን ነውና። ሰዎች ስለሠሩት ክፉ ሥራም ክፉ አያስብም በንጹሕ ልቡ ይቅርታ ያደርግላቸዋል እንጂ። ክፉ ሃሳብንም አይቀበልም።

ሰዎች ስለንጽሕናቸው የሚጨነቁ:- ስለሃሳባቸው ንጽሕና የሚጠነቀቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን በሕልማቸው ኃጢአት ሊሠሩ ወይም የቀደመ ኃጢአታቸውን ያስታውሱ ይሆናል። እነዚህ ሰዎች የቀደመ ኃጢአታቸውን ማስታወስና ማሰብ የለባቸውም ከዚያ ሃሳብ መንጻት አለባቸው። ኃጢአትን ከማለም ነጻ የሚሆኑበት የተወሰነ ጊዜም ያስፈልጋቸዋል። ይህ ጊዜም የቀድሞው የኃጢአት ትዝታ ከኅሊናቸው እንዲጠፋ ይረዳቸዋል። በዚህ ምትክም አእምሮአቸው ንጹሑንና ለንስሐ ሕይወት የሚስማማውን ሃሳብ እንዲመዘግብ ይሆናል — ያኔ የሚያልመው ነገርም ንጹሕ ይሆናል።

## ፬. ከማያስፈልጉ ነገሮች መንጻት

ከማያስፈልጉ ነገሮች መንጻት ማለት — ከሚያልፉና ጥቅም ከሌላቸው ነገሮች መንጻት ማለት ነው። እነዚህ የሚያልፉና የማይጠቅሙ ነገሮች ወይ የሚሠሩ፣ የሚነበቡ፣ የሚታዩ፣ የሚደመጡ፣ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ኃጢአትም ጽድቅም አይደሉም። እነዚህን ነገሮች የሚያዘወትር ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖርበትን፣ ራሱን የሚቀድስበትን፣ ንስሐ የሚገባበትን:- ጊዜ ያባክናል። ከዚህም የተነሣ መንፈሳዊ የሆነውን ነገር



ለመሥራት ጊዜ ያጣል። እነዚህ የማያስፈልጉና የማይጠቅሙ ነገሮች ለመንፈሳዊ ሥራ እንቅፋት ይሆናሉና ራሳችንን ከእነርሱ ማላቀቅና ማንጻት ያስፈልጋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «የሚታየው የጊዜው ነውና የማይታየው ግን የዘለዓለም ነው።» በማለት ስለተናገረ የምናየው ነገር የማይጎዳ ነገር ግን የሚያልፍ ነውና ጊዜአችንን ለሚጠቅምና ዘለዓለማዊ ለሆነው መንፈሳዊ ሥራ ማዋል ይገባናል። ፪ቆሮ.፬፥፲፰። የሚታየውን ጊዜያዊና ኃላፊ የሆነውን ነገር የማይመለከት ሰው እንደ ዳዊት:- «ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል» ይላል። መዝ.፸፪፥፳፰። ፍጹም የሆነው ወደ እግዚአብሔር መቅረብም ያለንጹሕ ልብ አይቻልምና የልብ ንጽሕና እጅግ አስፈላጊ ነው።

ከኃጢአት መንጻት ቅድስና እንጂ የልብ ንጽሕና አይደለም። ከኃጢአት መንጻት ከኃጢአት መለየት:- ኃጢአትን አለመሥራት ነው። የልብ ንጽሕና ግን በፍጹም ልብ፣ በፍጹም ሃሳብ፣ በሥራም ያለማቋረጥ ከእግዚአብሔር ጋር በሚስማማ ሕይወት መኖር ነው።

በዓለም ውስጥ ብዙ የሚታዩና የሚሰሙ ነገር ግን የማይጠቅሙ ነገሮች አሉ። ለእነርሱ ትኩረት አለመስጠትና ራስንም ከእነርሱ ማንጻት ይገባል። ዓይኖቻችን የሚያዩት ነገር ባገኙ ጊዜ ትኩረታችንን ለዚያ ነገር መስጠት አይገባም:- ዓይንን ብቻ ሳይሆን ሕዋሳቶቻችንን ሁሉ:- ሕዋሳት ሁሉ የሃሳብ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉና። ያን ጊዜ በአእምሮአችን የተቀረጸውን ሃሳብ ሥፍራ ስንሰጠውና ሳናተኩርበት ያሳለፍነው እንደሆነ ይህ የልብ ንጽሕና ቅድመ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል ወይም ደግሞ አእምሮአችንን ያስገዛንለትና ጊዜ የሰጠነው እንደሆነ የኃጢአትን ፍላጎት በውስጣችን ሊፈጥር ይችላል:- ይህ ሃሳብ በእግዚአብሔር ሰው ልቡና ውስጥ የኃጢአትን ፍላጎት ሳይሆን በልቡናው ውስጥ ለኃጢአትና ለዓለም ነገር በመሞት ላይ እንዲያተኩር የሚያነሣሣ ሃሳብ ሊፈጥርበት ይችላል።

እነዚህ የሚያልፉና የሚጠፉ ሃሳቦች ሌላው ቢቀር ጊዜ ያባክናሉ። ጊዜ የሕይወት አንድ ክፍል ነው። እግዚአብሔርም ጊዜን የሰጠን እንድንጠቀምበት፣ ነፍሳችንን እንድናድንበት፣ ሃሳባችንንና ልቡናችንን እንድናነጻበት:- ስሜታችንን ሁሉ ለእግዚአብሔር እንድናስገዛበት ነው እንጂ እንድናባክነው ስላይደለ በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል።

አእምሮን ጥቅም በሌለው ነገር ማስጨነቅ የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጥ የሌለ መሆኑን የሚገልጥ ነው። ስለዚህ በልቡናችንና በአእምሮአችን

www.ethiopianorthodox.org

ከእግዚአብሔር አስበልጠን ሥፍራ የምንሰጠውና የምናተኩርበት ነገር መኖር የለበትም።

ፍጹም ንጹሕ የሆነ ልብም ለሚያልፉና ለማይጠቅሙ የዚህ ዓለም ነገሮች ሁሉ የሞተና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሕያው የሆነ ልብ ነው። አእምሮው በማይታየው ሰማያዊ ነገር የተያዘ ስለሆነ ለሚታየው ኃላፊ ነገር አይገዛም። ያለእረፍትና ያለማቋረጥም ሰማያዊውን መለኮታዊ ምሥጢር ስለሚያስብ ለማይጠቅም ነገር ሥፍራና ጊዜ የለውም። ይህም ከንጽሕና ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ ነው።

ሰው በሚታዩ ነገሮች ሊሠራባቸው እንጂ የሚታዩት ነገሮች በሰው ላይ ሊሠሩበት አይገባም። ሰው ልቡን ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚያደርግ በሚታየው ነገር ቢሠራም ትኩረቱ ስለሚታየው ነገር አይደለም። በወንጌል «ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም:- ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል – ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል:- ሁለተኛውንም ይንቃል» እንደተባለ በሚታየው ዓለም ስንኖር የማይታየውን በማሰብ ትኩረታችንን ከሚታዩትና ከማይጠቅሙት የዚህ ዓለም ነገሮች ማራቅ ይጠበቅብናል። ማቴ.፮፥፳፬። ይህም ከንጹሕ ልብ የሚጠበቅ ነው። በመጽሐፍ «ነገር ግን ያለ ሃሳብ እንድትኖሩ እወዳለሁ።» ተብሏልና የሚታየውን ኣላፊ ነገር አለማሰብ የልብ ንጽሕና ምልክት ነው። ፩ቆሮ.፯፥፴፪። ለዚህ ነው ቀደምት አባቶቻችን «ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ:- በክርስቶስም በማመን ያለውን ጽድቅ አገኝ ዘንድ ስለ እርሱ ነገር ሁሉ ጉዳት እንደሆነ እቆጥራለሁ።» በማለት የሚታየውን ዓለም የናቁት። ፊል.፫፥፰። ዓለም በእነዚህ ቅዱሳን ዘንድ የተናቀች ስለነበረች እነርሱ በሰላም ይኖሩ ነበሩ:- ይህም ቅዱስ ጳውሎስ «በዚህች ዓለም የሚጠቀሙ በሙሉ እንደማ ይጠቀሙባት ይሁኑ:- የዚህች ዓለም መልክ አላፊ ነውና።» ያለውን በተግባር እንደፈጸሙት ያስረዳናል። ፩ቆሮ.፯፥፴፩።

ማንኛውም ሃሳብ በራሱ ውጤት የሌለው አይደለም ነገር ግን ለሌላ ሃሳብ ምንጭ ይሆናል። ሃሳብ በአእምሮአችን ውስጥ በሰፈነ ጊዜ ለተለያዩ ግምቶችና ሕልሞች ምንጭ ይሆናል። ለጸሎት በምንቆምበት ጊዜ ከእነዚህ ሃሳቦች የተነሣ በፊታችን የሚመላለሱት ልዩ ልዩ ነገሮች ተመስጦአችንን እንድናጣ ያደርጉናል። ስለዚህ የዚህ ዓለም ሃሳብና ሥጋዊ ስሜት ጊዜአችንን እንዳያባክነው መጠንቀቅ ይኖርብናል። የቀደመ ልማዳችን በኀሊናችን በመጣ ጊዜ ወዲያው በመነሣት «አቤቱ ከንቱ ነገርን እንዳያዩ ዓይኖቼን መልስ» በማለት መጸለይ ይገባል። መዝ.፻፲፰፥፴፯።



የአእምሮ መንቃትና ከሃሳብ ጋር መዋጋት ከአእምሮና ከልብ ንጽሕና ይቀድማል። ስለዚህ ለእግዚአብሔርና ለእርሱ መንግሥት እንግዳ የሆነ ሃሳብ ሁሉ ከእኛ መራቅ አለበት። ልቡናችንም እንዲሁ ከዓለማዊ ሃሳብ የተለየ መሆን አለበት። ሰማያዊ በሆነው ሃሳብ ደስተኞች ለመሆን ራሳችንን ከዓለም ማራቅ አለብን። የሰው ስሜቱ ከዓለም የተለየ ከሆነ ዓለማዊ የሆነውን ነገር ለማሰብ የሚያነሣሣው ነገር አይኖርም። ዓለማዊ የሆነ ነገርም ወደእርሱ በመጣ ጊዜ ይቃወመዋል:- አእምሮው በሰማያዊ ሃሳብ የተያዘ በመሆኑም ዓለማዊውን ነገር አያስበውም ምክንያቱም «አቤቱ ሕግህን እንደምን እጅግ ወደድሁ? ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው።» በማለት የሚያገኘውን ደስታ ያዘገይበታልና ነው። መዝ.፻፲፰፥፺፯።

ታዲያ ሰው ከልብ ንጽሕና ሊደርስ የሚችለው እንዴት ነው? ከልብ ንጽሕና ሊደርስ የሚችለው – ከኃጢአት ሲነጻ፣ ከሕልም፣ ከሃሳብና ከግምት ሲነጻ፣ እንዲሁም ከማይጠቅም ወይም ከማያስፈልግ ነገር ሲነጻ ነው። እነዚህ ሁሉ የንጽሕና አሉታዊ ገጽታዎች ናቸው።

## ፭. የንጽሕና አወንታዊ ገጽታ

ንጹሕ ልብ የፍቅረ እግዚአብሔር እንጂ የፍቅረ ዓለም ማደሪያ አይደለም። ንጹሕ ልብ ያላቸው ሰዎች የሚያደርጉትን ሁሉ እግዚአብሔርን በማፍቀር ያደርጋሉ እንጂ ስለታዘዙ አይደለም። ከኃጢአትም የሚለየው በልቡ ከሰፈነው ጥልቅ የእግዚአብሔር ፍቅር የተነሣ የኃጢአትን ጠቃሚ አለመሆን በመገንዘብ ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ባደረበት በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች በግልጽ ይታያሉ። እነርሱም «ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት፣ ነው። እነዚህን የሚከለክል ሕግ የለም።» ገላ.፭፥፳፪። እነዚህ ፍሬዎችም ይህ ሰው በሕግና በትእዛዛት ከመመራት አልፎ ስለፍቅር ብሎ ከኃጢአት መለየትንና መልካም መሥራትን ገንዘብ ከማድረግ ደረጃ ላይ መድረሱን ያመለክታሉ። ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ጋርም ያለው ግንኙነት ወደፍጹም ፍቅር ደረጃ ማደጉን ያሳያሉ። የሚሠራው መልካም ተግባር ሁሉ በልቡ ከሰፈነው ታላቅ ፍቅረ እግዚአብሔር የሚመነጭ ነው። ፍቅር የመንፈስ ፍሬና የልብ ንጽሕና ምልክት ነው።

ከፍቅር በተጨማሪ ደግሞ ሌሎች የመንፈስ ፍሬዎችም አሉ። እኛም ደግሞ ምናልባት ወደንጽሕና ሕይወት የሚያደርሰን ሁሉንም የመንፈስ ፍሬዎች ማፍራት ነውን? እንል ይሆናል። መልሱ አዎን ነው:- ምክንያቱም በመጽሐፍ «ለንስሐ የሚገባ ፍሬን አድርጉ» ተብሏል:- እንዲሁም ደግሞ

www.ethiopianorthodox.org

«ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል:- ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል።» ብሎ ተነግሯል። ሉቃ.፫፥፰። ዮሐ.፲፭፥፪። ስለዚህ ከዚህ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ለመድረስ ልንተጋ ያስፈልጋል። ከዚህ ንጽሕና በኋላ ለዘለዓለሙ የሚሰጠን ንጽሕና አለ – እርሱም ኃጢአትን ከማወቅ ንጹሕ የሆነ ልብ ነው።

## ፮. ልብን ኃጢአትን ከማወቅ ማንጻት

የልብ ንጽሕና በሁለት ሊከፈል ይችላል። አንዱ በዚህ ምድር ላይ እያለን የምናገኘው የልብ ንጽሕና ሲሆን ሁለተኛው ግን በዚህ ምድር ላይ ያለውን ሕይወት ፈጽመን ለዘለዓለም ስናልፍ የሚሰጠን የልብ ንጽሕና ነው። ይህን ዘለዓለማዊ የልብ ንጽሕና ለማግኘትም መናፈቅና በትጋት መጸለይም ይኖርብናል።

ክፉንና መልካሙን ከምታሳውቀው ዛፍ በበላን ጊዜ የቀደመ ንጽሕናችንን አጣን። ቀድሞ መልካሙን ብቻ የምናውቅ የነበርነው በኋላ ግን ክፉንና መልካሙን፣ ኃጢአትንና ጽድቅን ዐወቅን።

ክፉ የሆነ ኃጢአትን አለማወቅ በዚህ ምድር ላይ ሳሉ ሊደረስበት የማይችል የንጽሕና ደረጃ ነው። የበላነውን ፍሬ የተፉን እንደሆነ ግን ለዘለዓለም ሊሰጠን ይችላል። ያን ጊዜም ልንደርስበት እንችላለን። ኃጢአትን ከማናውቅበት ደረጃ ስንደርስ ከመልካም ነገር በቀር ምንም ክፉ ነገር የማናውቅ ፍጹማን እንሆናለን። ከበለስ ፍሬ ከመብላታቸው በፊት ለአዳምና ሔዋን የነበራቸውን ንጽሕና ገንዘብ እናደርጋለን።

እንግዲህ ኃጢአትን ከማወቅ መንጻት በዚህ ምድር ላይ የማይቻል ከሆነ ምን ልናደርግ ይገባናል? ልናደርግ የሚገባን በምድር ሳለን በንጽሕና መንፈሳዊውን ሕይወት በመኖር እግዚአብሔር ዘለዓለማዊውን የልብ ንጽሕና እንዲሰጠን መለመን ነው።

ክፍል ስድስት

# ንስሐን ከፈተና መከላከል (መጠበቅ)

## ፩. ወደ ኃጢአት አለመመለስ

ለሰው ከዕለታት አንድ ቀን ንስሐ መግባት ቀላል ነው። ነገር ግን አስፈላጊው ያለማቋረጥ ንስሐ መግባት መቻሉ ነው። ያለማቋረጥ ንስሐ መግባት የቻለ እንደሆነ የሕይወት ዘመኑን በንስሐ ስለሚኖር ወደኃጢአት አይመለስም። ስለዚህ የንስሐ ሕይወታችን የማይቋረጥ እንዲሆን ያገኘነውን የንስሐ ሕይወት ከፈተና መከላከል ይኖርብናል። ምክንያቱም ወደ ኃጢአት መመለስ ቀላል ነውና።

ሰው በንስሐ አማካኝነት ከአመለጠው በኋላ መልሶ በኃጢአት እንዲወድቅ የሚፈልግ ሰይጣን በተለያየ መንገድ ከመፈተን ፈጽሞ አያርፍም። ከረጅም ጊዜ በኋላም ቢሆን በሚችለው ዘዴና መንገድ ወደኃጢአት ሊመልሰው ይጥራል። ለዚህ የመሳፍንት ዘመን ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል።

በዚያ ዘመን እሥራኤል አምላካቸውን እግዚአብሔርን ትተው በጣዖት አምልኮ ከአሕዛብ ጋር አንድ ሆኑ – ተደባለቁ። ምንም እንኳ ኃጢአታቸው ከፍተኛ ቢሆን እግዚአብሔር ግን ከመካከላቸው መሳፍንትን አስነሥቶ ማራቸው። ቢሆንም «መስፍኑ ከሞተ በኋላ ወደ ኃጢአት ይመለሱ ነበር። ሌሎችንም አማልክት በመከተላቸው እነርሱንም በማምለካቸውና ለእነርሱ በመስገዳቸው አባቶቻቸው አድርገውት ከነበረው የከፋ ያደርጉ ነበር:- የእልከኛነት ሥራቸውንና መንገዳቸውን አልተውም ነበር።» መሳ.፪፥፲፱።

አንዳንድ ጊዜ የንስሐ ዘመናቸው እስከ አሥር ዓመት ይደርስ ነበር። ይሁን እንጂ እነርሱ ግን ዳግመኛ ወደኃጢአት ይመለሱ ነበር:- ይህም በመጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል። «ምድሪቱም አርባ ዓመት ዐረፈች:- የቄኔዝም ልጅ ጎቶንያል ሞተ። የእሥራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት እንደገና ክፉ ሥራ ሠሩ።» መሳ.፫፥፲፩–፲፪። «ምድሪቱም ሰማንያ ዓመት ዐረፈች...ናዖድም ከሞተ በኋላ የእሥራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት

www.ethiopianorthodox.org

እንደገና ክፉ ሥራ ሠሩ።» መሳ.፫፥፴፤ መሳ.፬፥፩። «ምድሪቱም አርባ ዓመት ያህል ዐረፈች... የእሥራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ።» መሳ.፩፥፴፩። መሳ.፮፥፩።

ይህን የመሰለው ከንስሐ በኋላ ወደ ኃጢአት መመለስ ከልቡናቸው ፈጽመው ወደ እግዚአብሔር በማይመለሱና በንስሐ ላይ ጥብቅ አቋም በሌላቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ በመደጋገም የሚታይ ነው። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ገና የኃጢአት ኑሮ ያልበቃቸውና ኃጢአትም የሚናፍቃቸው ናቸው። ውሻ ወደትፋቷ እንደምትመለስ ወደትፋት ኃጢአታቸው የሚመለሱ እነዚህን ቅዱስ ጴጥሮስ «በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዕውቀት ከዓለም ርኩሰት ከአመለጡ በኋላ ዳግመኛ በእርሷ ተጠላልፈው የተሸነፉ ቢሆኑ ከፊተኛው ኑሮአቸው ይልቅ የኋለኛው የባሰ ሆኖባቸዋል። ዐውቀዋት ከተሰጠቻቸው ከቅድስት ትእዛዝ የሚመለሱ ከሆነ የጽድቅን መንገድ ባላወቋትም በተሻላቸው ነበርና። ውሻ ወደትፋቱ ይመለሳል የታጠበች እርያ በጭቃ ለመንከባለል ትመለሳለች እንደተባለው ምሳሌ» በማለት ዘልፏቸዋል። ፪ጴጥ.፪፥፳–፳፪።

ብዙዎች ከጌታ ጋር እስከተወሰነ ደረጃ ሄደው ጉዞው ሲከብዳቸውና መስቀሉን ተሸክመው እስከመጨረሻው መዝለቅ ሲያቅታቸው የጀመሩትን ጉዞ ሳይፈጽሙ ይተውታል። ወይም ደግሞ ከጌታ ይልቅ ኃጢአትን መርጠው ወደዓለም ይመለሳሉ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለማያስተውሉት የገላትያ ሰዎች የተናገረው ለእነዚህም ይሠራል። ገላ.፫፥፩–፫። እነዚህም በመንፈስ ጀምረው በሥጋ ፈጽመዋልና። ሌላው ምሳሌ ደግሞ ዴማስ ነው። አብሮት የሚሠራ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ መሆኑን ቢመሠክርለትም በአገልግሎቱ እስከ መጨረሻ ዘመኑ አልዘለቀምና «ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና» በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሯል። ፊልሞ.፳፬ ፤ ፪ጢሞ.፬፥፲።

ለሐዋርያነት አገልግሎት ተጠርቶ ወንጌልን ይሰብክ የነበረውን ዴማስን የዓለም ፍቅር ወደኋላ ከመለሰው ከንስሐ በኋላ ሕይወትን ወደኃጢአት እንዳይመለስ በከፍተኛ ጥንቃቄ መጠበቅ ያስፈልጋል ማለት ነው። እንደዚህ ያሉትን ሌሎች ምሳሌዎችም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ:- አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ።» ካለ በኋላ «መጨረሻቸው ጥፋት ነው:- ሆዳቸው አምላካቸው ነው:- ክብራቸው በነውራቸው ነው:- ሃሳባቸው ምድራዊ ነው።» ብሏቸዋል። ፊል.፫፥፲፰–፲፱።



እንግዲህ ከንስሐ በኋላ ወደዓለም መመለስ ቀላል በመሆኑ የንስሐ ሕይወታችንን በጽኑ ካልጠበቅነውና ከኃጢአት ካልተከላከልነው ተመልሰን ወደኃጢአት ልንገባ እንችላለንና ንስሐ ገብተን በጀመርነው መንፈሳዊ ሕይወት ልንኩራራና ልንዘናና አይገባም። ዋናው ነገር የጀመርነውን የንስሐ ሕይወት የማይቋረጥና እስከ መጨረሻው ግብ የሚደርስ የኑሮ ፍሬ እንዲያፈራ ማስቻል ነው። ስለዚህ ንስሐ የምንገባ ሁሉ በመንፈስ ጀምረው በሥጋ እንደሚፈጽሙት መሆን የለብንም።

ሳኦል ከተቀባና ከነገሠ በኋላ ታላቅም በሆነ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር የጀመረውን ለመፈጸም ባለመቻሉና ወደ ኃጢአት ተመልሶ ስለበደለ የእግዚአብሔር መንፈስ ተወስዶበት የሚያስጨንቅ መንፈስ ተልኮበታል። ፩ሳሙ.፲፥፱–፲፩፤ ፲፮፥፲፬።

በእግዚአብሔር ቸርነት ከግብፅ የወጡት:- መና ከሰማይ ወርዶላቸው ውኃ ከአለት ፈልቆላቸው የተመገቡት፣ ሰማያዊም ሕግ የተሰጣቸው፣ «እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለንም» ዘጸ.፳፬፥፯። ያሉት እሥራኤላውያን ወደ ኃጢአታቸው ተመልሰው ብዙ ጊዜ በደሉ:- በእግዚአብሔርም ላይ አንጎራጎሩ:- የጥጃ ምስል ሠርተውም ጣዖት አመለኩ – ዘጸ.፴፪። በዚህም የተነሣ እግዚአብሔር ተቆጥቶባቸዋልና ተዋቸው – ተስፋ የገባላቸውንም ከነዓንን እንዳይወርሱ ሁሉም በምድረ በዳ ሞቱ። «መጨረሻቸው ጥፋት ነው» ተብሏልና። ስለዚህ የንስሐን ሕይወት ስለጀመርንበት ሳይሆን ስለምንፈጽምበት ሁኔታ አብዝተን ልንጨነቅ ይገባናል።

መናፍቃንም ቢሆኑ ሕይወታቸው በኑፋቄ የሚጀምር አይደለም። ለምሳሌ – አውጣኪ ጥሩ የቁስጥንጥንያ መነኩሴ ነበር፣ አርዮስም የታወቀ የአሌክሳንደርያ ካህን ነበር፣ ንስጥሮስም የታወቀ መምህርና የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስም ነበር። እነዚህ ሁሉ እንግዲህ መጨረሻቸው ኑፋቄ ሆነ እንጂ የጀመሩት በመንፈስ ነበር። ከዚህም ለንስሐ ሕይወታችን በእጅጉ ልንጠነቀቅለትና ከክፉ አወዳደቅም ልንከላከልለት የሚገባ መሆኑን እንማራለን።

ከመጥፋት ለመዳን ከሰዶም መውጣት ብቻውን በቂ አልነበረም – ወደሰዶም አለመመልከትም ጭምር እንጂ። የሎጥ ሚስት በመላእክት እጅ ተይዛ ከሰዶም ወጣች:- እሳቱም አላቃጠላትም። ነገር ግን ወደኋላዋ ብትመለከት የጨው ሐውልት ሆና ቀርታለች። ዘፍ.፲፱፥፲፮። ስለዚህ የንስሐን ሕይወት መኖር ከጀመርን በኋላ ወደኋላ ዞረን ትተነው የመጣነውን

www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአትና የዓለም ኑሮ መመልከት አያስፈልግም በንስሐ ሕይወት ተጠናክሮ ወደፊት መግፋት ነው እንጂ።

ወደኋላው የሚሄድ የገነባውን የሚያፈርስ ሰውን ይመስላል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለዚሁ ነገር ሲናገር «ብዙ ጊዜ በእርሷ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣ መሬት:- ለሚያርሷትም ደግሞ የምትጠቅምን አትክልት የምታበቅል — ከእግዚአብሔር በረከትን ታገኛለችና:- እሾህንና ኵርንችትን ግን ብታወጣ የተጣለች ናት:- ለመረገምም ትቀርባለች:- መጨረሻዋም መቃጠል ነው።» ካለ በኋላ ዕብ.፮፥፯—፰። ይህንኑ በሚመስል አነጋገር ደግሞ «የእውነትን ዕውቀት ከተቀበልን በኋላ ወድደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለኃጢአት መስዋዕት አይቀርልንምና:- የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ።» ብሎአል። ዕብ.፲፥፳፮—፳፯።

ስለዚህ ንስሐ በምንገባ ጊዜ መኩራት ሳይሆን መፍራት ይገባናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመኻል:- ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ።» በማለት ይመክረናል። ሮሜ.፲፩፥፳። ስለሆነም ልባችን በእምነት የጸና በእግዚአብሔርም የሚታመንና በእርሱም ኃይል ንስሐ በመግባት ሰይጣንን ድል የሚያደርግ መሆን ይገባዋል። ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ጴጥሮስ «ለሰው ፊት ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ ብትጠሩ በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ» ብለዋል። ሮሜ.፪፥፲፩። ፩ጴጥ.፩፥፲፯። ይህ ፍርሃትም ለመንፈሳዊ ሕይወት ጥንቃቄ ማድረግን የሚያመለክት ነው። ይህ ጥንቃቄም ተነሳሒው የንስሐ ሕይወቱን ወደኋላ ከመመለስ በመከላከል የቱን ያህል ጥብቅ እንደሆነ ያሳያል። በንስሐው ጊዜ ለእግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ማክበሩንና ታማኝነቱን ያመለክታል። ተነሳሒው ቀድሞ የነበረበት የኃጢአት ሕይወት ስለማይረሳውም ወደዚያ አይመለስም — «እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ — ንስሐም ግባ» የሚለውን ቃል ዘወትር ያስባልና። ራእ.፪፥፬።

ወደቀደመው የኃጢአት ሕይወት አለመመለስ ማለት ከንስሐ በፊት የነበሩትን ክፉ ልማዶች ፈጽሞ ማስወገድ ማለት ነው። ለምሳሌም:-

፩. አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቸርነት ዐውቆ ንስሐ ከመግባቱ በፊት ቁጡ ሊሆን ይችላል:- በንስሐ ዘመኑ ቁጣውን ካልተወ ንስሐ ገብቷል ሊባል አይችልም። ስለዚህ የቁጡነቱን ልማድ ፈጽሞ ከልቡናው ማስወገድ ይገባዋል። በመጽሐፍ «ፍቅር ያስታግሣል፤ ፍቅር ያስተዛዝናል፤ ፍቅር



አያቀናናም፤ ፍቅር በራስ አያስመካም፤ ፍቅር አያስታብይም፤ ፍቅር ለእኔ ብቻ ይድላኝ አያሰኝም፤ ፍቅር አያበሳጭም» የሚለው የቅዱስ ጳውሎስ ምክር ተመዝግቧል። ፩ቆሮ.፲፫፥፬—፭። እግዚአብሔር አምላካችንም ብስጭትንና ንዴትን አይወድም። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ይህን በተመለከተ «ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቁጣም የዘገየ ይሁን:- የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና» ሲል የተናገረው ለዚህ ነው። ያዕ.፩፥፳። ቅዱስ ጳውሎስም ስለዚሁ ሲያስተምር «መራርነትና ንዴት ቁጣም:- ጩኸትም:- መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገዱ:- እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ» ብሎአል። ኤፌ.፬፥፴፩—፴፪። ንስሐ የገባ ሰው ቁጣውንና ብስጭቱን ካልተወ በዚህ ልማዱ ሌሎችን ሰዎች ማሰናከሉ አይቀርም:- አሮጌውን እራፊ በአዲሱ ልብስ ላይ እንደመለጠፍ ነው። ማቴ.፱፥፲፮። ስለዚህ ከዚህ ክፉና ከፈቃደ እግዚአብሔር ውጭ ከሆነ ልማድ መለየትና ልቡናንም ከእርሱ ማጽዳት በንስሐ ለሚኖር ብቻ ሳይሆን ለክርስቲያኖች ሁሉ ተገቢና ጠቃሚ ነው።

ምናልባት ስለእግዚአብሔር ቤትና ስለሃይማኖታችን ልንበሳጭና ልንቆጣ እንችላለን። ቁጣው ራሱ ግን መንፈሳዊ ሊሆን ይገባል:- በመጽሐፍ «ተቆጡ:- ነገር ግን ኃጢአትን አታድርጉ» ተብሏልና። መዝ.፬፥፬። ይሁን እንጂ የዚህ መንፈሳዊ ቁጣ ግቡ ብቻ ሳይሆን ሂደቱና አገላለጡ:- አነጋገሩም ጭምር መንፈሳዊነት ያልጎደለውና ወደኃጢአትነት የማያመራ መሆን አለበት። መንፈሳዊ ነው በሚል ሰበብም የተጠናወተንን ክፉ ልማድ ለመሸፋፈን መሞከር የለብንም። እጅግ ቁጡ የሆንን እንደሆነና መራራ ቁጣ የምንቆጣ ከሆነ አገልግሎታችንን የምናስነቅፍ ከመሆኑም በላይ ጠባያችን ከክፉ አመል ያልነጻና ከሰዎች ጋርም መልካም ግንኙነት የማድረግ መንፈሳዊ ዘዴ የሌለን መሆኑን እናንፀባርቃለን — በዚህም እናሰናክላለን:- ንስሐችንም አማናዊ አይሆንም።

ስለእግዚአብሔር ቤትና ስለሃይማኖታችን በመቆርቆር የምንበሳጨው ብስጭትና የምንቆጣው ቁጣ ከዓለማዊውና ሥጋዊው ብስጭትና ቁጣ በይዘቱ፣ በባሕርዩና በአገላለጡ እንዲሁም በአፈጻጸሙ ፈጽሞ የተለየ ነው። መንፈሳዊ እና ሰማያዊ በመሆኑ በመንፈሳዊ ቃላት የሚገለጥና የሚነገር ትሑት በመሆኑ ወደኃጢአት አያመራም። ለምሳሌ አቢግያ ስለእውነት ከዳዊት ጋር በተከራከረች ጊዜ ጥበብና ማስተዋል በተመላበት አኳሁዋን ተናገረች እንጂ አልተቆጣችም ነበር። ፩ሳሙ.፳፭። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ኃጢአቷን ለመደበቅ ለሞከረችው ሳምራዊት ሴት

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአቷን በነገራት ጊዜ በመንፈሳዊና በማይጎዳ ሁኔታ እንጂ በቁጣ አልነገራትም። ዮሐ.፰።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች የሆንን ሁሉ ኃጢአትንና ወደኃጢአት የሚያደርሰንን ክፉ ልማዳችንን በመንፈሳዊ መንገድ እንጂ በቁጣ ልንቃወም አይገባም። ንስሐ ከመግባታችን አስቀድሞ የቁጡነትና የብስጩነት ልማድ ከነበረን ከንስሐ በኋላ በምንኖረው ሕይወት እግዚአብሔር እንዲደሰትብንና ንስሐችንም እውነተኛ እንዲሆን የመቆጣት፣ የመበሳጨትና የመናደድ ክፉ ልማዳችንን ፈጽሞ ከእኛ ማራቅ ያስፈልገናል።

፪. ሌላው ምሳሌ ደግሞ መራገምና መንፈሳዊ ወቀሳን ማደባለቅ ነው። አንድ ሰው ከንስሐ በፊት በነበረው ሕይወት ተራጋሚ ነበር – ንስሐ ገባ ወይም ንስሐ እንደገባ ራሱን ቆጠረ– ነገር ግን የተወሰኑ ልማዶቹን ከራሱ አላስወገደም – ከንስሐ በኋላም መራገሙንና መርዘኛ ንግግሩን አልተወም – ሌሎችንም ስለኃጢአታቸው ሲወቅስ ይገኛል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው በንስሐ የሚኖር መሆኑን የረሳ፣ የሚወቅሰውና መውቀስም ያለበት ራሱን ብቻ እንደሆነ የዘነጋ፣ የራሱንም ኃጢአት ያልረሳና ያልተወ ነው። በእርሱ ግምት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ዝለፍና ገሥጽ ምክርም» ሲል ለጢሞቴዎስ የነገረውን መፈጸሙ ነው። ነገር ግን መንፈሳዊውን ዘለፋ:- ተግሣፅና ምክር ግን አላወቀም። ፪ጢሞ.፬፥፪። የመገሠፅን ዘዴም ፈጽሞ ረስቶታል። እንዲህ ብሎ ለደቀመዝሙሩ ለጢሞቴዎስ የመከረ ቅዱስ ጳውሎስ የኤፌሶንን ካህናት ደግሞ «ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በዕንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠፅ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ» በማለት የመገሥፅን ዘዴ አስተምሯል። የሐዋ.፳፥፴፩። እኛ ሰዎችን ስንገሥፅና ስንመክር በፍቅርና በዕንባ ነው ወይስ በኩራትና በበላይነት ስሜት?

በንስሐ ሕይወት የሚኖር ሰው ማንንም አይገሥፅም። የሚገሥፅ እንኳ ቢሆን ሥልጡንነትን አይዘነጋምና በየዋህነት መንፈስ ተሞልቶ ይገሥፃል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ወንድሞች ሆይ:- ሰው በማናቸውም በደል እንኳ ቢገኝ – መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት። እናንተም ደግሞ እንዳትፈተኑ ራሳችሁን ጠብቁ» በማለት የተናገረውን ዘወትር ያስባልና። ገላ.፮፥፩። በንስሐ የሚኖር ሰው ሰውን የመገሠፅ አጋጣሚ ቢያገኘው ከንስሐው በፊት እርሱ ደግሞ አሁን በሚገሥፅበት ኃጢአት ወድቆ እንደነበረ ማስታወስና ማሰብ አለበት። ቀድሞ የወደቀበትን ኃጢአቱን የሚረሳና ሌሎችን በመገሠፅና በመውቀስ ብቻ የሚኖር ከሆነና በንስሐው የሚኩራራ እንደሆነ በንስሐው



እንዳልተጠቀመና የኩራት ክፉ መንፈስም እንደአሸነፈው ማወቅ ይኖርበታል። ይህ ሰው ገና ንስሐ አልገባምና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ትሳዳቢዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም» ሲል የተናገረውን በማሰብ በሌሎች ኃጢአት ከመሳደብና ሌሎችን ከመውቀስ ተቆጥበ ራሱን መመርመር ይኖርበታል። ፩ቆሮ.፮፥፲።

መራገምና መዛለፍ ለመንፈሳዊ አገልግሎት አመቺ አይደሉም:- ምክንያቱም መንፈሳዊው አገልግሎት የሚፈጸምባቸው ዘዴዎች ንጹሐን አይደሉምና።

በንስሐ የሚኖር ሰው ኃጢአቱን በማያውቀውና ምሥጢሩን ባልተረዳው ጥቅስ መሸፈን የለበትም መልካም አይደለምና። በሚናዘዝበትም ጊዜ ሳይደብቅ የቀደሙ ልማዶቹን ለምሳሌም ቁጡነቱን፣ ብስጩነቱን፣ ኃይለኛ ወይም ግንፍልተኛነቱንና ተዛላፊ ወይም ተራጋሚነቱን ከእሱ ማስወገድ አለመቻሉን ለንስሐ አባቱ መናገር አለበት። ምክንያቱም እነዚህ ክፉ ልማዶች በአዲሱ የንስሐ ሕይወቱም አልተለዩትምና ይህን ሕይወቱን ስለሚያበላሹበትና ንስሐውንም ከመንከባከብ ስለሚያግዱት ነው። መንፈስ ቅዱስ በእኔ አድሮ ሌሎችን ይገሥጻል በማለት መመጻደቅም ተገቢ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ሥራውን የሚሠራበት የራሱ መንገድና ጥበብ አለውና።

፫. ሌላው ደግሞ ንስሐ ከገባ በኋላም የቀደመ የግትርነት ጠባዩን ከራሱ ያላስወገደ ሰው ነው። ግትርነት ሁል ጊዜ ከኩራት ጋር የተያያዘ ነው። ከተሳሳተ በራስ መተማመን፣ በራስ ሐሳብ ብቻ ከመመራት፣ የሌሎችን አስተያየት ከመናቅ የሚመነጭ ነው። ይህን ግትርነቱንም በቤተ ክርስቲያን አካባቢና በሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት ሊጠቀምበት ይችላል። ሰው ሁሉም «እገሌ ከግትርነቱ የተነሣ ለማነጋገርና ለመወያየት አስቸጋሪ ነው» ይለዋል። ከዚህ ግትርነቱ ባሻገር በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ ከፍተኛ ኃላፊነት የተሰጠው፣ ንቁ፣ ሰባኪ፣ ስለመንፈሳዊነትም የሚናገር፣ የነገረ መለኮት ዐዋቂ፣ ዶግማውንና የቅዱሳንንም ታሪክ ሁሉ ጠንቅቆ የሚያውቅ በአጠቃላይ ሊቅ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ክፉ ልማዱ ግን አሁንም አብሮት አለና በንስሐ የሚኖር ነው ሊባል አይችልም። በእሥራኤል መካከል የነበሩት ተረፈ ከነዓናውያን ቀስ በቀስ እሥራኤላውያንን እግዚአብሔርን እንዳስረሷቸውና ጣዖት እንዳስመለኳቸው እንደ ተጋቡአቸውና እንደ ተዋለዱአቸው – ወደ ኃጢአትም ለመመለስ ምክንያት እንደሆኑአቸው ሁሉ ከንስሐ በኋላ ፈጽሞ ያልተወገዱ ክፉ ልማዶችም ወደኃጢአት

www.ethiopianorthodox.org

ለመመለስ ምክንያት ይሆናሉና መወገድ አለባቸው። ኢያ.፲፯፥፲፫። መሳ.፩፥፳፯–፴፫። መሳ.፫፥፩–፯።

ይህ ሰው ግን ግትርነቱን ለእውነት መቆም ነው ሊለው ይችላል። እውነት ግን የሌሎችን ሃሳብና አስተያየት ወደማክበርና ወደትሕትና ይጠራዋል። ቢሆንም አንዳንድ ኃጢአቶች «የበግ ለምድ የለበሱ» የሚያሳስቱ ሊሆኑ ይችላሉ። እውነታው ግን ያለፈው ጠባይ ወይም አመል አሁንም መኖሩ ነው። ይህ ሰውም በንስሐው አማካኝነት ከብዙ ኃጢአቶች ተላቅቆ ሊሆን ይችላል:- ይሁን እንጂ ካለፈ ኃጢአቱ ግን አልተላቀቀም – ወደንስሐ ሕይወቱም ይዞት ገብቷል። በአዲሱ ሕይወት ውስጥ አሮጌውን አመሉን ይፈጽማል። ከንስሐ በኋላ የቀደመ አመላቸውን መተው ያልቻሉ ብዙዎች ለመውደቅና ወደኃጢአት ለመመለስ ተገድደዋል። ብዙዎች ደግሞ ይህን ያለፈ ልማዳቸውን ባለማስተዋል በታላላቅ ኃጢአቶች ተዘፍቀዋል። ስለዚህ እኛም በውስጣችን ያለውን የቀደመ የግትርነት ጠባይ በማስወገድና የሰዎችን መልካምና መንፈሳዊ ምክር በትሕትና በመቀበል የንስሐ ሕይወታችንን ልንመራ ይገባናል።

፬. ሌላኛው ምሳሌ ደግሞ ንስሐ ከገባ በኋላም የሚፈርድና የሚተች ሰው ነው። ይህ ሰው ይህን የመፍረድና የመተቸት ኃጢአት እየፈጸመ ከኖረ ከረጅም ጊዜ በኋላ ወደ ንስሐ ሕይወት ይገባል። በዚህ ጊዜ ትኩረቱ ጎልተው በሚታዩት ኃጢአቶቹ ላይ በመሆኑ እንደቀድሞው ከመፍረድና ከመተቸት ለተወሰነ ጊዜ ተቆጥቦአል። የሚገርመው ነገር ግን ይህ ሰው በንስሐ ሕይወቱ መብሰሉን፣ ለእግዚአብሔርም ቅርብ መሆኑን፣ ከኃጢአትም የተለየ መሆኑን ማሰብ ሲጀምር ለጊዜው አቁሞት የነበረው የመፍረድና የመተቸት ኃጢአቱ መልኩን ቀይሮ በንስሐ ሕይወቱ ውስጥም ብቅ ማለቱ ነው። በንስሐ ያገኘውን መንፈሳዊ አመለካከት የራሱን ሥራ ለማየትና ለመመርመር ሳይሆን ሌሎችን ሊተችበት ተጠቅሞበታል። ይህም መንፈሳዊውን አመለካከት በሕይወት ውስጥ ማኖርና በንስሐ ሕይወት ማደግ ሳይሆን የመፍረድንና የመተቸትን ኃጢአት ከራስ ማራቅ አለመቻል ነው። ስለዚህ ከንስሐ በኋላ እንደገና የሚፈርድና የሚተች ሰው የቀደመ ልማዱን ለመተው አልቻለምና ወደነበረበት የኃጢአት ሕይወት ተመልሷል እንጂ የንስሐን ሕይወት እየኖረ አይደለም።

የሚፈርድና የሚተች ሰው ራሱን ከሌሎች የተሻለ አድርጎ ስለሚያምን ሁሉን ነገር ያለርኅራኄ ይተቻል በሁሉ ላይም ይፈርዳል። ለምን እንዲህ ታደርጋለህ ብለው በጠየቁት ጊዜም በነቢዩ ኤርምያስ ቃል «ተወግተው ስለሞቱ ስለሕዝቤ ሴት ልጅ ሰዎች ሌሊትና ቀን አለቅስ ዘንድ ራሴ ውኃ



ዓይኔም የዕንባ ምንጭ በሆነልኝ» በማለት ስለሌላው እንጂ ስለራሱ ሕይወት ማሰብ እንደሌለበት ለማስረዳት ይሞክራል። ኤር.፱፥፩። ነገር ግን ይህ ሰው ስለሌላ ሰው ከማልቀስ በፊት ስለራሱ ኃጢአት ማልቀስ በተገባው ነበር። ይህ ሰው ንስሐ ከገባ በኋላ ሊለቀስበት የሚገባ ኃጢአት በእርሱ ሕይወት ውስጥ መኖሩን በማስተዋል ራሱን ከዚህ ከማንጻት ይልቅ ዓይኖቹ የሌሎች ሰዎችን ኃጢአት ለማየት የተከፈቱ ስለሆኑ ሰዎችን ሲተችና በእነርሱም ሲፈርድ ይኖራል። ራሱን ደግሞ ጻድቅ አድርጎ «ንስሐ ከማያስፈልጋቸው» ሰዎች ጋር ይመድባል። ሉቃ.፲፭፥፯። በዚህ ደግሞ ፈሪሳዊውን ይመስላል ተመጻድቆአልና። ሉቃ.፲፰፥፱–፲፬። እርሱ በሳምንት ሁለት ቀን እንደሚጾመው፣ ቀማኛ፣ አመፀኛና አመንዝራ እንዳልሆነው ነገር ግን መመጻደቅን ከእርሱ ማስወገድ እንዳልቻለው ፈሪሳዊ ነው።

፭. ሌላው ሰው ደግሞ ንስሐ ከገባ በኋላ ስንፍናውን ከራሱ ማስወገድ ያልቻለ ሰው ነው። ይህ በሌሎቹ ኃጢአቶቹ ሁሉ ላይ ንስሐ የገባ ነገር ግን ስንፍናውን ያልተወ ሰው ነው። ስንፍናውም በአገልግሎቱ፣ በአምልኮቱ፣ በሥራው፣ በማንበቡ፣ በስብሰባ ተሳትፎው፣ ኃጢአቱን በመናዘዙ ሁሉ ውስጥ ሊንፀባረቅ ይችላል። ለምን እንደሚሰንፍ ሲጠይቁትም ‹ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማፍቀሬ በቂ ነው› በማለት መልስ ይሰጣል። ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር ለስንፍናው ምክንያት መሆኑ የሚገርም ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ግን «ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ:- በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ:- ለጌታ ተገዙ:- በተስፋ ደስ ይበላችሁ:- በመከራ ታገሡ:- በጸሎት ጽኑ።» በማለት ነው የሚመክረው። ሮሜ.፲፪፥፲፩–፲፪። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ራሱ «የሚወደኝ ትእዛዜን ይጠብቃል» ነው ያለው። ዮሐ.፲፭፥፲። ትእዛዙ ለሥራ መትጋትና በጸሎት መጽናት ከሆነ ይህ ሰነፍ ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚፈጽመው በስንፍናው ነውን?

፮. ሌላው ንስሐ ከገባም በኋላ የሚያጭበረብርና የሚያታልል ሰው ነው። ይህ ሰው በማጭበርበርና የተለያዩ ዝዴዎችን በመጠቀም ከፈለገው ግብ እንዴት ሊደርስ እንደሚችል ያውቃል። ንስሐ ከገባ በኋላም ይህን የማጭበርበርና የማታለል ልማዱን ከእርሱ አላስወገደውም። በንስሐ ሕይወት ውስጥ እያለም አልፎ አልፎ ወደዚያው ሊመለስ ይችላል። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ሊፈታ የማይችል ችግር መፈጠሩን በሰማ ጊዜ «ችግሩን እፈታ ዘንድ ለእኔ ተውልኝ» ይላል:- እንዴት ልትፈታዋለህ ሲሉትም ‹ዘዴውን ሁሉ ስለማውቀው እኔ በማውቀው ዘዴ አቃልለዋለሁ› ይላል። ንስሐ ከመግባቱ በፊት ይህን እየፈጸመ የኖረ በመሆኑ መፍትሔውን

www.ethiopianorthodox.org

መፈለግ አያቅተውም – ሰዎችም ይህን አስቸጋሪ ሁኔታ እንዴት አቃለለው? ሊሉ ይችላሉ። ከንስሐ በፊት የነበረውን በኃጢአት የኖረበትን ልማድ አልተወምና ከንስሐም በኋላ ስለተጠቀመበት ችግሩን ሊፈታው ችሏል። ይሁን እንጂ ይህ ሰው ንስሐ አልገባም – ክፉ ልማዱን ከልቡናው አላስወገደምና።

እርሱ ግን ከንስሐ በፊት ለዓለማዊ ጥቅም ያደርገው የነበረውን ከንስሐ በኋላ ለቤተ ክርስቲያንና ለእግዚአብሔር ብሎ ያደረገው በመሆኑ ሊጽናና ይችላል። ስለዚህ በሠራው የማጭበርበር ሥራ ራሱን አይወቅስም። ስለዚህም ከንስሐ ሕይወቱ ይወጣል – ይወድቃልም። የቀደመው አመሉ ምንም ሳይሻሻል አብሮት ስላለ አወዳደቁ የባሰ ይሆናል።

ከንስሐ በኋላ እንኳ በሰውኛ ጥበብ መመካቱ አብሮት በመኖሩና በራሱ ዘዴም በመታመኑ ይህ በመንፈሳዊነቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድርበታል ፍጻሜውም በንስሐ ሕይወቱ ከግብ ሳይደርስ መውደቅ ይሆናል። በእርሱ ዘንድ ንስሐ ማለት ዐበይት ኃጢአቶችን መተው ብቻ ይመስለዋልና።

፮. ሌላኛው ደግሞ ንስሐ የገባ ነገር ግን ራሱን የሚያጸድቅና የሚመጻደቅ ነው። የህ ራሱን ትክክለኛ አድርጎ መቁጠርን እንደመልካም የሚቆጥር ነው። በሁሉም ነገር እርሱ ምንም እንደማይበድል ሁሉ ማንኛውንም ምክርና እርማት አይቀበልም። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ምንም እንኳ በአገልግሎቱ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ ቢሆን ራሱን በማጽደቁና በመመጻደቁ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኃጢአቶችን ሊፈጽም ይችላል – ፈጽሞም ይሆናል። ስለዚህ በንስሐ ሲኖሩ ራስን ከማጽደቅና በሠሩትና በሚሠሩት መልካም ነገር በሚፈጽሙትም አገልግሎት መመጻደቅን ከራስ ማራቅ ይገባል።

፯. ሌላው ደግሞ ንስሐ ከገባ በኋላ በብስጭት የሚፈተን ሰው ነው። ይህ ሰው ከንስሐ በኋላ በሚኖረው መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የተለያዩ ፈተናዎችና ችግሮች ሲያጋጥሙት የሚበሳጭና ሰላሙን የሚያጣ ነው። ራሱንም እንደማይጠቅምና ተስፋም እንደሌለው ይቆጥራል። ብስጭት የሰይጣን ጾር ነው። የእግዚአብሔር ልጆች ብስጩዎች አይደሉም ምክንያቱም ከመንፈስ ፍሬዎች መካከል ደስታና ሰላም አሉና። ገላ.፭፥፳፪። ከብስጭትም የተነሣ ሰው ከመንፈሳዊ ጉዞው ሊወጣ:- ወደ እግዚአብሔርም የሚያደርሰውን መንገድ ሊስት ይችላል።

በመሆኑም ከንስሐ በኋላ በምንኖረው ሕይወት ከቀደመው አኗኗራችን ይዘን የመጣነውን ክፉ ልማድ እናውቅና ከእኛም እናስወግደው ዘንድ በነፃነትም እንድንኖር ራሳችንን በጥልቅ ልንመረምር ይገባል። ከነዓንን



የወረስን ሲመስለን በምድረ በዳ የጠፋን እንዳንሆን። ከአሮጌው ሕይወት የኃጢአት ቅሪት ራሱን ንጹሕ ያደረገ ሁሉ ያለድካም የእግዚአብሔርን መንገድ ያዘጋጃል:- የንስሐን ሕይወት ከጀመረ በኋላም ወደኋላ አይመለስም።

፰. ሌላውና የመጨረሻው ምሳሌ ከንስሐ በኋላ በገንዘብ ፍቅር ወይም በፍቅረ ንዋይ የወደቀው ሰው ነው። በንስሐ የሚኖር ሰው እንዴት በገንዘብ ይታለላል እንል ይሆናል። ይሁን እንጂ – ሰውየው ንስሐ ከመግባቱ በፊት ገንዘብ የሚወድና ስስታም ሊሆን ይችላል። በኋላም ንስሐ ገብቶ ወይም ንስሐ እንደገባ በማሰብ ከእግዚአብሔር ጋር በአዲስ ሕይወት ይኖራል። ምናልባትም በቤተ ክርስቲያን የታወቀ አገልጋይ ወይም በገዳም የሚኖር መነኩሴ ሊሆን ይችላል። በዚህ ደረጃ ቢደርስ እንኳ የቀደመው አሮጌው ኃጢአት (ፍቅረንዋይ) የረቀቀ ገጽታ ይዞ ሊከሰት ይችላል።

ፍቅረ ንዋይ ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለገዳም ነው በሚል ዳግመኛ ይመጣል። ይህም የሚከሰተው ከንስሐ ሕይወትና ከመንፈሳዊነት ጋር በማይጣጣም ሁኔታ ነው። በዚህ ደረጃ ሰውየው ‹እኔ ለገንዘቡ የምሳሳው ለእግዚአብሔር ቤት ብዬ እንጂ ለራሴ የማገኘው አንዳች ጥቅም የለም› በማለት ራሱን ያጽናናል። ምንም እንኳ የተናገረው እውነት ቢሆን ዓላማውና ገንዘቡ የተሰበሰበበትም ዘዴ መንፈሳዊ ያይደለ ዓለማዊ በመሆኑ ከፍቅረንዋይ ሊለይና ብሕትውና ወይም ዓለምን መናቅ ሊሰኝ አይችልም። ይህን የመሰለው ክፉ አመል በቤተ ክርስቲያንና በሀገር ገንዘብ ላይ ኃላፊነት ባላቸው ጥቂት ሰዎች ሕይወት ውስጥም ሊንፀባረቅ ይችላል። በእነዚህ ሰዎች ዘንድ የንስሐ ሕይወት አለ ለማለት አይቻልም።

ይህ ደሀዎቹን በማይረዱ ሀብታም አብያተ ክርስቲያናትም ሊታይ ይችላል። በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ያለው ገንዘብ የእግዚአብሔር አይደለምን? የሀብታሙ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ ጉባኤ መሪ ገንዘብ ስለመውደዱና ስለስስታምነቱ ለችግረኛውና ደሀው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ የገንዘብ ዕርዳታ እንዲደረግ በፍጹም አይፈቅድም። እንዲህ ዓይነቱ ሰው እንግዲህ በየትኛውም የኃላፊነትና የአገልግሎት ደረጃ ላይ ቢሆን የቀደመ የገንዘብ ፍቅሩን ከእርሱ ዘንድ ካላራቀ በንስሐ ሕይወት በመኖር ላይ ነው ሊባል አይችልም።

www.ethiopianorthodox.org

## ፲. በሁለት ሃሳብ አለማንከስ

ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ ሕዝቡን «እስከመ ቼ ድረስ በሁለት ሃሳብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ:- በኣል ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ» አለ። ፩ነገ.፲፰፥፳፩።

ማመንታት ልቡና በእግዚአብሔር አለመታመኑን:- ጽኑ ፍቅረ እግዚአብሔር አለመኖሩን:- ንስሐውም አማናዊና ፍጹም አለመሆኑን የሚገልጽ ነው። በፍጹም ንስሐ የገባ ሰው ሁለት ሃሳብ አይኖረውም። በአንድ ጊዜ እግዚአብሔርንም ዓለምንም ሊወድና እንደዚያም ዓይነት ሃሳብ ሊኖረው አይችልም። ሰው ሁለት ሃሳብ ሊኖረው የሚችለው ፈቃዱን እንጂ ልቡናውን ፈጽሞ ለእግዚአብሔር ያልሰጠ እንደሆነ ነው። ይህም ማለት እጆቹን ለሚያወጣው መልአክ ሰጥቶ ልቡን ግን ገና ከሰዶም – ከምትቃጠለዋ ከተማ ያላወጣ እንደሆነ ነው።

በልቡ ሁለት ሃሳብ ያለው ሰው የሚገባውን ንስሐም እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ብሎ እንጂ ቅድስናን በመሻት አይደለም። የዘለዓለሙን መከራና የገሃነምን ቅጣት በመፍራት ነው እንጂ በልቡ የቅድስና መሻትና ፍቅረ እግዚአብሔር ኖሮ አይደለም። ስለዚህ ከንስሐ በኋላ በልቡ ውስጥ መናወጥ ካለ ወደ ኃጢአት ይመለሳል እሊያም ልቡናው በሁለቱ ሃሳቦች መካከል ያመነታል።

ይህ ማመንታት ንስሐው ፍጹም ያልሆነ እንደሆነም ሊከሰት ይችላል። ለምሳሌ የሐናንያና የሰጲራ ሀብታቸውን ሸጠው ያገኙትን ገንዘብ በሐዋርያት እግር ሥር ማስቀመጥ ገንዘብን በመጥላትና በመናቅ እንዲሁም እግዚአብሔርን በመውደድ ሳይሆን በወቅቱ ከነበረው የሕዝቡ ሁኔታ ጋር ለመመሳሰል ነበር። ዓለምን መውደድና የገንዘብ ፍቅር ገና ከልባቸው አልተወገደምና ግማሹን ገንዘብና ንብረት ከፍለው አስቀሩ። የሐዋ.፭። የእኛም ንስሐ እንደሐናንያና ሰጲራ ከወቅቱ መንፈሳዊ ሁኔታ ጋር ለመመሳሰል መሆን የለበትም፥ ፍጹምና የኃጢአት ቅሪት ያልተተወለት እንጂ። ይህም ማለት በልማድ ላይ ያልተመሠረተና ልቡናን ከኃጢአት ፍቅር ነፃ በማድረግ የሚፈጸም ንስሐ ማለት ነው።

ፍጹም ያልሆነና ለመመሳሰል ተብሎ የሚፈጸም ንስሐ በሁለት ልብ ማመንታትን ይጋብዛል። ራሔል የአባቷን የላባን ቤት ትታ ያዕቆብን ተከትላ ስትሄድ ያዕቆብን ብትወደውና ከአባቷ ሀገር መውጣትን ፈልጋ ቢሆንም የአባቷን ጣዖትም ይዛ ነበር። የእግዚአብሔር ሰው የሆነውን ያዕቆብን



ወደደችው ጣዖቷን ግን ልታመልከው ይዛው መጥታ ነበር። መወሰንና የእግዚአብሔር ብቻ ለመሆን አልቻለችም ነበር:- የእግዚአብሔር ሰው የሆነ እርሷ የተከተለችው ያዕቆብ ግን የእርሷን ሕይወት ወደአምልኮተ እግዚአብሔር ለውጦታል። ዘፍ.፴፩፥፴፬።

ፈጽሞ በሙሉ ልብ የእግዚአብሔርን ሰዎች መከተል ወደመንፈሳዊ ጉዞ ያደርሳል:- ግቡም የሕይወት ለውጥና እግዚአብሔርን ማፍቀር ይሆናል። ይሁን እንጂ ከልብ ሳይሆን ሰውን አይቶ የሚጓዝ ወይም ንስሐ የሚገባ ሰው ወደኃጢአት እንዳይመለስ ያሰጋል። የእሥራኤል ልጆች ሙሴን ተከትለው በእርሱ መሪነት ወጡ:- ልቡናቸው ግን ፈጽሞ ከእግዚአብሔር ጋር ባለመገናኘቱ በመደጋገም ወደኃጢአት ሲመለሱ ታይተዋል። ዘጸ.32። ዘኍ.፲፩፥፬–፭። ዘኍ.፳፬–፳፭። መሳ.፲፩።

ስለዚህ ከንስሐ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንና የሚኖረን ግንኙነት እጅግ እየጠበቀና የንስሐ ሕይወታችንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየበሰለ መሄድ ይኖርበታል። እንዲህም የሆነ እንደሆነ በልቡናችን ዓለምን የምናስብበትና ወደኃጢአት የምንመለስበት:- ከእግዚአብሔርና ከዓለም አንደኛውን ለመምረጥ የምናመነታበት አጋጣሚም አይኖርም:- ምክንያቱም «ዓለምን መውደድ እግዚአብሔርን መጥላት ነውና» ያዕ.፬፥፬። እንዲሁም ደግሞ «ብርሃን ከጨለማ ጋራ ኅብረት የለውምና። ፪ቆሮ.፮፥፲፬። ራእ.፫፥፫–፲፮። ፩ሳሙ.፳፰፥፲፩።

ንስሐ የገባው ሰው ግን የዓለም የሆነውን ነገር ፈጽሞ ከራሱ መለየት አለበት። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ለሁለት ጌታ መገዛት አትችሉም» ብሏልና። ሉቃ.፲፮፥፲፫። ንስሐ ከገባን በኋላ ዓለም እንዳትስበንና በዓለማዊ ነገር እንዳንታለል ያስፈልጋል። ለዚህ ነው በንስሐ ሕይወት ውስጥ ጥንቃቄና የንስሐን ሕይወት ከፈተና መከላከልና መንከባከብ እጅግ አስፈላጊ ነው የተባለው።

ሰይጣን ንስሐ የገባውን ሰው በለዘብተኝነት ወይም በመካከለኛነት (Intermediate Path) ሊዋጋው ይችላል። «መካከለኛው መንገድ ብዙዎችን አድኗል» የሚሉት አነጋገር አለ። ጥቂት መንፈሳውያን አባቶች እጅግ ወደ ጠለቀ ክርስትና ሕይወት ወይም መንፈሳዊነት ለመድረስ የሚችኩሉትን ለመምከር ተጠቅመውበታል። ነገር ግን እጅግ አጥባቂ አለመሆን ማለት ፍጹም አለመሆን ማለት አይደለም በሕይወት ጉዳይ ላይ አጥባቂ አለመሆን የእግዚአብሔርን ሕግ ወደመተላለፍና ከፍጹምነት ወደመለየት በሰፊው ደጅም በመግባት ወደ እግዚአብሔር ለመጓዝ ወደመሞከር ያደርሳል።

www.ethiopianorthodox.org

በሕይወት ጉዳይ ላይ መልፈስፈስ መንፈሳዊ ጥንካሬንና የንስሐን ሕይወትም ጭምር ወደማጣት ያደርሳልና እንግዲህ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ሉቃ.፯፥፲፫።

በንስሐ ሕይወት የሚኖረው ሰው በሚታይ አምልኮቱና በመንፈሳዊነቱ ሊፈተን ይችላል። ከንስሐ ሕይወቱ ያገኘው መንፈሳዊ ኃይል በአምልኮቱ እንዲያድግ ግፊት ያደርግበታል። ይህ ግፊት ግን ጥልቅ ላይሆን ይችላል። በመሆኑም የሚሠራውን ሁሉ በጥልቅ ሳያስብበት ለማድረግ ብቻ ያደርጋል:- ያለመንፈሳዊ ተመስጦ ብዙ ይጸልያል:- ያለማስተዋል ብዙ ያነባል:- ሳይዘጋጅ ሥጋውና ደሙን ይቀበላል:- ያለምንም ውጤትም ራሱን ይፈትናል። ቀስ በቀስም ለታይታ ብቻ የሚያመልክ በልቡናው ፍጹም የሆነ አምልኮ የሌለው ወደመሆን ይቀየራል። የህ ታይታ እንደማይጠቅመው ባወቀ ጊዜም ይተወዋል — ከዚህ በኋላ መንፈሳዊውን ሕይወት ይሰለችና ወደቀደመው ኑሮው መመለስ ይፈልጋል።

በዚህን ጊዜም የሚመራውና የሚመክረው ሰው ያስፈልገዋል። የመንፈሳዊ አምልኮ ምንነትና እንዴትም በመንፈሳዊነት መኖር እንደሚቻል:- እግዚአብሔርም ከመንፈሳውያን ምግባራት — ከመጾም፣ ከመጸለይ፣ ከተመስጦውና ከሌላው ሁሉ በፊት እርሱን በፍጹም ፍቅር የሚወድ ልብ እንደሚፈልግ የሚነግረው ሰው ያስፈልገዋል። ከልብ ያልመነጨና ለታይታ ብቻ ተብሎ የሚፈጸመውን አገልግሎት እግዚአብሔር እንደማይወደውና እንደማይቀበለው በሚገባ መረዳት አለበት። ሁል ጊዜም እግዚአብሔር «ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው» በማለት የተናገረውን እያሰበ አምልኮቱንና መንፈሳዊ አገልግሎቱን ፍጹም ማድረግ አለበት። ማቴ.፲፭፥፰።

ለታይታ የሚኖር መንፈሳዊ ሕይወት ከንስሐ የራቀ ነው። መንፈሳዊነት የሚታይና የተገለጠ አይደለም — ጥልቅና ውስጣዊ ነው። ለዚህ ነው መድኃኒታችን ሕግን በመጠበቃቸው ብቻ በሕይወታቸው ውስጥ መንፈሳዊነት ሳይኖር ይመጻደቁ የነበሩትን ጸሐፍት ፈሪሳውያን ይገሥፃቸው የነበረው። እነርሱ በሚታይ ነገር የሚመጻደቁ እንጂ የንስሐ ሰዎች አልነበሩምና መንፈሳዊነትም በእነርሱ ዘንድ አልነበረም።

እኛም እንግዲህ ንስሐችን እንዲታወቅልን አምልኮታችን እንዲታይልን የምንሻ መሆን የለብንም። ሁል ጊዜም ልንጨነቅ የሚገባው ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚኖረን ፍቅርና ስለመንፈሳዊ ሕይወታችን ብቻ ነው። ይህ ፍቅረ እግዚአብሔርና መንፈሳዊነት በንስሐ ሕይወት ጸንተን እንድንኖርና በሁለት



ሃሳብ የማናመነታና የማናነክስ እንድንሆን ያደርገናል። በሁለት ሃሳብ የሚያነክሱ ሁሉ መጨረሻቸው ጥፋት ነው። ዘኊ.፴፬፥፴፭። መሳ.፲፩።

## ፫. የብርሃንና የጨለማ ልዩነት

ንስሐ ከገባንና የእግዚአብሔር ብርሃን በውስጣችን ከሆነ የንስሐ ሕይወታችንን ለመጠበቅ ከጨለማ ሥራ ሁሉ መለየት አለብን። ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጠን የመጀመሪያ መመሪያ ነው። በዘፍጥረትም «እግዚአብሔርም ብርሃኑን መልካም እንደሆነ አየ:- እግዚአብሔርም ብርሃንንና ጨለማን ለየ።» ተብሎ ተጽፏል። ዘፍ.፩፥፬። ይህ መመሪያ በብርሃንና በጨለማ ሥራ መካከል ኅብረት የሌለ መሆኑን ያስረዳል። ስለዚህ መርሖ በሐዲስ ኪዳንም «ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን አንድነት አለው» በሚለው የቅዱስ ጳውሎስ አነጋገር ተገልጧል። ፪ቆሮ.፮፥፲፬። ለመንፈሳዊ ሰው ጨለማንና ብርሃንን አጣምሮ መኖር አይቻለውም። ለዚህ ነው በእግዚአብሔር መንገድ የሚጓዝ ማንኛውም ሰው መንፈሳዊ ሕይወቱን ከኃጢአት ምክንያቶችና ከመሰናክል መለየትና ነጻ ማድረግ ያለበት።

ከዘፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እግዚአብሔር የሚፈልገውም ብርሃን ከጨለማ — መንፈሳዊ ሕይወትም ከኃጢአት የተለየ እንዲሆን ነው። ይህ የእግዚአብሔር ሕግና መመሪያ በተጣሰ ጊዜ ግን ኃጢአትን አስከተለ። የዚህ መጀመሪያም ሔዋን ከእባብ ጋር መተባበሯ ነበር — የጨለማ ሥራም ብርሃንን ሲያጠፋ ታይቷል። ዘፍ.፫። ሌላው አደገኛው ሕግን መተላለፍ ደግሞ ከጥፋት ውኃ ቀደም ብሎ የነበረው ነው:- «የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደሆኑ አዩ:- ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ።» ዘፍ.፮፥፪። የዚህ መጨረሻም የእግዚአብሔር ምድርን በጥፋት ውኃ ማጥለቅለቅና ከከፉ የጨለማ ልጆች ማጽዳት ሆነ። እግዚአብሔርም በጥፋት ውኃ ዘመን የብርሃን ልጅ የሆነውን ኖኅን ከጨለማ ልጆች ለይቶ አስቀረ። በኖኅ ልጆች ደግሞ ተንኮል በገባ ጊዜ እግዚአብሔር አብርሃምን ለራሱ ለየ — «ከሀገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ:- እባርክሃለሁ:- ስምህንም አከብረዋለሁ:- ለበረከትም ሁን:- የሚባርኩህንም እባርካለሁ።» በማለት አብርሃምን ጠርቶታል። ዘፍ.፲፪፥፩–፬። በዚህ ጥሪ እግዚአብሔር አብርሃምን የኃጢአትን ምድር እንዲተዋት፣ የልቡን ንጽሕና እንዲጠብቅ፣ ከክፉም ነገር እንዲርቅ፣ በእርሱ ያለውን ብርሃን በእነርሱ ካለው ጨለማ እንዲለይ ያዘዘው መሆኑ ግልጽ ነው። በኋላም እግዚአብሔር «በአሕዛብ ምድር ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ቃል ኪዳን

www.ethiopianorthodox.org

እንዳያደርጉ...ሴት ልጆቻቸውንም ከወንድ ልጆቻቸው ጋር እንዳያጋቡ» «የባዕድ ሴቶችንም እንዳያገቡ ከልክሏቸው ነበር።» ዘጸ.፴፬፥፲፩–፲፯። ምሳ.፩፥፲፯። የእግዚአብሔር ፈቃድ ልጆቹ ሁሉ ከክፉ ባልንጀርነት እንዲለዩ መሆኑን «ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ:- በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመ፣ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ» በማለት በነቢዩ ዳዊት አድሮ ተናግሯል። መዝ.፩፥፩። ቅዱስ ጳውሎስም በበኩሉ «ከኃጢአተኞች ጋር...እንዳትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ? እንደ እነዚህ ካሉ ጋር መብል እንኳ አትብሉ።» በማለት መክሯል። ፩ቆሮ.፭፥፲፩። ፍቁረ እግዚእ ቅዱስ ዮሐንስም «ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት (እነርሱ ያስተማሩትን የቀናውን እምነት) ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት። ሰላምም አትበሉት:- ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና።» ሲል መክሯል። ፪ዮሐ.፲፥፲፩።

ከኃጢአትና ከኃጢአተኞች መለየት ሲባል በምግባርና በዕውቀትም (በሃሳብም) ጭምር መሆኑን ማወቅ አለብን። ከውጭ የሚመጡት ተጽእኖዎች ሶምሶንን፣ ዳዊትንና ሰሎሞንን ታላላቆቹን ከጣሉ ደካሞች የሆንን እኛ ደግሞ ራሳችንን ከኃጢአትና ከኃጢአተኞች ወዳጅነት በመለየት ጠንቃቃ ልንሆን ይገባናል። ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ቤተ ክርስቲያንም የጨለማ ልጆች የሆኑ መናፍቃንን እየለየች በማውገዝ ቆይታለች። የሐዋ.፭። ፩ቆሮ.፭፥፭። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ልጆች ከሆንን የአባቶቻችንን የሐዋርያትንና የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ፈለግ በመከተል ከክፉ የጨለማ ሥራ መለየት ይኖርብናል።

ምናልባት እንዴት በአንድ ዓለም እየኖርን ከኃጢአትና ከኃጢአተኞች ለመለየት እንችላለን እንል ይሆናል። በከልል:- በመልክአ ምድር ከኃጢአተኞች መለየት ባንችል እንኳን በተግባር ግን ፈጽሞ ከኃጢአተኞች ጋር መተባበር የለብንም:- በሃሳብ፣ በምግባርና በምንኖረው መንፈሳዊ ሕይወት ከእነርሱ ፈጽሞ መለየት ይገባናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «አንዱ ሴሰኛ፣ ወይም ገንዘብን የሚመኝ፣ ወይም ጣዖት የሚያመልክ፣ ወይም ተሳዳቢ፣ ወይም ሰካራም ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ» እንዳለው ግንኙነታችንን በአስፈላጊ ነገሮች ብቻ ልንወስነው ይገባል። ፩ቆሮ.፭፥፲፩። አነጋገራችን መንፈሳዊ ከሆነ ከእነዚህ የጨለማ ልጆች ጋር ልንስማማ አንችልም:- «አነጋገራችን ይገልጠናልና።» ማቴ.፳፮፥፸፫። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም



«የእግዚአብሔር ልጆች...የተገለጡ ናቸው።» ያለው ለዚህ ነው። ፩ዮሐ.፫፥፲። ከዓለማውያን መካከል እንኳ ቢሆኑ ጠባያቸው፣ አመለካከታቸው፣ አነጋገራቸውና ማንነታቸው ይገልጣቸዋልና በዚህ እግዚአብሔር ብርሃንን ከጨለማ እንዴት እንደለየ በግልጽ ልንረዳ እንችላለን።

በንስሐ የሚኖርና ራሱን ከኃጢአት የለየ የእግዚአብሔር ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ የተገለጠና ከጨለማ ልጆች የተለየ የብርሃን ልጅ በመሆኑ መታበይ፣ መኩራትና ከሌሎች የተለየ የሆነ አድርጎ ራሱን መቁጠር የለበትም። መመጻደቅና ራሱን የተሻለ አድርጎ መገመትም ከእርሱ አይጠበቅም። ከእርሱ የሚጠበቀው በማንኛውም የኃጢአት ሥራ ከኃጢአተኞችና ከዚህ ዓለም የጨለማ ልጆች ጋር ከመተባበር ርቆ መገኘት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው አለመተባበር ብቻ ሳይሆን ይህን ዓለም መምሰልም አያስፈልግም። ሮሜ.፲፪፥፪። በንስሐ የሚኖር ሰው ኃጢአተኞችን በኃጢአታቸው አይመስላቸውም:- ስለመዳናቸው እየጸለ የላቸው ያዝንላቸዋል እንጂ ኃጢአተኞች በመሆናቸው አይፈርድባቸውም። ከኃጢአተኞች ጋር መተባበር ባለመቻሉም ስለድካሜ እንጂ የተሻልኩ ሆኜ አይደለም — የውጭው ዓለም በቀላሉ ሊያሸንፈኝ የሚችል — ሥጋዊ ፍላጎቴንም ለመቋቋም ኃይል የሌለኝ በመሆኔ መለየትን መርጬ እንጂ በመኩራትና በመመጻደቅ አይደለም ኃጢአቴን እኔ አውቀዋለሁና ይላል።

በዚህ ደግሞ ኃጢአተኞችን ወደንስሐ ለማምጣት ሲሉ ኃጢአተኞች በሚውሉበት ድረስ በመሄድ ጉብኝት ከሚያደርጉት ካህናት የተለየ ነው። እርሱ ከእነርሱ ጋር መደባለቅን ይሸሻልና ካህናቱ ግን በመካከላቸው ሆነው ወንጌልን ይሰብካሉ በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰሉ:- እውነተኛ ምስክሮች፣ የእግዚአብሔር መልእክተኞችና እንደራሴዎቹም ናቸውና። ስለዚህ ስንስሐ የሚኖረው ሰው እኔ ደካማና ኃጢአት በቀላሉ የሚያሸንፈኝ ስለሆንኩና የመቋቋምም ኃይል ስለሌለኝ ከኃጢአተኞች ባልንጀርነት ራሴን ማራቅ ይሻለኛል ይላል። እንዲህ ባለችው ትሕትናውም መንፈሳዊ ልቡን ይጠብቀዋል።

በእንዲህ ዓይነት ሕይወት የሚኖር የንስሐ ሰው እርሱ ሌሎችን የሚመክሩና ወደንስሐ የሚጠሩ በብርሃን የሚመላለሱት የብርሃን ልጆች ከደረሱበት ደረጃ ገና እንዳልደረሰና «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» የሚለው የጌታችን ቃልም የተነገረው ለማን እንደሆነ ያውቃልና ራሱን አያመጻድቅም። የንስሐ ሕይወቱን በመንፈሳዊ ትሕትና ከፈተና ይጠብቃል። «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» የተባለው እነርሱ ባሉበት

www.ethiopianorthodox.org

ጨለማ ለሚወገድላቸው ቅዱሳንና ንጹሐን የእግዚአብሔር ልጆች መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል። ማቴ.፭፥፲፬።

እነዚህ ቅዱሳን ባሉበት ሰይጣን አይኖርም:- ኃይልም የለውም ሰዎችም እንኳ እነርሱ ባሉበት ክፉ ነገርና ኃጢአትን አይናገሩም:- ቢናገሩ እንኳ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ወደአሉበት ሊደርሱ ያፍራሉ:- ይፈራሉ። የእግዚአብሔር ሰዎች ብርሃናት ናቸውና በእነርሱ ጨለማ የሆነ የኃጢአት ሥራ ይገለጣልና።

እንግዲህ እኛም የሻማ ጭላንጭል ያህል እንኳን የምናበራ ልንሆን ያስፈልጋል። ነገር ግን ከንስሐ በኋላ ገና ከዚህ ደረጃ ያልደረስን እንደሆነ ወደ ጨለማ እንዳንመለስ እጅግ በጣም ልንጠነቀቅ ይገባል። በሕይወታችን ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን» በማለት የተናገረውን ቃል ማስታወስ ይኖርብናል። ሉቃ.፲፪፥፴፭። ብርሃናችንም አስቀድሞ የእግዚአብሔርን መንገድና ፈቃዱንም እናውቅ ዘንድ ለራሳችን የበራና እኛም ደግሞ እንደ አምስቱ ጠባባት የተዘጋጀን መሆን ይኖርብናል። አምስቱ ጠባባት ሙሽራውን ለመቀበል መብራ ታቸውንና ዘይታቸውን አዘጋጅተው በመጠበቅ ላይ ነበሩና። ማቴ.፳፭። በኋላም ወደሠርጉ እንደገቡ እኛም ደግሞ እንገባ ዘንድ አርአያነታቸውን ልንከተል ያስፈልጋል።

በዚህ የጭላንጭል ያህል በሚያበራው የሻማ ብርሃናችን የጨለማን ሥራ ልንገልጠውና ከራሳችንም ልናርቀው ይገባል፣ ይህም ከክፉ ሃሳብና ፍላጎት መለየት ነው። ልቡናችን ከክፉ ሃሳብና ፍላጎት ፈጽሞ ካልተለየ እግዚአብሔር አምላካችንን ልናፈቅረው ከቶውኑ አንችልም። ስለዚህ ልባችንን ከዚህ ክፉ ፍላጎት በማንጻት ፈጣሪአችንን በፍጹም ልባችን በፍጹም ሃሳባችንም ልናፈቅረው ያስፈልጋል። ዘዳ.፮፥፭። ስለዚህም «ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ»...«ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም:- ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ» ያለውን የሐዋርያውን ቃል እናስታውሳለን። ፩ዮሐ.፪፥፲፭–፲፯። ምናልባትም ራሳችንን ከዓለም በዓለምም ካለው ፍላጎት ማራቅ ባይቻለን:- እግዚአ ብሔርን በቅዳሴ እንደተነገረው ሁሉ «አቤቱ ከአንተ የተቀደሰ ፈቃድ ጋር የማይስማማውን ሃሳብ ሁሉ ከእኛ አስወግድልን ብለን ልንለምነው ይገባል። ከኃጢአት ሃሳብም ራሳችንን ለመለየት መፍጠን ይኖርብናል። ምክንያቱም በትንሽ ቀዳዳ ወደልቡና የገባ ኃጢአት እስኪያጠፋና ልቡናን እስኪመርዝ ድረስ ሥር መስደዱ አይቀርምና።



ስለዚህ ቁጭ ብለን ለኃጢአት ምክንያት የሚሆን ሃሳብና ፍላጎት በውስጣችን ይኖር እንደሆነ ራሳችንን መመርመር አለብን። ምናልባትም እነዚህ ፍላጎቶች በእኛ ዘንድ ቢኖሩ ከእኛ ዘንድ ልናጠፋቸውና «እግዚአብሔርም ብርሃንን ከጨለማ ለይቷል» ልንላቸው ያስፈልጋል።

## ፬. ነፍስን መንከባከብ

ነፍስን መንከባከብ የንስሐን ሕይወት የመጠበቅ አስፈላጊና አወንታዊ ገጽታ ነው። ቀደም ብለን የተመለከትናቸው ክፉ ልማድን ማስወገድ፣ በሁለት ሃሳብ አለማመንታት፣ የብርሃንና የጨለማ ልዩነት የንስሐን ሕይወት ከመጠበቅ አንፃር አሉታዊ ጥንቃቄዎች ናቸው። ነፍስን መንከባከብ ደግሞ አዎንታዊ ጥንቃቄን የሚያመለክት ነው ጠንካራ ነፍስ ሰውን በንጽሕና ይጠብቀው ዘንድ ይችላልና።

ማንኛውም ሰው ለሥጋው እንደሚያስብ ሁሉ ለነፍሱም ማሰብ አለበት የሚባለው ለዚህ ነው። ሰው ሥጋውንም ነፍሱንም እኩል መጠበቅ ይኖርበታል። ከሁለቱ ለአንደኛው ብሎ የሚወስደው ጥንቃቄ ሌላኛውን የሚጎዳ መሆን አይገባውም አንዳንድ ሰዎች ለሥጋቸው በማሰብና ጾምን ካለመጾምና ካለመስገድ እንዲሁም ካለመጸለይ የተነሣ ነፍሳቸውን ይጎዳሉና። ልጆቹን የሚያሳድግ አባት ለሥጋቸው ብቻ ሳይሆን ለነፍሳቸውም ማሰብ አለበት። ነፍስ እየሞተች ትል የሚበላው ሥጋ በምቾት መፋፋት የለበትም።

የሥጋ ጤንነትና ድሎት ከነፍስ ጋር ካልተመጣጠነ ወደ መንፈሳዊ ውድቀት ሊያደርስ ይችላል። የነፍስ ጤንነት ግን ሥጋንም ጤነኛ ያደርጋል። ነፍስ ከታመመች ሥጋም በሽተኛ መሆኑ አይቀርም። ስለዚህ ከሥጋ ይልቅ ለነፍስ ጤንነት ልንጨነቅና መንፈሳዊ ሕይወታችንን ልንጠብቅ ያስፈልጋል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ሥጋህ ቢያሰናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣለው» ያለው ለዚህ ነው። ማቴ.፭፥፳፱–፴። በዚህ ትምህርቱም የነፍስ ጉዳይ እጅግ ጥንቃቄ ሊደረግለት የሚገባ አስፈላጊ መሆኑን አስረድቷል። በመሆኑም ነፍስን ለማዳን የሥጋን ፍላጎትና አስፈላጊም ከሆነ ሥጋን መሥዋዕት ማድረግ የሚገባ ሊሆን ይችላል:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለውና ደሙን ያፈሰሰው ነፍሳችንን ለማዳን ብሎ ነውና። ነፍሳችንም በመስቀል ላይ ለእኛ ቤዛ ሆኖ በፈሰሰው የክርስቶስ ደም የተገዛች ናት። ለእኛ ያለችን አንዲት ነፍስ ብቻ ናትና ብናጣት ሁሉን እናጣለን ብናድናት ሁለመናችን ይድናል – ሁሉን እናገኛለን:- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሰው ዓለሙን ቢያተርፍ ነፍሱንም

www.ethiopianorthodox.org

ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል? ለነፍሱስ ቤዛ ምን ይሰጣል?» ያለው በዚህ ምክንያት ነው። ማቴ.፲፮፥፳፮።

ነፍሳችንን ልናጠፋ የምንችለው እኛ ብቻ ነን:- ሰዎች ሥጋችንን ሊገድሉ:- ሊያሥሩ፣ ሊያሰቃዩትም ይችሉ ይሆናል – ነፍሳችንን ግን ምንም ሊያደርጉ አይችሉም። ነፍሳችን የሥጋ ሕይወትና ሰማያዊት ናትና ልንጠብቃትና ልንንከባከባት ይገባናል። ከዚህ በመነሣት ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን (ሥጋችን) ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን (ነፍሳችን) ዕለት ዕለት ይታደሳል።» ያለው። ፪ቆር.፬፥፲፮።

ሥጋችንን በየዕለቱ እንደምንመግበው ነፍሳችንንም እንዲሁ በየዕለቱ ከቃለ እግዚአብሔር ልንመግባት ይገባናል። ሥጋ እንደሚያድግ እንዲሁ ደግሞ ነፍስም በጸጋ ታድጋለች። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ «የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ:- ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው።» በማለት ተናግሯል። ዮሐ.፬፥፴፬። ነፍስም የምታድገው «ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ ነው» ማቴ.፬፥፬። ስለዚህ ነፍሳችን የእግዚአብሔርን ቃል እየተመገበችና ፈቃዱንም እየፈጸመች ልታድግ ይገባል። ሥጋችን በቀን ሦስት ጊዜ ይመገባል እንዲሁ ሁሉ ነፍሳችንም በተወሰነ ጊዜ ምግቧን ማግኘት የሚገባት መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ለሥጋችን የተመጣጠነ ምግብ በማዘጋጀትና በሕክምና ጤንነቱን ለመጠበቅ እንደምንጨነቅ ሁሉ ለነፍሳችንም ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደምግብና ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ ምፅዋት፣ ምግባር ትሩፋትን እንደ ሕክምና በማዘጋጀት ልንጨነቅላት ያስፈልጋል። ነፍሳችን ቅድስናንና ንጽሕናን የምትራብና የምትጠማ ናትና በየጊዜው ልንመግባት ይገባል። ማቴ.፭፥፮።

ሥጋችን ምግብ ሲያጣ እንደሚደክም ሁሉ ነፍስም ምግቧን የእግዚአብሔርን ቃል ስታጣ ትደክማለች። ከምግብ እጦት የተነሣ ሥጋ እንደሚታመም ነፍስም ከቃለ እግዚአብሔር እጦት የተነሳ ትታመማለች። ለሥጋ በሽታ ሐኪም እንደሚያስፈልገው ለነፍስ በሽታም መንፈሳዊ ሐኪም ያስፈልጋል። የነፍስ መንፈሳውያን ሐኪሞችም መምህራን ንስሐና መንፈሳውያን አማካሪዎች እንዲሁም የወንጌል ሰባኪዎች ናቸው። መድኃኒቱም የእግዚአብሔር ቃል የማይወሰን ስለሆነ እንደየበሽታው ዓይነት ሊወሰድ ይገባል።

ብዙ ጊዜ ለነፍስ ልናደርግ ከሚገባው አብልጠን ለሥጋ ስንጨነቅ እንታያለን። ስለዚህም አንድ መንፈሳዊ አባት ጠቢቡ ሰሎሞን «ባሪያዎች



በፈረስ ላይ ሲቀመጡ መሳፍንትም እንደባሪያዎች በምድር ላይ ሲሄዱ አየሁ» በማለት የተናገረውን ሲተረጉሙ– «በፈረስ ላይ የተቀመጠ ባሪያ ሥጋ ነው በምድር የሚሄድ መሳፍንትም ነፍስ ናት:- እንደ ሥጋ ክብርን አትሻምና ክብርን የሚሻ ሥጋ ግን ከፍ ከፍ አድርጉኝ ይላል» ብለዋል። መክ.፲፥፯። ስለዚህ ነፍሳችንን በሚገባት ሥፍራ አድርገን በእጅጉ ልንጠብቃትና ልንንከባከባት ይገባናል።

ሥጋችን እንደሚዋብ ሁሉ ነፍሳችንም መዋብንና ማጌጥን ትፈልጋለች። የነፍስ ጌጧ ግን ገድል:- ምግባርና ትሩፋት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ «በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ:- የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለው የማይጠፋው ልብስ...ይሁንላችሁ» እንዳለው የሙሽራ ልብስ ትለብሳለች። ፩ጴጥ.፫፥፬። ማቴ.፳፪፥፲፩–፲፪። ይህን የሠርግ ልብስ የለበሰች እንደሆን ወደሠርጉ ቤት ልትገባ ትችላለች። ነፍስ እጅግ ያማረ ሸማ ትለብሳለች:- እርሱም የቅዱሳን ጽድቃቸው ነው። ራእ.፲፱፥፰። በእግዚአብሔርም ፊት ነጭ ልብስ ተጎናጽፋ ትቆማለች። የእኛም ነፍስ እንግዲህ በመንፈስ ፍሬዎች ያጌጠች መሆን አለባት። ገላ.፭፥፳፪። በእግዚአብሔር ፊትም ከጸጋ ተራቁታ መታየት የለባትም። ራእ.፫፥፲፯።

ስለዚህ ሥጋችን ቢያጌጥ ምንም እንደማይረባን ዐውቀን ቅዱስ ዳዊት «ንግሥቲቱ በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋ በቀኝህ ትቆማለች» እንዳለ ንግሥት የምትሆን ነፍሳችንን የወርቅ ልብስ በሆነ የጽድቅ ሥራ አስጊጠን በመጨረሻው ቀን ሙሽራውን ለመቀበል እንደተዘጋጀች ሙሽሪት በእግዚአብሔር ፊት ማቆም አለብን። መዝ.፵፬፥፱። ራእ.፳፩፥፪። ስለዚህም በንጽሕናና በቅድስና ወርቅ የተለበጠና የከበረ ንጹሕ ልብ ሊኖረን ይገባል። ዘጸ.፳፰፥፲፭።

ነፍስን በመንከባከብና በመጠበቅ የሚከተሉትን ትእዛዛት ዘወትር ማስታወስ ይገባል።

ሀ. በመንፈስ ብንመላለስ የሥጋን ምኞት አንፈጽምም። ገላ.፭፥፲፮።

ለ. መንፈስ የሞላብን (መንፈስ ቅዱስ ያደረብን እንሁን) ኤፌ.፭፥፲፰።

ሐ. በመንፈስ የምንቃጠል እንሁን ሮሜ.፲፪፥፲፩።

በዚህም እግዚአብሔርን በመንፈስ እናመልከዋለን። ፊል.፫፥፫። በመንፈስ እንጸልያለን በመንፈስም እንዘምራለን። ፩ቆሮ.፲፬፥፲፭። የመንፈስ ፍሬዎችንም እናፈራለን። ገላ.፭፥፳፪። ምክንያቱም «በመንፈስ የሚዘራ ከመንፈስ የዘለዓለምን ሕይወት እንደሚያጭድ» እናውቃለንና። ገላ.፮፥፰።

www.ethiopianorthodox.org

ይህን በመሰለ መንፈሳዊ ሕይወት የተመላለስን እንደሆነ የንስሐ ሕይወታችንን ከፈተና እንጠብቃለን:- ወደኋላም ተመልሰን የተውነውን ኃጢአት አንሠራም። ስለዚህ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ማጠንከርና ማጽናት ይገባናል። የማይፈተን የለም:- በመንፈሳዊ ሕይወቱ ጠንካራና በፈተና የሚጸና ሰው ቤቱን በዓለት ላይ እንደሠራ ሰው ነውና ነፍሳችንን በጽኑ መሠረት ላይ ልናቆማት ያስፈልጋል። ማቴ.፯+፳፬–፳፭። ይህ ጽኑ መሠረትም የእግዚአብሔር ቃል ነው። ነፍሳቸውን ዘወትር የእግዚአብሔርን ቃል የሚመገቡ ሰዎች ዙሪያዋ በግንብ እንደታጠረ ከተማ ጸንተው ይኖራሉ።

ፍጹሙ ንስሐ እንግዲህ በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ የተመሠረተና ከእርሱ ጋር የሚያገናኝ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም» ያለው ለዚህ ነው። ፩ቆር.፲፫+፰። ጠቢቡ ሰሎሞንም «ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ አይችልም።» ብሏልና (መኃ.፰+፯)። በፍቅረ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ የንስሐ ሕይወት እስከመጨረሻ የጸና ይሆናል።

ስለዚህ ከንስሐ በኋላ ከእግዚአብሔር ፍቅር እንዳንለይ – ከእቅፉም እንዳንወጣ:- የናቅናት ዓለምና የተውነው ኃጢአታችን እንዳይናፍቀን፣ ወደነበርንበትም እንዳንመለስ፣ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር የገባንለትን ቃል ኪዳን እንዳናፈርስ በእጅጉ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል። ቀድሞ የነበርንበት የኃጢአት ኑሮና የውጤቱ መራራነት ትዝ እያለን እንድንጠላውና ራሳችንም ከኃጢአትና ከኃጢአተኞች ምግባርና ሃሳብ መለየት እንድንችል ተግቶ ከመጸለይ ጋር መምህራን ንስሐዎቻችንን በየጊዜው እያገኘናቸው በመንፈሳዊ ምክር የምንኖር ሰዎች መሆን ይገባናል። ፩ነገ.፪+፫። በራሳችንም ማስተዋል ከመጓዝ መጠበቅ አለብን በመጽሐፍ «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን በራስህም ማስተዋል አትደገፍ» ተብሏልና። መሳ.፲+፳። ስለዚህ ሥራችን ሁሉ:-

«ለሚጠፋ መብል ሳይሆን ለዘለዓለም ሕይወት ሊሆን ይገባል።» ዮሐ.፮+፳፯።

እግዚአብሔር አምላካችን የዘለዓለም ሕይወት በምናገኝበት ጽኑ ክርስትና ራሳችንን በምንመረምርበት ንጹሕ ልቡና በምክረ ካህን በምንኖርበት ትሕትና እንዲያጸናን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን።

www.ethiopianorthodox.org